
ኦፐሬሽን መቅደላ



አፕሬሽን መቅደላ

ብሥራት አጥላባቸው ኃይሌ

ሰኔ 2004 ዓ.ም.

ድርሰት: ብሥራት እጥላባቸው ኃይሌ
© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ሰኔ 2004 ዓ.ም.

<u>መታሰቢያ:</u> እሮጌ መቅደላ ላይ ለወደቀው ታላቁ ጀግና:

ለፊታውራሪ ገብርዬ (ገብረ ሕይወት)

ቀደምት ሥራዎች:

1: የፍርድ ቀን ዘመቻ
2: ሌላው ገጽታዬ
3: ቧልተኛው
4: ተለዋጭ ሰላይ
5: የስኬት ጉዞ
6: ግዙፍ የስኬት እርምጃዎች

በቅርብ የሚወጡ:

1. የቤይሩቱ ፍንዳታ (ድርሰት)
2. ሞሳድና ዘመቻ ሙሴ (እውነተኛ ታሪክ)
3. ቬሮኒካ (የፓውሎ ኮኤሎ)
4. ንጹሕ ወንጀለኛ (ጆን ግሪሸሃም)
5. የዘመናት እንቆቅልሽ (ጥናታዊ መጽሐፍ)

ምስጋና:- ለጌቱ ተገኝ እና ፋሲካ ግዛው በእርማትና በቴክኒክ እገዛ
ከጎኔ ሆነው ላደረጉልኝ ትብብር

ዋና አከፋፋይ
ጃዕፋር መጻሕፍት መደብር
አድራሻ:- ከብሔራዊ ቴአትር በስተጀርባ
ስልክ:-0911125320
:-0913844367

መግቢያ

ባልሳላት ጊዜው 1996 ዓ.ም መጀመሪያ አካባቢ ይመስለኛል። ለገሀር አካባቢ አንድ ምግብ ቤት ውስጥ ምሳ እስኪቀርብልኝ እየጠበቅኩ ነው። *"ዝቶኑ ሰባት ሰዓት ሆኗል ዜና አናሰማለን"_አለ ካናቱ በላይ የተሰቀለው ስፒከር። "በ1798 ዓ.ም ከመቅደላ አምባ በእንግሊዝ ጦር ተዘርፈው የተወሰዱ ታሪካዊ ቅርሶቻችን ከ140 ዓመታት በኋላ በውሰት ከለንደን አዲስ አበባ መጥተው ለአንድ ሳምንት ያህል በእንግሊዝ ኤምባሲ ውስጥ በኤግዚቢሽን ከታዩ በኋላ ወደ ለንደን ሊመለሱ ነው!"*

'እንዴ! ምን እየተደረገ ነው?' አልኩ ለራሴ። አገራችን ተወራ፣ ንጉሣችን ራሳቸውን እንዲያጠፉ ተገደው፣ መተኪያ የለሽ፣ ብርቅና ድንቅ ታሪካዊ ቅርሶቻችን መዘረፋቸው ሳያንስ ሌባው ራሱ "በውሰት" አምጥቶልን በኤግዚቢሽን ሊያሳየን? ማመን አቃተኝ። እናም ቀኑን ሙሉ ቅርሶቻችንን እዚሁ አገራችን ማስቀረት፣ ማስመለስ የሚቻልበትን መንገድ ሁሉ ሳስብ፣ ሳወጣና ሳወርድ ዋልኩ።

በዚህ ብለው በዚያ ያገኘሁት ማስመለሻ መንገድ አንድ ብቻ ነው። ማታ ቤቱ ገባሁና ይህን ብቸኛ ያልኩትን ዘዴ በጽሑፍ ማስፈር ጀመርኩ። ውጤቱም ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ በበርካታ ኮምፒውተር ቤቶችና በአያሌ ጓደኞቼ እጆች ሲጻፍና ሲታረም የኖረው ይህ "አፓሬሽን መቅደላ" የተሰኘ ርዕስ የሰጠሁት መጽሐፍ ሆነ። እናም ቅርሶቻችሁን ያስመለስኩበትን መጽሐፍ እነሆ!

ብሥራት አጥላባቸው ኃይሌ

ድማሬው

አሮጌ፡ መቅደላ -1966 ዓ.ም

ላንድ ሮቨሩን ደገፍ ብለው የቆሙት ባሕታዊ ቀጭን፣ ረዥም ቁመናቸው ከመከናው ጣራ እኩል ደርሷል። በዚያ ቅጥንታቸው ላይ የለበሱት ሰፊ ልብስ ተከህኖ፣ ራሳቸው ላይ ያደረጉት ጥቁር ቆብ፣ አገጫቸው ላይ የበቀለው ሹል እና የፍየል የመሰለ ፂም ተደማምረው ከቤተ—ክህነት ሰውነት ይልቅ እስቂኝ የሕንድ ፊልም ተዋናይ ገጽታን አላብሰዋቸዋል። በቀኝ እጃቸው ቀጫጭን ጣቶች መቁጠሪያቸውን እያሦሩ ይቆጥራሉ። እንደ ንሥር አሞራ ትናንሽ በሆኑ ዐይኖቻቸው እንዴ ከጋራው ባሻገር በመጥለቅ ላይ ያለችውን ፀሓይ፣ እንዴ ከፊት ለፊታቸው ራቅ ብለው የሚቆፍሩትን ሰዎች እያፈራረቁ ይመለከታሉ።

ጥቂት ራቅ ብሎ የቆመው የባሕታዊው የዘወትር አገልጋይና የሥጋ ዘመዳቸው ቀለመ፡ የደበዘዘ ካኪ ኮትና ሱሪ ለብሶ፣ ጥቁር የወታደር ጫማ ተጫምቶና ኤም-ዋን ጠመንጃውን አንግቦ አካባቢውንና ቆፋሪዎቹን በጥንቃቄ ይቃኛል። የዕድሜው በሃያዎቹ መጨረሻ ውስጥ የሚገኝ አንድ ወጣት በታጣቂውና በባሕታዊው መሃል ባለች አነስተኛ ጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ ተቀምጧል። በአለባበሱ ዘመናዊነት ይታይበታል። አንዴ ፀሓይቱን አንዴ ቆፋሪዎቹን በጭንቀት ሲመለከት ይቆይና የእጅ ሰዓቱን እየት አድርጎ ወደ ቆፋሪዎቹ ዞር በማለት "በርቱ፣ ቶሎ ቶሎ በሉ፣ ትሳሳላችሁ!" ሲል ይጮኻል።

ቆፋሪዎቹ አራት ናቸው። ሁሉም ቁምጣ ሱሪ ብቻ ነው የለበሱት። በቀኑ መሞቅና በቁፈራ ሥራቸው ምክንያት ከወገባቸው በላይ ራቁታቸውን ነበሩ። አንደኛው ቆፋሪ የግራ ክንዱ ጡንቻ ላይ የተነቀሰው የመስቀል ንቅሳት ደማውን አንስቶ በጣለ ቁጥር ከጡንቻው ጋር እየተወጠረ ጎልቶ ይታያል። በባሕታዊውና በእሸቢው መሃል የተቀመጠው ጎልማሳ የቁፈራውን ሂደት በአንክሮ እያስተዋለ "ይህ ቁፈራ ውጤቱ ምንም ይሁን ምን የዚያ ሰው የመስቀል ንቅሳት ምን ጊዜም አይረሳኝም" እያለ ያስባል።

ቀደም ሲል የቆፈሯቸው ሦስት ጉድጓዶች ውስጥ ምንም ነገር ባለመገኘቱ አራተኛው ጉድጓድ በባሕታዊው ጠቋሚነት እየተቆፈረ ነው። የጉድጓዱ ጥልቀት እየጨመረ፣ ጀምበርም እያዘቀዘቀች ብትመጣም ምንም ውጤት ባለመገኘቱ ሁሉም ተስፋ መቁረጥ ጀምረዋል።

"በርቱ! ትካላላችሁ!" አለ ጎልማሳው። ባሕታዊውም ድምጽ አልባ ጸሎታቸውን ያነበንባሉ።

ባለ ንቅሳቱ ሰው ተስፋ በቆረጠ ስሜቱና በዛሉ ክንዶቹ እንስቶ ያነዘረው ዲጂና የትቤ ክምር ላይ ያረፈ ይመስል መሬቱን ቀርድዶት ገባ። ሁኔታው ግራ ያጋባው ቆፋሪ ምላሩን እነሳና አፈርና ድንጋዩን በእጆቹ ማግለል ሲጀምር ባልደረቦቹም የዕርዳታ እጆቻቸውን ጨመሩለት። ቀስ በቀስም አንድ የዛገ፣ የሻገተና አፈር የበላው የብረት ሳጥን ብቅ አለ።

"እዚህ የተቀበረ ነገር አለ።" ሲል ባለ ንቅሳቱ ሰውዬ በድንገት ድምፁን ከፍ አድርጎ ሲጮህ ባሕታዊው፣ ታጣቂው እና ጎልማሳው ከተዘፈቁበት የጭንቀት ዓለም ምንጥቅ ብለው ወጡና ወደ ጉድጓዱ ተሯሯጡ።

ጎልማሳው ሰው ዱብ ብሎ ጉድጓዱ ውስጥ ገባና አፈርና ድንጋዩን በእጆቹ ማፈስ ሲጀምር ባሕታዊው እና ታጣቂው ከዳር ቆመው በጸጥታ ይመለከቱ ጀመር። "ዶማውን አምጣ!" አለ ጎልማሳው። አንዱ ቆፋሪ ዶማውን አቀበለው።

ለአያሌ ዘመናት አፈርና እርጥበት ያነተቡትን የብረት ሳጥን በዶማው መክፈት ብዙም አላስቸገረውም። ሳጥኑ ሙሉ በሙሉ ከተከፈተ በኋላ ዐይኖቹ በጉጉት እያንጸባረቁ እጁን ወደ ሳጥኑ ሰደደ። ፊራ ተባ የሚል ይመስላል፣ ሌሎቹም በጉጉት ያዩታል። የበለዙና የወየቡ ብረታ ብረቶች ከሚመስሉ ነገሮች ውስጥ አንዱን ብድግ አድርጎ በእጁ እየደባበሰና እያገላበጠ ሲመለከት ቆየና ወደ ባሕታዊው ቀና አለ። ፊቱ በፈገግታ እየበራ "አባቴ! ልክ ነዎት፣ ይህ የመቅደላ ጦርነት ትሩፋት ነው!" አላቸው።

አራቱ ቆፋሪዎች እና ጎልማሳው ከጉድጉድ ውስጥ እያቀበሉ፣ ባሕታዊውና አሽከራቸው ደግሞ ከውጭ እየተቀበሉ የወርቅ፣ የብር፣ እና የተለያዩ የብራና መጻህፍት ዐይነቶች በላንድሮቨሩ መኪና ተጫኑ። ይህ ሥራ ሲጠናቀቅ ጀምበር ከምዕራብ አድማስ ውስጥ ጠልቃ ቀኑ መጪለም ጀምሮ ነበር።

ጎልማሳው ቆፋሪዎቹን "እዚህ ጠብቁ!" አለና ከጉድጓድ ወጥቶ ወደ ላንድሮቨሩ ሄደ። የመኪናውን የኋለኛውን በር ከፍቶ በእነስተኛ የመንገደኛ ሻንጣው ውስጥ ከልብሶቹ ስር የተቀመጠውን ባለ ነጥብ አርባ አምስት ኮልት ሽጉጥ አውጥቶ አቀባበለ። እናም በቀጥታ ወደ ጉድጓዱ ሄደና ጠርዙ ላይ ቆሞ፣ ቆፋሪዎቹ እጅግ ተገርመውና አፋቸውን ከፍተው እያዩት፣ በጥንቃቄ እያለመ፣ ቁልቁል መተኮስ ጀመረ።

"ዘመቻ መቅደላ" ተጠነሰሰ!

ምዕራፍ አንድ

ከዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ገበት ብሎ የሚገኘው እንግሊዝ ትምህርት ቤት በኢትዮጵያ እና በእንግሊዝ ባንዲራዎች አሸብርቋል። ከአንድ መቶ አርባ ዓመታት በፊት ዓፄ ቴዎድሮስ በመቅደላ አምባ ላይ ያሰሯቸውን የታላቋ ብሪታኒያን ዜጎች በኃይል ለማስፈታት ወደ ኢትዮጵያ የዘመተውና በጀኔራል ሮበርት ናፒየር የተመራው ጦር መቅደላ አናት ላይ በጠላትነት ያውለበለበው የእንግሊዝ ባንዲራ ዛሬ እንግሊዝ ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ በ "ወዳጅነት" እየተውለበለበ ነው።

የፖሊስ ሰራዊት የደንብ ልብስ የለበሱና የእጭር ርቀት የመገናኛ ራዲዮ (ዋኪ ቶኪ) የያዙ ፖሊሶች ጥንድ ጥንድ ሆነው ከትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውጭ ያካባቢውን ጸጥታ ይቆጣጠራሉ። ግቢው ውስጥ ደግሞ የሲቪል ልብስ የለበሱ የደህንነት ባልደረቦች ተሰማርተዋል። ጥሪ ከተደረገላቸው የዲፕሎማቲክ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተጠሪዎች፣ እና በኢትዮጵያውያን እንግዶች መካከል ተቀላቅለው የእያንዳንዱን ሰው እንቅስቃሴ በጥንቃቄ ይከታተላሉ። የትምህርት ቤቱ ዋና መግቢያ በር ላይ የተመደቡ ሁለት የደህንነት አባላት ደግሞ ከአዘጋጅ ኮሚቴው አንድ አባል ጋር ሆነው የተጋባዥ እንግዶችን ማንነት እያረጋገጡ ወደ ቅጥር ግቢው ያስገባሉ።

እያንዳንዱ ጥሪ የተደረገለት ተጋባዥ እንግዳ የመጣበት አውቶ ሞቢል ወደ ግቢው እንደዘለቀ በቀልጣፋ አሽከርካሪው የኋላው በር ይከፈትለታል። እንግዳው፣ በተለይም የውጭ መንግሥታት አምባሳደሮች በተጋነነ ኩራትና በተጠና ፈገግታ ከመኪኖቻቸው በመውረድ ቀደም ብለው ከደረሱት መሰሎቻቸው ወይንም በእነርሱ አጠራር "ከአቻዎቻቸው" ጋር ሲቀላቀሉ ተሽከርካሪዎቹ ተመልሰው ከግቢው ይወጡና የትምህርት ቤቱን አጥር ተከትሎ በተነጠፈው የማቆሚያ ሥፍራ (ፓርኪንግ) ላይ ይቆማሉ።

በዛሬው ዕለት እዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ የአገር ውስጥና የውጭ ሀገር ዲፕሎማቶችን እንዲሁም የተለያዩ የዓለም አቀፍ ማሕበረሰብና ተቋማት አባላትን ያሰባሰበው "ኤግዚቢሽን" ነው። ምናልባትም ለመጪዎቹ ዐሥርተ ዓመታት በቀላሉ ሊዘነጋ የማይችል "ታሪካዊ" አውደ ርእይ።

አውደ ርእዩ የተዘጋጀው አዲስ በተገነባው አዳራሽ ውስጥ ነው። ወደ አዳራሹ የሚያደርሰው ሠላሳ ሜትር ርዝመትና የሦስት ሜትር ስፋት ያለው መንገድም የደንብ ልብስ በለበሱ ጥቂት ፖሊሶች ይጠበቃል። በአጠቃላይ የፀጥታን ጉዳይ በተመለተ ያልተደፈነ ቀዳዳ የለም።

የእንግሊዝ መንግሥት የወንጀል መከላከልና ምርመራ ተቋም "ስኩተ ላንድ ያርድ" ፖሊስ አባላት የሆኑ አምስት እንግሊዛውያን መኮንኖችም አዳራሹን ፈትሸው ከስጋት ነጻ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ሁለቱ እዚያው አዳራሹ ውስጥ ሲቀሩ ሦስቱ ደግሞ ይህንን ታሪካዊ ዐውደ ርእይ በይፋ መርቀው የሚከፍቱትን ታላቅ እንግዳ አጅበው ሊያመጡ ወጡ።

ቀደም ሲል ይህ ኤግዚቢሽን ሊዘጋጅ የታቀደው ለንደን ከተማ ውስጥ ነበር። የኤግዚቢሽኑን መታቀድ በተመለከተ የመገናኛ ብዙሃን ዜናውን እየተቀባበሉ በስፋት አስተጋቡት። በመቀጠልም በቅኝ ገዢዋ እንግሊዝ ቅርሶቻቸው የተዘረፉባቸው ሀገሮች ተወላጆችና ዜጎች በለንደን ከተማ ዌስት ሚኒስትር አቤይ (የመንግሥት መቀመጫ) እና በሙዚየሙ አካባቢ ተከታታይ የተቃውሞ ሠልፍ ማድረግ ጀመሩ። ይህም ሁኔታ በየጊዜው ሲነሳና ሲጣል የነበረውን የ "ቅርሳችን ይመለስ!" ጥያቄ በታላቅ ግለት በመቀስቀሱ የእንግሊዝ መንግሥት ስጋት ገባው።

ይህን ስጋት ለማስወገድም የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች የኢትዮጵያ ባሕል ሚንስትር እና "ቅርሳችን ይጠበቅ ማህበር" ቀደም ሲል ያቀረቡላቸውን ጥያቄ ተቀብለው አውደ ርእዩ አዲስ አበባ ከተማ ላይ እንዲዘጋጅ እናም ልዕልት ኢዛቤል ኤግዚቢሽኑን በክብር እንግድነት እንዲከፍቱ ተስማሙ

**********////////**********

የክብር እንግዳዋ ልዕልት ኢዛቤል ከሥፍራው ባለመድረሳቸው ጥሪ የተደረገላቸው ዲፕሎማቶች፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተጠሪዎችና የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ እንዲሁም የውጭ ሀገርና ያገር ውስጥ ጋዜጠኞች የልዕልቲቱን መምጣት በትዕግስት በመጠባበቅ ላይ ናቸው።

'ኢየሩሳሌም ፖስት' የሚል ሰፋ ያለ ባጅ ደረቷ ላይ ያንጠለጠለችው ዮዲት የልዕልቲቱን መምጣት ከሚጠባበቁት የውጭ ሀገር ዜና ወኪሎች አንዷ ናት። ጥቁር

ለማያዊ መልክ ያለው ጂንስ ሱሪና ነጭ ሸሚዝ ለብሳለች። ጥቁር፣ ረገርም ፀጉሯ ትከሻዋ ላይ ተነስንሷል። የአጥቢያ ኮከብ የመሰሉ ዐይኖቿ ይንባበጋሉ። ወዲህ ወዲያ ስትራመድ ባንገቷ ያንጠለጠለችው የመታወቂያ ባጅ የተወጠሩ ጡቶቿ ላይ እየነጠረ የሕዝበ አዳምን ዐይኖች ወደ "ውበት አምላ" ይጋብዛሉ። ቦርሳዋን በግራ ትከሻዋ አንጠልጥላ በቀኝ እጇ አነስተኛ የድምፅ መቅጃ (ቴፕ ሪኮርደር) ይዛለች።

ዮዲት የአዘጋጅ ኮሚቴው አባል ለሆኑት ዶክተር ሥራውብዙ አየለ፣ ለኢትዮጵያ ባሕል ሚኒስትር አቶ ኢብራሂም ከማል እና ለእንግሊዝ አምባሳደር ፒተር ክላይፍ ቃለ መጠይቅ አድርጋላቸዋለች። አሁን የሚቀራት ለዊንዱሶሯ ልዕልት የምታቀርበውና አጭሩን የ ጋዜጠኛነት ሙያዋን የምትቋጭበት "ቃለ መጠይቅ" ብቻ ነው። ገና ከወዲሁ "ቃለ መጠይቁ" ምን መልክ እንደሚኖረው በዐይነ ሕሊናዋ ታይታት ሳታውቀው ፈገግ አለች። ወዲያውኑ 'ሰው አይቶኝ ይሸን?' አለችና ዙሪያዋን ቃኘች። ሁሉም የትኩረት ማዕከሉ፣ የዐይኖቹ ማረፊያ አድርጓታል።

**********////////**********

አዳራሹ በኢትዮጵያና እንግሊዝ ባንዲራዎች አሸብርቋል። ሃያ ሜትር ርዝመት ሠላሳ ሜትር ስፋትና ፣ የጣራው ከፍታ አሥራ አምስት ሜትር ነው። በሰሜናዊ ጫፉ በኩል የተለያዩ ዝግጅቶች የሚቀርቡበት ሁለት ሜትር ከፍታ ያለው መድረክ ሲኖረው በስተግራ መውጫና መውረጃ ደረጃዎች ተሠርቶለታል።

ከፍታቸው አምስት ሜትርና ስፋታቸው አራት ሜትር የሆኑ ከብረት የተሠሩ ሁለት ግዙፍ ተንሸራታች በሮች በደቡባዊ ግድግዳው በኩል አሉት። ወደ መድረኩ ያለው 'መግቢያ' ሌላው 'መውጪያ' የሚል ጽሑፍ በእንግሊዝኛ እና አማርኛ ተጽፈውበታል። የአዳራሹ ምሥራቃዊ ግድግዳ በየአምስት ሜትር ርቀት ላይ ሦስት ስፋፊ መስኮቶች ሲኖሩት መስኮቶቹም የመከላከያ ፍርግርግ ብረት ተገጥሞባቸዋል።

በመስኮቶቹ በኩል በረድፍ ተራርቀው የተቀመጡ ስፋፊና ረጃጅም ጠረጴዛዎች ላይ ከመቅደላ አምባ በእንግሊዝ ጦር የተዘረፉ፣ የተለያየ መጠን ያላቸው የብራና መጽሐፍት ተደርድረውባቸዋል። እነዚህን የብራና መጻህፍት ቅርሶች ለማስጎብኘት በያንዳንዱ ጠረጴዛ የቆሙት ሁለት ከለንደን መዚየም የመጡ እንግሊዛውያን የታሪክ ምሁራን እና አንድ ሀበሻ ናቸው።

ሀበሻው ዶክተር አንዱዓለም ይፍረያው ይባላል። በአክሰርድ ዩኒቨርሲቲ የመካከለኛው ምሥራቅና የአፍሪካ ታሪክ መምህር፤ እንዲሁም በኢትዮጵያ ታሪክዊ ቅርሶች ዙሪያ ልዩ ክህሎት (ስፔሻላይዜሽን) ያለው የአርባ ሁለት ዓመት ምሁር ነው።

በደቡባዊ የአዳራሹ ግድግዳ በኩል መውጫና መግቢያ በሮችን ጣልቃ እያስገቡ በተዘጋጁ መደርደሪያዎች ላይ ዐይነታቸው የበዛ ባሕላዊና ሃይማኖታዊ ቅርሶች ተደርድረዋል። ከነዚህም ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ የጎብኚዎችን ዐይን ይስባል ተብሎ የተገመተው መትደላ አምባ ላይ ዓፄ ቴዎድሮስ ሕይወታቸውን በእጃቸው ካጠፉ በኋላ እንግሊዞች ከራሳቸው ላይ ቆርጠው የወሰዱት ሹሩባቸው ይገኝበታል።

ይህኛውን ዘርፍ ለማስጎብኘት የቆሙት አንድ ከለንደን ሙዚየም የመጡ እንግሊዛዊ ፕሮፌሰር እና ሁለት ኢትዮጵያውያን ናቸው። አንደኛዋ ወይዘሪት ራሄል ግዛው የተባለች የሦላሳ ዓመት ወጣት ስትሆን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪዋን፣ ከኤደንብራ ዩኒቨርስቲ ደግሞ ሁለተኛ ዲግሪዋን ይዛ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት በተጨማሪም "ቅርሳችን ይጠበቅ" የተባለውን ድርጅት በሥራ አስኪያጅነት ታገለግላለች። ሦስተኛው ባልደባረባዋ ያሬድ መልካሙ ይባላል። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪውን፣ ከዚያም የኤደንብራ ዩኒቨርሲቲ በሰጠው የነፃ ትምህርት ዕድል ሁለተኛ ዲግሪውን አግኝቷል። በአሁኑ ጊዜ በለንደኑ የብሪቲሽ ናቹራል ሂስትሪ ሙዚየም ውስጥ በምሥራቅ አፍሪካ ክፍል በተመራማሪነት በመሥራት ላይ ይገኛል።

ያሬድ እንደ ራሄል ሁሉ የ"ቅርሳችን ይጠበቅ" ቋሚ አባልና ንቁ ተሳታፊ በመሆን እያሉ ቅርሶችን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመለስ በሚደረጉ ጥረቶች ሁሉ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከተና በማበርከትም ላይ ያለ ወጣት ምሁር ነው። ባለም ዓቀፍ መጣጥፎች ላይ በርካታ የጥናት ጽሑፎችን ስለሚያቀርብና ድምፁንም ከፍ አድርጎ "ቅርሶች ለባለቤቱ ሕዝብ ይመለሱ" የሚል መልዕክቱን ስለሚያሰማ በቅርስ ዘራፊ ሀገሮች ዘንድ ጥላቻን፣ ቅርሶቻቸው በተዘረፉባቸው ሕዝቦች ደግሞ ከበሬታን ለማትረፍ በቅቷል።

መድረኩ ላይ የተደረደሩትን ጥንታዊና ሃይማኖታዊ ስዕሎች፣ እንደዚሁም የተለያዩ ቅርሶች ለማስጎብኘት የተመደቡት ያፈት ኖህ እና ሳምሶን ኃይሌ ናቸው።

ያፈት የ12ኛ ክፍል ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ በኢትዮጵያ አየር ኃይል የተዋጊ ሄሎኮፕተር አብራሪነት ሥልጠና ወስዶ በምክትል መቶ አለቅና ማዕረግ ሲመረቅ ሀገሪቱ በእርስ በርስ ጦርነት የምትታመስበት ወቅት ነበር። የሰሜን ኢትዮጵያ አውደ ውጊያ ላይ ሄሊኮፕተሩ በአማፂያን ተመትቶ ሲወድቅ በደረሰበት አደጋ ከሰራዊቱ ተገለለ።

እንደገና ወደ ሰዕል ትምህርት ቤት ተመለሰ። "ሰዕል እና ጦርነት አንድ ዐይነት ሙያ ናቸው!" የሚል ፍልስፍናውን እያራመደ ነበር በጥሩ ውጤት የተመረቀው። ይህንን የሰዕል ሙያውን ወደ ፈረንሳይ ሀገር ተጉዞ በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ በመማር ከማበልፀጉም በላይ በተለይም በጥንታዊት ኢትዮጵያ ሃይማኖታዊ ሰዕሎች ላይ 'ስፔሻያላይዝ' በማድረግ የምርምርና ጥንታዊ ሰዕሎችን የማደስ 'ረስቶሪሽን' ባለሞያ በመሆን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማገልገል ላይ ይገኛል።

ሌላው የያፈት ባልደረባ የሃያ ስምንት ዓመቱ ወጣት ሳምሶን ኃይሌ በቀድሞው መንግሥት የአየር ወለድ ሰራዊት ውስጥ በሻምበልነት ማዕረግ ያገለገለና በሰሜን ኢትዮጵያ ተጧጥፎ በነበረው የእርስ በእርስ ጦርነት ውስጥ በደረሰበት የመቁሰል አደጋ ከሰራዊቱ የተሰናበተ ወጣት ነው። በአሁኑ ጊዜ 'ብራና' አስጎብኚ ድርጅት በአስጎብኚነት እንዲሁም በቅርሳችን ይጠበቅ ድርጅት ውስጥ በአባልነት እያገለገለ ይገኛል።

ምንም እንኳ ሳምሶን የሌሎች ባልደረቦቹን ያህል በጥንታዊ ቅርሶች ላይ የጠለቀ ምሁራዊ ክህሎት ባይኖረውም ከትውልድ ትውልደ ሲተረክ የሚችል የአስጎብኚነት ድርሻውን ለመወጣት በከፍተኛ ጉጉት ቦታውን ይዞ የኩባር እንግዳዋን በመጠባበቅ ላይ ይገኛል።

**********////////**********

ከትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውጭ በጣም የጎላ የማስጠንቀቂያ ድምጽ (ሳይረን) ተሰማ። ወዲያው አንዲት አነስተኛ ዘመናዊ የፖሊስ መኪና አናቷ ላይ ያለውን ቀይ መብራት እያንቦገቦገችና ሳይረኗን እያጮኸች ገባች። ቀጥሎም እጅግ ዘመናዊ በሆኑ ቢ.ኤም.ደብሊው ሞተር ብስክሌቶች የታጀበውና የዩናይትድ ኪንግደምን ባንዲራ የሚያውለበልበው ብርማው ሮልስ ሮይስ ሊሞዚን የዊንድሶሯን ልዕልት ኤልሳቤት ይዞ ግቢውን ዘለቀና አዳራሹ መታጠፊያ ሲደርስ ቆመ።

ሮልስ ሮይሱን በቅርብ ርቀት ይከተል ከነበረው ጥቁር ሰማያዊ ዘመናዊ ሬንጅ ሮቨር መኪና ውስጥ ሦስት እንግሊዛውያን የልዕልቲቱ አጃቢዎች በጥርጣሬ ወረዱ። ሁለቱ ከልዕልቲቱ ሮልስ ሮይስ ፊትና ኋላ ቆመው በጥቋቁር ሰፋፊ መነፅሮቻቸው የተሰበሰበውን ሰው ሲቃኙ እንደኖው አጃቢ የልዕልቲቱን መኪና የኋላ በር በዝግታ ከፈቱው።

ካሜራና የድምጽ መቅጃዎችን የያዙና ወደ ልዕልቲቱ ሊሞዚን ለመጠጋት የሞከሩ የዜና ወኪል አባላት የደንብ ልብስ በለበሱ ፖሊሶች ከእንቅስቃሴያቸው ተገደቡ። የዊንድሶር ልዕልት ኢዛቤል በታላቅ ግርማ ሞገስና በፈገግታ ከአውቶሞቢሉ ወርደው ለተሰበሰበው እንግዳ ቀኝ እጃቸውን ለሰላምታ አውለበለቡ።

ንጣቱ ከፀሓይ ብርሃን ጋር ዐይን የሚያጥበረብር ነጭ ኮትና ወደ ጉልበታቸው ወረድ የሚል ቀሚስ ለብሰዋል። ተረክዙ ረዥርም ጥቁር ጫማ ተጫምተዋል። ሰፊና ክብ ጥቁር ባርኔጣ አድርገዋል። ደረታቸውን በከፊል ያጋለጠው ጥቁር፣ ስስ፣ ዳንቴል መሰል ሽሚዛቸው በመያገር የወጠሩ ጡቶቻቸውን አጉልቶ ያሳያል።

ልዕልት ኢዛቤል በወርቅ ሃብል አንገታቸው ላይ ያንጠለጠሉትና ደረታቸው ላይ ወዲህ ወዲያ እያለ በፀሓይ ብርሃን የሚያንፀባርቀው ትልቅ የአልማዝ ፈርጥ የተሰበሰቡትን እንግዶች አፋቸውን በአድናቆት እንዲከፍቱ አስገድዷቸዋል።

'እያቶችሽ በዘመነ ቅኝ ግዛት ከሕንድ የዘረፉት ዝነኛው አልማዝ ነው!' አለች ጋዜጠኛ ዮዲት በሐሳቧ። በኢትዮጵያ የእንግሊዝ መንግሥት አምባሳደር ሚስተር ፒተር ክላይፍ እና የኢትዮጵያ ባሕል ሚንስትር አቶ ኢብራሒም ከማል ለዕልቲቱ ሰላምታ በመስጠት በክብር ተቀበሏቸው። ልዕልቲቱ በነጭ ጓንት በተሸፈነ ቀኝ እጃቸው ነው የጨበጧቸው።

**********//////////**********

አምባሳደሩ ልዕልቲቱን ወደ አዳራሹ መምራት ሲጀምሩ የሮልስ ሮይሱን በር የከፈተላቸው እንግሊዛዊ አጃቢያቸው ግራ ቀኙን በንቃት እየቃኘ በቀኝ እጁ የመናገሪያ ማይክራፎኑኑ ወደ አፉ አስጠግቶ "ሮያል አንድ! ትሰማኛለህ?" አለ። የመገናኛ መሣሪያው መናገሪያ የኮት ኮሌታ ላይ የሚለጠፍ፣ ማዳመጫው ወይንም መልዕክት መቀበያው ደግሞ ጆሮ ላይ የሚሰካ አነስተኛ መሣሪያ ነው። "ሮያል አንድ! ካን ዮ ሪድ ሚ?" አለ ደገመና።

ያገኘው መልስ ግን አዳራሹ ውስጥ የሚገኙ ባልዳረቦቹን ድምጽ ሳይሆን የሚንጫጫ የራዲዮ ሞገድ ወይንም ሺሺታ ብቻ ነበር።

ልዕልቲቱ በአምባሳደሩና በኢትዮጵያዊው ሚንስትር እየተመሩና በተጋባዥ እንግዶች ታጅበው ወደ አዳራሹ የሚያመራው መንገድ ላይ ሲገቡ የታሰረ ሮዝ ሪቫን ጠበቃቸው። እንዲት ዕድሜዋ ዐሥር ወይንም አሥራ አንድ ዓመት የኾናት ታዳጊ ልጃገረድ የተዋበ ያገር ልብስ ለብሳ፣ በጌጠኛ ስፌት ላይ መቀስ ይዛ፣ ወደ ልዕልቲቱ ቀረበች።

ልዕልት ኢዛቤል መቀሱን እንስተው ሪቫኑን ግራና ቀኝ ለሁለት ከቆረጡት በኋላ ቁራጩን ጨርቅና መቀሱን ስፌቱ ላይ አስቀምጠው ወዳጀቧቸው እንግዳዎች ዞሩና በፈገግታ ሲያጨበጭቡ እንግዶቹም እላቸውን ተከትለው አጨበጨቡ። የካሜራ መብራቶችም ተበለጨለጩ።

"ሮያል 1....ሮያል1..." በጭንቀት የተወጠረው እንግሊዛዊ አውንም በመገናኛ መሣሪያው ጥሪውን ያስተላልፋል። ነገር ግን ምላሽ የለም።

በልዕልቲቱ ቀዳሚነት "ኤግዚቢሽኑ ወደ ተዘጋጀበት አዳራሽ ጉዞ ተጀመረ።

**********////////**********

"የተከበሩ ልዕልት!" የሚል ጎላ ያለ ድምጽ ተሰማ። የጥሪው ድንገተኛነትና ጩኸት በወቅቱ ጭንቀት ውስጥ የነበረውን እንግሊዛዊ አሻቢ አስበረገገውና የቀኝ እጁን በአስገራሚ ፍጥነት ወደ ግራ ሽንጡ በኩቱ ውስጥ ሰደደው። ዮዲት አነስተኛ የድምጽ መቅጃዋን ይዛ ወደ ልዕልቲቱ ተጠጋች። ይህን ጊዜ አሻቢው እንግሊዛዊ ፈጠን አለና አስቆማት።

"ክብርት ልዕልት ኢዛቤል! በዛሬው ዕለት ለንብኚዎች በኦፊሴል መርቀው የከፈቱት ቅርስ፣ አያቶችዎና ቅድመ አያቶችዎ ከዚህ ሀገር የዘረፉት መሆኑን አያውቁምን?"

የተሰበሰቡት እንግዶች በዮዲት ጥያቄ ሲደናገጡ፣ ልዕልት ኤልሳቤት የተነካ ክብራቸውን እና በሃፍረት የቀላ ገጽታቸውን ለመሸፈን እንደምንም ፈገግ አሉና "ተዋት! አላልኳት።" አሉ አሻቢያቸውን። ዮዲት አነስተኛ ሪኮርደሯን ይዛ ተጠጋች።

"ጥያቄዬን ሰምተዋል ልዕልት?"

"እሞን ሰምቼሻለሁ" ብለው ወደ አዳራሹ መራመድ ሲቀጥሉ እንግሊዛዊው አምባሳደር በሱተንፊራ ሚኒስትሩ አቶ ኢብራሂም ከማል በስተቀኝ አጅበዋቸው መጓዝ ጀመሩ።

"የዘረፋችሁትን ቅርስ ለባለቤቱ መመለስ እንጂ ለባለቤቱ ሕዝብ "አውሳችሁ" ማለትበኝት ተገቢ ነውን?"

"አየሽ?" አሉ ልዕልት ኢዛቤል ወደ ፊት እየተራመዱ። "በዛሬው ዕለት የንብኝት ፕሮግራም ብቻ አይደለም ይዤ የመጣሁት። እነዚህ ታሪካዊ ቅርሳችሁን ለባለቤቱ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት የሚመለሱበትን መንገድ ለማመቻቸትም ጭምር ነው የመጣሁት።"

"ሮያል አንድ! በደንብ አይሰማኝም።!" አለ የልዕልቱ አጃቢ። "ምን? መጣሁ!" አለና ፈጠን ባለ አረማመድ ልዕልቲቱን አልፎ ወደ አዳራሹ ሲያመራ የሲቪል ልብስ የለበሱ ሁለት ኢትዮጵያውያን የደህንነት ባልደረቦች ፈጠን ብለው ተከተሉት። ዮዲትም በጥንቃቄ እየቃኘቻቸው ወደ ልዕልቲቱ በጣም ተጠጋችና የድምጽ መቅጃዋ ላይ አንድ ቁልፍ (በተን) ተጫነች። ልክ በዚህች ቅጽበት የእንግሊዙ አምባሳደር የዮዲት እጅ ላይ ባየው ነገር ደንግጦ ፊቱ ደም መሰለ። ልዕልቲቱ ደግሞ እጅግ የመገረምና የመደነቅ ስሜት ገጽታቸው ላይ እስኪነበብ ድረስ የዲትን ትኩር ብለው አይተዋት ለሚመጣው ነገር ሁሉ በሚያሰደንቅ እርጋታ ተዘጋጅተው ቆሙ።

**********/////////**********

እንግሊዛዊው የልዕልቲቱ ጠባቂና ሁለቱ የደህንነት አባላት የአዳራሹ መግቢያ በር ላይ ለመድረስ አምስት ሜትር ያህል ርቀት ሲቀራቸው ሁለት ሰዎች ከአዳራሹ በፍጥነት እየሮጡ በመውጣት አውቶማቲክ መሣሪያቸውን ወደ ሰማይ እየተኮሱ ወደ ልዕልቲቱ ገሰገሱ። ምድር ቀውጢ ሆነች። ተጠሪ እንግዶቹ በሙሉ እና ከጋዜጠኞቹ ከፊሉ በድንጋጤና በሽብር ነፍሱን ለማዳን መሬት ላይ ሲረበረብ አምባሳደሩ፣ ሚኒስትሩ፣ ዮዲት እና ልዕልት ኢዛቤል ብቻ ባሉበት እንደቆሙ ተገኙ። እንግዶች መሃል ተቀላቅለው የነበሩ የደህንነት አባላት ሽጉጦቻቸውን እየመዘዙ ወደ ዮዲት ሲወድሩ ተጨማሪ የፌደራል ፖሊሶች እየተሯሯጡ ወደ ግቢው ዘለቁ።

ሦስቱ የደህንነት አባላት በተመሳሳይ ቅጽበትና ፍጥነት ነበር እጆቻቸውን ወደ ወገባቸው የሰደዱት። ከአዳራሹ የወጡት ሁለት ታጣቂዎች በርካታ ጥይቶችን ሦስቱ የደህንነት አባላት እግር ሥር በመተኩስ እጆቻቸውን ወደላይ እንዲያነሱ አዘዟቸው። እንግሊዛዊው ትዕዛዛቸውን ተከትሎ እጆቹን ሲያነሳ ሁለቱ አበሾች ግን በትዕዛዙም ሆነ እግራቸው ሥር በተተኮሱት ጥይቶች ሳይደናገጡ ጥቋቁር ማካሮቭ ሽጉጦቻቸውን በፍጥነት እየመዘዙ መዘዙ።

በዚህ ወቅት ነበር "እቁመ! ቦምብ!" የሚል የሴት ድምጽ የተሰማው። ሁለቱ የደህንነት ሠራተኞች ለቅጽበት ያህል ግራ ተጋብተው ታዩ። የታጣቂዎቹን ግንባር በጥይት መንደል? ወይንስ ወደ ተሰማው የቦምብ ማስጠንቀቂያ ጥቃት መሰንዘር? እጅግ አስቸጋሪ ከሆኑ የሁለትና የሦስት ሴኩንዶች ማመዛዘንና ማመንታት በኋላ ከጀብደኝነት ይልቅ ባለ ሞያነት (ፕሮፌሽናልነት) አመዘነና ሦስቱም የደህንነት ባልደረቦች ከ ኋላቸው ወደ ተሰማው የቦምብ ማስጠንቀቂያ ዞሩ። "አይ ሃቭ ኤክስፕሉሲቭ!" አለች ዮዲት ከውብነት ወደ አስፈሪነት የተለወጡ ዐይኖቿን እያጉረጠረጠች።

የቀኝ እጇን የልዕልቲቱ ጡቶች መሃል አስገብታ በግራ እጇ አንድ ቀለበት ነገር ወደ ላይ ከፍ አድርጋ ለደህንነት ሠራተኞቹ አሳየቻቸው።

"ለመተኮስ ከሞከራችሁ የልዕልቱ ደረት ውስጥ የያዝኩትን እና መጠበቂያው የተነቀለውን ቦምብ አለቀዋለሁ። ተኩሳችሁ ብትመቱኝም ውጤቱ ተመሳሳይ መሆኑን እወቁ!"

አምን ተኩሰው ቢመቷት እንኳ በእጇ አጥብቃ የጨበጠችውን የቦምቡን የመጠበቂያ ቅጠል (ሴፍቲ) መልቀቋ አይቀርምና ዮዲትን ተኩሶ መጣል በተዘዋዋሪ መንገድ ልዕልቲቱን መግደል እንደሚሆን አበሾቹም ሆኑ እንግሊዛውያኑ እጃቢዎቿ አበክረው ተገንዝበውታል። ካዳራሹ የወጡት ሁለቱ ታጣቂዎችም በፍጥነት ገስግሰው ልዕልቲቱ፣ አምባሳደሩ እና ክቡር ሚኒስትሩ ላይ አስራኤል ሠራሽ ባለ ዘጠኝ ሚሊ ሜትር አዚ አውቶማቲክ መሣሪያዎቻቸውን ደገኑባቸው።

የትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢና አካባቢው ቀውጢ ሆነ። የሞባይልና የሳተላይት ስልኮች እንዲሁም የፖሊስ መገናኛ ራዲዮ ሞገድ ክባቢ አየሩን አጥለቀለቀው። መሬት ላይ ወድቆ የነበረው ዲፕሎማት፣ ባለሥልጣን እና ሌላውም ቀልቡን ሲገዛ ከወደቀበት እየተነሳ እግሬ አውጪኝ! አለ። ነፍሱን ለማዳን ሽሽቶ የነበረውና ወድቆ የተነሳው ጋዜጠኛ

ሁሉ እንደገና እየተመለሰ የጠለፋውን ትዕይንት በካሜራው መቅረጽ ጀመረ። በተለይም የውጭ ዜና ተቋማት ዘጋቢዎች ይህንን በሕይወት ዘመን አንዴ ብቻ ሊገኝ የሚችል እነርሱ 'ሴንሴሽናል' የሚሉትን ዜና በቀደምትነት ለማስተላለፍ የሚያደርጉት መንሰፍሰፍ እና ርብርቦሽ ብቻውን በጣም አስገራሚ ትዕይንት ነበረ።

የፖሊስና የደህንነት አባላት ልዕልቲቱን፣ አምባሳደሩን እና ሚኒስትሩን ከነ አጋቾቻቸው ከበው "እጅ ወደ ላይ! መሣሪያችሁን ጣሉ!" እያሉ ለአጋቾቹ ትዕዛዝ ይሰጣሉ። የመሣሪያውን ቃታ ለመሳብ የደፈረ ግን አልነበረም። ምክንያቱም የልዕልቲቱ ነጫጭ ጡቶች ውስጥ ኤፍ-ዋን የእጅ ቦምብ የወሸቀው የዮዲት እጅ ቦምቡን እንደሚለቀው አበክረው ተገንዝበውት ነበርና።

"ሚስተር አምባሳደር፣ በጥንቃቄ አዳምጡኝ!" አለች ዮዲት በተጣራ እንግሊዝኛ። "ማንም ሰው የኃይል እርምጃ ለመውሰድ ቢሞክር የልዕልቲቱ ደረት ላይ የያዝኩትን የእጅ ቦምብ አለቀዋለሁ!" ብላ ወደ ሚኒስትሩ አቶ ኢብራሂም ዞረችና በዐማርኛ "ክቡር ሚንስትር! ልዕልቲቱ በፈንጂ እንዳትበጣጠስ ከፈለጉ የፖሊስና የደህንነት አባላት መሣሪያቸውን አዙረው ግቢውን ለቀው እንዲወጡ ትዕዛዝ ይስጧቸው!" አለች። ከአዳራሹ የወጡት ሁለት ታጣቂዎችም ተመሳሳይ ትዕዛዝና ማስፈራሪያ እያሰሙ በአምባሳደሩና በክቡር ሚኔስትሩ አናት ላይ በርካታ ጥይቶችን አዘነቡ።

አምባሳደሩ እንግሊዛዊውን አኻቢ ጠርተው "የነዚህ አብዶች ተግባር አስኪለይለት ድረስ ማንም የኃይል እርምጃ እንዳይወስድ!" የሚል ቀጭን ትዕዛዝ ሰጡትና ወደ ሚኒስትር ኢብራሂም ዞረው በመለማመጥ ሁኔታ እያስተዛዘኑ ተመለከቷቸው። የባህል ሚኒስትር አቶ ኢብራሂም ለጥቂት ሴኮንዶች ሊያቅማሙ ቆዩ። ምንም ፍርሀት አይታይባቸውም። የተከበሩ የሀገራቸው እንግዳ ልዕልት ኢዛቤል ያውም ዐይናቸው እያየ እንዲህ ዐይነቱ አደጋ ላይ በመውደቃቸው የተሰማቸው ከሃፍረት የመነጨ ቁጣ ሰውነታቸውን ያንዘፈዘፈዋል። እንደምንም ቁጣቸውን ወደ ውስጥ ዋጡና "ኢንስፔክተር!" አሉት እነ ዮዲት ላይ ማካሮቭ ሽጉጡን ደግኖ የነበረውን አንዱን የደህንነት አፈሰር።

"አቤት!" አላቸው። "ለክብርት እንግዳችን ለልዕልቲቱ ደህንነት ሲባል ምንም ዐይነት የኃይል እርምጃ እንዳትወስዱ! ይህን መንግሥታዊ ትዕዛዜን ለሁሉም የፖሊስና የደህንነት አባላት አስተላልፍ። ይህን ትዕዛዝ በመተላለፍ በልዕልቲቱ ሕይወት ላይ አደጋ

እንዲደርስ ምክንያት የሆነ ማንኛውም የፀጥታ ሠራተኛ በሕግ ተጠያቂ ይሆናል! አሁን ባልደረቦችህን አዘዝና ወደ ኃላ ላባቸው!" ብለው የማያወላዳ ትዕዛዝ ሰጡት።

የፖሊስና የደህንነት አባላት ሁሉ ትዕዛዙን ተግባራዊ ለማድረግ ፈጽሞ ደስተኞች ባይሆኑም ሌላ ምርጫው አልነበራቸውም። እያቅማሙና እየተጓደዱ ወደ ኃላቸው መንቀሳቀስ ሲጀምሩ ዮዲትና ሁለቱ ታጣቂዎች በፈዝ ፈገግታ ተመለከቷቸው።

**********////////**********

"ወደ አዳራሹ!" አሉና ሁለቱ ታጣቂዎች አምባሳደሩን እና ክቡር ሚንስትሩን በኡዚ አፈሙዝ ሲገፏቸው፤ ዮዲትም ሁለት ነጫጭ ጡቶች መሃል የወሸቀችውን ቦምብ የጨበጠ እጇን እንዳጠበቀች ወደ ልዕልቲቱ ጆሮ አፏን አስጠግታ "ዮር ኤክሰለንሲ.....ሙቭ!" አለቻቸው ከፈገግታ ጋር።

ሦስቱ ጠላፊዎችና ሦስቱ ታጋቾች ወደ አዳራሹ ማምራት ሲጀምሩ እንግሊዛዊው የልዕልት ጠባቂና ሁለቱ ኢትዮጵያውያን የደህንነት አባላት በዝግታ እርምጃ በዐሥር ሜትር ርቀት ላይ ይከተሏቸዋል። በዚህ ሁኔታ ተጉዘው ሦስቱ ታጋቾች፤ ዮዲት እና አንድ ታጣቂ አዳራሹ ውስጥ ሲገቡ ሦስተኛው ታጣቂ ወደ ደህንነት አባላቱ ዞረና ኡዚውን ደግኖ ቆመ። ከኋላው የአዳራሹ ተንሸራታች በር ከውስጥ በኩል በማይታዩ ሰዎች እየተገፋ ሙሉ በሙሉ ሰመግጠም የአንድ ሜትር ብቻ ክፍተት ሲቀረው ቆመ።

በሩ ላይ ብቻውን የቆመው ታጣቂ እንግሊዛዊውን እጃቢ ወደ እርሱ እንዲመጣ በተጣራ እንግሊዘኛ አዘዘው። ሁለቱ አበሾች ሊከተሉት ሲሉ እንግሊዛዊው በእጁ ምልክት አስቆማቸው። ምንም እንኳ እንግሊዛዊው እና አበሾቹ አለቃና ጭፍራ ባይሆኑም ሁሉም ከአንድ የሙያ ባሕር የተቀዱ በመሆናቸውና ምክንያቱም ስለሚገባቸው ትዕዛዙን ተቀብለው ባሉበት ቆሙ።

ግቢው አሁንም ይተራመሳል። ሲቪል እና የደንብ ልብስ የለበሱ የፀጥታ አባላት የተከበሩትን ዲፕሎማቶች እና ሌሎችም ተጋባዥ እንግዶችን እንዲሁም የሀገር ውስጥ እና የውጭ ዜና ዘጋቢዎችን እየደጋገፉና እየተለማመጡ፤ በመጡበት መኪና እያሳፈሩ የትምህርት ቤቱን ቅጥር ግቢ ሲያስለቅቁ ይታያሉ።

"ያፈት አባላለሁ!" አለ የአዳራሹ በር ላይ የቆመው ታጣቂ። "በዛሬው ዕለት በዐይኖችህ የተመለከትከውን እገታና ጠለፋ የምመራው እኔ ነኝ። የምሰጥህን ትዕዛዝ

በትክክል ከፈፀምክ የልዕልታችሁን ሕይወት አደጋ ላይ የሚጥል ችግር አይኖርም። የኃይል እርምጃ ለመውሰድ የምትሞክሩ ከሆነ ግን ለሚፈለው የልዕልት ኢዛቤል "ለማያዊ" ደም ተጠያቂ ትሆናላችሁ። ጥቁርም ይሁን ነጭ ሁሉም የጸጥታ ሠራተኛ የትምህርት ቤቱን ቅጥር ግቢ ለቆ እንዲወጣ አዘዝ። እየሰማኸኝ ነው?"

"እምን!" አለ እንግሊዙ ያፌት ነኝ ያለውን ታጣቂ በቁጣና በጥላቻ እየተመለከተ። "የምታቅለሸልሽ ሰው ብትሆንም ለጊዜው ትዕዛዝህን አስፈፅማለሁ። በዚህ አጋጣሚ አንድ ነገር ልነግርህ እወዳለሁ። አሰና ኮቱን ገለጥ አድርጎ በማህደር ወገቡ ላይ የታጠቀውን ትልቅ ሽጉጥ ሰደፉን በቀኝ እጁ መታ መታ እያደረገ "መቼም ይሁን መቼ ግን በጣም በቅርብ ጊዜ ይሄ የአሸባሪ አንጎልህ ውስጥ አንድ ጥይቅ እንደምከትልህ በርግጠኝነት ነግርሃለሁ!" አለው።

ያፌት ፈገግ ብሎ ሽጉጡን ተመለከተና ወደ እንግሊዙ ቀና ብሎ "እ!" አለው በማድነቅ። "ነጥብ ሃያ ሁለት ሚሊ ሜትር ብራውኒንግ! በጣም ኃይለኛ ሽጉጥ ነው። በዚህ ዐይነቱ ሽጉጥ ብሞት ቅር አይለኝም። እኔ ደግሞ ሁለት ነገሮችን ላስጠነቅቅህ እወዳለሁ። አንደኛ፡ ስትተኩስ ላለመሳትህ እርግጠኛ ሁን። ተኩሰህ ከሳትከኝ ድጋሚ የመተኮስ ዕድል አታገኝምና! ሁለተኛ፡ እዚያ አዳራሽ ውስጥ ዓፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውን የገደሉበት ሽጉጥ ለትርኢት ተዘጋጅቷል። አንተና እነዚያ "ኤስ.ኤ.ኤስ" የምትሏቸው ኮማንዶ ተብዬዎች አንዳች የኃይል እርምጃ ብትሞክሩ በህበሻው ንጉሥ ሰማያዊ ደም (ንጉሣዊ ደም) የታጠበው ሽጉጥ ከአንድ መቶ ስድሳ ዓመታት በኋላ በእንግሊዛዊቷ ልዕልት ሰማያዊ ደም ይታጠብና ታሪካዊ ብቀላውን ይወጣል! ተግባባን?"

"ወቅቱ ሲደርስ ማን ዒላማውን እንደሚስትና ማን እንደሚመታ እናያለን። ለጊዜው ግን የልዕልቲቱና የአምባሳደሩ ሕይወት በእጅህ ነውና ትዕዛዝህን አስፈጽማለሁ።"

ያፌት ከፈገግታ ጋር ራሱን ወዘወዘና ወደ ኢትዮጵያውያኑ የደህንነት አባላት ዞረ። "አሁን ትዕዛዜን በጥንቃቄ አድምጡኝ" አላቸው።

"እንደኛ፡- የፀጥታ ሠራተኞችን ባስቸኳይ ከግቢው ታስወጣላችሁ። ሁለተኛ፡ ጥያቄዎቻችንን እንዲቀበሉን ያገር ውስጥ ጉዳይ ሚንስትሩን ባስቸኳይ ማነጋገር እንሻለንና እዚህ ሥፍራ በዐሥራ አምስት ደቂቃዎች ውስጥ እንዲገኙልን!"

እንደኛው የደህንነት ሠራተኛ በሞባይል ስልኩ በፍጥነትና በዝቅተኛ ድምጽ መልዕክት ያስተላልፋል። "አሁን አብረን እንቀላቀስ" አለ ያፌት ነኝ ባዩ ታጣቂ።

አሁን የደህንነት አባላቱ መገረምና ግራ መጋባት ታየባቸው። "እንተ ከእኛ ጋር? የት ልትሄድ ነው?"

ያፌት ሳቁን ለመቆጣጠር ታገለ። "አያችሁ? በኔ ላይ ምንም ዐይነት ችግር አለመድረሱን ካረጋገጣችሁ የኔ ጓደኞችም በልዕልታችሁ፣ በአምባላደሯችሁ፣ እና ከለንደን በመጡት አስጎብኝዎቻችሁ ላይ ምንም ዐይነት ችግር አለመድረሱን ያረጋግጣሉ። አሁን አብረን እንሂድና ግቢው ከተጋባዥ እንግዶችና ከጸጥታ አባላት ነጻ መሆኑን እናረጋግጥ!"

ይህን ሲናገር መደበኛ የሆነ የንግድ ሥራ (ቢዝነስ) ድርድር የሚያቀርብ ይመስል ድምፁ የተረጋጋና ዘና ያለ ነበረ።

"በጣም ጥሩ!" አለ አንደኛው የደህንነት ሠራተኛ የሞባይል ስልኩን እየዘጋ። "ጥያቄህን የሚቀበሉ የመንግሥት ባለ ሥልጣናት እየመጡ ነው። ተከተለኝ።"

ያፌት፣ እንግሊዙና የደህንነት አባላቱ ወደ ዋናው ግቢ በር በዝግታ በማምራት ላይ ሳሉ ኤ.ኬ 47 አውቶማቲክ ጠመንጃ በታጠቁ አራት ፌዴራል ፖሊሶች የታጀቡና የሲቪል ልብስ የለበሱ ሁለት አረጋውያን ግቢውን ዘልቀው ወደ አዳራሹ ሲታጠፉ በአምስት ሜትር ርቀት ላይ ተያይተው ቆሙ። "ያፌት ነኝ" የሚለው አጋች ላይ ፖሊሶቹ መሣሪያቸውን ሲወድሩ ሁለቱ ባለሥልጣን የሚመስሉ ሰዎች በዐይን ምልክት ብቻ መሣሪያቸውን ዝቅ እንዲያደርጉ አዘዟቸው።

"ያፌት አባላለሁ" አላቸው ለአፍታ እፍጥጦ ካያቸው በኋላ። አራቱ ፖሊሶች ጣቶቻቸውን የክላሺን ኮቭ ጠመንጃ ቃታ ላይ አሳርፈው አሳት የሚተፉ በሚመስሉ ዐይኖቻቸው ያፌትን ይገረምሙታል። እርሱ ግን ከናካቴው ወደ አነርሱ አልተመለከተም፣ መኖራቸውንም የሚያውቅ አይመስልም።

"ኮሎኔል ሰናይ አባላለሁ። እርሱ ሻለቃ ፍቅሩ ነው።" በማለት ጠና ያሉት መኮንን ራሳቸውን እና ባልደረባቸውን አስተዋወቁ።

ድርድሩ ተጀመረ!

ምዕራፍ ሁለት

"ይህ የኢትዮጵያ ራዲዮ ነው። የለዓቱን ዜና እናሰማለን። ካንድ መቶ አርባ ዓመታት በፊት ከመቅደላ አምባ በሰር ጀኔራል ሮበርት ናፒየር በተመራው የእንግሊዝ ጦር ተዘርፈው የተወሰዱ በርካታ የታሪክ ቅርሶች በውስት ወደ አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ በእንግሊዝ ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ በኤግዚቢሽን እንደሚታዩና ኤግዚቢሽኑን በክብር እንግድነት ተገኝተው የሚከፍቱት የዊንድሶር ልዕልት ኤልሳቤት እንደሚሆኑ፣ የእንግሊዝ ኤምባሲ ቃል አቀባይ አስታወቀ።"

ዶክተር ሥራውብዙ አየለ የምሽቱን ቀዝቃዛ አየር ከአስገራሚው ዜና ጋር እየኮመኮሙ በሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ደረሱ።

ቦሌን የሚያርገበግበው ነፋስ አካባቢውን ቀዝቃዛ ገሃነም አስመስሎታል። ወዳጅ ዘመዱን ለመቀበል ወይም ለመሸኘት የተሰበሰበው ሁሉ በብርድ ይንዘፈዘፋል። ዶክተር ሥራውብዙ መስኩቱን ዝቅ አድርገው፣ ቀዝቃዛውን አየር እየማጉ የምሽቱ ብሪቲሽ ኤርዌይስ በረራ የሚያመጣላቸውን እንግዳ መጠበቅ ጀመሩ።

ከዐርባ አምስት ደቂቃዎች ቆይታ በኋላ ግዙፉ ኤር ባስ የመንገደኞች ማመላለሻ ጀት የቦሌን አካባቢ ሲሰፍበት ቆይቶ በደህና አረፈ። ከሌላ የአርባ አምስት ደቂቃዎች ቆይታ በኋላ ገቢ መንገደኞች የጉምሩኩን ቁጥጥር እያለፉ ከተርሚናሉ መውጣት ጀመሩ።

ዶክተር ሥራውብዙ ሁለት የመንገደኛ ሻንጣዎችን በጋሪ የሚያስገፉ፣ በቀኝ እጁ ላምሶናይት ቦርሳ የያዘ፣ በአርባዎቹ የዕድሜ ክልል የሚገመት አንድ መንገደኛ ሲመለከቱ በታላቅ እፎይታ ተንፍሰው ወደ ሰውዬው አመሩ። እንግዳውም ተቀባይ የፈለገ ይመስላል። ዐይኖቹን በተሰበሰበው ሕዝብ ዙሪያ ሲያማትር ከዶክተር ሥራውብዙ ጋር ተያየና እርሱም ገፅታው በእፎይታ ፈገገ።

"እንኳ በደህና መጣህ።" አሉ ዶክተር ሥራውብዙ እጃቸውን ለሰላምታ እየዘረጉ።

"እንኳን በደህና ቆየኸኝ። ቀባሪ አያሳጣህ የሚለው የአገራችን ምርቃት 'ተቀባይ አያሳጣህ' በሚል መለወጥ አለበት።" አለ ዶክተር አንዱዓለም እሱም እጁን ለሰላምታ ዘርግቶና በፈገግታ ተፍለቅልቆ።

እነርሱ ከፊት ጋሪው ከኋላቸው እየተከተለ ወደ ዶክተር ሥራውብዙ ሜርሴዲስ አመሩ። ሻንጣዎች በመርሴዲሱ የኋላ መጫኛ ውስጥ ከተጫኑ በኋላ ዶክተር አንዱዓለም

ለጋሪ ገፈው ጉርሻ ለመስጠት የኪስ ቦርሳውን ሲያወጣ "የለም ተው! እኔ ብር ይገርለሁ።" አሉ ዶክተር ሥራውብዙ ኪሳቸው እየገቡ። ጋሪ ገፊው በግልምጫ አነሳቸው። ዕድለኛው ጋሪ ገፊ የሃያ ዶላር ጉርሻውን ተቀብሎ ዶክተር ሥራውን "ዐሥር ብርዎን ናና ከረሜላ ግዙበት!" ብሏቸው ወደ ተርሚናሉ ከነፈ። እንግዳው በሳቅ ጧ! ብሎ ፈነዳ።

ሁለቱ ዶክተሮች ወደ መሐል አዲስ አበባ ጉዞ እንደ ጀመሩ ነበር። በናፍቆትና በጉጉት ሲጠብቁት የነበረውን ርዕስ እንስተው መጨዋወት የያዙት። ወሬያቸውን ነፋስ እንኳ እንዲሰማው ስላልፈለጉ ይመስላል መስኮቶችን ዘግተውና ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው ነው የሚያወሩት።

"ኤግዚቢሽኑ አዲስ አበባ እንዲዘጋጅ መደረጉ ከሰማይ የወረደልን በረከት መሆኑ ይሰማኛል።" አለ ዶክተር ሥራውብዙ።

"አዎን ኤግዚቢሽኑ ከሰንደን ወደ አዲስ አበባ በመዞሩ ለዘመቻ መቅደላ ስኬት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።" አለ ዶክተር እንዱዓለም።

"በተደረገው ሰውጥ ሁሳችንም ተደስተናል። ነገር ግን አንድ ጥርጣሬ አሁንም ያብሰለስለኛል።" አሉ አረጋዊው ዶክተር።

"ምን ዐይነት ጥርጣሬ?" እንዱዓለም ጠየቀ።

"እነዚህን ተንኮለኛ ፈረንጆች መቼም አላምናቸውም። ማን ያውቃል? ከመቅደላ የተዘረፉ ቅርሶቻችንን በድንቅነሽ ለውጡን ቢሉንስ?"

ሁለቱ ዶክተሮች ተያዩና በሳቅ አሸኩ። "በነገራችን ላይ ባሕታዊው ዛሬውኑ ሊያይህ ይፈልጋል።" አሉ ዶክተር ሥራው።

"ምነው ምን አጣደፈው? ገና ከመንገድ ከመግባቴ?"

"ጊዜ የለም፤ ዘመቻ መቅደላ መንከባለል ጀምሯል።" አሉ ዶክተር ሥራው።

'ባትለኝም አውቃለሁ' አለ ዶክተር እንዱዓለም በሐሳቡ። ይህን እና ያንን እያወጉ ሒልተን ሆቴል ሲደርሱ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሆኖ ነበር። ዶክተር እንዱዓለም ከሰንደን ከመነሳቱ በፊት ያስመዘገበው ምቹ የሒልተን ክፍል ውስጥ ሻንጣዎቹን አስገብተው፤ ላምሶናይቱን ብቻ ያዘና በጥድፊያ ወጡ።

**********////////**********

ከግማሽ ሰዓት ጉዞ በኋላ በሰሜናዊ አዲስ አበባ አቅጣጫ መስፍን ሐረር መንገድ የሚገኘው የባሕታዊው መኖሪያ ቤት ደረሱ። የቅጥር ግቢውን በር የከፈተላቸውን ሰው ዶክተር ሥራውብዙ ሰረጂም ጊዜ ያውቀዋል። ምክኒያቱን ባያውቀውም ሰውዬውን በጣም ይጠላዋል። ለብዙ ዓመታት የባሕታዊው ጠባቂና ሹፌር ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል። ዶክተር ሥራውብዙ እና ዶክተር አንዱዓለም በሜርሴዲሱ ግቢውን ዘልቀው ሲገቡ በሩን የከፈተላቸው የባሕታዊው አገልጋይ ምን ጊዜም የማይፈታ ሬቱን እንደቋጠረ አንገቱን በመጠኑ ሰበር አድርጎ ሰላምታ አቀረበላቸው። ሁለቱ ዶክተሮች ከመኪናው ወርደው ገና በረንዳውን ከመርገጣቸው የላሉኑ በር ተከፈተና ባሕታዊው "እንዱዓለም ደህና መጣህ? ግቡ።" አሉ።

በስልሳዎቹ የዕድሜ ክልል የሚገመቱት ባሕታዊ ጥቁር የቀሳውስት ልብስ ለብሰው የመነኮሳት ቆብ ደፍተዋል። እጉድጓዳቸው የተወሸቁት፣ ትናንሽ እና ልቦናን ሰርስረው የሚያዩ የሚመስሉ ዐይኖቻቸው፣ ክሳታቸው፣ እና የሾሪ ሪዛቸው ልዩ ግርማን አላብሰዋቸዋል።

እንግዶቹ በታላቅ አክብሮትና ትህትና "እንደምን ነምት አባ።" እያሉ እጅ ነሱዋቸው። 'ይሄ ቂስ መስቀል የለውም?' ሁለቱም ዶክተሮች እያሰቡ ገቡ።

"ዶክተር እንዱዓለም እንኳ በደህና መጣህ! ስንጠብቅህ ነበር። ግቡ! ግቡ! ሶፋው ላይ አረፍ በሉ።" አሉና ባሕታዊው እንግዶቹ እንደገቡ በሩን ከኋላቸው ዘጉት።

ሁለቱ ዶክተሮች ዕድሜ ጠገቡ ሶፋ ላይ አረፍ ሲሉ የተቀበላቸው ጠረን የብዙ ምዕተ ዓመታት ዕድሜ ያለውን፣ አየር ያልበረዘው የእያሌ ብራና መፃህፍት ጠረን ነበር። ከግድግዳው ተጠግቶ በቆመው መደርደሪያ ላይ የተለያየ መጠን ያላቸው በርካታ የብራና መፃህፍት ተገጥግጠውበታል። በሌላ ማዕዘን ላይ በቆመ መደርደሪያ ላይም በአወሮፓውያን ሊቃውንት፣ የታሪክ ምሁራን የተጻፉ አያሌ መፃህፍት ተደርድረዋል። የምግብ ቤቱ ጠረጴዛ ላይ አንድ ጥንታዊ የብራና መጽሐፍ ተከፍቶ አጠገቡ ማስታወሻ ደብተርና ብዕር ተቀምጦ ይታያል። ባሕታዊው የጥናት ሥራቸው ላይ እንደነበሩ ሁለቱ ዶክተሮች ተገነዘቡ።

ቤቱ የአሥራ ሦስተኛው ወይንም የአሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያዊ መላፍንት መኖሪያ ቤት ላለመሆኑ ብቸኛ አስረጂው ከወደ ጥግ የሚታየው ቴሌፎንና አሮጌው ሶፋ ብቻ ናቸው።

"ሻይ ይዘጋጅላችሁ?" አሉ ባሕታዊው ከፊት ለፊታቸው ባለው ነጠላ ሶፋ ላይ እየተቀመጡ። በሰርሳሪ ዐይኖቻቸው ት...ክ ብለው እያዩዋቸው። ዶክተሮቹ ምንም ነገር እንደማይፈልጉ ከምስጋና ጋር አሳወቁ።

"እሺ ዶክተር አንዱዓለም!" አሉ ባሕታዊው ከእላቸው የሚወጣ በማይመስል አስገምጋሚ ድምፅ። "ታሪካዊ ቅርሶቻችን ለንደን ላይ በኤግዚቢሽን መታየታቸው ቀርቶ ወደ አዲስ አበባ እንደሚመጡ ካሳወክን ጊዜ አንስቶ ኦፐሬሽናችንን አዲስ አበባ ላይ ለማድረግ ወስነናል። ባልደረቦቻችንም ተነግሯቸው በደስታና በቁርጠኝነት ዝግጅታቸውን እያስኬዱት ነው። ለመሆኑ ቅርሶቻችን አዲስ አበባ የሚገቡት መቼ ነው?"

ዶክተር አንዱዓለም "እህህ!" ብሎ ጉሮሮውን አጠራና ወደ ባሕታዊው ዘመም እንደማለት አለ።

"እንግዲህ ሁሉም ነገር እንዳሰብነው ያለ እንከን ከተካሄደ ከዛሬ ጀምሮ ባሉት ሠላሳ ቀናት ወይም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቅርሶቹ አዲስ አበባ ገብተው የእንግሊዝ ኤምባሲ ይረክባቸዋል ብዬ አምናለሁ።

"ከለንደን አዲስ አበባ ለማድረስ ሠላሳ ቀናት የሚፈጀው ለምንድነው? ቅርሶቻችን ከመቅደላ ተዘርፈው እስከ ምጥዋ የተጓዝኩት በገሀሪ ተጭነው ነበር። ዛሬስ ከለንደን ወደ አዲስ አበባ የሚጓዙት በግመል ተጭነው ይሆን?"

በባሕታዊው የስላቅ ጥያቄ ሁለቱ ዶክተሮች ፈገጉ። ዶክተር አንዱዓለም መለሱ።

"ዋናው ችግራችን እነዚህን ጥንታዊ እና በዋጋ የማይተመኑ ወይንም 'ፕራይስ-ለስ' የሆኑ ቅርሶች ከለንደን አዲስ አበባ አምጥተን በኤግዚቢሽን ካሳየን በኋላ እንደገና ወደ ለንደን ለመመለስ ግዴታ ኢንሹራንስ መግባት አለብን። ሆኖም ግን ብዙዎቹ ትላልቅ ኩባንያዎች ለቅርሶቻችንን ዋስትና የጠየቁት ዋጋ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ነበር ጊዜ የወሰደብን። ሌላው ችግራችን ደግሞ አመቺና አስተማማኝ የሆነ የአየር ማመላለሻ፣ ጥብቅ ጥበቃና እጀባ የሚያደርግ የሴኩሪቲ ተቋም ማፈላለግ ነበረ። አሁን እነዚህንም አያሚላን ነው።"

"ሴኩሪቲ ጥበቃ ስትል ቅርሶቹን የሚያጅቡና የሚጠብቁ ሰዎች አብረው ይመጣሉ ማለትህ ይሆን?" አሉ ባሕታዊው የተለየ ንቃት እየታየባቸው።

"እምን እንደዚያ ማለቱ ነው።" አለ ዶክተር አንዱዓለም የባሕታዊው ስጋት እየገባውና ውስጡን ፈገግ እያለኘው። እነዚህ ቅርሶች ያዲስ አበባ ቆይታቸውን አብቅተው ወደ ለንደን እስኪመለሱ ድረስ በጉዞውም ሆነ በአውደ ርእዩ ወቅት "የስኮትላንድ ያርድ ጸጥታ አባላት ጥብቅ ጥበቃ እንዲያደርጉ መመሪያ ተሠጥቷቸው ነው የሚመጡት። እዩ እባቱ ፈረንጆቹ ከዋጋ ሁሉ በላይ ተመን የለሽ ግምት የሚጧቸውን የጥበብ ምንጭ የሆኑ ቅርሶች ላፍታ ታህል ጊዜ እንኳ ከዕይታቸው ሊለዩዋቸው አይሹም።"

ባሕታዊው ፍታ ያህል ዶክተር ሥራውብዙ /ላይ ዐይኖቻቸውን ተክለው በሐሳብ ይዋኘቁ ይመስል ሹል ጢማቸውን ወደታች ሲሰቡ ቆይተው "ባንተስ በኩል ለምቻችን ዝግጅታቸውን ምን አያደረሱት ነው?" ሲሉ ጠየቁት።

"በእኛ በኩል . . ." አሉ ዶክተር ሥራውብዙ የውይይቱ ሙሉ ተሳታፊ በመሆናቸው አየተደሰቱ። "በእኛ በኩል ዝግጅቱ ተጀምሮ ጥሩ እርምጃ እያሳየ ነው። ለንደን ላይ አቅደነው የነበረው አፓሬሽን ወደ አዲስ አበባ ሊለወጥ መቻሉ ሁሉንም ባልደረቦቻችንን በጣም አስደስቷል። በተረፈ ነገ ከቀትር በኋላ በኔ ቢሮ በሚደረገው ስብሰባችን ዶክተር አንዱዓለም ተገኝቶ ለአባላቱ ማብራሪያ ይሰጣቸዋል።

"በጣም ጥሩ!" አሉ ባሕታዊው ጢማቸውን እየጎነተሉና ዶክተር ሥራውብዙን እየተመለከቱ። "ሌላው ደግሞ አንድ እንድታጣራ የምፈልገው ነገር አለ። እነዚያ እስራኤሎች ያንን የዕላተ ሙሴ አሰሳና ፍለጋቸውን እንደገና ጀምረዋል የሚል መረጃ ደርሶኛል። በእርግጥ ጀምረውት ከሆነ ለምን በዚህ ወቅት እንደ ጀመሩት ማወቅ ይኖርብናል። ምናልባት ከዚህ ወቅታዊ የቅርሶች ኤግዚቢሽን ጋር የተዛመደ አንዳች ተንኰል ይኖረው ይሸናል። ለማንኛውም ዐይንና ጆሮህን ቀስረህ ነገሩን በንቃት ተከታተልልኝ።" ካሉ በኋላ ባሕታዊው አሁንም በትካዜ የሚቆዝም የሚመስል ፊታቸውን ወደ ዶክተር አንዱዓለም መልሰው "ትርጉሙን አዘጋጅተህ ጨረስክ? ይዘኸውስ መጣህ?" ሲሉ ጠየቁት።

ዶክተር አንዱዓለም ጥያቂውን ያልጠበቀው ይመስል "እ . . . ? ትርጉም አሉኝ? እ . . . . አምን ይገር መጥቻለሁ። የጨርስኩ ይመስለኛል።" ሲል እጉተመተመና

እግሩ ስር ወለሉ ላይ አኑሮት የነበረውን ላምሶናይት ቦርሳ ብድግ አድርጎ የቡና ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠው። ከግራ ደረት ኪሱ ውስጥ የንባብ መነፅር አውጥቶ ዐይኖቹ ላይ ሰካውና የላምሶናይቱን መክፈቻ ቁጥሮች እያዞረ ቦርሳውን ከፈተው። ውስጡን ፊታትሾ አንድ ዳንስ ያለ የታሸገ ፖስታ እስኪያወጣ ድረስ ባሕታዊው እና ዶክተር ሥራውብዙ በፀጥታ ይጠብቁት ነበር።

"ከነበረብኝ የሥራ ጫና እና የጊዜ አጥረት አኳያ እንከን የለሽ ነው ለማለት ባልደፍርም የተቻለኝን ያህል! ማለትም የተገነዘብኩትን ያህል ተርጉሜዋለሁ ብዬ እምናለሁ። በሶፍት ኮፒ ማለትም በዲስክ ብቻ ነው ጠቅላላ የትርጉም ሥራውን የያዝኩት። እናም ከእንድ ዲቪዲ ሌላ ምንም ዐይነት የወረቀትም ይሁን ሌላ ኮፒ የለም።" አለና ዶክተር አንዱዓለም ጥንታዊውን እነስተኛ የብራና መጽሐፍ ትርጉም የያዘውን ዲቪዲ የታሸገበት ፖስታ ለባሕታዊው አቀበላቸው።

"ጥሩ! እኔም እመለከተዋለሁ።" ባሕታዊው እሽጉን ፖስታ በእንክሮ እየመረመሩ ሲተክዙ ቆዩና ወደ ሁለቱ ዶክተሮች ቀና ብለው "ይገርማል!" አሉ። "ምስጢረ ጥበበ ሕዋዊ ወ ምድራዊ የተባለውን የብራና መጽሐፍ በዝና ብቻ ነበር የማውቀው። እስከ ዛሬ በእጄ ካልገቡት ጥቂት ድርሳናት አንዱ ነው። በእንግሊዞች እጅ መኖሩንም አላውቅም ነበር። ለኤግዚቢሽኑ ከለንደን ሲመጣ አየዋለሁ ብዬ አምናለሁ። የአንድ ሰው ስምና አድራሻ እነሆ ተቀበለኝ። ለተነሳንበት የጋራ ዓላማ የሚረዳን ነገር ሊኖረው ስለሚችል አግኝተህ አነጋግረው።" አሉና ባሕታዊው ስምና የስልክ ቁጥር የተፃፈበት እነስተኛ ወረቀት ለዶክተር አንዱዓለም አቀበሉት።

"እንድ የምጠይቅዎ ነገር አለኝ" አሉ ዶክተር ሥራው።

"እንደ ምን ያለ?"

"የገንዘብ ጉዳይ። ተጨማሪ ገንዘብ ያስፈልገናል።" ከነገ ጀምሮ የቁሳቁስ ግዢ እና የቤት ኪራይ ስለምንጀምር ወጪ . . ."

"የገንዘብ እጥረት አለብን። ለዚህ ኦፐሬሽን ወጪ የምናደርገው ገንዘብ የመነጨበት ጉድጓድ በጣም ትንሽ መሆኑን እንተም አበክረህ ታውቀዋለህ!" አሉ ባሕታዊው። በሰርሳሪ ዐይኖቻቸው ዶክተር ሥራውብዙን ለለሥር ሴክንዶች ያህል ሲመለከቱት ከቆዩ በኋላ . . . ." ሆኖም ግን እዚህ ከደረስን በኋላ ንዋይ አነሰን ብለን

ግንባራችንን እናጥፍም። ነገ ወደ ረፋዱ ላይ በተለመደው ባንክ ቤትና በተለመደው የሒሳብ ቁጥር አንድ መቶ ሺህ ብር ገቢ ይደረግልሃል። በተረፈ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን!" አሉና ዕድሜ ያደከማቸውን አጥንቶቻቸውን እያንቋቋ ከመቀመጫቸው ብድግ አሉ።

'በመቀበልም ማሰናበትም የማያምርበት መነኩሴ' አለ አንዱዓለም በልቡ። ሁለቱ ዶክተሮች ባሕታዊውን ተሰናብተው ሲወጡ ልክ ከምሽቱ አምስት ሰዓት ሆኖ ነበር። ጎዳናው ከተልከሰከሰ ውሾች እና አልፎ አልፎ የመብራት ምሰሶ ስር የተራቆተ ገላቸውን እያሳዩ ከቆሙ ጥቂት ሴተኛ አዳሪዎች በስተቀር ጭር ብሏል። ሴቶቹ እየሮጡ መኪናዎችን ለማስቆም ከንቱ ሙከራ ያደርጉ ነበር።

ምዕራፍ ሶስት

ከቀኑ ስባት ሰዓት ላይ ዶክተር ሥራውብዙ ዶክተር አንዱዓለምን በሚርስዲላቸው አሳፍረው ከሒልተን ሆቴል ወጡ። የአዲስ አበባ ፀሓይ ከተማውን በሙሉ ኃይሏ ታንፍረዋለች። አሳዳሪ የለሽ ውሾች በየመኪናው ጥላ ሥር ተንጋለው፤ ምላሳቸውን በረጅሙ እየጮለጮሉ ያለከልካሉ። በመንገድ ላይ የሚታዩት ሴቶች አለባበስ በአብዛኛው ገላቸውን ያራቆተ ቢሆንም የዕለቱ ሙቀት (በተለይም ግሎባል ዋርሚንግ) ይቅርታ ሊያስደርግላቸው ይገባል።

ዶክተር ሥራውብዙ መኪናቸውን ኢትዮጵያ ሆቴል አጠገብ የሚገኘው ባለ ሁለት ፎቅ አሮጌ ሕንፃ ስር ሲያቆሙ በአካባቢው የሚርመሰመሱት የመጽሔት፤ የጋዜጣ፤ የፊልም፤ የሲጋራ ነጋዴዎችና ለማኞች ከበቧቸው።

ሁለቱም ከመኪና ወርደው ዶክተር ሥራውብዙ በርቀት መቆጣጠሪያ የመኪናቸውን በሮች ከቆለፉ በኋላ "ብራና አስጎብኚ እና የጉዞ ወኪል" የተባለው ድርጅቱ ወደ ሚገኝበት ፎቅ መግቢያ አመሩ።

"አ! ቢሮህን የከፈትከው ጥሩ ቦታ ላይ ነው።" አለ ዶክተር አንዱ ዓለም ደረጃዎቹን እየወጡ።

"እምን ሥፍራው ጥሩ ነው። ነገር ግን ባሁኑ ጊዜ ቢዝነስ በጣም ቀዝቅዟብናል።"

"ምን አቀዘቀዘው?"

"አይስ ላንድ የፈነዳው አሳተ ገሞራ ያስከተለው አቧራ በድፍን አውሮፓ የአውሮፕላን በረራ ማስናከሱን አልሰማህም?" አሉ ዶክተር ሥራው ትንፋሻቸው እየተቆራረጠ። አንደኛውን ፎቅ ጨርሰው ሁለተኛውን ተያይዘውታል።

"ዶክተርም ይሁን ማንም ሰው ነጋዴ ከሆነ ገበያ የለም ወይም ቀዝቅዟል ለማለት ምክንያት አያጣም።" አለ ዶክተር አንዱ ዓለም። ሁለቱም ተያይተው ተሳሳቁ። የሁለተኛውን ፎቅ ደረጃዎች ጨርሰው ማረፊያው ላይ ሲደርሱ ከፊት ለፊታቸው "ብራና አስጎብኚና የጉዞ ወኪል" የሚል ጽሑፍ የተለጠፈበት ቢሮ ተቀበላቸው።

ዶክተር ሥራውብዙ ቀደም አሉና የቢሮውን በር ከፍተው በመያዝ አንዱዓለምን "ግባ" አሉት። የድርጅቱ ጸሐፊ ካቀረቀረችበት ሥራዋ ቀና ብላ ከፈገታ ጋር ብድግ አለች። "ጤና ይስጥልኝ ዶክተር አንዱዓለም እንኳ በደህና መጣህ!"

"መቅደላዊት። እንኳ ደህና ቆየሽኝ!" አላት እጅዋ ን እየጨበጠ።

"ዶክተር ሥራውብዙ፣ ሰዎቹ ቢሮው ውስጥ እየጠበቋችሁ ነው።" አለች ጸሐፊዋ።

በለንደን እና አዲስ አበባ መሃል ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚመላለሰው እንዱዓለም መቅደላዊትን ለሁለት ዓመታት ያውቃታል። 'ስሟም ውበቷም አስደላች ነው። በጣም ወጣት ከመሆኗ አንፃር አዛውንቱን ቀጣሪዋን አንተ ማለቷ ያስገርማል።' አለ በሐሳቡ።

ዶክተር ሥራውብዙ የግል ቢሯቸውን በር እጀታ ይዘው ፊታቸውን አዞሩና "መቅደላዊት" አሏት።

"አቤት ዶክተር።"

"አሁን ስብሰባ ስለምንጀምር ማንኛውንም አንግዳ መልሽልኝ። የውስጥ ስልክም እንዳታስተላልፊ።" አላት።

"እሺ ዶክተር።"

ሁለቱ ዶክተሮች ተከታትለው ወደ ውስጠኛው ቢሮ ከመግባታቸው ዙሪያውን በአግራሞት እየተመለከቱ ባሉበት ቆሙ። በተለይ ዶክተር ሥራውብዙ ቢሮ ውስጥ የተሰበሰቡትን ሰዎች የሚቃኙት አስተያየት 'ይህ የራሴ ቢሮ ነውን?' የሚሉ ይመስላል።

ዮዲት የዶክተር ሥራውብዙን ጠረጴዛ ላይ ጠልጠል ብላና ሚኒ ስከርት ቀሚሷ ያራቆታቸው ጭኖቿን አነባብራ ተቀምጣለች። ጥቁር፣ ረዥም ፀጉሯ ትከሻዋ ላይ ተነስንሷል። በረጃጅም ጣቶቿ የተለኩሰ ማርልቦሮ ሲጋራ ይዛለች።

ያፈት ምቹው የቆዳ ሶፋ ላይ ተቀምጦ የካው ቦይ ቡት ጫማ ያጠለቀባቸውን ሁለት እግሮቹን የቡና ጠረጴዛው ላይ አሳርፏል። ያሬድና ራሄል ትልቁ ሶፋ ላይ ጐን ተቀምጠው በለሆሳስ ድምጽ ያወራሉ። ሳምሶን ነጠላ ሶፋ ላይ ተቀምጦ ከጣራ በላይ ይስቃል። ያፈትና ዮዲት እየተጫጫኹ ይነታረካሉ። ሁሉም ለእፍታ ያህል ወደ ተከፈተው በር ዞር ብለው አዲስ ገቢዎቹን ተመለከቱና ከዮዲት በስተቀር ሌሎቹ ከመቀመጫቸው ተነሱ። "ዌል ካም ዶክተር አንዱዓለም! እንኳ በደህና መጣህ . . ." እያሉ ተራ በተራ ጨበጡት፣ አቀፉት።

ዶክተር ሥራውብዙ ራሳቸውን በትዝብት እየነቀነቁ "ምነው እንደዚህ ጋጠ ወጥ ኾናችሁ::" እባክህ ዶክተር እንዱዓለም ተቀመጥ!" አሉት የጽሕፈት ጠረጴዛቸው አጠገብ ያለ ምቹ የቆዳ ወንበር እያመለከቱ:: እንዱዓለም ተቀመጠ::

"የኔ አመቤት" አሉ ዶክተር ሥራውብዙ ዮዲትን በግልምጫ እየተመለከቱ:: "መልካም ፈቃድሽ ከሆነ ጠረጴዛዬን ልትለቂልኝ ትችያለሽ?" "አሉና ምቹ የቆዳ ወንበራቸው ላይ ተቀመጡ::

"ኦ ዶክተርዬ!" አለችና ከጠረጴዛው ወርዳ ተጪሶ ያለቀ የሲጃራ ቁራጭን መተርኮሻው ላይ አጥፍታ በማራኪ አረማመድ ወደ ዶክተር እንዱዓለም ቀረበች::

"ዶክተር እንዱዓለም እንኳ በደህና መጣህ!" አለችው::

ዶክተር እንዱዓለም በአጭር ቀሚስና በጠባብ ሸሚዝ የተከሸነው ውብ ቁመናዋን ከታች ወደ ላይ ቃኝቶ "እንኳ ደህና ቆየሽኝ ዮዲት:: ባለፈው ስንለያይ ይሄ ማርልቦሮሽ ዳግም አያገናኘንም ብዬ ስግቼልሽ ነበር!" አላት ከፈገግታ ጋር:: "ሰላምታ ያልለጠፍሽም ከዶክተር ሥራውብዙ ጋር የያዝሽውን የጠረጴዛ ይዞታ ይገባኛል ሙግት በተሸናፊነት እስክትለቂ እየጠበኩ ስለነበረ ነው:: ለመሆኑ የጠረጴዛውንም ካርታ ማስረከብ ይኖርብሽ ይሆን?"

በዶክተር እንዱዓለም ቀልድ ሁሉም ሳቁ::

"እባክህን ያሬድ ያንን መስኩት ከፈተውና 'ጉዲት' ያቦነነችውን ጢስ አስወጣልኝ" አሉ ዶክተር ሥራውብዙ::

"ተወው!" አለች ዮዲት:: እየተውረገረገች ሄዳ መስኩቱን ከፈተችውና ተመልሳ ከያሬት አጠገብ ያለ ባዶ ሶፋ ላይ ተቀመጠች:: ይኼኔ በመስኩት የገባው ኃይለኛ ነፋስ የሲጋራውን ጉም መበተን ጀምሮ ነበር::

ዶክተር ሥራው ጠረጴዛቸው ላይ የተቀመጠ ፔርሙስ ከፍተው በክዳኑ ወፍራም ቡና ቀዱና ተጎነጨለት:: ከፎቱ ሥር የሚገኘው ካፌ አንድ ፔርሙስ ወፍራም ቡና ለዶክተር ሥራውብዙ ማቅረብ የተለመደ ገበያው ነው::

"የጠዋቱን ስብሰባ የሰረዝነው . ." አሉ ዶክተር ሥራውብዙ ቡናውን ጨልጠው ከባያውን እያስቀመጡ:: "ዶክተር እንዱዓለም ሌሊት ስለገባ ማረፍ ስለነበረበት ነው:: ስብሰባችንን የምንጀምረው እርሱ በሚሰጠን ገለፃ ይሆናል:::

አንዱዓለም ሁሉንም አንድ በአንድ ቃኛቸውና ዐይናቹን ባዶ ሥፍራ ላይ በማሳረፍ ንግግሩን ጀመረ።

"ከዛሬ ጀምሮ በሠላሳ ቀናት ውስጥ በ "ውስት" የተሰጡንን ታሪካዊ ቅርሶች ከለንደን ናቹራል ሂስትሪ ሙዚየም ወደ አዲስ አበባ እናመጣለን። የቅርሶቹን ዐይነትና ብዛት የሚዘረዝር ሰነድ ይዣለሁ።"

አንድ ኮፒ ክላምሶናይት ቦርሳው አውጥቶ ቀረብ ለሚለው ያፈት አቀበለውና ..." አንድ ኮፒ ብቻ ነው የያዝኩት። ተራ በተራ ልትመለከቱት ትችላላችሁ። ሌላ ኮፒ ማባዛት ግን አይቻልም። ለሴኩሪቲ ጉዳይ ሲባል!" አለ ማስጠንቀቂያውን ጫን አድርጎ።

"ፊ . . .ው!" ዮዲት ረጂምና የጉላ ፉጨት ስታሰማ ሁሉም ወደ እርሷ ዞሩ። "በጣም ጥሩ የሴኪውሪቲ ማስጠንቀቂያ ነው ዶክተር ጀምስ ቦንድ!" አለችው። ሁሉም በሳቅ አውካኩ። አንዱዓለም ንግግሩን ቀጠለ።

"አጠቃላዩ ዕቅድ ማለትም የብሪቲሽ ናቹራል ሂስትሪ ሙዚየም ዕቅድ ይህንን ይመስላል። አስፈላጊ የተባሉትን ቅድመ ዝግጅቶች ሁሉ ካጠናቀቅን በኋላ ቻርተር ባደረግነው የንግድ አውሮፕላን ቅርሶቹን እንጭናለን። አዲስ አበባ፣ ቦሌ አየር ማረፊያ ስንደርስ የእንግሊዝ ኤምባሲ በሚያቀርባቸው ሁለት ልዩ ካሚዎኖች በሣጥን የታሸጉት ቅርሳ ቅርሾች ይጫኑና ቀበና ወደሚገኘው የእንግሊዝ ኤምባሲ ቅጥር ግቢ ይወሰዳሉ። ከቦሌ ጀምሮ እስከ እንግሊዝ ኤምባሲ በሚደረገው ጉዞ ላይ እና ኤግዚቢሽኑ ተጀምሮ እስኪያበቃ ድረስ የሴኩሪቲ ኃላፊነቱን የሚረከበው የፌዴራል ፖሊስ ቢሆንም ሁለት የስኮትላንድ ያርድ ፖሊሶችም ቅርሶቹን ለመጠበቅ ተመድበዋል።"

"ቅርሶቹ እንግሊዝ ኤምባሲ ከደረሱ በኋላ እኔና አብረውኝ የሚመጡ ሦስት እንግሊዛውያን የለንደን ሙዚየም ባለደረቦቹ፣ እንዲሁም ከባህል ሚንስትር እና ከኤንባሲው ከተውጣጡ ሰዎች ጋር በመሆን እያንዳንዱን ቅርስ ከጭነት ወይንም ከሺፕመንት ሊስቱ ጋር አመሳክረን እንመዘግባለን። የሚቀጥለው ሥራ ኤግዚቢሽኑን ማደራጀት ነው።"

ሁሉም ጸጥ አረጭ ብለው እያደመጡት ነው።

"የእንግሊዝ ትምህርት ቤት አዳራሽ ውስጥ የሼልፍ ማቆም፣ የኤሌክትሮኒክስ ሴኪውሪቲ መሣሪያዎችን፣ ካሜራዎችን መገጣጠም እና ሌሎችም አስፈላጊ ዝግጅቶች

ተጠናቀው ሲያበቁ ቅርሶቹ ወደ ትምህርት ቤቱ በተመላላይ ማጓጓዣና ጥበቃ ተወስደው በየፊርጃቸው ይተመጣሉ። ልዕልት ኤልሳቤት በተያዘላት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት አዲስ አበባ ለመግባት አንድ ቀን ሲቀራት ቅርሶቹ ለትዕይንት ዝግጁ ይሆናሉ። ይህንን ኤግዚቢሽን በኦፊሴል የምትከፍተው የዊንድሶሯ ልዕልት ኤልሳቤት ናት።"

"ልዕልት ኢዛቤል? የማን ልዕልት ናት? ጠያቂው ሳምሶን ነበር።

"የዊንድሶር ልዕልት ኢዛቤል።"

"ለምን እርሷ ሆነች?" ራሄል ጠየቀች።

"ቀደም ሲል የአፍሪካ ቀንድ አገሮችን ለመጎብኘት የተያዘላት ፕሮግራም ነበር። የቅርስ ማስመለስ ዘመቻው ላይ ዲፕሎማሲያዊ እገዛዋን እንድትሰጥ በማሰብ የኢትዮጵያ መንግሥት ነው አጋጣሚውን ተጠቅሞ ኤግዚቢሽኑን እንድትከፍት የጋበዛት።"

"በጣም ድንቅ አጋጣሚ ሆነልን!" አለ ያፈት።

"አጃቢ ጠባቂዎቿ ስንት ናቸው?" ሳምሶን በድጋሚ ጠየቀ።

"በየትኛውም ሥፍራ ስትዘዋወር ከንኗ የማይለዩ ጠባቂዎቿ አምስት ናቸው። በውጭ ሀገሮች ጉብኝት ስታደርግ ሦስት የስኮት ላንድ ያርድ ፖሊስ ባልደረቦች ይጨመሩላታል። ማለትም ከሠላሳ ቀናት በኋላ አዲስ አበባን ጨምሮ በምታደርገው የምሥራቅ አፍሪካ ጉብኝቷ ከስምንት ያላነሱ አጃቢዎች ይኖሯታል ብለን እናምናለን።" አለና ዶክተር አንዱዓለም አድማጮቹን ቃኛቸው። ዮዲት ማርልቦሮ ሲጋራ ለኩሰችና ከወንበሯ ተነስታ ወዲህ ወዲያ እየተንጎራደደች ሲጋራዋን ስትምግ ሁሉም በአንክሮ ተመለከቷት። በጨረሻም ዶክተር አንዱዓለም ፊት ቆመችና "ዶክተር ጀምስ ቦንድ!" ስትል ንግግሯን ጀመረች። አንዱዓለምን ጨምሮ ሁሉም ፈገግ አሉና የምትናገረውን በጉጉት ጠበቁ።

"ዶክተር ጀምስ ቦንድ። የኛ ዕቅድ የተከበሩትን ታሪካዊ ቅርሶቻችንን መጥለፍ ወይንም ማስመለስ እንጂ አንዲት የእንግሊዝ ግብር ከፋይ ሕዝብ ሽክም የሆነች ልዕልትን ማገት አያካትትም። በዘረፋ የተወሰዱብንን እና በ 'ውስት' የመጡ ቁሳቁሶችን መልሰን መገረፍ አንድ ነገር ነው። የታላቋ ብሪታኒያን አምባሳደር፣ እንዲሁም የኢትዮጵያን የባሕል ሚኒስቴር ማገት ሌላ ጉዳይ ነው። በዚህ ሁሉ የተወሳሰበ ነገር ላይ የልዕልቲቱ

ጣልቃ መግባት በኦፐሬሽናችን ላይ ምን ዐይነት እንድምታ ይኖረዋል?" ዮዲት ጥያቄዋን ስትጨርስ ወደ ወንበሯ ተመልሳ ተቀመጠች።

"ይህን ጥያቄ እኔ መልስ ብለጥበትስ?" አለች ራሄል። ሁሉም ወደ እርሷ ዞሩ። መልስ የሰጣት ባይኖርም ቀጠለች።

"እየሽ ዮዲት? አሁን በምንገኝበት ዘመነ ግሎባላይዜሽን ዓለም አቀፍ የኾነ 'ፀረ ሽብር' ዘመቻ በተያዘበት ጊዜ ልዕልትም አገትሽ ወይንም ተራ የአውሮፕላን መንገደኛ ድርጊትሽ የሚፈረጀው በ'አሸባሪነት' ነው። ስለዚህ ማንንም ብናግት 'አሸባሪ' መባላችን አይቀርም። እንደውም ይህችን 'ባለ ሰማያዊ ደም' ከሰማይ የወረደችልን በረከት አድርገን ማየት አለብን። ምክንያቱም የተዘረፉብንን ቅርሶች በኃይል ለማስመለስ በምናደርገው ትንቅንቅ ልዕልቲቱንም አብረን ብናግት በእርሷ ምክንያት ከፍተኛ ዓለም አቀፍ የሚዲያ ትኩረት እንስባለን ብዬ አምናለሁ።"

"እ!" አለች ዮዲት በፈዝ ቃና። "ዋናው ግባችን ዓለም አቀፍ የሜዲያ ትኩረት ፍለጋ አልመሰለኝም ነበረ።"

"እዚህ ላይ!" አለ ያፈት ጣልቃ ገብቶና ድምጹን ከፍ አድርጎ። "ወደ ጎላ ተመልሰን ሥራችን በሚያስከትለው ውጤት ላይ መነታረኩ አስፈላጊ አይመስለኝም። ምክንያቱም ገና ከመጀመሪያው ይህን የጠለፋና እገታ ተግባር ለመፈፀም ስንነሳ . . . በሂደቱ ሕይወታችንን ለማጣት እንደምንችልም አምነንበት ነው የገባንበት።"

"አዎን ይህ ትክክል ነው።" አሉ ዶክተር ሥራውብዙ። "የዛሬው ስብሰባ ዋናው አላማ ልዕልቲቱን ማገት ስለሚያስከትለው ውጤት አይደለም። ካስፈለገ ልዕልቲቱን ከታጋቾቹ መሃል መልቀቅም እንችላለን።

ሳምሶን ከወንበሩ ተፈናጥሮ በመነሳት "በፍጹም! አይደረግም! እንለቃትም!" ሲል በደም ፍላት ጮኸ። የዘመቻ መቅደላ አባላት በሳቅ አወኩ።

"እንለቃትም!" አሉ አረጋዊው ዶክተር ሳቃቸውን ሲጨርሱ። ሳምሶንም በራሱ ስሜታዊነት እየሳቀ ተመልሶ ተቀመጠ።

"አዎን! ዋናው ነገር....." አለ ዶክተር አንዱዓለም..... "ለንደን ላይ አቅደነው የነበረው ሥራ ወደ አዲስ አበባ መዞሩ ብዙ ውስብስብ አደጋዎችን የሚያስወግድልን ከመሆኑም ሌላ ቅርሶቻችንን ወደ መጨረሻው ማረፊያቸው በጣም ያቀርብልናል።

"መልካም ብለሃል።" አሉ ዶክተር ሥራው። "ካሁን በኋላ የምናወራው ስለ ሥራ ክፍፍል ነው። ባልሳሳት ቀደም ሲል ያደረግነው የሥራ ክፍፍል ቀጣይ ይሆናል።" አሉና ወደ ራሄል ፊታቸውን አዞሩ።

"ወይዘሪት ራሄል። ከነገው ዕለት ጀምሮ ኤግዚቢሽኑ የሚካሄድበትን አዳራሽና አካባቢውን ታጠኚያለሽ። በተለይም የትምህርት ቤቱን አዳራሽ አጠቃላይ አሠራርና አቀማመጥ በተመለከተ ፕላኑን በወረቀት ላይ አስፍረሽ ታቀርቢያለሽ።" ላምሶን የመሣሪያዎቹን ግገር፣ ያፈት የሄሊኮፕተሩን መረጃ ጉዳይ ትጨርሱና በቶሎ ወደ ልምምድ እንገባለን። ዮዲት ከቤተ—እስራኤሎች ቡድን ጋር ተገናኝተሽ ተጨማሪ የለው ኃይል የምናገኝበትን ድርድር ታደርጊያለሽ። የቃል ኪዳኑን ታቦት (ጽላተ ሙሴ) ፍለጋ አዲስ አሰሳ ጀምረዋል የሚል ወሬ ስለሚናፈስ ትክክለኛነቱን ታጣሪያለሽ። እኔ የትርሶቹን ማረፊያ ሥፍራ ለማዘጋጀት ከነገ ወዲያ ወደ ሰሜን ስለምጓዝ ራሄል በያዝሽው ሥራ ላይ አስተማማኝ ቤት . . . አ . . ሴፍ ሃውስ ትከራያለሽ።"

"የገንዘብ ጉዳይስ?" ላምሶን ጠየቀ።

"አንድ መቶ ሽህ ብር በአዲሱ አካውንት ገቢ ስለተደረገ ለመሣሪያ ግገር አስፈላጊ የሚሆነህን በቼክ እየፈረምኩ አስጥሃለሁ።"

"ለግገር ወደ ክልሎች ብጓዝስ?"

"በጥራው የተወሰነ ይዘህ ትሄዳለህ። ተጨማሪ ካስፈለገህ አመቺ በምትለው ባንክ በሐዋላ ይላክልሃል።"

"እዚህ ላይ" አለ ያሬድ። "ወደ ኋላ መመለስ አይሁንብኝና ቤተ እስራኤሎችን በዚህ ፕሮጀክታችን ማሳተፍ አዋቂነት አልመሰለኝም።"

"ምን መሰለህ?" አሉ ዶክተር ሥራውብዙ። "ፈላሻዎችን . . . አ . . . ይቅርታ፣ ቤተ እስራኤሎችን በዚህ ኦፐሬሽናችን ውስጥ የምናሳትፍበት ሊሚት (መጠን) አለን። ቤተ እሥራኤሎቹ ከኤግዚቢሽኑ የሚፈልጉት ነገር አለ። አሱን ለማግኘት ሲሉ እንደሚተባበሩን አምናለሁ።

"ምንድነው የሚፈልጉት?" ያሬድ ጠየቀ።

"ዮዲት፣ ይህን አንቺ ብታብራሪውስ?"

ዮዲት ከመቀመጫዋ ተነስታ ወዲህ ወዲያ መንጎራደድ ጀመረች። ፊቷ ቅጭም ብሎ በሐሳብ ባሕር ውስጥ የሰጠመች መስላለች። እርምጃዋን ገታ አድርጋ የዶክተር ሥራውብዙ ጠረጴዛ አጠገብ ስትደርስ ደገፍ ብላ ቆመች።

"ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚማልዱኝ የተበተኑት ሴቶች ልጆቼ ቁርባኔን ያመጡልኛል።"

ትንቢተ ሶፎንያስ - ምዕራፍ 3 ቁ. 9-10

አለትና ለጥቂት ሴኮንዶች የ 'ኦፕሬሽን መቅደላ' አባላትን ስታያቸው ቆየች።

"እግዚአብሔር ቁርባኔን መልሱልኝ ያለው የቃል ኪዳን ታቦት ነው። ስለዚህ የቤተ— እስራኤሎች ቡድን አጥብቆ የሚፈልገው ነገር ይህንን ጽላት ነው። ከዚህ ኢግዚቢሽን የሚፈልጉት ሌላ ነገር ካለና ካላወቁኝ አሳውቃችኋለሁ።"

"እሱን እኛም አጥብቀን የምንፈልገውና የምንጠብቀው የእምነታችን ማረጋገጫ ነው።" አለች ራሄል።

"ቤተ—እስራኤሎች ለምን በዘመቻ መቅደላ ይላተፋሉ? ለማንኛውም እኔ እንደሚገባኝ ከሆነ የቃል ኪዳኑ ታቦት ራሱ የመኖሪያ ሀገርና ሥፍራውን መርጧል። በማንም ኀላፊነትና ፈቃድ ሊነቃነቅ አይችልም።" አለ ያፈት።

"እ! ግሩም አባባል!" አለች ዮዲት። "እኛ ቤተ—እስራኤሎች በኦፕሬሽን መቅደላም ይሁን በማናቸውም ኢትዮጵያዊ በሆኑ ጉዳዮች ለምን እንደምንላተፍ ልንገራችሁ?" አለችና በፀጥታ ተመለከተቻቸው። መልስ የለጣት የለም።

"እውን ነብር ሸንጉርጉርነቱን ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊነቱን ይለውጣልን?"

የኦፕሬሽን መቅደላ አባላት በመሉ ከመቀመጫቸው ተነስተው አጨበጨቡላት። ዮዲት በፈገግታና በእክብሮት እጅ ነሳች።

"ለተነሳው የያሬድ ጥያቄ በቲ ሌክቸር ያገኘን ይመስለኛል።" አለ ሳምሶን።

ሁሉም በሳቅ አውካኩ።

"ዶክተር አንዱዓለምን መሸኘት አለብኝ። እናንተ የቀራችሁ ነገር ካለ መነጋገር አለያም እንደተለመደው ተራርቃችሁ መውጣት ትችላላችሁ። በተረፈ ነገ በዛሬው ሰዓት ስብሰባ ይኖረናል።" አሉና ዶክተር ሥራውብዙ ከመቀመጫቸው ሲነሱ አንዱዓለምም ፈለጋቸውን ተከትሎ ብድግ አለ።

የዘመቻ መቅደላ አባላት ከስብሰባ ሲወጡ "ያላስፈላጊ ሰዎችን" ትኩረት ላለ መሳብ በተራራቀ ጊዜ አንድ ወይንም ሁለት እየሆኑ መውጣት የተለመደ ጥንቃቄ የታከለበት አሠራራቸው ነው።

ምዕራፍ አራት

የዘመቻ መቅደላ አባላት ትውውቃቸው የሚጀምረው ከወጣትነት የትምህርት ቤት ዘመን አንስቶ በመሆኑ ከመላመድ፣ ከመቀራረብና ከመፈቃቀድ የተነሳ የአንዳንዶቹ ግንኙነት ከዓላማና የጋራ ከሆኑ እሳቤያዊ እንድነቶችም አልፈው የፍቅር ግንኙነትን እስከ መመሥረት የደረሱም ስለነበሩ ከዶክተር ሥራዊ ቢሮ ሲወጡ በዚህ ግንኙነት መሠረት የተጣመሩት ያፌትና ዮዲት፣ እንዲሁም ራሄልና ያሬድ ነበሩ።

በቅድሚያ ያፌትና ዮዲት አብረው ወጡ። ደረጃውን ሲወርዱ ያፌት እጇን ይዞ የሚያነጠንጡ ጡቶቿን በስርቆሽ እያየ ምራቁን ዋጠና "እሁን ወዴት ነው የምናመራው? ወደ ሆቴልሽ እንሄድም?" ሲል ጠየቃት።

"እኔ ወደ ምመርጠው ሥፍራ ነው የምንሄደው።" አለች ቆጣ ብላ። ስትቆጣ ጠይም ፊቷ ፍም ስለሚመስል ይበልጥ ታምራለች። "ደግሞም ወደ እኔ ሆቴል የመሄድ መብት ማንም አልሰጠህም!"

"እንቺ ያረፍሽበት ሆቴል ንግድ ቤት ነውኮ! ዳንኪራ ልረግጥበትም አችላለሁ።"

"ለኔ ብለህ አዶክርቤም ጨፍርበት!" ያፌት ከልቡ ሳቀ።

ከኢትዮጵያ ሆቴል ደጃፍ የሚቆሙት አነስኛ ታክሲዎች ተርታ ሲደርሱ ዮዲት ያንዱን ላዳ ታክሲ መስኮት መታ መታ አደረገችው። አሽከርካሪውም ያኑብ የነበረውን የስፖርት ጋዜጣ በፍጥነት አጥፎ "አቤት!" አላት።

"ቦሌ ሚኒ ስንት ልክፈልህ?"

"ሃምሳ ብር።" ጥቂት እንኳ አላመነታም።

"በጣም አበዛኸው። ሠላሳ ብር ልክፈልህ።"

"ከአርባ ብር በታች አያዋጣኝም። ነዳጁን ጨመሩብን እኮ!"

"ይሁን!" አለች ዮዲት የኋላውን በር እየከፈተች። ያፌት ተከትሏት ገባ።

ከኢትዮጵያ ሆቴል ወደ ቀኝ ታጥፈው የመስቀል አደባባይ ቀይ መብራት ሲያቆማቸው ዮዲት ከቦርዋ መመልከቻ መስታወት አውጥታ ከንፈሯን ቻፕስቲክ መቀባባት ጀመረች። መስቀል አደባባይን አልፈው የቦሌን መንገድ እስኪጀምሩ ድረስ ፀጉሯን በመስተዋት እያየች ታስተካክል ነበር።

"ለውብትሽ አትጨነቂ። የጥራት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት አሰጥሻለሁ።" አለ ያፈት።

"እትጨነቅ!" አለችው በለላ ድምፅ። "ደግሞም ያንተ ሰርተፍኬት ፎርጂድ ሊሆን ይችላል።" አለችው።

"የኳራው ስብሰባ . . ."

"ኡ.....ፍ! ኖ ሾፕ ቶክ!" ብላ ቆረጠችው።

"ግን . . . ቦሌ ሚኒ ለምን የእኔ እመቤት?"

"ሃምበርገርና ጁስ አምሮኛል።" አለችና ዮዲት መስታወቷን ቦርሳዋ ውስጥ ከተተች። አሁን ወሱ ሰፈር መጠምዘዣ ላይ ለመድረስ ሃያ ሜትር ያህል ይቀራቸዋል።

"እባክሽ እዚህ አይቤክስ እንግባ" አለ ያፈት።

"አይኸንም!" አለች በቁጣ። ያፈት አየት አድርጓት ዝም አለ።

አንዴ ወደ ፊት አንዴ ወደ ኋላ ስታማትር የቆየችው ዮዲት ከጥቂት ደቂቃዎች ጉዞ በኋላ "ይቅርታ ወንድሜ" አለች አሽከርካሪውን። "ሐሳቤን ለወጥኩኝ። መኪናህን እዙርና ወደ አይቤክስ ሆቴል አድርሰን።"

የተገረመው ሹፌር ፍሬቻውን አብርቶ መኪናውን ሲያዞር ያፈት የፌዝ ፈገግታ ብልጭ አደረገ።

.....//////////.....

አይቤክስ ሆቴል ሲደርሱ "ወደ ግቢው ልግባ?" ሲል ሾፌሩ ጠየቃት።

"የለም እዚህ ይበቃል።" ዮዲት ቦርሳዋን ከፍታ ባለ ሃምሳ ብር ኖት አወጣችና ያዘው አለችው። ሹፌሩ ከምስጋና ጋር ተቀበለ።

ዮዲትና ያፈት የሆቴሉን ሎቢ ዘልቀው በእጅ ብቻ እየተፈለፈለ የተሠራና የተዋበ ባሕላዊ ምቹ ወንበር ላይ አረፍ አሉ።

ዮዲት ማርልበሮ ሲጋራዋን ስታቀጣጥል ያፈትም ከፓኬቱ አንድ አውጥቶ ለኮሰ። "መቼ ነው የራስህን ፓኬት የምትገዛው?"

"እንኢንስ ሌላ ልጣ ይቅርና በክንፈርሽ ያረጠብሽውን ባጤስ ደስ ባለኝ።" ዮዲት ሳቀች።

አስተናጋጁ መጥቶ ከፈገግታ ጋር ሰላምታ ሰጣት።

ቻፕ፡ እና በደሉ ስፔሻል" ብላው ያፈትን እየት አረገቸው። እርሱም በደሉ ቢራ አዘዘ

ታምሪያለሽ" አላት አስተናጋጅ ሲሄድ።

'አድናቶት አልሻም።" አለች ሲጋራዋን እየማገች።

'ለምን?"

"የሰው ልጅን በቀላሉ የሚያጠፋና ማንነቱን ከሚያስረሱ ነገሮች ካሉ አድናቶት፤ አዳናቂ እና መደነቅን መሻት ናቸው። እንደ ኮንቪዶር ቤልት ሳታውቀው ወደ ገደል ይዞህ ሸው ይ ል።"

አስተናጋጁ ቢራቸውን ከፍቶላቸው፣ ቺፕስና ኬችአፑን በወጉ አስቀምጦ እስኪሄደ በዝምታ ተሸበቡ። ዮዲት አልፎ አልፎ ከወዲያኛው ማዶ ሶፋ ላይ ተቀምጦ ኒውስ ዊክ ይሁን ታይምስ መጽሔት የሚያነበውን አውሮፓዊ ታስተውላለች። ያፈት ደግሞ ከንፈሯን ያራሰ የቢራ አረፋ በምላሷ ልላ፣ ብርጭቆውን ስታስቀምጥ ለትንግርት ይመለከታታል።

"ዮዲት?"

"እ?"

"እንቺ ቢራውን ጠጪ። እኔ አረፋውን ከከንፈርሽ በምላሴ ልላስ።"

ዮዲት ከልቧ ሳቀችና "ወደው አይስቁ!" አለችው። "አሁንስ ልቤን አነፈርከው።"

'በላት በጨማ ልብሽን ላፍርሰው... ብሏል ጥላሁን ገሰሰ። እኔ ሳጫወትሽ እንቺ ግ አንደ ተኮ ጎደ ውስጥ እያሰብሽ እየተጫወትሽኝ ነው።"

"እንዴት?" አለኝ ዮዲት ነቃ ብላ። እያንዳንዱ የፀጉሯ ዘለላ ቀጥ ብሎ ሲቆም ተሰማት።

"ታክሲ ውስጥ የፊት መስተዋት አውጥተሽ ፊትሽን የምታስተካክይ መስለሽ ወደ ኋላ የምትመለከቺው ማንን ነበረ? የሚከታተለን ማን ነበረ?"

"እ . . ልገባኝም" አለችና ቢራዋን ተጎንጭታ አስቀመጠች።

"አየሽ ዮዲት። ከፕሮፌሽናል ሰው ጋር መሆንሽን የረሳሽው መሰለኝ። ቦሌ ሚኒ ውስድን ብለሽ ታክሲ አዘዝሽ። ከመሐል መንገድ ወደ አይቤክስ መልስን ስትይ አዘዝሽው። አይቤክስ እስክንደርስ አንዴ በመስታወትሽ ሌላ ጊዜ ግራ ቀኙን በዐይናችሽ

ትቆጣጠሪያለሽ። አሁን ደግሞ የምታወሪ፣ የምትጠጪ፣ የምታጨሺ እያስመሰልሽ እዚያ ማያ መጽሔት የሚያነብ የሚያስመስለውን ተራ የፈረንጅ ሰላይ በወያኔ ቱራኛ ትክታተያለሽ። ሁለታችሁም ቀሽም ሰላይና ተሰላይ ናችሁ! ለመሆኑ ሰውዬው ማን ነው?"

ዮዲት ቱና ተንፍሳ ቢራዋን ጨለጠችና የሲጋራ ፓኮዋን ይዛ ከወንበሯ ተነሳች።

"ስማ ያፌት ከክንፈራ የቢራ አረፋ መላስ የምትፈልግ ከሆነ ሩም ሰርቪስ አዘዝና ክፍሌ ውስጥ ጠብቀኝ። እኔ ከራሌፕሽን ፍሰክ ስልክ ደውዬ መጣሁ።"

"ለምን ከክፍልሽ ወይንም በሞባይልሽ አትደውይም?"

"አሁን ለመጠቀም የምፈልገው ከራሌፕሽን ነው። ደግሞ ምንም የሚያጣላህ ነገር የለም።" አለችው ትዕግስቷን ጨርሳ።

**********//////////**********

"እሺ ጀምስ ቦንድ! ይህ ሁሉ የድብቆሽ ጨዋታ ዓላማው ምንድነው?"

አውሮፓዊው ሰውዬው ደንገጥ ብሎ ያነብ ያስመስለው ከነበረው መጽሄት ላይ ቀና ሲል ዮዲትን አያትና "ተቀመጭ ዮዲት። ከቴል አቪቭ የተላከልሽ አንድ አስቸኳይ መልዕክት አለኝ።" አላት።

"ታዲያ ለምን በተለመደው የግንኙነት ሜካኒዝም አልተጠቀምክም ቤን?" አለችና አጠገቡ ካለው ሶፋ ላይ እየተቀመጠች ሲጋራዋን ለኮሰች።

"የተለመደውን የግንኙነት ሜካኒዝም ብጠቀም ላገኝሽ የምችለው ከሁለት ሳት በኋላ ነበረ። ድንገተኛ (አስቸኳይ) ጉዳይ ስለተከሰተ ነው የተከተልኩሽ። ግን ሌላ ሰው አብሮሽ መኖሩን ስመለከት ማንነቱን ላለማላወቅ ስል በስውር ተከተልኩሽ።"

ቤን አዲስ አበባ የገባው በቤልጂዩም ፓስፖርት ቢሆንም የቤተ—እስራኤሎችን ማሕበር ለመቆጣጠር የተላከ የሞሳድ ወኪል ነው።

አስተናጋጁ በድጋሚ ያመጣለትን ቢራ ከፍቶ እስኪሄድ ጠበቀና አንድ አነስተኛ ወረቀት አቀበላት።

"የተከበርሽ ውድ ልጅ" ብሎ ይጀምራል። ዮዲት 'በጣም አስቸኳይ' ብላ ተረጎመችው። "የንግድ ባዛር ሲከፈት የፍየል ቆዳ መግዛት እንፈልጋለን . . . ! (ኤግዚቢሽኑ ሲከፈት የቤራና መጽሐፍ መጮለፍ እንፍልጋለን)" ዮዲት እንዲህ

እየተረጎመች ደብዳቤውን ዘለቀችው። አጠር ያለውና በኮድ የታሠረውን መልዕክት አንብባ ስጥጨርስ ወረቀቱን እኪሷ ስትከት የቤን ዐይኖችም አብረው ኪሷ ውስጥ ሲገቡ ተመለከተችና "አወድመዋለሁ" አለችው።

"ይገባኛል።" አላት።

"ለመሆኑ ቤን . . . ይህን ጥንታዊ መጽሐፍ ገና ይዘቱንና ምንነቱን ሳያውቁ እንዴት ለማስረቅ ወሰኑ?" ስትል ጠየቀችው።"

"እሱን ለእነርሱ ብንተውላቸውስ?"

"በጣም ጥሩ ቤን።"

"ሌላ የቀረ ነገር አለ" አላት። "ከዚህ የቅርስ ማስመለስ ኦፐሬሽናችሁ በስተ ጀርባ ያለውን ዋናውን ሰው ማንነት ለማወቅ እንፈልጋለን። ዶክተር ሥራውብዙ የቅርሳችን ይጠበቅ ድርጅታችሁ ፕሬዚዳንት ቢሆንም ዋናው አንቀላቃሹ ግን "ባሕታዊው" በሚል መጠሪያ የሚታወቅ ሰው እንደሆነ ቴል አቪቮች ያምናሉ። ማንነቱን እንድታጣሪላቸውም ይፈልጋሉ። የቴልአቪቭ ሰዎች በጣም ግፊት አደበዙብኝ ነውና ጊዜ መስጠት የሌለብሽ አስቸኳይ ተልዕኮሽ ነው።"

"አየህ ቤን! እኔ በየቀኑ አዳዲስ ትዕዛዞች በተቀበልኩ ቁጥር እነዚያን ሁሉ ትዕዛዞች ለመፈፀም በማደርገው እንቅስቃሴና ሩጫ ዐይን ውስጥ ልገባ እችላለሁ። እናም የቅርሳችን ይጠበቅ ባልደረቦቼ የሁለት ዓለም ሰላይ መሆኔን በቀላሉ ሊጠራጠሩኝ ይችላሉ።"

"ዮዲት የምትናገሪው እውነት ነው። ነገር ግን ይህ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመጨረሻ ጊዜ የምታከናውኚው ተልዕኮሽ እንደሚሆን ተነግሮኛል። ይህ ጥንታዊ መፃህፍት ለሀገራችን እስራኤል የጽላተ ሙሴን ያህል ተፈላጊነት አለው። ተደራራቢ ትዕዛዝ የተሰጠሽ በዚህ ምክንያት ነው። ስለዚህ የተቻለሽን ሁሉ ማድረግ አለብሽ።" አለና ቤን አተኩሮ ተመለከታት።

"የተቻለኝን ብቻ ሳይሆን ከዚያም በላይ እጥራለሁ። የገንዘብ ጉዳይ እንዴት ነው? ተጨማሪ ያስፈልገኛል።"

ቤን ቢራውን ተጎንጭቶ አስቀመጠና ከኩቱ ደረት ኪሱ ውስጥ የታሸገና ምንም ጽሑፍ የሌለበት ፖስታ አውጥቶ አቀበላት። ዮዲት በፍጥነት ኪሷ ከተተችውና ተነሳች።

"አንድ ነገር እነግርሃለሁ!" አለችው። "ጥላህን ከላዬ ላይ አንሳ! (በስውር አትከታተለኝ) ደህና ዋል።" ብላ ጥላው ሄደች።

ቤን የግራ ደረት ኪሱ ውስጥ እጁን ላከና አንዲት በጣም ትንሽ የድምፅ መቅጃ ቴፕ ተጭኖ አጠፋት። ዛሬውኑ ድምጹ ወደ ዲጂታል ይለወጥና በሳተላይት መገናኛ ወደ ቴል አቪቭ ይላካል።

ዮዲት ደረጃዎቹን እየወጣች ወደ ክፍሏ ስታመራ 'አንተ ደደብ! የቀዳኸው ድምፄ ከእስራኤላዊነት ይልቅ ለኢትዮጵያዊነት የማደላ መሆኔን ሊነግራቸው አይችልም' አለች በሐሳቧ።

ምዕራፍ አምስት

ያሬድ እና ራሄል ከዶክተር ሥራውበዙ ቢሮ ሲወጡ ሃስተኛው ጥንድ ናቸው። የዓላማና የፍቅር ጥንዶች። እጅ ለእጅ ተያይዘው የሁለቱን ፍቅ ደረጃዎች እያዘገሙ ወርደው ወደ ውጪ ብቅ ሲሉ ከተማውን ስታንፍረው የዋለችው ፀሐይ በረድ ብላ እየጠለቀች ነበር። ራሄል የቶዮታ ሊፍት ባክ መኪናዋን በር ከፍታ ወንበሯን ከያዘች በኋላ ከኋኗ ያለውን የተሳፋሪ በር መቆለፊያ ወደ ላይ ሳበችው። ያሬድ በሩን ከፍቶ ገባና መስኮቱን ዝቅ አድርጎ በሩን ዘጋው።

"ሒሳብሽ ስንት ነው?" አለች ራሄል የፓርኪንግ ሠራተኛዋን። ቲኬት ተቆጥሮ ሒሳብ ተከፍሎ ሲያበቃ ራሄል ሞተር አስነስታ መኪናዋን ማንቀሳቀስ ጀመረች። ያሬድ ሲጋራውን አቀጣጥሎ በረጅሙ ማገለት።"

"ምናለበት እናንተ ሱሰኞች ለማናጨሰው ብታዝኑልን" አለች ራሄል ማርሽ እየለወጠችና ከኢትዮጵያ ሆቴል ወደ ስታዲየም የሚያመራውን ትራክ ጎዳና እየተቀላቀለች።

"እናንተስ ምናለበት ይህን መዐዛው የሚለነፍጥ ሽቶ እየነሰነሳችሁና ውብ ገላችሁን እያራቆታችሁ ባታማልሉን?" አለ ያሬድ። ራሄል ፈገግ አለችና የነዳጅ መሰቀኪያውን ተጫነችው።

"ይህ ኦፐሬሽናችን ከለንደን ወደ አዲስ አበባ መለወጡ ታላቅ አፎይታ ሰጥቶኛል። ታውቃለህ ያሬድ? የቅርሳችን ኤግዚቪሽን አዲስ አበባ ላይ እንዲዘጋጅ የተደረገው ለውጥ የተነሳንበትን የጠለፋ ዓላማ ስኬት በእጅጉ እንደሚያቀላጥፈው አምናለሁ።"

"እምን ልክ ነሽ" አለና የሲጋራውን ጢስ በመስኮት ወደ ውጭ ካወነነ በኋላ ወደ ራሄል ዞረ። "ይህ ሁላችንም በአንድ ልብ የተስማማንበት ጉዳይ ነው። ቅርሶቻችንን ለንደን ከተማ ውስጥ ለማስመለስ የምናደርገው ተጋድሎ የመገናኛ ብዙሃኑን ትኩረት ከመሳብና የተረሳውን የ 'ቅርሳችንን መልሱ' ጥያቄ እንደ አዲስ ከማቀጣጠል ያለፈ ውጤት አይኖረውም ነበር። አሁን እዚህ ሀገራችን ላይ መሆኑ ግን ከፕሮፖጋንዳ ዘመቻም በላቀ ሁኔታ ቅርሶቻችንን ከዘራፊዎቹ እጅ ቀምተን የማምለጥ ዕድላችንን ከፍ ያደርገዋል።"

ይህን ሲላት የሐሊቱን ዳገት ጨርሰው ወደ ግራ በመታጠፍ የዳግማዊ ምኒልክን ቤተ መንግሥት በስተቀኛቸው ትተው እየተጓዙ ነበር።

"ያም ሆነ ይህ ተልዕኮአችን ባይሳካ እንኳ እኔ የምፈልገው ከሃገሬ ቅርሶች ጋር ወደ መቃብሬ መውረድ ነው። በተረፈ በሂደቱ ለሚከሰተው ወይንም ሊከሰት ስለሚችለው "እገጭ አጓ" ብጋት ቀርቶ ደንታ የለምኝ።" አላት እጅግ ተከሳትሮ።

"እገጭ-እጓ" ሲላት ለሚጠብቀን ፍልሚያና ለምንከፍለው መስዋዕትነት ማለቱ እንደሆነ ገብቷታል። እሷም ሆነች ባልደረቦቿ ታሪካዊ ቅርሶቻቸውን ከዘራፊዎች እጅ መልሰው በኃይል ለመቀማት በሚደረግ ተጋድሎ ሕይወታቸውን እንኳን መስዋዕት ለማድረግ ግንባራቸውን እንደሚሰጡ ከልቧ ታምናለች። ራሄል ይህን ስታስብ ምንነቱ የማታውቀው አንዳች ደስ የሚል መቀት መላ አካላቷን ሲወራት ተሰማትና 'የጀብደኝነት ጉጉት ነው? ወይስ የውሲብ ፍላጎት? ሁለቱም መሆን አለበት!' ስትል አሰበችና የመኪናዋን መሪ ዘውራ የድል ሐውልትን እየዞረች ያሬድን እየት አደረገችው።

"ያሬድ"

"አቤት"

"ቀኑ እስኪደርስ ቸኩያለሁ!"

"እኔ ግን በዚህች ደቂቃ አፖርትመንትሽ የምንደርስበትን ቅፅበት ነው የናፈቅኩት።"

ይህን ሲነጋገሩ ከዳግማዊ ምኒሊክ ትምህርት ቤት ፊት ለፊት የሚገኘው ሕንፃ ስር መኪናዋን አቆመችና "ደርሰናል!" አለችው በፍትወት ስሜት በጉጉት እያየችው።

**********/////////**********

ሳምሶን ከዶክተር ሥራው ቢሮ ለመውጣት የመጨረሻው ሰው ነበር። "ዛሬ አዳርህ እዚህ ነው?" ብለውት ራሄልና ያሬድ እንደወጡ ወደ መቅደላዊት ቢሮ ገባ። መቅደላዊት የእርሱን መውጣት ብቻ ነበር የምትጠባበቀው።

"የኔ ቆንጆ!" አላት ወደ ዴስኳ ተጠግቶ። "ይቅርታ መቅዲ! አንቺን ለማግኘት ብዙ ነው ወደ ኋላ የቀረሁት።"

መቅደላዊት ፊቷ ቀላ። "እኔም ሥራ በዝቶብኝ ጊዜው አልታወቀኝም ነበር።" አለችና ከወንበሯ ተነስታ መጋረጃዎችን መሸፈን፣ መብራቶችን ማጥፋት ጀመረች።

ሳምሶን እንቅስቃሴዋን ሁሉ በትኩረት እየተከታተላት "መቅደላዊትን የመሰለች ቆንጆ ባልዳረባዬን ብቻዋን ትቼ አልሄድም። እሸኝሻለሁ" አላት።

የቢሮውን መግቢያ በር ከፍታ ያዘችና "እግዜር ይስጥልኝ ሸኚ አያስፈልገኝም። ተነስ ቢሮውን ልዝጋበት!" አያለች በእጇ ወደ ውጭ አመለከተችው።

"ታዛዥ ነኝ የኔ ቆንጆ።" አወጣለሁ። ዛሬ በታክሲ እትሄጂም። በኮብራ ነው ቤትሽ የማደርስሽ።"

ቢሮውን እየቆለፈች "ኮብራው እኮ የዶክተር ሥራብዙ ነው። ያንተ መሰለህ እንዴ?" አለችው።

"ቢሆንስ? ምናለበት?" አላት እየሳቀ።

'ብራና አስጎብኚ' የሚል መለያ ጽሑፍ የተለጠፈበት እጅግ ዘመናዊ ቶዮታ ላንድ-ክሩዘር ውስጥ ገብተው ቦታ ቦታቸውን ያዙ። በቅርቡ መንግሥት ለአስጎብኚ ድርጅቶች በለጠው የቀረጥ ነፃ እና የብድር ፈቃድ የዶክተር ሥራውብዙ ብራና አስጎብኚ ድርጅትም ሦስት ላንድ ክሩዘሮችን ሲያስገባ አንዱ መኪና ላይ ሳምሶን ተመደበ።

"ዛሬ አራት አጋብዝሻለሁ።" አለ ሳምሶን አጭር ቀሚሷ ያጋለጠው ጭኗን እየተመለከተ።

"አራቱ በቀረብኝና ሕይወቴን እቤት ባደረስካት" አለችና ቀሚሷን ወደ ታች ሳብ . . . ሳብ አደረገችው። የሽሙጥ ፈገግታ ፊቷ ላይ ይታያል።

"ምናለበት መቅደላዊት ዛሬ ምርጥ አራት ልጋብዝሽ።"

"ይልቅስ ዐይኖችህን መንገዱ ላይ ተጠቀምባቸው። ያለዚያ የምትጋብዘኝ አራት ሳይሆን የሬሳ ሳጥን ይሆናል።"

ከልቡ ሳቀና የነዳጅ መስጫውን በኃይል ረገጠው። መቅደላዊት በፍርሃት ራደች።" የሜክሲኮ አደባባይን ሀረው ወደ መካኒሳ እየወረዱ ሳለ "መቅዲ" አላት።

"እቤት"

"የት ልጋብዝሽ?"

"የትም! ቤቴ ጣለኝ"

"እባክሽ ዛሬ ልጋብዝሽ?"

"እንግዲህ አትችክ ሳምሶን!"

"እሺ የኔ እመቤት።።" አለና ሳምሶን በረጅሙ ተነፈሰ።

"ነገ ወይ ከነገ ወዲያ ፊልድ እወጣለሁ። ከዚያ ስመለስ ግን ሞቅ ያለ ግብዣ አጋብዝሻለሁ።"

"እዚህ ላይ ይበቃኛል" አለችው።

"ቤቱ አላልሽኝም?" በድንገት ፍሬን ሲረግጥ የመኪናው ጎማዎች ተንሲያጠጡ። መንገደኞች እየዞሩ አዩዋቸው።

"እዚህ ግሮሠሪ ሾፒንግ አለብኝ።" ብላው በሩን በቀኝ እጅዋ ስትከፍት ሳምሶን የግራ እጅዋን ለቀም አድርጎ ጣቶቿን ሳማቸው። መቅደላዊት ፊቷ ቀላ። እጅዋን መንጭቃው ከመኪናው ወረደች።

"ቻው የኔ ቆንጆ። ከፊልድ መልስ እንገናኝ!"

በሩን በኃይል ብትወረውረውም የንዴቷን ያህል ጮኽ የልቧን አላደረሰላትም።

"አንድ እርምጃ ነው። ብራቮ ሳምሶን! እስከ ዛሬ መዘግየቴም ይቆጨኛል።" ሲል ከራሱ ጋር አወራና ኮብራውን አስነፈው።

ሳምሶን መካኒሳ አካባቢ ባለሁለት ክፍል የግለሰብ ቤት ተከራይቶ ነው የሚኖረው። አከራይዋ ወይዘሮ ሐብለ ባላቸውን በሞት ያጡ የአንዲት ሴት ልጅ እናት ናቸው። የ20 ዓመት ወጣት ልጃቸው ገነት የሁለተኛ ዓመት ኮሌጅ ተማሪ ናት። ወይዘሮ ሐብለ ሳምሶንን በጣም ይወዱታል። ወደ መስክ ወጣ ባለ ቁጥር ከሰልም ይሁን እንጨት ሳይዝላቸው አይመጣም። የበዓላት ወቅት ከሆነማ ቢያንስ አንድ ዶሮ አንካችሁ ማለቱ አይቀሬ ነው።

"ኧረ ተው አንተ ልጅ! ከኩተማ በወጣህ ቁጥር የግድ አንድ ነገር ይዘህ መምጣት አለብህ እንዴ? አበልህ በኔ ከሰል ማለቁ ነውኮ!" ይሉታል። "እናት የለኝ፣ አባት የለኝ። ሚስት የለኝ፣ ድስት የለኝ። ያሉኝ አንድ ዘመዴ አርሶ ነዎትኮ!"

ከልጃቸው ገነት ጋር "እንዲቀራረብላቸው" አጥብቀው ይሻሉ። አንዳንዴ ለጠበል ጠዲቅ፣ ለቡና ወይ ለዓውደ ዓመት ግብዣ ከጠሩት . . . "ምናለ አምላኬ! ይህች ልጅ አፈር ከመልበሴ በፊት ፍሬ አፍርታ ባሳየችኝ።" ይሉታል። እርሱም ይገባዋል።

ግቢው ሰፊና የመኪና ማቆሚያ ስላለው ነበር ከሁለት ዓመት በላይ የኖረው። ዋናውን በር የወደዘሮ ሐብለ የቤት ሠራተኛ ስትከፍትለት "ገነት አለች!" ሲል ጠየቃት።"

"እምን ጋሼ ሳምሶን አለች።"

"ጥሪያት!! አለና ቤቱን ከፍቶ ገባ።

ሳምሶን የመኝታ ቤቱን መብራት አብርቶ ልብሱን አወላልቆ ፒጃማ ሲለብስ "ሳምሶን! ጠራኸኝ?" እያለኝ ገነት ወደ መኝታ ቤቱ ገባች።

"አ . . . አም!" አለ የስፖርት ቱታ ሱሪውን ወደ ላይ እየሳበ። "አንቦ ውሃ. . . ምናምን ትገዢልኛለሽ።"

"ምናምን . . .የስንት?" አለችው የመኝታ ቤቱ በር ላይ ቆማ እጅግ ደስ የሚል ፍልቅልቅ ፊገግታ እየመገበችው። እርሱም ሳቀና . . ."ከሽሚዝ ኪሴ መቶ ብር አውጪና . . . ባለ 50 ብር የሞባይል ካርድ፣ አንድ ፓኬት ዲላይት ሲጋራ፣ እና ላንቺም የፈለግሽውን ነገር ግገር" አላት።

"ኮሽ! ኮካ አምሮኝ ነበር!" ደስ የሚል ፊገግታዋን መኝታ ቤቱ ውስጥ ፏ! አርጋለት ሄደች።

ሳምሶን ሳሎን ገባና ሶፋው ላይ ጋደም ብሎ የሞባይል ስልኩን መምታት ጀመረ። "ያለምት ቀሪ ሒሳብ አነስተኛ ነው። አባክዎን ተጨማሪ ካርድ ገዝተው . . . ." ሳምሶን ስልኩን ዘጋና "ይድፋሽ!" ብሎ የቡና ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠው። 904ትን 'ዩድፋሽ' ብሎ ነው የመዘጋባት።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ገነት የታዘዘችውን ሁሉ ሸምታ ለራሷም ኮካ ይዛ ገባች። "ካርዱን አምጪው!" አለ ሳምሶን ከተጋደመበት ቀና ብሎ። እግሩን ጠረጴዛው ላይ ዘርግቶ የካርዱን ቁጥሮች የሞባይል ስልኩ ላይ መመላት ጀመረ።

"ስለ ኮካው አመሰግናለሁ። ለማማ ቡና ላፈላ ስለሆ፣ ኪደርስ አጠራሃለው።" አለችው ወደ በሩ እያመራች።

"ቱንክ ዩ ገኒ!"

"ሒሳብዎን በትክክል ሞልተዋል . . ." ወዲያው ሌላ ቁጥር መታ። ዘጋ። ሞከረ። በሦስተኛው ሙከራ በኋላ መጥራት ጀመረ። በሁለተኛው ጥሪ "ሐዳር አስጎብኚና የጉዞ ወኪል!" የሚል ድምጽ ተሰማው።

"እባክሽን የኔ እመቤት ድሬዳዋ የእንድ ጉዞ ትኬት ፈልጌ ነበር።" "ለመቼ ነው ጌታዬ?"

"ከነገ በስቲያ በመጀመሪያው በረራ።"

"ቦታ መኖሩን አረጋግጪ ልደውልልዎ። ስልክ ቁጥርዎን ሊሰጡኝ ይችላሉ?"

"በሚገባ!" ሳምሶን የሞባይል ቁጥሩን ሰጣት። "በዐሥር ደቂቃ ውስጥ እደውላለሁ ጌታዬ።"

ካሁን በኋላ ለሚያደርጋቸው ጉዞዎች እና እንቅስቃሴዎች ሁሉ በሌሎች የጉዞ ወኪሎች መጠቀም እንዳለበት ዶክተር ሥራውብዙ መመሪያ ሰጥቶታል። ሌላ የስልክ ጥሪ እያደረገ ገነት የገዛችለትን ዲላይት አንስቶ አንድ ሲጋራ አቀጣጠለ። ይሄኔ "ሄሎ?" የሚል ቀጭን የሴት ድምጽ ተሰማው።

"እባክዎን ሮበሌን ፈልጌ ነበር።"

"ማን ልበል?"

"ሳምሶን ነኝ፤ መቶ አለቃ ሳምሶን።"

ስልኩ ጠረጴዛ ላይ ሲቀመጥ "ሮበሌ! ወሪያ ሮበሌ! የሚል የሴትየዋን ጥሪ ሊሰማ 'ተመስገን ጌታዬ! አድራሻ ወይ ስልክ ቁጥር ይለውጣል ብዬ ፈርቼ ነበር' ሲል አሰበ።

"ሄሎ ማን ልበል?" የሚል የተሰባበረና ጥፍጥ የሚል ዐማርኛ ተሰማው።

"ሮበሌ! ሳምሶን ነኝ። መቶ አለቃ ሳምሶን!"

"ወሪያ ሳምሶን! ደህና ነህ? በጣም ብዙ ጠፋህ። አንተ በካ . . . ቱሪስት ካልመታ ዲሬ ዳዋ አይመታም?"

"ሮበሌ! በጣም ሥራ በዛብኝ። ከነገ ወዲያ ድሬዳዋ እመጣለሁ። ያንን አዘጋጅ ያልኩህን አቃ አፈልጋለሁ። ለመሆኑ አሁንም ይገኛል። አይደለም?"

"ሳምሶን እንዴት ይጠይቅል? የኔ ካል ይተራተራል? አለ ካልኩ አለ።"

"እሺ ሮበሌ ከነገ ወዲያ እመጣለሁ። ተዘጋጅና ጠብቀኝ።

"ቤቱ ቤትህ ነው። ይጠብቅሃል!"

ሳምሶን ስልኩን ዘጋና ለመቅደላዊት እየደወለ 'ኦፐሬሽን መቅደላ እና መቅደላዊት የተገጣጠሙበት አጋጣሚ' ሲል አሰበ።

ምዕራፍ ስድስት

የ "ዘመቻ መቅደላ" ስብሰባ እንዳበቃ ዶክተር ሥራውብዙ እንዱዓለምን በመኪናቸው አሳፍረው ወደ ሒልተን ሆቴል ተጓዙ።

እንዱዓለም ሒልተን ሆቴል ክፍሉን ከፍቶ ተከታትለው እንደገቡ በሩን ከውስጥ ዘግቶ ኮቱን አወለቀና ወንበር ላይ እያስቀመጠ "እነዚህን ባልደረቦቻችንን ከልቤ እደንቃቸዋለሁ። ተቀመጥ ዶክተር።" አለና እርሱም ምቹውን ወንበር ስቦ ተቀመጠ።

"እኔም እንዳንተው!" አሉ አዛውንቱ ዶክተር። ከኔ በስተቀር ሁላችሁም በዕድሜ፣ በትምህርት ደረጃና፣ በአስተሳሰብም ተቀራራቢ ናችሁ። ለዘመቻ መቅደላም ሆነ ለቀደምቶቹ የቅርስ ማስመለስ ትግላችን ባሕታዊው ትክክለኛዎቹን ሰዎች መመልመል ያውቅበታል።"

"እኔም እንዳንተው አስባለሁ" አለ ዶክተር እንዱዓለም ዘና ብሎ ሲጋራውን እየለኮሰ። "ምን ያህል ትክክል እንደሆነ የምናረጋግጠው ግን ከዘመቻ መቅደላ በኋላ ነው።"

አረጋዊው ዶክተር እንዱዓለም የተናገረውን በዝምታ ሲያሰላስሉ ቆዩና....."እሺ ወደ ቅርሶቻችን ነገር ስንመጣ....." አሉና አንጠልጥለው ተውት።

እንዱዓለም "ዝርዝሩን አብረን እንመልከተው" አለና የላፕ ቶፕ ኮምፒውተሩን ቁልፎች እየተጫነ የመረጃ ቋቱን መፈተሽ ጀመረ።

"አምን ይሄውልህ!" አለና ኮምፒውተሩን ወደ ዶክተር ሥራው አዙሮ ጠጋ አደረገላቸው። "ወዲህ ጠጋ በልና ተመልከት።" አዛውንቱ ዶክተር የንባብ መነጽራቸውን አስተካክለው ቀረብ አሉ።

"ተመልከት! የብራናው ብዛትና ዐይነት ብቻ ልክ የለውም። እንዳውም እዚህ ዝርዝር ውስጥ ያልተካተቱት ወይንም ወደ አዲስ አበባ በውስት ከሚመጡት ውስጥ ያልተካተቱት እያንዳንዳቸውን አምስት ሰው እንኳ ሊያነሳቸው የማይቻሉ ግዙፍና ድንቅ የብራና መጽሐፍት ነበሩ። ነገር ግን ለኤግዚቢሽን ሊያውሱን ቀርቶ እዚያው ለንደን ሙዚየም ውስጥ እንኳ የተሰየ ፈቃድ ከተሰጣቸው ጥቂት ሰዎች በስተቀር ማንም አጠገባቸው እንዲደርስ አይፈቀድለትም።

"ልዩ ፈታድ ወይንም ሌኩውራቲ ክሊራንስ ካላቸው ጥቂት ሰዎች መሃል አንዱ አንተ መሆንህን አውቃለሁ" አሉ ዶክተር ሥራው።

"እምን። ነገር ግን በጣም ውሱን ለሆኑት የብራና መፃህፍት ብቻ። ለምሳሌ 'መጽሐፈ ጥበብ' የተባለውን በግዕዝ ቋንቋ የተፃፈ የብራና መጽሐፍ ለማጥናትና ለመተርጎም የፈቀዱልኝ ገፅዙን መረዳት ተስኗቸው ሳይሆን አጠቃላይ ይዘቱ በምስጢራዊ አፃፃፍ ዘይቤ ላይ የተመሠረተና ሊፈቱት ስላልቻሉ ነው እኔ እንድመረምረውና እንድፈታው የፈቀዱልኝ። እነዚህ ፈረንጆች . . ."

"አንተም የምርምር ውጤትህን አምጥተህ ለባሕታዊው አስረክብክ!" አሉ ዶክተር ሥራውብዙ።

"ያንን በማድረጌ ቅር ይልሃል? ባሕታዊውን አታምነውም እንዴ? የምርምሩ ሁሉ ሲቅ እና የዘመቻ መቅደላ መሪ ማን ሆነና?" አለ ዶክተር አንዱዓለም ኮስተር ብሎ።

"የለም የለም! እንደርሱ ማለቴ አይደለም። ከባሕታዊው በላይ ማን የሚታመን ይኖራል?" አሉ ዶክተር ሥራው እንደ መደንገጥ ብለው።

አንዱዓለም እንዳልሰማ ሆኖ ኮምፒውተሩን መፈተሽ ቀጠለ።

"እናስ? ትርጉሙን እና የምስጢር አፈታቱን በትክክል አጠናቀቅክ?"

"መልሱን ለጊዜው ላቆየውና ስለ መጽሐፉ አንዳንድ ጉዳዮችን ልንገርህ።" አለ ዶክተር አንዱዓለም።

"መልካም" አሉ አዛውንቱ ዶክተር። የተለየ ጉጉት እና የማወቅ ፍላጎት እየታየባቸው።

"ምስጢረ ጥበብ የብራና መጽሐፍ በእንግሊዞች እጅ የወደቀው የታላቋ ብሪታኒያ ጦር የመቅደላን አምባ ከተቆጣጠረ በኋላ ነው። ዓፄ ቴዎድሮስ ከመላ ሀገሪቱ አድባራትና ገዳማት የሰበሰቧቸውን ቅርሶች በተለይም ብዛት ያላቸው የብራና መጽሐፍት መቅደላ አምባ ላይ ማከማቻታቸውን ታውቃለህ።"

ዶክተር ሥራው ራሳቸውን በአዎንታ ነቀነቁ።

"ከዓፄ ቴዎድሮስ ሕልፈተ ሕይወት በኋላ የእንግሊዝ ጦር ቅርሶቹን ሙልጭ አድርጎ ዘርፎ፣ በክብት ጀርባ ጭኖ ሲወስዳቸው የጦሩ አባላት የሆኑት የእንግሊዝና የሕንድ ወታደሮችም በግላቸው የዘረፏቸውን ቅርሶች ተሸክመው ሄደዋል። ይህ 'ምስጢረ

ጥበበ ሕዋዊ ወ ምድራዊ የተባለ መጽሐፍ በአንዱ እንግሊዛዊ ወታደር እጅ ወድቆ ነበር ። እናም ከአንድ መቶ ዓመታት በኋላ የዚያ ወታደር ተከታታይ ቤተሰብና ወራሽ የሆነ ሰው በከፊል የሻገተውን እና የተጎሳቆለውን መጽሐፍ ለ ብሪቲሽ የተፈጥሮ ታሪክ ሙዚየም ወኪሎች በጥቁር ገበያ ሸጠላቸው።

"ለመሆኑ ስለ ምን ዐይነት ጥበበ ነው የሚያትተው?"

"ምሕንድስና፣ ሥነ-ከዋክብት፣ ሕክምና፣ ወዘተ። አሉቱን አንደ ቅቤ በሚለንጥቅ የእጅ መሣሪያ ተራራውን እየፈለፈልክ ሕንፃ ማነፅ። ወንዝና ሐይቁን ጠልፈህ ለመስኖ እርሻ ማዋል። ሳይንስ እንኳን መፍትሄ ያላስገኘላቸውን በሽታዎች በተለያዩ ዕፀ-መድኃኒት መፈወስ። የተፈጥሮ ሚዛን ተዛብቶ ድርቅ በሆነ ወቅት ዝናብ የምታዘንብበት፣ ሲበዛም የምታቆምበት ጥበብ ... ወዘተ። ይህን የመሳሰሉና ሌሎችንም "ኤሶቴሪክ" (ጥቂት ሰዎች ብቻ የሚገነዘቡት ዕውቀት፣ ጥበብ) የያዘ ብርቅና ድንቅ መጽሐፍ ነው።"

ዶክተር ሥራውብኩ በዝምታ ሲቆዝሙ ቆይና....."ለመሆኑ ቀደምት ኢትዮጵያውን ይህንን ሁሉ ምስጢራዊ ጥበብ ለምን ምስጢራዊ እደረጉት ብለህ ታምናለህ?

አንዱዓለም እጅግ ተገርሞ ዶክተር ሥራውብዙን ሲመለከት ቆየና..... "የዘመናችን ኃያላን መንግሥታት የኒውክሊዩር ጦር መሣሪያዎቻቸውን እና ቴክኖሎጂውን ለምን በምስጢር ያዙት ብለህ ታስባለህ?" ሲል ጠየቃቸው።

ዶክተር ሥራውብዙ ፈገግታ አሳይተውት ዝም ሲሉ አንዱዓለም ቀጠለ። "ይህን ላንተ ማስረዳት አላስፈላጊ ይመስለኛል።"

ከዚህ በኋላ ከሰንደን ወደ አዲስ አበባ ለአውደ ርእይ የሚመጡትን ታሪካዊ ቅርሶች አንድ በአንድ እየዘረዘረና የኮምፒውተር ስክሪኑ ላይ እያሳየ ሲያስረዳቸው አረጋዊው ዶክተር በከፍተኛ ተመስጦ ሲከታተሉት ቆዩ።

"ኦፕሬሽን መቅደላ የሰው ኃይል እጥረት አለበት ብዬ አስባሁ። አለ አንዱዓለም።

"እኔም እንዳንተ አስባለሁ። አንተ፣ እኔ፣ ያፈት፣ ያሬድ፣ ዮዲትና ራሄል። ሰባት የሰው ኃይል ብቻ ነን።

"ዶክተር አንዱዓለም ወደ ዶክተር ሥራው ዞሮ በፈገግታ አያቸውና "እኔና አንተ ከቁጥር እንገባለን? ማለቱ ዋናውን የአገታና ጠለፋ ሥራ ስናከናውን እንደ ወጣቶቹ ባልዳረቦቻችን ወታደራዊ ልምድ የሌለን እና ቅልጥፍናው የሚያንሰን ነን።"

"ተው ባክህ!" አሉ አረጋዊው ዶክተር። "በውትድርና ሙያ ውስጥ ባናልፍም የጦር መሣሪያና አተኳኮሱን ባሕሉ ያደረገ ቤተሰብ ውስጥ ነው ያደግንው!" ይህን ሲናገሩ ከአያሌው ዓመታት በፊት የተኮሷቸው ጥይቶች እና ዓሊማው ታወሳቸውና ሰውነታቸው በመጠኑ እንደ መራድ ሲል ዶክተር አንዱዓለም በስጋት ተመለከታቸው።

"ምነው ዶክተር? ደህናም አይደለህ?" ሲል ጠየቃቸው።

"ደህና ነኝ" አሉና ከወንበራቸው ተነሱ። "ለካስ ጊዜው በጣም መሽቷል። ወደ ቤቱ ልሂድ። ነገ ከቀትር በኋላ ... በስምንት ሰዓት ስብሰባ መኖሩን ታውቃለህ" አሉ ወደ በሩ እያመሩ።

"እምን" አለ አንዱዓለም በሩን እየከፈተላቸው። "ነገ እና ተነገ በስቲያ አንዳንድ ያልተቋጩ ጫፎችን ቋጥሬ ላበቃ ወደ ለንደን ስለምበር ምናልባት የመጨረሻው ስብሰባዬ ሊሆን ይችላል። ከአንድ ወር በኋላ ቅርሶቹን ይገፍ ስመለስ ነው የምንገናኘው። ለማንኛውም ነገ እዚያው ቢሮህ እንገኛለን።"

ዶክተር ሥራውብዙን አስወጥቶ በሩን ዘጋና ወንበሩ ላይ አረፍ ብሎ ሞባይል ስልኩን ደወለ።

"ሄሎ! ወፈር ያለ ድምጽ"

"ሻለቃ ፍቅሩ ነምት?"

"ማን ልበል?"

"የባሕታዊው መላክተኛ!"

ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ዝምታ ሰፈነ። ሻለቃው የስሙትን አጣጥመውና ተንትነው ለመጨረስ አራት ሴኮንዶች ያህል ፈጀባቸው። 'አንድ ቀን ዕርዳታህን የምፈልግበት አጋጣሚ ይመጣል። የባሕታዊ መላክተኛ ነኝ ካለህ.....' ሻለቃው ከብዙ ዓመታት በፊት "ባሕታዊው" የተናገሩት ታወሳቸው። "ምን ልርዳምት?" አሉ።

"በእካል ተገናኝተን ብገልፅልምት ይሻላል።"

"በምን ጉዳይ ላይ? ማን ልበል?"

"ዶክተር አንዱዓለም ይፍረደው እባላለሁ። በቅርቡ ከለንደን ሙዚየም ነው የመጣሁት። የታሪካዊ ቅርሶች ባለ ሞያ ነኝ። ከመቅደላ አምባ የተዘረፉ ቅርሶችን በተመለከተ ጥናታዊ መጽሐፍ እያዘጋጀሁ ስለሆነ እርስዎ ሊረዱኝ እንደሚችሉ ተነግሮኛል።"

"ጥናታዊ መጽሐፍ..... ምናምን..... የቆየ ጨዋታ" አሉ ሻለቃው በሐሳባቸው።

"እሺህ የኔ ወንድም!" አሉት። "መቼም ቅርሶቹን የዘረፉትን ሌቦች እንድጠቁምህ ፈልገህ ከሆነ ልረዳህ አልችልም። ምክንያቱም ለንደን ሙዚየም እስክ ሠራህ ድረስ አንተ ራስህ የሌቦቹ አባሪ ነህ።"

ዶክተር አንዱዓለም በሳቅ ፈነዳ።

"ደግሞም" አሉ ሻለቃው ... "እኔ የተወለድኩት የመቅደላ ጦርነት ከተደረገ ካንድ ተኩል ምዕተ ዓመት በኋላ ስለሆነ ለዘጋቢ መጽሐፍህ ዋቢ ልሆንህ አልችልም።"

አንዱዓለም እንደምንም ብሎ ሳቁን ከገታ በኋላ "እምን ጌታዬ የሌቦቹ አባሪ ልሆን እነላለሁ። ነገር ግን ዘጋቢ መጽሐፍ ከማዘጋጀት ሊያግደኝ አይችልም" አላቸው።

"ሰማንኛውም ልረዳህ የምችለው ነገር ካለ ወደ ኋላ አልልም።"

"አመሰግናለሁ ጌታዬ። በጣም አመሰግንዎታለሁ። የሚመችዎት ከሆነ ነገ ጧት በ3:00 ሰዓት ሒልተን ሆቴል ብንገናኝስ?"

"የለም ሒልተን አይሆንም። ጧት በአራት ሰዓት ሒል-ቶፕስ ሬስቶራንት እንገናኝ።" አሉና ሻለቃው መልስ ሳያጠብቁ ስልኩን ዘጉት።

'እንዴት ልለያቸው፣ ሊሰዩኝ?' አለ አንዱዓለም በሐሳቡ። የሞባይል ስልኩን ዘግቶ ሌላ ቁጥር እየደወለ ፈገግ አለ። 'ፖሊስ አይደሉ!'

ጥሪው ሊያበቃ ትንሽ ሲቀረው ተመለሰ።

"ሄ ... ሎ ... ው !"

"ዮዲት?"

"አዎ!"

ለሁለት ደቂቃዎች ያህል በገበትተኛ ድምፅ እና በዘወርዋራ ቃላት መመሪያ ሰጣት። "የፈርኦንን ቡና ከጠጣሁ በኋላ" አለችው። ስልኩን ዘጋው። እንደገና ደወለና የክፍል አገልግሎት ማዘዝ ጀመረ። ቀለል ያለ ራት ... ቡና።

ምዕራፍ ሰባት

ቀኑ ብሩህ ፀሓያማ፣ አየሩም ቀዝቀዝ ያለና አስደሳች ነበረ። ነገር ግን ኢትዮጵያውን በመገናኛ ብዙሃን የሰሙት የዕለቱ ዜና አስደንጋጭ ነበረ። ከሁሉም ኢትዮጵያውያን በላይ አስደንጋጩን ዜና ከሥፍራው በቀጥታ (Live) ከሚተላለፈው ዜና በዐይናቸው እያዩትም ማመን ያቃታቸው የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚንስትር ነበሩ። ዜናውን በድንጋጤ እየተክታተሉ ሳያውቁት እጃቸውን ወደ ጠረጴዛው ስልክ ሰንዘሩ። ልክ በዚህች ቅፅበት ልዩ ረዳታቸው አቶ ግርማይ በርሔ የጠቅላይ ሚንስትሩን ቢሮ ሳያንኳኩ በጥድፊያ ከፍተው ገቡ።

"ስሙት?" አሉ ረዳታቸው።

ጠቅላይ ሚንስትሩ በእጅ ምልክት ረዳታቸውን ዝም አሰኙና . . . "ኮሌኔል ሰናይን አገናኝኝ!" ብለው ዐይኖቻቸውን ክትልቁ የቴሌቪዥን አስክሪን ላይ ሳይነቅሉ የስልኩን እጀታ አቀበሏቸው።

ጠቅላይ ሚንስትሩ የመገናኛ ብዙሃን የሚያሰራጩትን ዜና የሚከታተሉት ከፊት ለፊታቸው የሚገኘው ግድግዳ ጋር ተያይዘው በተተከሉ የቴሌቪዥን አስክሪኖች ሲሆን ሥራቸው ፋታ ሲሰጣቸው፣ ጥቂት ማረፍ ሲፈልጉ፣ ወይም ትኩረት የሚያሻው ዜና ሲያጋጥማቸው የመረጡትን ቻናል በርቀት መቆጣጠሪያው ድምፁን ክፍ በማድረግ ይሰማሉ። አሁን የሚመለከቱትን አስደንጋጭ ዜና ግን ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጣቢያ በስተቀር ሌሎቹ ዓለም አቀፍ ጣቢያዎች በሙሉ እየዘገቡት ስለሆነ የየትኛውን ጣቢያ ድምጽ ክፍ እንደሚያደርጉ ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል ተቸግረው ነበር። የቢ.ቢ.ሲን ጣቢያን ድምጽ ክፍ አደረጉት።

"ዚስ ኢዝ ላይፍ . . . ፎሮም አዲስ አበባ! ፕሪንሰስ ኢዛቤል አፍ ዊንድሶር ሃዝ ቢን ኪድናፕድ ራይት ኢንፍሮንት አፍ ማይ አይስ!"

ከእንግሊዝ ኮሚውኒቲ ትምህርት ቤት ዜናውን በቀጥታ የምታስተላልፈው የቢ.ቢ.ሲ. ዘጋቢ ዐይኖቿ በጉጉትና በደስታ እንባ ሊያመነጩ የተቃረቡ ይመስላሉ። ለአንዲት ሴኮንድ እንኳ ልፍለፋዋ ገታ አይልም።

"ኦ . . . ማይ ጋድ! ሺ ሃድ ኤ ቦምብ!"

"ዜይ አር ፋየሪንግ አውቶማቲክ . . . ."

"አቶ ኪሩቤል . . . ኮሎኔል ሰናይ ቀርቧል!" አሏቸው ረዳታቸው ድምፃቸውን ክፍ አድርገው።"

"እ? እሺ!" አሉና ስልኩን ተቀበሉ።

"ሄሉ ሰናይ! እየሰማህ ነው? ሰማህው?" አሉ ጠቅላይ ሚንስትሩ። አሁንም ዐይኖቻቸውን ከኩቲሌቪዥኑ ስክሪን ላይ አልነቀሉም።

"ሰማሁት። በጣም ያሳዝናል! አሁን በቲሌቪዥን እየከታተልኩ ነው..." አለ ከወዲያኛው ጫፍ የሚመጣው ድምጽ።

"ሥራህን በአግባቡ አልሠራህም!" አሉ ጠቅላይ ሚንስትሩ። ድምፃቸው እንደ ሳሙራይ ካታና (እጅግ ስለታም የጃፓኖች ጎራዴ) የሰላ ቅላጼ ነበረው።

የደህንነት ኃላፊው ኮሎኔል ሰናይ ለሁለት ወይንም ሦስት ሴኮንዶች ያክል ደንግጠው ዝም አሉ። ነገር ግን የደነገጡት በጠቅላይ ሚንስትሩ አባባል ይሁን ወይንም ዐይኖቻቸው ሥር እንደ ኧርሪት በሚንቆረቆረው አስገራሚ ዜና . . . እርግጠኛ አልነበሩም።

"ሥፍራውን ዙሪያውን በወጥታ ኃይሎች አስከብቤአለሁ።"

"ስማ! አሁን ስለ ከበባ እና ስለሚደረገው ትንትንት ዕቅድ አንድትነግረኝ አልፈልግም። ይህ ጉዳይ.....ይህ ያገራችንን እና የመንግሥታችንን ክብር የሚጎዳ የሽብር ተግባር ያለ አንዳች የደም መፋሰስና ተጨማሪ ኪሳራ መክሸፍ አለበት!"

"አዎን ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር!"

"አሁኑኑ አንድ የምርመራ ቡድን ይዘህ ባስቸኳይ ወደ ሥፍራው ሂድ። አጋቾቹ የሚፈልጉትን አውቀህ ሁኔታውን እንድታሳውቀን!"

"እሺ ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር። እኔም የምርመራ ቡድኑን እያዋቀርኩ ነበ . . ."

"ስማ! ከተከበረችው የክብርት እንግዳችን ከልዕልት ኤልላቤት አናት ላይ አንዲት ዘለላ ወጉር አንኳ ቢጎድል ቀሪውን የሕይወት ዘመንህን የምትጨርሰው ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ በማንበብ እንደሆነ አወቅ!"

"እሺ አቶ ኪሩቤ . . ."

ጠቅላይ ሚንስትሩ የደህንነት ኃላፊያቸው የሚናገረውን ከመጨረሱ በፊት ስልኩን ቀፎው ላይ አስቀመጡና ከፊታቸው ወደ ቆሙት ልዩ ሪዳታቸው ዞሩ። "ረጂም እና አስቸጋሪ ለሆኑ ሰዓታት ተመቻችተህ ተቀመጥ!" አሉና የስልክ ጥሪ የሚደረግላቸውን ባለ ሥልጣኖቻቸውን ስም ነገሯቸው። አቶ ግርማይም የመጀመሪያውን የስልክ ጥሪ ለአድዋ ኮማንዶ ክፍለ ጦር አዛዥ በመደወል ጀመሩ።

ምዕራፍ ስምንት

በተለምዶ 'ደህንነት' በሚል አጭር መጠሪያ የሚታወቀው የሀገር ውስጥ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ከወትሮው የተለየ ምንም ዐይነት እንቅስቃሴ ባይታይበትም የዐረ ሽብር ክፍል ኃላፊው የኮሎኔል ሰናይ ቢሮ ግን በአስጨናቂ ውጥረት የተሞላ ይመስላል። መስኮቱ ተዘግቶ መጋረጃው ተጋርዷል። በሩ ከውስጥ ተቆልፏል። ከጽሕፈት ጠረጴዛቸው ኋላ ከተቀመጡት ኮሎኔል ሰናይ በስተቀር በጠረጴዛው ዙሪያ የተቀመጡት ሦስቱም ባልደረቦቻቸው ሲጋራቸውን በላይ በላዩ እያቀጣጠሉ ክፍሉን በጢስ አፍነውታል።

የአገታና ጠለፋው ዜና ከተሰማ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚንስትር በሰጡት ትዕዛዝ መሠረት ኮሎኔል ሰናይ በሙያቸው የተካኑ ያሏቸውን ሦስት የሥራ ባልደረቦቻቸውን ወደ ቢሮአቸው አስጠርተው የምርመራ ቡድኑን መሥርተው ሥራ ከጀመሩ ሃያ ደቂቃዎች ያህል አልፏቸዋል።

አስካሁኗ ደቂቃ ድረስ ከኮሎኔል ሰናይ በስተቀር የጠቅላይ ሚንስትሩ "ጓታና" (እጅግ ስለታም የጃፓኖች ጎራዴ) የጨረተው ሰው ባይኖርም የምርመራ ቡድኑ አባላት በሙሉ ዋና መዲናቸው ውስጥ በተፈጸመው የሽብር ተግባር ልባቸው እየደማ ነበር።

ኮሎኔል ሰናይ ዕድሜያቸው በሃምሳዎቹ አጋማሽ ውስጥ የሚገኝ፣ መካከለኛ ቁመት ያላቸው ሰው ናቸው። ዱሮ 'አባዲና' ይባል ከነበረው ፖሊስ ኮሌጅ በምክትል መቶ አለቅና ማዕረግ ተመርቀዋል። በወታደራዊው መንግሥት ዘመንም ወደ ውጭ ሀገር በመጓዝ የምዕራቡንና የምሥራቁን ዓለማት የፖሊስ ትምህርት የተማሩና ለረጅም ዓመታት በምርመራና በመረጃ (ኢንቴሊጀንስ) ዘርፍ ያገለገሉ የፖሊስ መኮንን ናቸው።

ከርሳቸው በስተ—ቀኝ የተቀመጡት ሌተና ኮሎኔል ዘገየ በርሔ የዐርባ አምስት ዓመት ሰው በጸረ ሽብር ፖሊሳዊ ሙያ እንግሊዝ አገር ሄደው የሠለጠኑ፣ በርካታ ልምዶችና ውጤቶችን ያስመዘገቡ መኮንን ናቸው። ከእርሳቸው ቀኖሎ ሻለቃ ፍቅሩ በላይ ተቀምጠዋል።

ሻለቃ ፍቅሩ በጣም ቀጭን እና ረጅም ናቸው። ከሃምሣ ዓመት ዕድሜያቸው አንሣር ጸጉራቸው ሙሉ በሙሉ ቢሸብትም ራስ በራነት አልደፈራቸውም። በምክትል መቶ አለቃነት ከሠንዳፋ ፖሊስ ኮሌጅ ተመርቀው በውጭ ሀገራትም የሠለጠኑ፣ በወንጀል ምርመራና መከላከል ስማቸው የተጠራ የፖሊስ መኮንን ናቸው።

ኮሎኔል ሰናይ በስተ—ግራ የተቀመጠው ከሁሉም ወጣት የሆነው የ35 ዓመቱ ጎልማሳ መቶ አለቃ ሣሙኤል ኃብተማርያም ነው። ከሰንዳፋ የፖሊስ ኮሌጅ በምክትል መቶ አልቅና ማዕረግ ተመርቋል። ለሁለት ዓመት ያህል በወንጀል መርማሪነት እንደሠራ ወደ ቀደሞዋ ምሥራቅ ጀርመን ተልኮ የፖሊሳዊ ትምህርት ተከታትሏል። በጣም አንባቢ፣ ተመራማሪ፣ እና አስተዋይ የወንጀል ምርመራ ባለሙያ ነው።

"ጠቅላይ ሚንስትሩ" አሉ ኮሎኔል ሰናይ የሥራ ባልደረቦቻቸውን ተራ በተራ አተኩረው እያዩ። "ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ነው ይህን የምርመራ ቡድን አዋቅሬ ባስቸኳይ ሥራ እንድንጀምር ያዘዙት። ከጊዜ እጥረትና ከሁኔታው አስቸኳይነት አንፃር ከአራታችን ያለፈ የሰው ኃይል ማካተት አስፈላጊ መስሎ አልታየኝም። ሆኖም ግን ይህ የምርመራ ቡድን የሌሎችንም ክፍሎችና ተቋማት እገዛና ትብብር የመጠየቅና የመጠቀም ሙሉ ሥልጣን ተሰጥቶታል። በዚህም መሠረት ለሦስታችሁም ስቴሽን ዋገን ተሽከርካሪ ከነ አሽከርካሪው ተመድቧል። የምትፈልጉትን ማቴሪያል ከግምጃ ቤት፣ ገንዘብም ከገንዘብ ቤት ወዲ ማድረግ ትችላላችሁ። ከጠቅላይ ማዘዣ ጋር የራዲዮ ግንኙነት የምታደርጉበትን ዕለታዊ ኮድ ከመገናኛ ኃላፊው ይዛችሁ ትሠማራላችሁ።"

ጭፍሮቻቸውን አንድ በአንድ ቃኝተው ሲጋራ ለኮሱ።

"የሥራ ድርሻችንን በግልጽ ብናውቀውስ?" ሌተናል ኮሎኔል ዘገየ ጠየቁ።

"ወደ እሱ ልምጣ . . . ." ኮሎኔል ሰናይ ገና መልስ መስጠት ሲጀምሩ እስክ አሁን አቀርቅሮ ማስታወሻ ደብተሩ ላይ ያለ አረፍት ይጽፍ የነበረው መቶ አለቃ ሣሙኤል...! "ላቋርጥዎት ይቅርታ" አላቸው።

"ቀጥል" አሉት አለቃው።

"እኔ የሥራ ድርሻዬን መርጨ አሁኑኑ ሥራ ብጀምርስ?"

ኮሎኔል ሰናይ ፈገግ ብለው ዝም ሲሉት ብድግ አለና "አሁኑኑ ጊዜ ላላጠፋ ወደ ባሕል ሚኒስቴር መሄድ አፈልጋለሁ።" አለ ማስታወሻውን እየዘጋ።

"እዚያ እስክደርስ መምጣቱን በስልክ ቢያሳውቁልኝ በቀጥታ ምክትል ሚኒስትሩን ለማግኘት ይረዳኛል።" ከዚና ማሠራጫዎች እንደ ተረዳሁት ሚንስትሩ ታግተዋል።"

"መሄድ ትችላለህ! ቀጥል" አሉና ኮሎኔል ሰናይ ጠረጴዛው ላይ የተቀመጠውን የሞባይል ስልካቸውን አንስተው ቁጥሮችን መምታት ጀመሩ።

"ሄሉ! ኮሎኔል ሰናይ ነኝ። ደህና ዋልክ ግርማ! የላሬውን 'ክራይሲስ' በተመለከተ አንድ መርማሪያችን የናንተን ትብብር ፍለጋ ወደ ቢሮህ እያመራ ስለሆነ አንድትቀበለው ልጠይቅህ ነው።"

"ምን? እምን። የሚፈልገው መረጃ ይኖራል።"

"እሺ። በጣም አመሰግናለሁ።" አሉና ሞባይሉን ዘግተው ከማስቀመጣቸው ተንጫረረ። እንደገና አነሱት። "ሄሉ? . . . ኦ. . . ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር!"

የጠቅላይ ሚኒስትሩን ስም የሰሙት ሁለቱ ባልደረቦቻቸው ኮሎኔል ሰናይ ላይ አፈጠጡ።

"የምን የምርመራ ቡድን? ሲሉ ጠየቁና በገመታ ማዳመጥ ቀጠሉ።

"እሺ! እሺ! አስፈላጊውን ሁሉ እናደርጋለን።"

ስልኩን ዘግተው በቀጥታ ኮሎኔል ዘገየን ተመለከቱ።

"አንተን የሚመለከት ጉዳይ ስለሆነ ኃላፊነቱን ትወስዳለህ።" አሉ ኮሎኔል ሰናይ።

"ምንድነው?"

"አንድ የፀረ ሽብር ግብረ ኃይል እና አንድ የስኮትላንድ ያርድ ፀረ ሽብር ምርመራ ቡድን ከለንደን ወደ አዲስ አበባ በመብረር ላይ እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አሳውቀውኛል። አንተ በስኮትላንድ ያርድ ፖሊስ የሠለጠንክ ስለሆነ ከማንም የተሻለ ከእንግሊዝ ፖሊስ ጋር ትውውቁ አለህ። ቡድኑም አዲስ አበባ ሲገባ ከቦሌ ተቀብልና በማናቸውም እንቅስቃሴውና ከመንግሥታችን ጋር በሚኖረው ግንኙነት ሁሉ በአገናኝ መኮንንነት ትሠራለህ።"

"የእንግሊዝ ፖሊስ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ምን ዐይነት ጁሪስዲክሽን አለው?" ሲሉ ሌሎ ዘገየ ጠየቁ።

"ምንም የለውም!" አሉ የምርመራ ቡድኑ መሪ ቆጣ ብለው። ሆኖም ግን ይህ የጁሪስዲክሽን ጥያቄና ጥያቄው የሚቀርብበት ወቅት አይደለም። የታገቱት የእንግሊዝ ልዕልት፣ አምባሳደር እንዲሁም ሌሎች አምስት የእንግሊዝ ዜጎች ናቸው። ከዚህም በላይ አሸባሪነትን የመዋጋት የጋራ ዓላማ ያስተሳስረናል። ከሁሉም በላይ ደግሞ..."

"ይገባኛል!" በማለት ኮሎኔል ዘገየ አቋረጡዋቸው።

"ሻለቃ ፍትሩ። እኔና አንተ አሁኑኑ ወደ ኤግዚቢሽኑ ሥፍራ አብረን በመሄድ ጠላፊዎቹ የሚያቀርቡት ዲማንድ (ጥያቄ) ካለ ለማወቅ እንሞክራለን። "አሱና ኮሎኔል ሰናይ ሞባይላቸውን ይዘው ብድግ አሉ። ልክ በዚህች ቅጽበት ስልኩ ጮኸ።

"ሄሎ"

"እሺ..እሺ.... ሚንስትሩ እየመጡ ነው በልና አለዝበው። እኔ መንገድ ሾፌሬያለሁ።" አሱና ስልኩን ዘግተው ደወሉ።

"ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር። አጋዦቹ ያገር ውስጥ ጉዳይ ሚንስትሩን አናነጋግር ያላሉ ....።"

ስልኩን ዘግተው፣ ኪሳቸው ጨምረው ወደ ሌሎል ዘገየ ሁሩ።

"ዘገየ። የለንደኑ ቡድን አዲስ አበባ እስኪደርስ የጠላፊዎቹን ማንነት፣ የሁሉንም ማንነት የሚያረጋግጥ 'ፐርሰናል ፕሮፋይል እና አይደንቲ ኪት' ታዘጋጃለህ።" ብለው ወደ በሩ ሲያመሩ ሁለቱ መርማሪዎችም ተነሱ።

"ይህንን ለመፈጸም የኤግዚቢሽኑን አዘጋጅ ኮሚቴ ትብብር ማግኘት አለብኝ።" አሉ ኮሎኔል ዘገየ።"

"ታገኛለህ! ሂድ።" አሉ ኮሎኔል ሰናይ ክቢሮአቸው ለመውጣት እየተጣደፉ።

ሌተና ኩሎኔል ዘገየ ከአለቃቸው ቢሮ እንደወጡ በቀጥታ ወደ አንድ ዘመናዊ ስቱሽን ዋገን ሄዱና በሩን ከፍተው፣ ተመቻችተው ከተቀመጡ በኋላ "ወደ ቦሌ!" አሉት ሾፌሩን። መኪናው ተነስቶ ዋናውን ጎዳና እንደያዘም የሞባይል ስልካቸውን መደወል ጀመሩ።

"ሄሎ ሳሙኤል! እግረ መንገድህን አንድ ነገር አጣራልኝ።"

"ኤግዚቢሽኑን አዲስ አበባ ለማዘጋጀት ከባህል ሚንስትር ጋር በጋራ የሠሩ ያዘጋጅ ኮሚቴውን አባላት ዝርዝር.....።"

ምዕራፍ ዘጠኝ

ያፌት ነው አስቀድሞ የነቃው። ዐይኖቹን ገልጦ እያጨናበሰ ደጋግሞ አዛጋና ወደ ቀኝ ገልበጥ ሲል በክፈል ከተራቆተው የዮዲት ገላ ጋር ተላተመ። 'ይህን የተዋበ ገላ ከማቀፍና ከመቆጣጠር የተሻለ ምን ደስታ ይገኛል?' ሲል ራሱን ጠየቀና ዐጉሯን መደባበስ ጀመረ። ዮዲት በጀርባዋ ስትገላበጥ ከወገቧ በላይ ተራቆተች። ያፌት የሴት ውበትን ከሁሉም ነገር በላይ ያስቀመጠበትን እምነቱን የሚያፋልስ አንድ አባባል ትዝ አለው። እና ካሬኒና ከተሰኘው የቶልስቶይ መፍሐፍ። "The more a man devotes himself to beauty the further he moves away from goodness." ሰው ራሱን ለውበት እያስገዛ በሄደ መጠን ከመልካም ሥነ-ምግባር ሁሉ እየራቀ ይሄዳል።" ውበትን ማድነቅ እንዴት ያስከስሳል? ሊገባኝ አይችልም! አለ በሐሳቡ።

ከንፈሯን ጠበቅ አድርጎ ሲስማት ፊቷን እንደ ማሸሽ አደረገችና ዐይኖቿን ገለጠች። ያፌት እንደገና አሞጥሙጦ ሲቀርባት "ኡ . . . ፍፍፍ!" አለችና በግራ እጇ ደረቱን ተጭና ገፋችው።

"ዮዲት። እባክሽ እቀፊኝ።"

• "አትችክ! "አለችው በቁጣ። ወዲያው ብድግ ብላ አልጋው ጠርዝ ላይ ቁጭ አለች። ያፌት ሙሉ በሙሉ ከተራቆተው ገላዋ ላይ ዐይኖቹን መንቀል አልቻለም።

"አሁን አንድ ሥራ ስላለኝ ትቼህ መሄዴ ነው። ከፈለክ ቆይተህ መውጣት ትችላለህ።" አለችና ተነስታ በዝግታ እና እጅግ በሚማርክ አረማመድ ወደ መታጠቢያ ቤት አመራች።

"የት ነው የምትሂጂው?" አላት።

"አይመለከትህም!"

"እያንዳንዷን እንቅስቃሴሽን የምቆጣጠርበት ጊዜ ይመጣል!"

"ዮዲትን የሚቆጣጠር እንኳንስ ከዚህኛው ምድር ይቅርና ከሰባተኛው ሰማይም አይመጣም!" አለችና መታጠቢያ ቤት ገብታ ዘጋችው። ዮዲት ግማሽ ሰዓት ከፈጀ እጥበት በኋላ ከባኛ ቤት ተመልሳ ስትወጣ ያፌት ልብሱን ለባበሶና አልጋው ጠርዝ ላይ ተቀምጦ ሲጋራ ለለኩስ ሲል አገኘችው።

"እባክህን እስክወጣ ድረስ አታጢስ! ትምባሆ ታጥኜ መውጣት አልሻም።"

"እሺ የኔ ቆንጆ! የተፈጥሮን ውበት መበከል አልሻም!" አለ ሲጋራውን ወደ ፓኮው፣ ፓኮውን ወደ ኪሱ እየጨመረ።

ዮዲት ፈገግ አለችና "እመሰግናለሁ" ብላው መልበስ ስትጀምር ያፈት ብድግ ብሉ ወደ ዮዲት ሄደና "ጉድ ባይ ኪስ ስጪኝ" አላት ወደ አፏ ተጠግቶ።

"ችክ! አለችና ጉንጩን በአንፈሯ ነካ አደረገችው።

"ከሰዓት በኋላ ሥራውብዙ ቢሮ አይሻለሁ" አላት ወደ በሩ እያመራ።

"ገዛነም አይዛለሁ!"

ያፈት እየሳቀና ራሱን እየወዘወዘ በሩን ከፍቶ ወጣና ከኋላው ዘጋው። ዮዲት ለብሳ ጨርሳ ቦርሳዋን ስታነሳ የሞባይል ስልኳ ንዝረት ተሰማትና አወጣችው።

"ምን ቀረሀ ያፈት?" አለች በተሰላቸ ድምፅ።

"ዮዲት፣ ያ የትናንቱ ጥላሽ ሉቢው ውስጥ ተቀምጠልሻል።"

"ቱንክ ዩ!" ብላው ስልኳን ዘግታ ቦርሳዋ ውስጥ ጣለችው። ለሴኮንዶች ያህል ስታስብ ቆየችና ለራሷ ፈገግ ብላ በሩን ከፈታ ወጣች።

ከአሥራ አምስት ደቂቃዎች በኋላ ዮዲት የጽዳት ሠራተኛዋን ልብስ ለብሳና፣ ራቷን በሻሽ ሸፍና ባጠገቡ ስታልፍ አይሁዳዊው የሞሳድ ሰላይ ቤን ሳያስተውላት ቀረ። ከአሥር ደቂቃዎች በኋላም ለዕዳት ሠራተኛዋ የሃያ ብር ጉርሻ እና የሥራ ልብሷን አስረክባት የደንበኛዋ ታክሲ ውስጥ ገባች።

"እንደምን አደርሽ?" አላት ላዳ ታክሲ የሚያሽከረክረው ደንበኛዋ።

"ደህና አደርክ? ወደ ቱሊ መድሐኒዓለም።"

ዮዲት እጅግ አስፈላጊ እና የማይቀር ካልሆነባት በስተቀር ከማንም ሰው ጋር መነጋገር እና የተሰየ ትኩረትን መሳብ አትሻም። በገዘምታ ተንዙው ኤድናሞል ሲኒማ ሲደርሱ የሃምሳ ብር ኖት ጥላለት ወጣችና "መሄድ ትችላለህ፣ አመሰግናለሁ" ብላው በሩን ዘግታ ወደ ተቃራኒው አቅጣጫ መራመድ ጀመረች። አሽከርካሪው ደጋግሞ አመስግኗት አደባባዩን ዞሮ ሄደ።

ዋናውን መንገድ ተከትለው በተርታ የተደረደሩትን ሱቆች እየቃኙ በዘግታ ስትራመድ ካፈ አየሩላሌም" የሚል ማስታወቂያ የተሣፈበት ማራኪ የንግድ ቤት በር ላይ ስትደርስ ወደ ውስጥ ገባችና ከወደ ጥግ ያለ ወንበር መርጣ ተቀመጠች።

'ኡፍ! ሰው ለምንድነው ሴት ላይ የሚያፈጠው?' አለች በሐሳቧ። የነበሩት ጥቂት ደንበኞችም ሆኑ የካፌው አስተናጋጅች እየሰረቁ ይመለከቷት ነበር።

"ምን ልታዘዝ?" አለ ፈገግተኛው አስተናጋጅ።።

"ቡና እንደ ወረደ" አለችውና ከቦርሳዋ ማርልቦሮ አውጥታ ለኮሰች።

አሁን ሁሉም ሰው እንደ ተላመዳት ሁሉ ትኩረቱን ቀይሯል። ዮዲት ወፍራም እና ጥዑም መዐዛ ያለው ቡናዋን ፉት እያለችና ሊጋራዋን እየማገች ዘና አለች። የጧት ልማዷ ነው። የዚህችን ጣጠኛ ዓለም እንቅስቃሴ ከመጀመሯ በፊት ወፍራም ቡናዋን እና ሊጋራዋን አጣጥማ ሁለቱንም እኩል መጨረስ አለባት። አሁንም ቡናዋን ጨልጣ ሊጋራዋን መተርኮሻው ላይ ካጠፋች በኋላ አስተናጋጁን በእጅ ምልክት ጠራችው።

"እቤት!" አላት በፈገግታ።"

"ቡናችሁ አይጣፍጥም!"

"ጥሩ ቡና ነው እኮ። ምን ጎደለው?"

"የፈርኦን ቡና የላችሁም?"

"እኔ አላውቅም። ሙሴን ልጠይቀው?!"

"ቀይ ባሕርን አቋርጠህ?"

መልስ ሳይሰጣት ጥሏት ሄደ። እዚህ ሥፍራ በመጣች ቁጥር ዕለታዊ በሆነ ኮድ (ምስጢራዊ ቃል) መጠቀም አለባት። ያለዚያ አበክሮ የሚያውቃት የካፌው "አስተናጋጅ" ወደ ውስጥ አያስገባትም።

ከአምስት ደቂቃ ቆይታ በኋላ ተመልሶ መጣና "የፈርኦን ቡና ተጥዷል። ተከተይኝ።" አላት።

ዮዲት ከወንበሯ ተነስታ ተከተለችው። የኋለኛውን ከፍል በር ከፈት አድርጎ ሲያሳልፋት ወደ ውስጥ ገባች። አስተናጋጁ በሩን ከኋላዋ ዘግቶ ተመለሰ።

"ሻሎም! ውቢቷ ዮዲት" አላት አንድ ዕድሜው በሠላሳዎቹ መጨረሻ ዓመታት የሚገመት፣ ቀጠን፣ ረዘም ያለ ጎልማሳ። ከወንበሩ ተነስቶ ወደ ዮዲት በፈገግታ መጣ።

"ዮዲትዬ ደህና ነሽ?!" ጉንጭዋን ሳማት።

"ሃይ ጌዲ!"

"ነይ ተቀመጭ የኔ ቆንጆ። ዛሬ ምን እግር ጣለሽ?" አርሱም ተመልሶ ከጽሕፈት ጠረጴዛው ኋላ ተቀመጠ።

"ስማ ጌዲ . . ."

"ምን ትጋበገር?"

"ቡና ጠጣሁ። ስማ ጌዲ ..."

"እየሰማሁ ነው። የኔ ወለላ!"

"ኡኳ። አታቋርጠኝ። ስማ ...እ.. ቱልአቪቮች እየተከታተሉኝ ነው።"

"ለምን?"

"እኔ እንጃ!" አለችው ትከሻዋን እየናጠች።

"ማንነቱን ለይተሻል።"

ዮዲት በጠባብ ጂንስ ሱሪ የተከሸኑ እግሮቿን አንስታ የጌዲዮን ጠረጴዛ ላይ ሰቅላ ወደ ኋላዋ ደገፍ አለችና ሲጋራዋን አቀጣጠለች። በረጅሙ ምጋ ሳበችለትና ባዶውን አየር ዥዝዝ ብላ እያየች ጢሱን በረጅሙ ክስንፈሯ ለቀቀችው።

ይህ ሁሉ ሲሆን ጌዲዮን በዝምታና በትዕግስት ያያታል። አስተያየቱ ወሲባዊ ጉምገፖት ለመሆኑ አያጠራጥርም።

"ፊልድ ኦፊሰሬ ነው።" አለችው በዝግተኛ ድምጽ። ክቤን ሌላ የሚከተለኝ አለመኖሩን ማረጋገጥ አለብኝ አለች በሐሳቧ።

"ፊልድ ኦፊሰርሽ ከሆነ ለምን በስውር ይከታተልሻል? አርሱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አንቺን የማግኘት መብት አለው እኮ።"

"ስማ ጌዲ! እኔ ይህንን ጉዳይ ላንተ ማብራራት የለብኝም። የፊልድ ኦፊሰር ተግባርና መብቱም እስከ ምን ድረስ የዘለቀ እንደሆነ አውቃለሁ። አንተም ታውቃለህ። ነገር ግን በትናንትናው ዕለት ነው። ቤን በምስጢር ዋጋ "ለምን? አላውቅም አለችው።

"እየሸ ዮዲት። ፊልድ ኦፊሰርሽ ለመሆኑ አርግጠኛ ነሽ? በመኪና ነው ይከታተልሽ የነበረው?"

"አዎን በመኪና ሲከተለኝ ነበር። ወደ ሆቴሌ ስመለስ ቤን ሎቢው ውስጥ ተቀምጦ፣ በመጽሔት ተከልሎ ሲመለከተኝ አየሁት። ዛሬ ጧት ከሆቴሌ ስወጣ ሎቢው ውስጥ አድፍጦ ሲጠብቀኝ ነበር። የጽዳት ሠራተኛ ተመስዬ ሸወድኩት።"

"ትናንት በመኪና ይከታተልሽ የነበረው ሰው ቤን ለመሆኑ እርግጠኛ ነሽ?"

"እርግጠኛ አይደለሁም። የሚያሽከረክረው መኪና ፍጥነት ስለነበረው መልኩን በደንብ አላየሁትም።"

"ምን ዐይነት መኪና?"

"ቡናማ ቀለም ያለው ላንድ ክሩዘር።"

"የውጭ ሀገር ዜጋ ለመሆኑ እርግጠኛ ነሽ? አንቺን ለመከተሉም?"

"አዎን!" አግሯን ከጠረጴዛው አንስታ መሬት አሳረፈችና ፊቷን ወደ እሱ በጣም አስጠግታ "እንድ ውለታ ልጠይቅህ?" አለችው። "የተወደድሽ ማታ ሃሪ? ምን ልታዘዘ?" አላት። ማታ ሃሪ ብሎ ሲጠራት ዮዲት ፈገግ አለች።

ማታ ሃሪ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ገነኛ የነበረችና እጅግ የተዋበች ፈረንሳዊት የናዚ ጀርመን ሰላይ ናት። የጠላት ሰላይ መሆኗ ከተረጋገጠ በኋላ በጥይት ተደብድባ የሞት ጽዋ መጨለሟን ዮዲት በስለላ ሙያ በሠለጠነችበት ጊዜ ስሟና ተግባሯ በተደጋጋሚ እየተነሳ በትምህርቷ ውስጥ ተጠቅሶላታል።

"ሁለተኛ ማታ ሃሪ ብለህ አትጥራኝ!" አለች ቆጣ ብላ።

"ለምን የኔ ቆንጆ?" ከወንበሩ ተነስቶ ተንጠራራ።

"የሞት ምልክት ስም ነው።"

ጌዲዮን ከልቡ ሳቀና ጠረጴዛውን ዞሮ ወደ ዮዲት መጣ። "የኔ ቆንጆ! ማን ከሞት ይቀራል?" አላትና አጠገቧ ቆሞ ፀጉሯን እያሻሸ በትኩረት ተመለከታት።

"ይህን የሚከታተለኝን የውጭ ሀገር ዜጋ ምንነትና ማንነት እንድታጣራልኝ እፈልጋለሁ።"

"ላሬ ጧት ቤን ሆቴልሽ ውስጥ እንደነበረ ነግረሽኛል። ለመሆኑ እዚህ ድረስ ተከትሉሽ ይሆን?"

"በጣም እርግጠኛ ነኝ አልተከተለኝም።" ያለቀ ሲጋራዋን መተርከሻው ላይ አጠፋች።

"እየሽ ዮዲት። እኛ የቤተ እስራኤልን ማሕበረሰብ ነው የምንወክለው። ተግባራችንም እዚህ ሀገር የቀሩ ቤተ እስራኤሎችን መርዳትና ታሪክዊ እና ሃይማኖታዊ

ቅርሶቻችንን መስብሰብ ብቻ ነው። አስራኤልን ጨምሮ የማንም ወኪል አይደለንም። ስለዚህ ከማንኛውም መንግሥትም ሆነ ተቋም ጋር ለመጋጨት አንሻም።"

"የኢትዮጵያን ቅርሶች ለመግዛትና በድብቅ ከሀገር ለማውጣት ስትሞክሩ ከመንግሥት ጋር፣ እያጋጨንም ትላለህ? ከዚህ የዘረፍከውን . . . ማለት አ . . . የሰበሰባችሁትን ቅርስ ወደ አስራኤል ስታሻግሩ አስራኤልን አላገላገላችሁም?" አለች ዮዲት እጅግ ተገርማ።

ጌዱዮን ፊቱን ወደ ዮዲት አድርጎ ጠረጴዛው ላይ ተቀመጠ።

"እየሽ ዮዲት። ተቀዳሚ ተግባራችን እኔና አንቺን ጨምሮ ቤተ—እሥራኤሎችን መርዳትና ማገልገል ነው። ለማንኛውም ከማንም ጋር ቢያላትመኝም የሚከታተልሽን ሰው አጣራለሁ። በተረፈ ዝግጅታችሁ እንዴት ነው?"

"ዝግጅታችን እስከ አሁን በጥሩ መልኩ እየተከናወነ ነው።"

"ነገር ግን ብቃት ይጎድላችኋል ብዬ አሰጋለሁ።"

"እሱን ለኛ ተውልን። ብቃት ያነሰን መስሎ ከታየህ የጠየቅንህን ዕርዳታ ተባበረን።"

"ለምን እንተባበራችኋለን?" አላት አያሾፈ።

"ስማ አንተ ደደብ!" አለችው ቆጣ ብላ "ማንኛውም አይሁድ ትብብርና ድጋፍ ተጠይቆ ዕርዳታውን በነፃ ለማሰ አያውቅም። ይህ የአይሁዶች ባሕል ነው። አንተ ወይንም ይህ "የቤተ— እሥራኤሎች ማሕበርህ ከእኛ ቡድን ጋር የሚተባበረው በልዋጩ ልንሰጣችሁ የምንችለው ነገር አንዳለ ስለምታምኑ ነው።"

"እምን የኔ ቆንጆ በጣም ልክ ነሽ። በዚያው ልክ ስህተትም አለብሽ።"

"ምን ዐይነት ስህተት?"

"ውለታ ፍለጋ ስንል እንደምንረዳችሁ ተናግረሻል። መልካም! በኤግዚቢሽን ለመታየት ከሚመጡት ቅርሶች መሃል እኛ የምንፈልገው አንድ ጥንታዊ የብራና መጽሐፍ እንደሚገኝ ነግራሻለሁ። ነገር ግን እኛ ለናንተ ድጋፍ ለመስጠት የተስማማንበትን ሌላ ምክንያት ሳትጠቅሽው በማለፍሽ እዝኔብሻለሁ።" አላት የቀልድና የማፌዝ ቅያሜ ገፅታ እያላያት።

"ነበር ሻሮንጉርጉርነቱን፣ ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊነቱን መቀየር ስለማይችል?"

"አምን የኔ ቆንጆ! አላት።

"ብራቮ ጌዲ!" ብላ ከወንበሯ ተፈናጥራ ተነሳችና "አሁን ግና ኦፐሬሽን መቅደላ እንደሚሳካ እርግጠኛ ሆንኩ!" ብላ ተጠመጠመችበት።

ወደ ደረቱ አስጠግቶ ያዛትና "አሳካዋለሁ!" አላት።

ምዕራፍ አስር

ራሄል 'የጧት ወፍ' ናት። እናም ቀድማ የነቃችው እርሷ ናት። ያሬድ አጠገቧ ያንቀላፋል። ምንም እንኳ ራሄል የጧት ወፍ ብትሆንም ዛሬ ግን ባይነጋ እየተመኘች ነው የነጋባት። ዕድሜ ለ "ዘመቻ መቅደላ" የትምህርት ቤት ዘመን ፍቅረኛዋ ያሬድን ከለንደን እምጥቶ አጠገቧ አስተኝላት። እንሶላውን ወደ ታች ዝቅ አድርጋ የያሬድን ሰፊ፣ ፀጉራም ደረት በለስላሳ ጣቶቿ እየዳሰሰች በሐሳብ ወደ ኋላ ነጎደች።

አብረው ተምረዋል። አብረው ተመርቀዋል። የሚወዷቸውን ነገሮችና ልማዶች ተጋርተዋል። በጣም ተቀራራቢ እምነቶችና ሐሳቦች አሏቸው። ይህ ሁሉ አብሮነትና መላመድ እንዲሁም መግባባት ቀስ በቀስ ወደ ፍቅር ጥምረት አደገ። ለዚህም ይመስላል ያገራቸውን ታሪክ እና ቅርሶች አስክ አምልኮት በደረሰ ፍቅር ስለሚወዱ 'ቅርሳችን ይጠበቅ' መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅትን መሥርተው የተዘረፉና ወደ ባዕድ ሀገሮች የተጋዙ ቅርሶችን ለማስመለስ በጋራ ይከመዋል፣ ታግለዋል። ዛሬ ደሞ እጅግ ለላቀውና ጀብደኛ ለሆነው 'ዘመቻ መቅደላ' ተልዕኮ ጎን ለጎን ተሰልፈዋል። ከሁሉም በላይ ያሬድ አልጋ ውስጥ የሚለጣት ፍቅር ነፍሷን በፍቅር ካቴና ከርችሞታል።

ራሄል ያሬድን እየታከክች በላዩ አልፋ ከአልጋ ወረደችና አገጩን በጣቶቿ እየነካካች "ያሬድ . . . ያሬድ . . . አትነሳም? አንድ ሰዓት ሞልቷል።" አለችው። ጠዋት አንድ ሰዓት ላይ ቀስቅሽኝ ብሏት ነበር።

ጥቂት አጉተምትሞ ዐይኖቹን ገለጠና በረጅሙ ተነፈሰ። "ተነስ የኔ ቆንጆ። ወደ ላንፎርድ እሄዳለሁ። ሶፊያን ሥራ ከመግባቷ በፊት ማግኘት አለብኝ።" አለችውና ረሽቦም ፒጃማዋን እየጎተተች ወደ መታጠቢያ ቤት ገባች።

"ሶፊያ ማን ናት? ሊላት አሰበና ተወው። አይመለከተውም። እሱም ተነሳና፣ ልብሱን መለባበስ ጀመረ።

ራሄል ከመታጠቢያ ቤት ወጥታ፣ ለባብሳ፣ ለሁለቱም ቁርስ አስናድታ፣ ተመግበው ሲወጡ ልክ ሁለት ሰዓት ሆኖ ነበረ። የመኪናዋን በር ስትከፍት ከሰዓት በኋላ እንደሚገናኙ ወስነውና ተሳስመው ተለያዩ። ያሬድ በእግሩ የስድስት ኪሎን ዳገት፣ ራሄል በመኪናዋ የአራት ኪሎን ቁልቁለት ወጣው፣ ወረደችው።

ራሄል የመኪናዋን ፊት ወደ መንገዱ አዙራ የትምህርት ቤቱን አጥር ይዞ የሚገኘው ፓርኪንግ ላይ ስትቆም አያሌ ዘመናዊ አውቶሞቢሎች እየመጡ ትምህርት ቤቱ መግቢያ ላይ ተማሪ ልጆቻቸውን እያወረዱ ይመለሳሉ። መኪናዋ ውስጥ ተቀምጣ 'ጠያም ዘለግ ያለ' የተሰኘውን የአስቴር አወቀን ዘፈን እየኮመኮመች እያንዳንዱን መኪና ትቃኛለች።

አምን በመጨረሻም አየቻት። ሶፊያ ባሏ በሚያሽከረክራት ቶዮታ ሊፍት ባክ መኪና መጣች። ሶፊያ ባሏን ስማ፣ አስፋልቱን ማቋረጥ ስትጀምር ራሄል ከመኪናዋ ወርዳ በፍጥነት ተከተለቻት።

"ሶፊ!"

ዘወትር ሶፊያን አቆመና በእጁ ወደ ራሄል አመለከታት።

'ማን ናት አሏ?' በሚል አስተያየት ቆማ ጠበቀቻት። ራሄል ፊቷን በፈገግታ ሞልታ ቀረበቻት።

"ውይ! ራሄልዬ! ምን አግር ጣለሽ?" ሶፊያ በደስታ እየጮኸች አብሮ አደግ ጓደኛዋ ላይ ተጠመጠመችባት።

"ሶፊያ እንደምን ነሽ? በስንት ጊዜያችን ተያየን?" አለች ራሄል ጓደኛዋን በፈገግታና በናፍቆት ዐይን እያየቻት።

"በጣም ደህና ነኝ ራሄል። አንቺስ? ዛሬ ምን አግር ጣለሽ? መቼም አግብተሽ፣ ወልደሽ፣ ልጅ ትምህርት ቤት ላደርስ መጥቺ ነው አንዳትይኝ!"

"አይ ሶፊ ለዚህ ዐይነቱ ወግ ማዕረግ አልደረስኩም። ግን ወደዚያው ለማቅናት ገዘ የጀመርኩ ይመስለኛል። ዛሬ እንኳ የመጣሁት ያንቺን ዕርዳታና ምክር ፈልጌ ነው።"

"ምነው? ምን ገጠመሽ?" አለች ልበ ቀናዋ ሶፊያ የባልንጀራዋን ፊት በኃላፊነት ስሜት እየተመለከተች። "ምን የምረዳሽ ነገር አለ?"

"ይሄውልሽ ሶፊ፣ ከዳሮ ዐይ ፍሬንዴ ጋር.....እእእ.....አንቺ የምታውቂው አይመስለኝም.....ለንደን ነበር የሚኖረው። አሁን በቅርቡ ወደ ሀገር ቤት መጥቶ ልንጋባ ተና ተና እያልንልሽ ነው።"

"እ. . .እንዴት ደስ ይላል! እንኳ ለዚህ አበቃሽ የኔ ቆንጆ! ኮንግራ!" አለችና ሶፊያ ጓደኛዋን ከልብ በመነጨ የደስታ ስሜት አቅፋ ከሳመቻት በኋላ በፈገግታ

እየተፍለቀለቀች..... "በቃ ገባኝ! ሚዜሽ ልታደርጊኝ እንዳይሆን ብቻ ለሚዜነት ትንሽ አላረጀሁብሽም? ግን አንቺ ከጠየቅሽኝ ደስታውን አልችለውም!"

ሶፊያ ያነሳችው ሐሳብ ፈጽሞ ያልጠበቀችው የሆነባት ራሄል ጥቂት ግራ ተጋባች። እርሷ የመጣችበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ያቀደችውን የሐሰትና የእብለት ዘዴ ከጓደኛዋ ልበ ቀና ሐሳብ ጋር ስታመሳዝነው የሐፍረት ሽውታ ፊቷን አቀላው።

"እምን ሶፊዬ። ከመጣሁበት ጉዳይ አንዱ የሚዜ ጥያቄ ነው። መቼም እምቢ እንደማትይኝ አተማመናለሁ። ሌላውና ቀላሉ ጉዳይ ደሞ የሠርግ መደገሻ አዳራሽ ለመጠየቅ ነው የመጣሁት። ይሄ ትምህርት ቤታችሁ መጠነኛና ጥሩ አዳራሽ እንዳለው አውቃለሁ። ያንቺን ሠርግ ታድሚበት የለ?"

"እምን የኔ ውድ ራሄል። ግን እኮ ለውጭ ሰው አይከራይም! እኔም እዚህ የደገስኩት እንደምታውቂው የትምህርት ቤቱ የስታፍ አባል በመሆኔ ነው።" ብላ ሶፊያ ጥቂት ካሰበች በኋላ "ሌላ ቦታ አዳራሽ አጣሽ? ለማንኛውም ነይ እንግባ . . . ቢሮዬ ተቀምጠን እናውራ።" አለችና የራሄልን ክንድ ይዛ ወደ ግቢው መራቻት።

"እምን ሶፊያ እንደምታውቂው ወቅቱ የሠርግ ጊዜ ነው። አዳራሽ የተባለ ሁሉ በሙሉ ተይዟል።" ራሄል ከሶፊያ ጋር ታውራ እንጂ በጥቁር፣ ሰፊ መነጽር የተከለሉት ንቁ ዐይኖቿ እየተቅበዘበዙ የግቢውን ጠቅላላ ንድፉን፣ መንገዶቹ፣ የሕንፃዎቹን አቀማመጥ እና በመካከላቸው ያለውን ርቀት ሁሉ እያስተዋሉ መረጃውን ወደ አዕምሮዋ ያስተላልፉ ነበር።

"እምን ራሔሌ። ወቅቱ የሠርግ ስለሆነ አዳራሹ ሁሉ ይከራያል፣ ዋጋውም ይንራል።" አለች ሶፊያ የቢሮዋን በር በቁልፍ እየከፈተች። ሁለቱ ጓደኛሞች ከገቡ በኋላ ሶፊያ ከጽሕፈት ጠረጴዛዋ ጏላ ወንበር ላይ ተቀምጣ ጓደኛዋንም እንድትቀመጥ ጋበዘቻት።

"ራሄልዬ ሻይ፣ ቡና፣ ኬክ ምን ልዘዝልሽ?" አለቻት ተመቻችተው ከተቀመጡ በኋላ።

"የለም ሶፊዬ። ቁርሴን አድርሼ ነው የወጣሁት። ለመሆኑ አዳራሹ ምን ያህል ሰው ይይዛል?"

"እስከ አራት መቶ የሚችል ይመስለኛል። ሌላም ችግር አለ። ቀኑን በትክክል ባላውቀውም ሰሞኑን አንድ የባሕል ይበሉ የምንትስ ኤግዚቢሽን ይታይበታል ተብሉ አዳራሹ እየታደሰና እየተዘጋጀ ነው። ለመሆኑ ያንቺ ሠርግ መቼ ነው?"

"እምን ሰምቻለሁ። የቅርሳ ቅርስ ኤግዚቢሽን ነው አሉ። የኛ ዩኒቨርሲቲም ዝግጅቱ ላይ ስላለበት ሰምቻለሁ። ሆኖም ግን ኤግዚቢሽኑ የታቀደው በዚህ ወር መጨረሻ ላይ ነው። የኔ ሠርግ ደግሞ ከሁለት ወራት በኋላ ነው" አለች ራሄል። 'አቤት ውሸት ለካስ እንዲህ ቀላል ነው!' ስትል አሰበች።

"ይሄ መልካም ነው። ግን ቅድም እንዳልኩሽ ለትምህርት ቤቱ የስታፍ አባላት ወይንም ለቅርብ ቤተሰቦቻቸው ካልሆነ በስተቀር አዳራሹን ለቢዝነስ አያከራዩም።" ብላ ጥቂት አሰብ አደረገችና ጓዳኛዋን እያስተዋለችት... "ግን ራሄልዬ አንቺን የአክስቱ ወይንም የአጎቱ ልጅ ባደርግሽ ማን ይከለክለኛል?" ስትል በፈገግታ ጠየቀቻት።

"ሶፊዬ! እኔ አላ . . .ምንም!" ራሄል ብድግ ብላ የጓደኛዋን እጅ ሳመችው። "እውነት ቤተሰቤ ናት ብለሽ አዳራሹን ልታስፈቅጅልኝ ነው?"

"ላንቺ ለውድ ጓደኛዬ? ምንም አትጠራጠሪ። እስቲ ለማንኛውም ለሠርግሽ ይብቃል! ያንላል የሚለውን ከወዲሁ ለመወሰን እንድትችይ ለምን አዳራሹን አላስጎበኘሽም?"

ምዕራፍ አስራ አንድ

ዶክተር አንዱዓለም የጉሀ ሰዓቱ ከሚቱ አንድ ሰዓት ላይ ቀስቀሰው። ሁለት ሰዓት ተኩል ሲሆን ገላውን ተጣጥቦ "ሻለቃውን የሚመስጥ" ሲል የመረጠውን ዘናጭ ሙሉ ልብሱን ለባበሰ። እንግሊዝ ሀገር በሥራ ዓለም ሲኖር የእንግሊዞችን ባሕርይና ሥነ—ምግባር ቀርጿል። በተለይም የሥራ ባሕርዩ እና የመኖሪያ አካባቢው 'አፐር-ክላስ' ከሚሉት ወግ አጥባቂውና የላይኛው መደብ አባላት ጋር እንዲውልና እንዲያመሽ ስላደረገው በአለባበሱም ሆነ በአነጋገር ዘዴው እንዲሁም በሥነ—ምግባሩ ሁሉ እንግሊዞቹ "እንግሊሽ ጄንትል ማን" የሚሉትን ዐይነት ሰው ሆኗል። አጠቃላይ ቁመናውን በመስተዋት ፈትሾ፣ ኮምፒውተሩን በትከሻውን እንግቦ ከክፍሉ ወጣና በአሳንሱር ወደታች ወረደ።

ከሒልተን ግቢ ውጭ ቢጫ ቀለም የተቀቡ በርካታ ላዳ ታክሲዎች ተደርድረዋል። አንዱዓለም ይዞታው ጥሩ ወደመሰለው አንድ ታክሲ ተጠጋና "የኔ ወንድም ሂልቶፐስ ሬስቶራንት ታደርሰኛለህ?" አለው።

አሽከርካሪው ፈገግ ሲል የፊት ጥርሱ ወላቃ ቢሆንም ከወጣትነቱ ጋር ያምርበታል።

"አዎን ጌታዬ! እመልስዎታለሁ ወይንስ ማድረስ ብቻ?"

"አድርሰህኝ አንድ ሰዓት ያህል ትጠብቀኝና ትመልሰኛለህ።"

"ሁለት መቶ ብር ብቻ ይከፍላሉ።"

"በጣም አልበዛም?" አለ አንዱዓለም ከፈገግታ ጋር።

"የለም አልበዛም ጌታዬ። ጥሩ ዋጋ ነው። መንግሥት በነጋ በጠባ ነው ነዳጅ የሚጨምርብን።

አንዱዓለም የጎላውን በር ከፈተና ገባ። ሹፌር ሞተር አስነስቶ ወደ ምኒልክ ቤተ-መንግሥት ዳገቱን ሲያያዘው..." ማነው ስምህ?" አለው አንዱዓለም።

"ቸርነት!" አለ አሽከርካሪው።

"ሁለት መቶ ብር እየጠየክ ምኑን ቸርነት ሆንክው?"

"ጌታዬ ስምና ተግባር እኩ ከተለያዩ በጣም ሰነበተ።" አለው በጎላ መስተዋት እያየው።

አንዱዓለም ጧ! ብሎ ሳቀ። 'ደግነቱ እዚህ ሀገር ችግሩ የመብዛቱን ያህል አስቂኙም እንደዚያው ነው' ሲል አሰበና ..." ጥሩ አባባል ነው የተናገርከው!" አለው።

አሁን ወደ ቀኝ ታጥፎ የጣዛንቺስን ከዚያም ወደ ግራ ታጥፎ በቀለበት መንገድ እየከነፈ ነው።

"ሁለት መቶ ብዙ አይምሰልዎት። አንደኛ የሐልቶፕስ ዳገት ራስ ዳሽን ማለት ነው። ሁለተኛ ነዳጁ ንሮአል። ኑሮውማ! ው...ው.!አይነሳ።"

ትራፊኩ ቀላል ስለነበረ ከዐሥር ደቂቃዎች በኋላ የሂል ቶፕስን ዳገት መውጣት ሊጀምሩ ..." ውነትም ኃይለኛ ዳገት ነው!" አለ አንዱዓለም።

"በጣም ኃይለኛ እንጂ ጌታዬ! የዘመኑ ኢንቬስተር ተብዬ ካላጣው መሬት ጋራ ላይ ሬስቶራንት መሥራት ምን ይባላል? የድሀ መኪናን ለማፈንዳት ነው እኮ! ኮብራና ፕራዶ ከሚነዳ ሀብታም በስተቀር ድሀ አይድረስብን እንደማለት ነው እኮ!"

አንዱዓለም ሳይወድ ፈገገ አለ።" ሬስቶራንት የት ቢገነባ ይሻላል ትላለህ?"

"ሚዳማና አመቺ ሥፍራ ላይ ነዋ!"

'አምን እኛ አበሾች ሁሉም ነገር ሜዳ በሜዳ ቢሆንልን እንወዳለን።' አለ በሐሳቡ። አሁን ሂል ቶፕስ ግቢ ገብተው ታክሲው ቆሟል።

"የምትፈልገውን ነገር እያዘገከ ጠብቀኝ።" አለውና ከታክሲው ወርዶ ሬስቶራንቱ ገባ።

ከፊል አዲስ አበባን ወለል አድርጎ የሚያሳይ አነስተኛ ኮረብታ ላይ የተመሠረተውና በአብዛኛው በውጭ አገር ዜጎች የሚዘወተረው ሬስቶራንት ጥቂት ደንበኞችን ብቻ በማስተናገድ ላይ ነበር።

ለእይታ አመቺ ቦታ መርጦ ከተቀመጠ በኋላ አስተናጋጁ ሜኑ አምጥቶ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠና ማዘዝ የሚፈልገውን ነገር በትህትና ጠየቀው።

የአቦነይ ጭማቂ፣ ኢንግሊሽ ኦመሌት እና ቡና አዘዘ። ከዐሥራ አምስት ደቂቃዎች በኋላ ከበታቹ የተንጣለለችው አዲስ አበባን እያስተዋለ ሲቆዝም ቁርሱ ቀረበለት። የአቦነይ ጭማቂው ተፈጥሮአዊ ጣዕም እጅግ ያስደስታል። 'እንደወረደ' የተጨመቀው ቡና እንኳንስ ቃናው ሽታው ብቻ መንፈስ ያረካል። አንዳቸውም ለው

ሠራሽ ማዳበሪያና ኬሚካል ያልነካቸው ናቸው። 'ዘመቻ መቅደላ ከተሳካ እኔም ለንደን እና የማዳበሪያ ምግቦቿን ደህና ሁኑ.....'

"ባልሳሳት ዶክተር አንዱዓለም ነህ"

ዶክተር አንዱዓለም ከሰጠመበት የሐሳብ ባህር ብትት ብሎ ባነነ። "እ? አዎን ጌታዬ!" አለና ብድግ ብሎ ወደ አንግዳው ሰው እጁን ለሰላምታ ዘረጋ።

የሰውዬው እጅ ቀጭን እና ከጥንካሬው የተነሳ እንደ ሞርሳ አጥብቆ የሚይዝ ነው። "ሻለቃ ፍቅሩ?" አላቸው እጁን እስኪለቁት ድረስ ተጨንቆ።

"እዎን መቀመጥ እችላለሁ?" አሉ እጉድጓዳቸው ውስጥ በተወሸቁ ትናንሽ ዐይኖቻቸው አተኩረው እየተመለከቱት። "እዎን ጌታዬ ይቀመጡ። አለ አንዱዓለም። በመጨረሻም እጁን ሲለቁት በእፎይታ እየተነፈሰ ተቀመጠ።

ሻለቃ ፍቅሩ ወንበር ስበው ተቀመጡ። ዕድሜአቸውን በሃምሳዎቹ አጋማሽ ገመተው። ረጅምና ቀጥ ያለ ቁመናቸው፣ እንደ ሃጫ በረዶ የነጣው ፀጉራቸውና ከሁሉም በላይ ኮስታራና ስሜታቸውን የማያስነብብ ገፅታቸው ማርኮታል።

ሬስቶራንቱን ለሦስት ሴኮንዶች ያህል ዙሪያውን ቃኙት። አስተያየታቸውን ያስተዋለው ዶክተር 'ይህ ሰው በጣም ፕሮፌሽናል ነው' ሲል አሰበ። እጃቸው ላይ ያሰሩትን ዲጂታል ሰዓት መልክት አድርገው..... "የመቅደላ ጦርነት ከተከናወነ አንድ መቶ አርባ ሁለት ዓመታት ዐሥራ ሁለት ሰዓታት አልፈውታል። 'አፍተር ኦል ዚስ ይርስ' ምን ትፈልጋለህ?" አሉት።

አንዱዓለም ሳይወድ ፈገገ።

"እሺ ዶክተር አንዱዓለም ስለ መቅደላ መጽሐፍ ልትደርስ ወይንስ መጽሐፉን ወደ መቅደላ ለመመለስ ተነስተሃል?" አሉት።

ዶክተር አንዱዓለም የመደንዘዘ ስሜት ተሰማው። ሻለቃ ፍቅሩ ስለ ዘመቻ መቅደላ ያውቃሉ ብሎ አልገመተም።

"ይህን መሰሉን ሐሳብ ማን አወራዎት ጌታዬ?"

"ወፍ!"

"ወፊቱ አሳሳች ናት ጌታዬ። እኔ የመጽሐፍ ደራሲ ነኝ።

"ዶክተር አንዱዓለም ቡና አዘዝልን እና ዘና አንበል። "አሉት የሲጋራ ፓኬትና ላይተር ክጃኬታቸው ኪስ አውጥተው አቀጣጠሉና ለአንዱዓለም ዘረጉለት። "የለም አመሰግናለሁ።" ብሎ የራሱን ማርልቦሮ ለኮሰ።

ቡናው ቀርቦ ሁለቱም ጠጥተው እስኪያበቁ ስለ መቅደላ አምባ ጦርነት አንስተው ተወያዩ። "አፄ ቴዎድሮስ ያን ሁሉ ቅርስ እግራቸው ከረገጠው ሥፍራ ሁሉ እየሰበሰቡ መቅደላ አምባ ላይ ለምን አከማቹ?" ሲሉ ሻለቃ ፍቅሩ ረገጥ አድርገው ጠየቁት።

ዶክተር አንዱዓለም በሕይወት ዘመኑ ብዙ ጊዜ የቀረበለት ተደጋጋሚ ጥያቄና ሰፊ ትንታኔ የሰጠበት መልስ ስለሆነ ፈገግ አለ።

"ቅርሶቹን በአንድ ማዕከላዊ ሥፍራ አሰባስቦ ለመጠበቅ..."

"የለም አንዱዓለም" ሲሉ አቋረጡት። ስማ ዶክተር ይህንን 'ታሪክ 101' ሌክቸርህን ለተማሪዎችህ አቆየውና ትክክለኛውን ምክኒያት ልንገርህ። ወይንም የጎደለውን ነገር ልመ·ላልህ።"

"እዳምጣለሁ።"

"አፄ ቴዎድሮስ ሀገራቸውን ይወዳሉ። ቅርሶቻቸውንም እንደሚወዱ አያከራክረንም። መቅደላን የታሪካዊ ቅርሶች ቤተ·መዝክር ለማድረግ ያላሰባቸው 'ሞቲቭ' ክቅን ልቡና የመነጨ ቀና ሐሳብ ሊሆን ይችላል። አይመስልህም?"

"አልጠራጠርም!"

"ነገር ግን ከአፄ ቴዎድሮስ ጀርባ ይህን መልካም እና ቀና ሐሳብ የጫረባቸው ሌላ አካል አይታይህም?"

"አይታኝም።"

"ሌክሬት ሶሳይቲ... ፍሪ ማሶን... ወ.ዘ.ተ. የሚባል ነገር አልሰማህም?"

"ሰምቻለሁ። እናስ?"

"ጀምስ ብሩስ 'የዓባይን መነሻ ለማግኘት' ብሎ ወደ ኢትዮጵያ መጣና መጽሐፉ ሄኖክን ሰርቆ ሄደ። አሉ የምስጥራዊው ቡድን (ፍሪማሶን) አባል ለመሆኑ ትጠራጠራለህ?"

"አልጠራጠርም። የተረጋገጠ ሃቅ ነው።"

"አየህ ዶክተር ይህ ለሺህ ዓመታት በዓለም ላይ ተንሰራፍቶ የኖረ ምሥጢራዊ ቡድን ዐይናቹን ኢትዮጵያ ላይ የጣለው ጀምስ ብሩስ መጽሐፉ ሄናክን ሰርቆ ከወሰደላቸው በኋላ ነው። ምሥጢራዊው ድርጅት ጥንታዊ ዕውቀትና ጥበቦችን እያሰሰ ይዘርፋል፤ ይቀማል፤ ይሰበስባል፤ ያከማቻል ያጠናል። ለካስ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር አለች! ያውም ከማይገኙ ጥንታዊና ምስጢራዊ ዕውቀቶች (ሌሶቴሪክ) ጋር!" አሉና በሚሲዮን እና በሌሎችም የ"ድጋፍ" ሽፋን ዘመቱባት። እሜ ቴዎድሮስ በዙሪያቸው የነበሩት "አማካሪዎቻቸው" በሙሉ ፍሪማሶን ለመሆናቸው የምትጠራጠር ከሆነ ንገረኝና ከልቤ ልታዘብህ።" አሉ ሻለቃው።

"ይታዘቡኝ አጠራጠራለሁ።"

"ሻለቃው ፊገግ አሉ። "እንግሊዛውያኑ የዓፄ ቴዎድሮስ አማካሪዎችና ረዳቶች ጆን ቤል እና ፕላውዴን፤ ሌሎቹም በዙሪያቸው የነበሩት ስኮቲሾች እና እንግሊዞች ሁሉም ፍሪማሶን ናቸው። አንድ ቀን ይህችን ኋላ ቀር እና አልባሌ አገር በቁጥጥራችን ሥር አድርገን ቅርሶቿን እና የጥበብ ሥነ—ጽሑፎቿን እንዘርፋለን ሲሉ ከንጉሡ ጀርባ ዶለቱ.....።"

"እናም....." አለ በተመስጦ የሚያደምጣቸው ዶክተር።

"እናም ለዓፄ ቴዎድሮስ ከየአድባራቱና ገዳማቱ ሁሉ ብርቅዬዎቹን የብራና ድርሳናትና ሌሎችም ቅርሶች "እንዳይባክኑ እንዳይጠፉ" በአንድ ሥፍራ ሰብስበው ያስጠብቋቸው የሚል ምክር ሰጧቸው። 'አውሮፓ ቢሆንማ ቤተ—መዘክር የሚባል ነገር አለ' አሏቸው። የምስጢራዊው ድርጅት አባላት አንድ ቀን ጠራርገው ሊወስዱት ያመቻቸዋል፤ ይቀላቸዋልና። ገባህ?" አሉ ሻለቃው።

አንዱዓለም ሥጋውን ሊያቃጥል የደረሰ ሲጋራውን መተርኮሻው ላይ አጠፋውና "ሊሆን የሚችል ነው። ለመሆኑ በምን መልኩ ነው ሊረዱን የሚችሉት? ባሕታዊው እንዳገኝዎት አዘዙኝ እንጂ የነገሩኝ ዝርዝር ጉዳይ የለም።" አላቸው።

"ዶክተር አንዱዓለም ለማንኛውም እኔ ልረዳህ ወይንም ልረዳችሁ የተነሳሁት እንደናንተ ለቅርሶቻችን "ፋናቲካል" ፍቅር ስላለኝ አይደለም። አሉት እንደ መፍገግ ብለው።

ግራ ተጋብቶ አያቸው። "ታዲያ ለምንድነው?"

"ለባሕታዊው ብዙ ነው። የባሕታዊው ውለታ አለብኝ። በተጨማሪም ሀገሬን የምወድና የመቅደላ አካባቢ ተወላጅም ነኝ።"

ዶክተር አንዱዓለም በስሜት ተውጦ ወደ ፊት ጠጋ አለና በንቃት ማዳመጡን ቀጠለ።

"ከብዙ ዓመታት በፊት በጣዕረ-ሞት ተይዛ የነበረች ሕይወቱን ከሞት ያተረፉልኝ ባሕታዊው ናቸው። ለሰባት ቀናት በተከታታይ ቅጠላ ቅጠሉን እፉቱ እየጨመቁ ጠብታውን ሰያጠጡኝ፤ ሥራ ሥሩን ሲያበሉኝ በጥቂት ቀናት ውስጥ ከአፀደ ሞት ተመልሼ ጤናማ ሕያውቱን መኖር ጀመርኩ።"

"ምን ነበር የታመመት?" አለ አንዱዓለም አጢሶ በጨረሰው ሲጋራ ሌላ ሲጋራ እየለኮሰ።

"ተወው ምን ያደርጋል? ወይንም ባሕታዊውን ጠይቃቸው። ሰባቱንም ቀን ሰባት የተለያዩ ዕጽዋት እንደሰጡኝ ግን ሳልነግርህ አላልፍም።"

"እውነትዎን ነው?" አለ አንዱዓለም ከመደነቁም ባሻገር በቅርቡ ያጠናውን እና የተረጎመውን፤ ዕድሜ ጠገቡን 'መጽሐፈ ጥበብ'ን እያሰበ።

"ይህ ብቻ ወይንም ቅጠላ ቅጠል ብቻ አልነበረም።" አሉና ሻለቃ ፍቅሩ ቀጠሉ። "በየዕለቱ ዕፀ መድኀኒቱን ሲሰጡኝ ወይንም መድኀኒቱን ከመስጠታቸው በፊት የሚያነበንቡት ዐሉት መሰል መነባነብ ወይንም 'ሪቹዋል' ነበረ። የሚገርመው ነገር ያንን ሪቹዋል ወይንም መነባንብ ሲደግሙት ጤናማ ያልሆነው ወይንም የታመመው አካሌ ሲያገግም የሚታወቀኝ ይመስለኝ ነበር።"

"የሚነግሩኝ ታሪክ ዕውነት ከሆነ እጅግ ያስደንቃል።"

"ሕያው ዕውነት ነው! አንዱዓለም። ከማወራህ የበለጠ አንተ ብዙ ነገር እንደምታውቅ አውቃለሁ።"

"ለመሆኑ በምን መልኩ ነው ሊረዱን የሚችሉት?"

"ጠቃሚ ኢንፎርሜሽን ሲኖር ለዚያች ልጅ አቀብላታለሁ።" አሉት።

'ይህን ሽማግሌ ፖሊስ ዝቅ አድርጌ ገምቼው ነበረ።' አለ በሐሳቡ። ዮዲት ፈዕሞ በማይጠረጠር ሽፋን ሬስቶራንቱ ውስጥ ተቀምጣ ሻለቃውን እንድትቆጣጠርና እንድታጠና ነበር ባለፈው ምሽት ስልክ ደውሎ ትዕዛዝ የሰጣት። ዶክተር አንዱዓለም ዮዲትን በምልክት ጠራትና ከሻለቃ ፍቅሩ ጋር አስተዋወቃት።

ምዕራፍ አስራ ሁለት

ከቀትር በኋላ 8 ሰዓት ላይ የ 'ዘመቻ መቅደላ' አባላት በሙሉ ዶክተር ሥራውብዙ ቢሮ ተገኝተዋል።

ዶክተር ሥራው ከፔርሙሉ ቡና እየቀዱ "የሚፈልግ አለ?" ሲሉ ጠየቁ። ሁሉም እንደሚፈልጉ ሲያሳውቁ አንድ በአንድ በመሰላቸት ተመለከቷቸውና "የሚፈልግ ቀድቶ መጠጣት ይችላል።" ብለው የራሳቸውን መጎንጨት ሲጀምሩ ሁሉም በሳቅ አወኩ። ራሄል ተነስታ እየቀዳች ካደለች በኋላ የራሷን ይዛ ወደ መቀመጫዋ ተመለሰች።

"እስካሁን ሁላችሁም ያቀረባችሁት ሪፖርት እንደሚያሳየው የሥራ ድርሻችሁን በእጥጋቢ መልኩ እየተወጣችሁ ነው። ለኦፕሬሽን መቅደላ መሳካት እጅግ አስፈላጊ የሆነውን ግብዐት ለማሟላት ሳምሶን ነገ ወደ ድሬዳዋ እንደሚበር አሳውቋል። ምናልባት ሌላ የቀረ ወሳኝ ነገር ካለ 'ሴፍ ሐውስ' ብቻ ነው። ይህንን በተመለከተ ከራሄል መስማት እፈልጋለሁ።"

"አስተማማኝ ቤት ፍለጋ ብዙ ዞሬያለሁ። የመጨረሻውን ምርጫ ለመወሰን ሳምሶን አብሮኝ ቢመለከተው ጥሩ ነው። ምክንያቱም ቤቱ የመሣሪያዎቻችን መደበቂያ ብቻ አይደለም። "እቅዳችንን ያለ ስጋት የምናጠናበትና ተግባራዊ ልምምድ የምናደርግበት ስለሆነ የሳምሶንን ፕሮፌሽናል ወታደራዊ ሐሳብ እፈልጋለሁ።"

"የት አካባቢ ነበር ያገኘሽው?" ሳምሶን ጠየቃት።

"ኮተቤ አካባቢ።"

"መልካም።ይህን ስብሰባ ስናበቃ አብረን እንሄዳለን።"

በመቀጠልም ረዘም ያለ ጊዜ የወሰደው ኤግዚቢሽኑ በልዕልት ኢዛቤል ተመርቆ ሲከፈት ማን ምን ዐይነት ግዳጅ እንደሚወጣ፣ ምን ዐይነት ያልታሰቡ ሁኔታዎች ሊከሰቱ እንደሚችሉ፣ የሰው ሕይወት መጥፋትን፣ የደም መፍሰስን፣ እና ቅርሶቹን አደጋ ላይ የሚጥሉ ድንገተኛ ሁኔታዎችን እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል፣ ዘመቻው እስኪሳካ ድረስ እያንዳንዱ ተሳታፊ ሊወስደው ስለሚገባ የምስጢር አጠባበቅና ራሱንም ከፀጥታ ኃይሎች እንዴት መሰወር እንዳለበት የመሳሰሉት ዝርዝር ጉዳዮች በጥልቀት ውይይት ተደረገባቸው።

"ሥነ—ሥርዓት!" በሚል ተቃውሞ ከውይይት የታገደው ቅርሶቹ በኃይል ከተያዙ በኋላ የመጨረሻውን የማረፊያ ወይንም የመደበቂያ ሥፍራ ሁላችንም ማወቅ አለብን የሚለው ጥያቄ ብቻ ነው።

ይህ ኤግዚቢሽን አዲስ አበባ ላይ እንደሚደረግ ከታወቀበት ጊዜ አንስቶ የዘመቻ መቅደላ ተሳታፊዎች በሙሉ ለሦስት ወራት ያህል ባወጡት እና በተስማሙበት ዕቅድ መሠረት ቅርሶቹ ዋልድባ ገዳም ይደርሳሉ። ከዚያ በኋላ የመጨረሻውን የመደበቅ ሥራና ኃላፊነት ለባሕታዊው አስረክበው አባላቱ ከተዘጋጀላቸው "ተቀባይ" ጋር በየአቅጣጫው ይበታተናሉ።

የቅርሶቹን የመጨረሻ መጠለያ ሥፍራ በተመለከተ ኃላፊነቱን ለባሕታዊ ብቻ የመስጠቱ ውሳኔ በአንድ የተቃውሞ ድምጽ (በዶክተር ሥራው) ብቻ ከተወሰነ በኋላ ይህን ርዕስ እንደገና አንስቶ መወያየት ማብቂያ የሌለው አተካራ፣ አንዲያም ሲል መከፋፈልን ሊፈጥር ይችላል ሲሉ ተስማምተውበታል።

ዶክተር አንዱዓለም ኮምፒውተሩን እየተመለከተ የቅርሶቹን ዝርዝር ለአባላቱ ሲያነብ ሁሉም በጥልቅ ሐዘንና የቁጭት ስሜት አደመጡት። ይህን ሁሉ የተዘረፈ ብርቅና ድንቅ ቅርስ በማናቸውም መንገድና ዘዴ ለማስመለስ የተሠለፉ መሆናቸውን እያሰቡ ደማቸው ከመንተክተክ የተነሳ እንዳንዴ የምክንያታዊነትን መሥመር እየዘለሉ በጋለ ስሜታዊነት ውስጥ ይዘፈቁም ነበር።

"ዘመዴን ዛሬ ጉብኝቼዋለሁ።" አለች ዮዲት። ('ዘመዴ' ጌዲዮን ማለቷ ነው።)

"ምን ውጤት ተገኘ?" አንዱዓለም ነበረ ጠያቂው።

"እጃቸውን ሊያቀቡሉን ተስማምተዋል።"

ሁሉም የእፎይታና የደስታ ስሜት እየታየባቸው ድምጽ የለሽ ጭብጨባ አሰሙ።

"የጠየቁት ዋጋ የለም?" ሥራውብዙ ጠየቁ።

"አንድ የብራና መጽሐፍ ብቻ።"

"አርዕስቱ?" አንዱዓለም ጠየቀ።"

"መጽሐፈ ጥበብ!"

"አንዱ ዓለም ፈገግ አለና የንባብ መነጽሩን አስተካከለ። የዚህን ብራና መኖር እኔ ራሴ በቅርቡ ነው ያወኩት። ቤተ—እስራኤሎች እንዴት አወቁ?"

"ይህን መመለስ የሚችለው ሞላድ ብቻ ይመስለኛል።" አለች ዮዲት።

"የፕሮፖጋንዳ ሥራ ጉዳይ እስካሁን አልተነሳም" አለ ያሬድ።

ዶክተር ሥራውብዙ በተቀመጡበት እንደ መፍነክነክ እያሉ "እ . . ህህህ" ሲሉ ጉሮሮአቸውን አፀዱ። ሁሉም በዝምታ ጠበቋቸው።

"አፐሬሽን መቅደላን ለማሳካት የምናሠራጨውን ፕሮፖጋንዳ በተመለከተ የቀረን ዝግጅት ዶክተር እንዱዓለም ከለንደን የሚልክልኝ የቅርሶቹን ገጽታ የሚያሳይ ፊልም ብቻ ነው። እርሱ ሲደርሰኝ ዝግጅቱ ይጠናቀቃል። በተረፈ የፕሮፖጋንዳ ፊልሙን ለየትኛው ሚዲያ እንደምንሰጥ የሚወሰነውና ኃላፊነቱን የምወስደው እኔ መሆኔን ተስማምተንበታል።"

"በጣም ከባድ ኃላፊነቶችን ትከሻው የሳበጠ ዶክተር ላይ በመጫናችን የኋላ ኋላ እንዳይቆጨን!" አለች ዮዲት ሲጋራ እየለኮሰች።

ከፍተኛ የሳቅ ፍንዳታ ተከሰተ። "ወቸው ጉድ! እንዳው ምን ዐይነቷ ነውረኛ ናት?" አሉ አዛውንቱ ዶክተር ሥራው ራሳቸውን እየነቀነቁ።

"እየህ ዶክተርዬ?" አለች ዮዲት። "እትፍረድብኝ። መቃብሬን በእጁ እንዳታስቆፍረኝ ስለ ሰጋሁ ነው!" አለችና የብር ጉልላት የመሳሰሉ ዐይኖቿን አስለምልማ እየቻቸው።

ባልደረቦቿ ምን ማለቷ እንደሆነ አልገባቸውም። ሊጠይቋትም አልፈለጉም። ዶክተር ሥራው ከጥልቁና ከጨለማው ልቡስ ጥላቸው ውስጥ አንድ ዐይነት የማስጠንቀቂያ ደወል ሲደውል ተሰማቸው። ምን ማለቷ እንደሆነ ሊጠይቋት ሲሉ እነዚያ ውብ ዐይኖቿ ውስጥ ጥቃቅን የአሳት ፍንጥርጣሪዎች ሲፈነጥቁ ታያቸውና ጥያቄያቸውን ዋጡት።

"የናንተስ 'የመጨረሻው ወንጌላችሁ' ተዘጋጀ?" ሲል ያሬድ እንዴ ሳምሶንን እንዴ ያፌትን እየተመለከተ ጠየቀ።

ያፌትና ሳምሶን ጨምሮ ሁሉም በሳቅ አወኩ። ሳምሶን እንደምንም ሳቁን ገታ አደረገና "እምን አዘጋጅተናል" ብሎ በ 'A4' ግማሽ ወረቀት ላይ የያዘውን ማስታወሻ ማጤን ጀመረ።

"አባክህ ቀጥል። የታላቁ እስክንድርን የጦር ዕቅድ የምታነብ አታስመስል!" አለችና ዮዲት ከመቀመጫዋ ተነስታ እየተውረገረገች በመሄድ የተከፈተው መስኮት እጠገብ ቆማ ሲጋራ ለኮሰች።

"ለነገሩ" አለ ሳምሶን። "ለነገሩ የኛ ዘመቻ መቅደላ ከታላቁ እስክንድር የጦር ዕቅድ ቢበልጥ እንጂ አያንስም። ወታደራዊ ወይንም የትጥቅ ንቅናቄያችንን በተመለከተ ድርሻችንን ሰይተን አውቀናል፤ ደግመን ደጋግመንም ተወያይተንበታል። የቀረ ነገር ቢኖር ራሄል ሴፍ ሐውሱን ስታገኝልን እና የትምህርት ቤቱን ንድፍ ስታመጣልን በአሸዋ ገበታ እና በጦር መሣሪያዎች የታገዘ፣ ግን ተኩስ አልባ የሆነ ልምምዳችንን ለአሥራ አምስት ቀናት ያለማቋረጥ እንቀጥላለን።" አለና ቤቱን በዙር ተመልክቶ ዐይኖቹ ያፌት ላይ ሲያርፉ "የተከበሩ ሻምበል ይቀጥሉ!" አሰው።

"የዲሲፕሊን ጉዳዮችን ነው የማወሳው" አለ ያፌት። ኦፐሬሽን መቅደላን ለማሳካት እያንዳንዳችን መከተል ያለብንን ሥነ—ምግባር ደንብ ወይንም በያሬድ አባባል.....*'የመጨረሻው ወንጌላችን'* ይህንን ይመስላል።"

1ኛ፡ ማንኛውም የኦፐሬሽን መቅደላ አባል በፀጥታ ኃይሎች ካልተተኮሰበት ወይንም በኃይል የመያዝ ሙከራ ካልተደረገበት በስተቀር በፍፁም የታጠቀውን መሣሪያ እይተኩስም።

2ኛ፡ ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ ቢሆኑና አንድ አባላችን የመቁሰል አደጋ ቢደርስበት ሌሎች አባሎች የቆሰለውን ጓደኛችንን በተኩስ ሽፋን ውስጥ ገለል እናደርገዋለን እንጂ በምንም ዐይነት በወደቀበት ትተነው እንሄድም። ወይንም ግዳጃችንን አንፈጽምም።

3ኛ፡ የቆሰለ ባልደረባችን ከሞት የማይድንና በፀጥታ ኀይሎች እጅ መውደቁ የማይቀር ከመሰለው በራሱ ውሳኔ ሕይወቱን ማጥፋት ይችላል።" (እዚህ ላይ ራሄል አማትባ ዐይኖቿን በሁለት እጆቿ ሸፈነች) ያፌት ቀጠለ።

"ሆኖም ግን የደረሰበት አደጋ ሕይወቱ በራሱ እጅ ለማጥፋት የማያስችለው ከሆነ በቅርብ ርቀት ላለ ባልደረባው እንዲጨርሰው መጠየቅ ይችላል። የተጠየቅንም 'ሰርቪሱን' የመስጠት ግዴታ አለብን!"

ዮዲት "ፊውውው!" ብላ በረጅሙ አፏጨችና "ይህ የአልቃይዳ ሕግ ነው! ለማንኛውም ዶክተር ሥራውብዙን ቆስሎ ባገኘው እንዳሰናብተው እስኪጠይቀኝ ድረስ

እንኳ አልጠብቀውም። ስትል ሁሉም ከልባቸው በሳቅ አወኩ። ዶክተር ሥራው ግን ሰውነታቸው ተሸማቆ ፊታቸው ወየበ።

4ኛ፡ ምናልባት ነገሮች ተበላሽተው ቅርሶቹ በፀጥታ ኀይሎች እጅ የሚወድቁ ከመሰለን በያዝናቸው ሆስቴጅስ (ለብለዊ ጋሻ) ተጠቅመን ወደ ተለዋጩ የማምለጥ ዕቅድ እንገባለን እንጂ በምንም ዐይነት መልኩ ቅርሶቹን ማጥፋት ወይ ማውደም አይቻልም። ቅርስ ከሌለው ሕዝብ ቅርሶቹ የተዘረፉበት ሕዝብ ይሻላል። አይመስላችሁም?"

መልስ የሰጠው የለም። እሱም አልጠበቀም። "

5ኛ፡ አፕሪሽኑ ተጠናቆ የማምለጫ መሥመራችንን ከያዝን በኋላ ማንኛውም አባል የራሱን መሥመር ተከትሎ በዕቅዱ መሠረት ይጓዛል እንጂ የቅርሶቹን የመጨረሻ ማረፊያ ለማየት ወይም ለመከተልና ለማወቅ መሞከር የለበትም። ይህን የሞከረ አባል የከሀደት ወንጀል እንደ ፈፀመ ይቆጠራል።" አለና ያፌት ዙሪያውን ተመልክቶ "ኤዲት የተደረገው ወንጌላችን የታከለበት እነዚህ አምስት ነጥቦች ብቻ ናቸው።" ብሎ ንግግሩን ቋጨ።

ራሄል ቦርሳዋን ብድግ አድርጋ ስልኳን አወጣች። ንዝረት ላይ አድርጋው ነበር።

"ሄሎ!"

"እምን ደህና ነኝ።"

"የት?"

"እሺ በዐሥራ ዐምስት ደቂቃዎች ውስጥ እደርሳለሁ።" ,ስልኩን ቦርሳዋ ከከተተች በኋላ ሌላ ዐዲስ ነገር ከሌለ የቤት ኪራዩን ጉዳይ ለመጨረስ መሄዴ ነው። ሳምሶን አብረን ብንሄድስ?" አለችው።

"ጥሩ!" አሉ ዶክተር ሥራው። "እንደተለመደው ሁለት ሁለት እየሆንን በየዐሥር ደቂቃዎች ልዩነት እንወጣለን። ራሄልና ሣምሶን በቅድሚያ መውጣት ትችላላችሁ።" ራሄልና ሳምሶን ወጡ።

ምዕራፍ አስራ ሶስት

"ባሕታዊው" በሚል አጭር ቃል ይጠራሉ። በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ከአሥራ ዘጠን ሃምሳዎቹ መጨረሻ ዓመታት ጀምሮ በርካታ ምዕመናን በሚታደሙባቸው ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት ላይ አጋጣሚውን በመጠቀም በየገዳማቱ፣ አድባራቱ፣ አብያተ ክርስቲያናቱ እየተገኙ ሲሰብኩና ሲያስተምሩ ይታወቃሉ። ምእመናን በጸሎትና በንስሐ አማካይነት መንግሥት ለማያትን የሚወርሱበትን ሃይማኖታዊ ሥነ—ምግባር በማስተማር ስብከቱን ይጀምሩና ቀስ በቀስ ወደ ቀጣዩ አጀንዳቸው ይሻገራሉ።

"ለሃይማኖታችን የጽናት መሠረት የሆኑና በዘረፋ ወደ ውጭ ሀገሮች የተጋዙት ታሪካዊና መንፈሳዊ ቅርሶቻችንን የማስመለስ ዘመቻ መጀመር አለበት። እስከ ዛሬ እነዚህን ቅርሶቻችን ለማስመለስ መንግሥትም ሆነ የቤተ-ክርስቲያኒቱ መሪዎች በቂ ጥረት አላደረጉም።" የሚለው ጩኸታቸው በምዕመናን ዘንድ ተወዳጅና ተደማጭ አደረጋቸው።

"ሃይማኖትን ለማጽናት፣ የሀገርና የእምነት ቅርሶችን ለማስመለስ ከአግዚአብሔር የተላኩ የመናፍቃን መቅሰፍት ናቸው።" ተብሎ በስፋት ተነገረላቸው።

ምዕመናን በሚለግሱት ሙዳዴ ምዕዋት ዘረፋ የበለፀጉ፣ በቅርስ ዘረፋና በተለይም በታቦታት ሽያጭ ሙስና ላይ የተሰማሩ የቤተክርስቲያን መሪዎች ደግሞ "ሃሳዊ - መሲህ" የሚል ታርጋ ለጠፉባቸው። በየክብረ በዓላቱ ቀስቃሽ ሃይማኖታዊ ሰበካቸውን እንዳያካሂዱ መሠናክሎችን ጋረጡባቸው። በ"ባሕታዊው" ላይ የመጀመሪያው ጥቃት የተሰነዘረው በቱአሱጂ (መንፈሳዊ) ኮሌጅ የመጨረሻ ዓመት ተማሪ በነበሩበት ጊዜ ነው።

ወጣቱ ተማሪ ለውጥ ጠያቂ ወይንም ሪፎርሚስት ሆኖ ስለተገኘ 'ኮሚኒስት' የሚል ስም ወጣለት።

ለቤተክርስቲያን የሚገባ ሙዳዴ ምዕዋት እና ስዕለት ቁጥጥር ይደረግበት። ለታሪካዊ ገዳማት አስቸኳይ ጥገና ይደረግላቸው። በየገዳማቱ ተበታትነው የተቀመጡ ለብልሽትና ለስርቆት የተጋለጡ ቅርሶች ተሰብስበው ቤተክርስቲያን በምታሠራው ቤተመዘክር ይቀመጡ። ተዘርፈው ከሀገር የወጡ ቅርሶችን ለማስመለስ የሃይማኖት መሪዎች አዲስና ሰፊ ዓለም አቀፍ ዘመቻ ይጀምሩ። ይህንንም ዘመቻ የሚመራ

በሃይማኖት አባቶችና በታወቁ ምሁራን የተዋቀረ ኮሚቴ ይመሥረት.....::" በማለት የሚያነሳቸው ተደጋጋሚ ጥያቄዎችና ቅስቀሳዎች ጥርስ የገባ ሥጋ አደረጉት::

ወጣቱ የመንፈሳዊ ኮሌጅ "መናፍቅ" እንዲህ እያለ አረጀ::

"ባሕታዊው" መጠሪያቸው ሆኖ ቀረ:: ተዘርፈው በባዕዳን እጅ የሚገኙትን ቅርሶች ለማስመለስ "ዓለም -አቀፍ" ብለው የሰየሙት የዘመቻ ሐሳብ የውጭ ሀገር ጠላቶችንም አፈራላቸው:: ይህን ዘመቻ የሚመራ ኮሚቴ የመመሥረት ሕልማቸው አልሳካ ሲላቸው ተመሳሳይ አላማና እምነት ያላቸውን ለውጥ ናፋቂ ወጣቶችና ሰዎችን አሰባስበው "ቅርሳችን ይጠበቅ" የተባለውን መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋም መሠረቱ:: ተቋሙንም ለረዥም ዓመታት በዳይሬክተርነት ከመሩና ጠንካራ ድርጅት ካደረጉት በኋላ ዶክተር ሥራውብዙ አየለን በፕሬዝዳንትነት፣ ወይዘሪት ራሄል ግዛውን በሥራ አስኪያጅነት ተክተው ወደ ጥናትና ምርምር ሥራ ፊታቸውን አዞሩ::

በድፍን ኢትዮጵያ ባሕታዊ የማያውቁት፣ ያልጎበኙትና ምርምር ያላካሄዱበት ገዳም የለም:: ያላዩት፣ ያላጠኑትና ያልመረመሩት የብራና መጽሐፍ አይገኝም:: እንኳንስ በሀገር ያሉትን ይቅርና በባዕዳን ቤተ—መዘክሮች ቁጥጥር ሥር ያሉትንም ብዙዎቹን ተዘዋውረው መርምረዋል:: ለአያሌ ዓመታት ባደረጓቸው ጥረቶች ወደ ሀገር ያስመለሷቸው ቅርሶች ቀላል የሚባሉ አልነበሩም:: በርካታ ሀገሮችና መራሔ መንግሥታትን ጎብኝተዋል:: በእነዚህ ጉዞአቸው ነገሥታት፣ የነዳጅና የንግድ ቱጃሮች፣ ሊቃውንቶችና ሌሎችም የባሕታዊው "አስተናጋጆች" ነበሩ::

በስፋት እንደሚነገረው ከሆነ (ባሕታዊው የራሳቸውን ዝና ተርከው አያውቁም) በተለያዩ ኢትዮጵያዊና ጥንታዊ የሕክምና ጥበበ በተለይም ዕፀ መድኀኒት በመጠቀም በጽኑ የታመሙ በሽተኞችን ፈውሰዋል:: ከተራ ሰዎች አንስቶ በሞት አፋፍ ላይ የነበሩ ኢትዮጵያንን እና የውጭ አገር መራሄ መንግሥታትን በመጎብኘት ከገዳይ ደዌዎቻቸው ፈውሰዋቸዋል:: በዚህም የፋይናንስ አቅማቸውን እንዳጠናከሩ በስፋት ይወራል::

የቤተክርስቲያኒቷ መሪዎች "ባሕታዊው የታመሙ ባዕዳን ቱጃሮችን የሚፈውስ በሰይጣናዊ ጥበቡ ነው::" ሲሉ፣ ብዙሃኑ ምዕመናን እና ኢትዮጵያ ላይ ጥላቸውን የጣሉ ባዕዳን ደግሞ "ይሄ ቂስ የሕክምና ጥበቦችን እና የፈዋሽ ዕፆችን ምስጢራዊ ዕውቀቶች የያዙ የብራ መጽሐፍት አግኝቷል::" ይላሉ::

በተለይም "ባሕታዊው"ን የሚያስታውሱ ሁሉ "ዘመቻ መቅደላ" ከመከናወኑ ከጥቂት ወራት በፊት መስቀል አደባባይ በተከበረው የደመራ በዓል ላይ ያደረጉትን ንግግር ወይንም ስብከት ያስታውሳሉ.....::

".....አንድ ሥርዓተ—መንግሥት ተለውጦ አዲስ ቢተካ የቀድሞውን መንግሥት ፈጥሮ የነበረው ግለሰባዊ፣ ማሕበራዊና ተቋማዊ አሳቡ እስካልተለወጠ ድረስ አዲስ መንግሥትና አዲስ ሥርዓት ተመሠረተ ማለት ጥፋትን ባገር ላይ መጋበዝ ነው። ለተራበ፣ ለደኸየ፣ ሥልጣን የጨበጠን እንዲያመልክ ለተገደደ፣ ከሁሉም በላይ ታሪካዊና የማንነት መገለጫ የነበሩ ቅርሶቹን ለተራቆተ ሕዝብ የተሻለ ሥርዓት አመጣሁ የሚል አዲስ ተቋም ብሔራዊ አንድነትና ፍቅርን ያጠነክራል እንጂ አይንድም። ብሔራዊ ስሜትን፣ ታሪክን፣ የማንነት መገለጫ ቅርሶችን ይንከባከባል እንጂ ለለባ አያደርግም።" በተመስጦና በጋለ ስሜት ከሚያደምጠው ሕዝብ የማያቋርጥ ከንፈር መጠጣና የሐዘን እንባ ይወርወዳል። አንዳንዱ ባሕታዊው ንግግራቸውን ለመቀጠል የሕዝቡን ዝምታ ለመጠበቅም እየቆመ ይቀጥላሉ።

"ቅርሶቻችን የማንነታችን አሻራ ብቻ አይደሉም። የዕውቀትና የጥበብ ማሕደሮቻችን ናቸው። ዛሬ ነሮች ከሚመጻደቅበት ቁሳዊ ዕድገታቸው የበለጡና የረቀቁ ኢትዮጵያዊ ጥበቦቻችንን ባዕዳኖች እያስዘረፉ ለማጋዝ ን ተሌት ሲባዝኑ አንዳንድ ሕሊናቸውን ለአፍቅሮተ ንዋይ የሸጡ የኃይማኖትና አባቶችና ሌሎች ዘጎችምነው፡ "ድንቅነሽን በዕርዳታ ቀየርንላችሁ!" ሲሉን በየቤታችን፣ በየልቦናችን የደም ፅንባ ያነባን ለንቶቻችን ነን? ይህች ጥንታዊትና የተባረከች ሀገር ተነስታ ወድቃለች፣ ወድቃም ተነስታለች። ምናልባት ዛሬ ወድቃለች ብለን የምናምን ካለን መውደቅና መነሳት ዑደታዊ ነውና መነሻዋ፣ መበልጸጊዋና በዓለም ገጽ ላይ ተገቢ ክብሯንና የማዕረግ ሥፍራዋን የምታስመልስበት ጊዜ እጅግ በጣም መቅርቡን በልዑል እግዚአብሔር ስም አሰረግጡ ነግራችኋለሁ!" እልታውና ዕብጨባው አደባባዩን ዋጠው።

"ይሄ ተብታቢ ደብተራ ሕዝባዊ አመጽ ሊያስነሳ ያቀደ ይመስለኛል" አለ ራቅ ብሎው ከቆመት ሲiiል ለባሽ የደህንነት አባላት አንዱ።

"ለማንኛውም እኛ ሪፖርት እናደርገዋለን!" አለ ሌላው ባልደረባው።

ያም ሆነ ይህ ባሕታዊው "ስማ!" ከሚሉበት አደባባይ ተነስተው እነሆ ዛሬ "ዘመቻ መቅደላ አሳት ላይ እንደ ጥቁር አለት ቀጥ ብለው ቆመዋል።

ምዕራፍ አስራ አራት

ከቀኑ አሥራ አንድ ሰዓት ላይ ሳምሶንና ራሄል መገናኛን አልፈው ኮተቤን እየተቃረቡ ነው።

"እኔ የማይገባኝ ነገር ምን መሰለህ ሳምሶን? ወደ ገጠር ወጣ ብለን የተኩስ ልምምድ የማናደርገው ለምንድን ነው? መሃል አዲስ አበባ፣ ያውም አንድ ግቢ ውስጥ የተደረገ የደረቅ መሣሪያ ልምምድ ምን ያህል ብቁ ያደርገናል?"

"ከብቃት አኳያ ብዙም ብቁ አያደርግም። ከመካከላችን አንዳችም ወታደራዊ ልምምድ የሌለሽ አንቺ ነሽ። ላንቺ ብቻ ብለን ሁርሶ የጦር ማሰልጠኛን በሊዝ እንግዛ?"

ራሄል በተሰነዘረባት ተረብ ፈገግ አለች። "ደግሞም መተኮስ አይጠበቅብሽም። የተከበረችውን ልዕልት አንድ ሥፍራ ላይ አስቀምጠሽ ካጫወትሻት ይበቃናል።"

"የታላቋ ብሪታኒያን ልዕልት ማጫወት በራሱ መታደል ነው!" አለችው እየቀለደች።

"እኔ የቸኮልኩት ለምን መሰለሽ?"

"ለምንድነው?"

"ያቺ የቀበጠች ልዕልት በመሣሪያ አፈሙዝ እና በቦምብ ተፈጥሮ ስትያዝ ምን እንደምትመስል ለማየት።"

"እንግሊዞችን አታውቃቸውም! እንደኔ ግምት የንጉሣዊ ቤተሰቧን እና የመንግሥቷንም ክብር ለመጠበቅ ስትል የመጣውን አደጋ ፍንክች ሳትል የምትቋቋመው ይመስለኛል።"

"አይመስለኝም" አላት ሳምሶን።

ይህን ሲነጋገሩ ኮተቤን አልፈው ጥቂት ከተጓዙ በኋላ ወደ ቀኝ የሚታጠፍ ያስፋልት መንገድ ይዛ ሠላሳ ሜትር ያህል እንዳሸከረከረች አንድ ሰው የእጅ ምልክት አሳያት።

"ጎሽ! ደላላው ይሄውና" ብላ ቆመች። የቤት አከራይ ደላላው አንድ ቀይ ቀለም የተቀባ የብረት በር ላይ መጥሪያውን ተጫነ። በሩ ሲከፈት ራሄልን ከነመኪናዋ አስገባት።

ግቢው አጠቃላይ ስፋቱ አንዱ ሺህ ካሬ ሜትር ሲሆን ዋናው ቤት የተሠራው አንድ መቶ ካሬ ሜትር ላይ ነው። ከቤቱ ኋላ ከግምብ አጥሩ ጋር ተያይዘው በመዳዳ የተሠሩ ሰርቪስ ቤቶች፣ አንድ የመታጠቢያና መፀዳጃ ቤት፣ የምግብ ማብሰያ፣ እና የዕቃ ቤት አለው። ግቢው ሙሉያውን በግንብ አጥር ታጥሮ የተሰባበሩ ጠርሙሶች ተሰክተውበታል።

ሳምሶን እና ራሄል በደላላው አማካይነት የቤቱ ባለቤት ከሆኑት ባልቲት ጋር ተዋወቁ። ወይዘሮ የሺ ይባላሉ። ዕድሜያቸው ከሃምሳ አምስት ዓመት ከፍ ያለ ይመስላሉ። ቀደም ሲል ደላላው ለራሄል እንዳጫወታት በቅርቡ ባለቤታቸው በሞት ተለይተዋቸዋል። የወይዘሮ የሺ ሁለት ሴቶች እና አንድ ወንድ ልጃቸው በአሜሪካን ሀገር ነዋሪዎች ናቸው። ወይዘሮ የሺም ለከፍተኛ ሕክምና ወደ አሜሪካ ሊሄዱ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ጨርሰዋል። ስለዚህ ቤቱን አከራይተውና ለታናሽ እህታቸው ውክልና ሰጥተው ለመሄድ ከልጆቻቸው ጋር ተማክረው ወስነዋል።

ሳምሶንና ራሄል ቤቱን አንድ በአንድ ጎበኙት። በአከራይዋ ፊት መነጋገር ስላልቻሉ በመተያየት እና በዐይን ምልክት ብቻ 'ለምንፈልገው ተግባር ተስማሚ ቤት ነው።' ተባባለዋል። ይህን ቤት የወደዱት አንደኛ ከከተማ ወጣ ያለ መሆኑ፣ ሁለተኛ ከዋናው መንገድ መራቁ፣ ሦስተኛ ለዘመቻ መቅደላ አባላት ሁሉ መያዝ በቂ ክፍሎች ስላሉት፣ አራተኛ በአካባቢው ከሁለት የከብት ማደለቢያና ከአንድ የዘይት መጭመቂያ ድርጅቶች በስተቀር የቅርብ ነዋሪዎች (ጎረቤቶች) አለመኖራቸው፣ እንዲሁም በየጊዜው ብቅ ጥልቅ እያለ የሚጎበኝ አከራይ አለመኖሩ ናቸው።

ጥቂት የማይባል ጊዜ ከፈጀ ውይይትና ድርድር በኋላ ራሄል የአንድ ዓመት የኪራይ ዋጋ ሠላሳ ስድስት ሺህ ብር በስሚ ቼክ ጽፋና ፈርማ ለወይዘሮ የሺ አስረከበቻቸው። የቤቱ የኪራይ ውልም ተጽፎ አከራይ፣ ተከራይና ምስክሮች ከፈረሙበት በኋላ አንድ ቅጅ ለተከራይዋ ራሄል፣ ሌላው ቅጅ ደግሞ ለአከራይዋ ተሰጠ። ይህን ጊዜ ነበር ሳሎኑ ውስጥ ትልቁ ሶፋ ላይ ጋደም ብለው ሠራተኛቸው ያፈላችውን ቡና ፉ . . .ት! እያሉ ራሄልን እና ሳምሶንን እያንሿሿሩ ይመለከቱ የነበሩት ወይዘሮ የሺ "ለመሆኑ፣ ቤተሰብ አለሽ? እርሱ ወንድሜ ባልተቤትሽ ይሆን?" ሲሉ ጠየቋት።

"የለም ወይዘሮ የሺ። ሳምሶን የሥራ ባልደረባዬ ነው። ባለቤቱ በቅርቡ ከውጭ ሀገር የመጣ ሰው ነው። ልጆች የለንም። እንድ ወንድሜና አንዲት እህቴም ከባሕር ማዶ ስለሚመጡና እዚህ አንድ ዓመት ያህል ስለሚቆዩ እነርሱን ለማስተናገድ ስል ነው ከአቅሜ በላይ የሆነ ቤት የተከራየሁት።"

"ይሁና! ይሁና!" አሉ ወይዘሮ የሺ። "ለመሆኑ ባልተቤትሽና እህት ወንድሞችሽ የመጡት ታመሪካ ይሆን?"

"አይደለም" አማማ። እነርሱ ከእንግሊዝ ሀገር ነው የመጡት።"

"መቼ ነው ቤቱን የምትገቢበት?"

"ነገ ቀሰም ቀቢዎች ይገፍ እመጣና ሙሉ ቀን አሳድሼ ከጨረስን ተነገ ወዲያ ለልንገዶቼ የመኝታና ሌሎች አስፈላጊ አቃዎች ገዝቼ የራሴንም አስዊኜ እገባለሁ።"

"መልካም! መልካም! እኔም ነገ ውክልና የሰጠኋት ታናሽ እህቴን አስጠራና አስተዋውቅሻለሁ። አድሳቱን ተመጀመርሽ በፊት አቃየን ዊኜ እህቴ ቤት እገባለሁ።"

"ለመሆኑ የወኪሷ እህትም ቤት የት ነው?"

"ወደ ካራ ነው የኔ ልጅ።"

ቡናቸውን ጠጥተው መልካሙን ሁሉ ተመኝተው ተለያዩ። ከምሽቱ አንድ ሰዓት አካባቢ። ራሄል ሰደሳላው ተጠቢውን ዋጋውን ሰጥታ አሰናበተችው።

"ምነው ፈጠንሽ? ያሬድን ይዘሽ አዲሱ ቤት ዛሬውኑ ልትገቢ ነው እንዴ? " አላት ላምሶን ወደ መሃል ከተማ ጉዞ እንደ ጀመሩ።

ፈገግ ብላ "ነገረኛ!" አለችውና ነጻጅ መስጫውን ረገጠችው።

.....////////.....

"ብራና አስጎብኚ ድርጅት" ሲካሄድ የነበረው ስብሰባ ሲያበቃ ከቢሮው የወጡት ሁለተኛ ምድቦች ያፌትና የዲት ናቸው። ድምፃቸውን በጣም ዝቅ አድርገው ተቀራርበው እያወሩ የፎቁን ደረጃዎች ጨርሰው ከሕንፃው እንደ ወጡ የፓርኪንግ ሥፍራው ላይ ከተደረደሩት ታክሲዎች ውስጥ ወደ መረጧቸው ሁለቱም በየፊናቸው አመሩ።

"ወደ አይቤክስ ሆቴል" አለ ያፌት።"

"ቦሌ ወንድማማች ሕንፃ" አለች ዮዲት።"

ሁለቱም ተሣፍረው ጉዞ ጀመሩ። ዮዲት የጎላ ወንበር ላይ ተቀምጣ በተደጋጋሚ ወደ ጎላዋ እየዞረች ትመለከታለች። የሚያልፉ መኪኖችን ትቃኛለች። ሰዓቱ ትራፊክ የበዛበት በመሆኑ አሉምፒያ አካባቢ ሲደርሱ ጉዞአቸው የኤሲ መስለ።

"የኔ እህት" አለ አሽከርካሪው። "በእውነቱ በዚህ የተጨናነቀ ሰዓት ያውም ከኢትዮጵያ ሆቴል ቦሌ ድረስ ሠላሳ ብር በመስማማቴ ጤነኛ አይደለሁም!" አለ እየተበሳጨ።

ዮዲት በውስጧ ፈገግ አለችና "በመስማማትህ በጣም ዕድለኛ መሆንህን አሁንኑ ታያለህ።" ብላ ከጅንስ ሱሪዋ ሦስት ባለ አሥር ብር ኖቶችን አውጥታ ካቀበለችው በኋላ "ከግማሽ መንገድ ልትመለስ ነው። ቦታ ስታገኝ በቶሎ አውርደኛ" አለችው።

የታክሲ አሽከርካሪው ግራ ተጋብቶ ደምበል ሕንፃ አጠገብ ሲያቆም ዮዲት በፍጥነት ወረደችና በተርታ ቆመው ለተሳፋሪ ጥሪ ከሚያደርጉት ሚኒ ባስ ታክሲዎች መሃል የሞላውን

መርጣ ገባች። ወዲያው ረዳቱ በሩን ዘግቶ ጉዞ ሲጀምሩ እዚህ ድረስ ያመጣት ላዳ ታክሲ ወደ መስቀል አደባባይ አትጣጫ ዞሮ ሊመለስ እየችው።

'ወደ ቦሌ መልካም ጉዞ ሚስተር ቤን!' አለች በሐሳቧ።

**********////////**********

በኢትዮጵያ የሕገመንግሥታዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ቻይና መንግሥት ልዩ መልዕክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ሚስተር ዠዋን ዬንግ ፉ ከሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚንስትሩና ከጠቅላይ ሚንስትሩ ልዩ ረዳት ጋር ስብሰባ ለማድረግ ቀጠሮ በተያዘላቸው መሠረት ሦስቱ ሰዎች በሚንስትሩ ቢሮ ውስጥ ስብሰባ ተቀምጠዋል።

"ከወዳቻችን የቻይና መንግሥት የተላከልንን የመረጃ ሪፖርት ተመልክተነዋል" አሉ ሚንስትሩ አምባሳደሩን እየተመለከቱ። እጅግ የጠበቀ ምጣኔ ሀብታዊና ፖሊቲካዊ ግንኙነትና ቁረኝት ካለን ከቻይና መንግሥት የደረሰን መረጃ በጣሙን አስደስቶናል። እኔም ከቡር ጠቅላይ ሚንስትራችንን ወክዬ የመግሥታችንን ምስጋና ላቀርብልዎ እሻለሁ።"

"አንዳንድ የውጭ ሀገር የስለላ ተቋማት" አሉ የተቅላይ ሚንስትሩ ልዩ ረዳት። "በቅርቡ አዲስ አበባ ከተማ ሊደረግ የታቀደውን የጥንታዊ ቅርሶች ኤግዚቢሽን አስመልክቶ አሉታዊ እንቅስቃሴዎች ለማድረግ፣ ለምሳሌ ታሪካዊ ቅርሶችን ለማሰረቅ እንዳቀዱና ይህንም ለማሳካት ላንዳንድ ብሔራዊ ኃላፊነትና ፍቅር ለጎደላቸው ዜጎቻችን በርካታ ገንዘብ በማስሰስ ላይ መሆናቸውን እኛም ደርሰንበታል።"

"ይህን ጉዳይ በተመለከተ የኔኛም የመረጃ ምንጮች ሳይታክቱ በመንቀሳቀስ ያገኟቸው አያሌ መረጃዎች ስላሉ ሁሉን አቀናጅተን ተገቢውን ርምጃ እንወስዳለን።" አሉ የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚንስትሩ።

"ሀገሬ" አሉ አምባሳደር ፉ ትናንሽ ዐይኖቻቸው ላይ የሰኩትን የንባብ መነጽር ወደ ኋላ እየገፉ። "ሀገሬ ለወዳጇ ኢትዮጵያ ምንጊዜም ቢሆን ጠቃሚ ተግባራትን እና ድጋፎችን እንዲሁም የሚንተሊጀንስ ትብብሮችን ከማድረግ ወደ ኋላ እንደማትል በመንግሥቴ ስም ላረጋግጥልዎ ወዳለሁ!"

**********////////**********

ምዕራፍ አስራ አምስት

ዶክተር ሥራውብዙ አየለ በምቹ ሜርሴዲስ መኪናቸው ዶክተር እንዱዓለም ይፍረደውን ሒልተን ሆቴል ቅጥር ግቢ ውስጥ ካደረሱት በኋላ በአራት ኪሎና በጊዮርጊስ አሻቅበው ወደ ሰሜን ማዘጋጃ ሲከንፉ ከሒልተን ሆቴል ቅጥር ግቢ ውጭ የቆመችው እና ከኋላዋ ያፈት የተሳፈረባት ላዳ ታክሲ ስትከተላቸው በፍጹም አላስተዋሉም። የሚያስተውሉበት ቀልብም አልነበራቸውም።

በሞባይል ስልካቸው ደጋግመው ይደውላሉ። "የደወሉላቸው ደንበኛ ስልክ ለጊዜው ጥሪ አይቀበልም!" የሚል ተደጋጋሚ ምላሽ ያገኛሉ። "ይቺ....." እየተራገሙ፣ እየተሳደቡ፣ መኪናውን እንዳከነፉ ነበር የባሕታዊው መኖሪያ ቤት ደጃፍ ላይ የደረሱት። ከኋላ ሲከተላቸው የነበረው ታክሲ ከሃያ ሜትር ርቀት ላይ ሲቆም አዛውንቱ ዶክተር በኋላ መመልከቻ መስታወት ቢያዩትም ፊፀሞ የተለየ ትኩረታቸውን ሳይስብ ቀረ።

'ይሄ ቀፋፊ!' አሉ ዶክተሩ ዋናውን በር ለከፈተላቸው የባሕታዊው ታማኝ አገልጋይ የውሸት ፈገግታ እያሳዩት። ግቢውን ዘልቀው መኪናቸውን አቁመው ወረዱ። ልክ የሳሎኑ በር ላይ ደርሰው ለማንኳኳት እጃቸውን ብድግ ሲያደርጉ በሩ ተከፈተ።

"ዶክተር ሥራውብዙ ግባ!" አሉ ባሕታዊው በሩን ይዘውላቸው። ብዙዎች ከነ ማዕረጋቸው ይጠሩዋቸዋል። እሳቸውም ስማቸውን ከነ ማዕረጉ ይወዱታል። ሆኖም ግን እኚህ የሰዎችን ልቡና ሰርስረው የሚያዩ የሚመስሉት ባሕታዊ "ሥራውብዙ" ብለው ሲጠሯቸው ልባቸው ይሸበርባቸዋል። ለምን እንደሆነ ባይገባቸውም የእውነት ... "ሥራው ብዙ" የሚሏቸው ይመስላቸዋል።

"ደህና ዋሉ አባቴ! ሥራ እንዳላስፈታሁዎት ይሰማኛል።" አሉና የቡና ጠረጴዛውን እልፍ ብለው አንዱ ነጠላ ሶፋ ላይ አረፍ አሉ። ከባሕታዊው ጋር ያላቸው እውቅና በርካታ ዓመታትን ያስቆጠረ ነው። ብዙ ውጣ ውረዶችንም አብረው አልፈዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በተለይም የዘመቻ መቅደላ ጥንስስ ተጥሎ ተግባራዊነቱ መንከባለል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ዶክተር ሥራው ከባሕታዊው ጋር በግምባር ሲገናኙ አልያም በሌሉበት ስለ እርሳቸው ሲያስቡ ልባቸው ይሸበርባቸዋል። 'ሥራው ብዙ!'

ባሕታዊው የንሥር አሞራ የመሰሉ ሰርሳሪ ዐይኖቻቸውን ዶክተሩ ላይ እንደተከሉ "የዛሬው ስብሰባ እንዴት ተከናወነ?" ሲሉ ጠየቋቸው።

"እ. .ህ ..ህ. .ህ!" አረጋዊው ዶክተር ጉሮሮአቸውን አፀዱ። "ስብሰባው መልካም ነበር። አብዛኞቹ እጅጓዶች ቀደም ብለን የተነጋገርንባቸው ቢሆኑም ዛሬም ተንትነን በተደጋጋሚ ተወያይተንባቸዋል። በመሃላችን ምንም የሐሳብ ልዩነት የለም።"

"የቅርሶቹን የመጨረሻ መጠለያ ሥፍራ በተመለከተስ?" አሉ ባሕታዊው አሁንም ዐይኖቻቸውን ከዶክተሩ ላይ ሳይነቅሉ።

" እ . . እምን እሱን በተመለከተ ያው ቀደም ባሉት ጊዜያት ተነስቶ እንደነበረው ሁሉ ዛሬም 'ሁላችንም ማወቅ አለብን' የሚል የተቃውሞ ጥያቄ ቀርቦ ነበረ። የዚህ ጥያቄ አከራሪ አራማጅ ያቺ ዮዲት ናት! መቼም የርሷን ያህል አደገኛ በጥባጭ ከቶም አይገኝም!" አሉ ረገጥ፣ ጠበቅ አድርገው ዮዲትን እየከሰሱ።

"እንዲያ ነው?" አሉ ባሕታዊው "እርሷን ለኔ ተውልኝ። ሌላስ ተቃዋሚ የለም?"

"የለም አባቴ። ዋናው አቀንቃኝ እርሷ ናት።"

"የቤተ—እስራኤሎችን ቡድን በተመለከተስ?"

"ይቺው ዮዲት ናት ኮንታክታችን። አንድ ቀላል ክፍያ ብቻ እንደሚጠይቁንና በኦፐሬሽን መቅደላ እንደሚረዱን ቃል መግባትቸውን ነግራናለች።"

"መልካም የምሥራች ነው። ለመሆኑ የጠየቁት ወሮታ ምንድን ነው?"

"መጽሐፍ ጥበብ።"

ባሕታዊው ምንም ዐይነት ለየት ያለ ስሜት አላሳዩም። "ይሁና! እኛም ምስጢራዊውን የአበው መጽሐፍ እንፈልገዋለን። ይልቁንስ ቤተ—እሥራኤሎች 'ዘጠና ደቂቃ በኤንቴቤ' የተሰኘውን መጽሐፍ ቢጠይቁን አይሻላቸውም ኖሯል?

አስካሁን ያላወቁት ፍርሃት ያሸበራቸው የነበሩት ዶክተር በባሕታዊ ምላሽ ከልባቸው ተንከትክተው ሳቁ። ሳቃቸውን አብቅተው ቀና ሲሉ ባሕታዊ እንደ ድንጋይ ሙት በሆኑ ዐይኖቻቸው ት. . . ክ ብለው ሲመለከቷቸው አዩና ወዲያው ወደ ፍርሃት ዓለም ተመለሱ።

"እየህ ዶክተር። አንዳንድ ነገሮች ለሁሉም የሰው ዘሮች የተሠሩና የታለሙ ናቸው። አንዳንድ ነገሮች ደሞ ለተወሰኑ ሰዎች ወይንም ሕዝቦች ብቻ የተከለሉ ናቸው። ለምሳሌ አየርን ተመልከት። የማነው? የሁሉም! መጽሐፈ ጥበብን ተመልከት። የማነው? ለማነው የተፃፈው? በማን ነው የተፃፈው? የኢትዮጵውያን! ለኢትዮጵያውያን!

በኢትዮጵያውያን! በቃ! ይሄው ነው። እኛ ታልሙድን ወይንም የዳዊትን ዙፋን ጠይቀናቸዋል? አልጠየቅንም። እነርሱ የኛን ለምን ይጠይቃሉ? ስለጠየቁም እንሰጣቸውም።"

"ጽላተ ሙሴ የማን ነው?" አሉ ዶክተር ሥራው። ጥያቄው ካፋቸው ከመለጣቸው በኋላ ቢፀፀቱም ባሕታዊ ግን እንዳች የተለየ ስሜት አልታየባቸውም።

"ጽላተ ሙሴ የኛ ነው። ከእስራኤል ሀገር የመጣውም በራሱ ፈቃድ ነው እንጂ አበሾች ወይ እሥራኤሎች ከምኩራቡ ብድግ ስላደረጉት አይደለም። እንዳው የታሪክ አተካራ ሳስማብዛት እንጂ የቀድሞዎቹ እሥራኤሎች የኩሽ አበሾች ናቸው ብንል አውነት አይደለም?"

ዶክተሩ መልስ አልሰጡም። ባሕታዊው ረኽቦ፣ ቀጭን፣ ያረጀ ሰውነታቸውን ከሶፋው ላይ እያንቋቋ ብድግ አሉና በዝግታ ወደ መጻሕፍት መደርደሪያው ሄዱ። ከግማሽ ደቂቃ በኋላ የመረጡትን እንዲት አነስተኛ መጽሐፍ ይዘው ተመለሱና ዶክተር ሥራው ፊት ተቀመጡ።

ዶክተር ሥራው መጽሐፉን አንስተው ተመለከቱት።

"ቅዱስ ማርቆስ ኢትዮጵያዊ ነው" ይላል ርዕሱ። ደራሲው አባ ተስፋ ሥላሴ የተባሉ ታዋቂ የቤተ—ክህነት ምሁር ናቸው። ዶክተር ሥራው መጽሐፉን በጉጉት እያገላበጡ "አባ ተስፋ ሥላሴን አውቃቸዋለሁ። ይህን መጽሐፍ መድረሳቸውን ግን አላውቅም ነበር። ይህች ሀገር እኮ . . . . ."

"ተጽፎ የማይዘለቅ ታሪክ ያላት ሀገር ናት!" አሉ ባሕታዊው የዶክተሩን ንግግር አቋርጠው።

"እምን ተጽፎ የማይዘለቅ!"

"ለማንኛውም አሁን የተያዘው ጨዋታ የዜግነት፣ የቅርስ ውርስ፣ ወይንም የንብረት ይገባኛል ጥያቄ ጨዋታ ብቻ አይደለም። ጨዋታው የዕውቀት፣ የጥበብና የታሪክ ዘረፋና የማስመለስ ጥያቄ ነው።"

"ነጮች ጥቁሩን ጠቢብ ነጭ ቀለም ቀብተው ፊረንጅ ማድረግ ከጀመሩ ሰንብተዋል። አንተም ጥሩ አድርገህ ታውቀዋለህ። ፓይታጉራስ" የሚል የግሪክ ስም ሰጥተው ፊረንጅ ያደረጉት ጠቢብ የጥንታዊቷ ግብፅ፣ (አሁን ግብፅ ትባል እንጂ

የጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ግዛት ነበረች) ኢትዮጵያዊው ቶት ነው። የጥንታዊው ሄርሜቲክ ፍልስፍና እና ጥበበ ፈጣሪው ቶት ነው። በግሪኮች ነጭ ቀለም ተቀብቶ ፈረንጅ ነው ተባለ። ሆኖም ግን ስሙን ለውጠው ነጭ ለማድረግ እንደሞከሩት ሁሉ ጥበቡን መውረስና መጠበብ አልቻሉም። ምክንያቱም ጥበቡ የእነርሱ አልነበረም። ሊገባቸውና ሊካኑትም አልቻሉም። ስለዚህ ዛሬም ድረስ የአበሾችን የቆየ፣ በምስጢር የተጠበቀ ጥበብ ለመስረቅና ለመውረስ የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። ለወሮታቸው ክፍያ መጽሐፈ ጥበብን መጠየቃቸውም ከዚህ ጭብጥ የተለየ ሌላ ግብ የለውም።" አሉ ባሕታዊው።

"እምን ይህማ በጣም ግልጽ ነው....." ብለው ሥራውብዙ መናገር ሲጀምሩ ባሕታዊው አቋረጧቸው።

"አሁን ፈረንጆቹ የመጡበት ልዩ ዘዴ አፍቅሮ ንዋይ ለተጠናወታቸው ዜጎቻችን በርካታ ዶላር እየከፈሉ ቅርሶቻችንን፣ በተለይም የብራና መጻሕፍታችንን እያስሰረቁ ማጋዝ ነው።" አሱና ላፍታ ታህል ዶክተሩን በጸጥታ ማስተዋል ጀመሩ።

"ያም ሆነ ይህ" ሲሉ ባሕታዊው ንግግራቸውን ቀጠሉ። "ባዕዳን የጥበብና መንፈሳዊ ድርሳኖቻችንን እጃቸው የደረሰበትን ያህል ቢዘርፉንም ከሞባይል እና ከሳተላይት ወይንም ከጠፈር ቴሌስኮፕ የዘለለ ጥበበ ላይ መድረስ አልቻሉም።"

"እሱስ ማለቴ ቴሌስኮፑ፣ ሳተላይቱ፣ ታላቅ ሥልጣኔ አይደለም?" ዶክተር ሥራው ራሳቸውን እደፋፍረው ጠየቁ።

"እንደ ግንዛቤህ ነው።" አሉ ባሕታዊው። "አምን ሞባይልና ሳተላይት በብርሃን ፍጥነት ግንኙነት ለማድረግ ያስችላሉ። ቴሌስኮም በጊዜ ዋሻ ውሰጥ ወደ ኋላ ለመጓዝ ያስችላል። ነገር ግን ብርሃን በሴኮንድ 330 ሽህ ኪሎ ሜትር ከሚጓዝበት ፍጥነት የእጥፍ እጥፍ መጓዝ የሚችል 'መንፈሳዊ ሞባይል እና ቴሌስኮፕ' መጠቀም ከቻልንስ? የትኛው ቴክኖሎጂ ወይንም ሥነ ጥበብ ሊበልጥ ነው?

ዶክተር ሥራው አፋቸውን ከፈት አድርገውና ወደ ፊት ዘመም ብለው ተመስጠው ማዳመጥ ቀጠሉ።

"ዮሐንስ ኬፕለርን ታውቀዋለህ?" አሉ ባሕታዊው ጆናስ የሚለውን የፈረንጅ ስም በኢትዮጵያዊ አፍ እየጠሩ። "የሥነ—ከዋክብትን ሥነ—ዑደት ወይንም ሥነ—ምሕዋር ሳይንስ 'ከማግኘቱ' ወይንም በእነርሱ ቋንቋ "Discover" ከማድረጉ በፊት

ከኢትዮጵያ በጀምስ ብሩስ ተሰርቆ የተወሰደሉትን 'መጽሐፈ ሔኖክ' ማለትም የሥነ—ከዋክብት ወይንም በዘመናዊው የሳይንስ ስያሜ አስትሮ ፊዚክስ በዝርዝር እና በጥልቀት የያዘ የዕውቀት መጽሐፋችንን ሲያጠና እንደነበረ ይታወቃል። እንግዲህ ፈረንጁ ኬፕለር ያበሻው ሔኖክ የፃፈን የጥበብ መጽሐፍ "መጽሐፈ ሔኖክን" አጥንቶ ሲያበቃ ነው "ዲስከቨሪውን" ለዓለም ያወጀው።

"ይህን ሁሉ አላውቅም ነበር" አሉ ዶክተሩ።

"የሚቀጥለው ሳምንት የአድዋ ድል በዓል የሚከበርበት ታላቅ ቀን ነው አይደል?" አሉ ባሕታዊው።

"እ . . . አዎን አባ!"

"ይህ መልካም አጋጣሚ ነው!" አሉና ባሕታዊው ጥቂት ቆዘሙ። "የቅርሳችን ይጠበቅ ማሕበር የተዘረፉ ቅርሶቻችንን ስለ ማሰመለስና ያሉትንም ደሕንነት ስለ ማስጠበቅ የበዓሉ ዋዜማ ዕለት ጋዜጣዊ መግለጫ ይሰጣል። ስለዚህ አንተና ራሄል የማሕበሩ አመራሮች ናችሁና ስብሰባውን ጠርታችሁ፣ ተወያይታችሁ፣ ዝርዝር መግለጫውን እንድታዘጋጁ ይሁን።"

"አዎን አባቴ ልክ ነው እናዘጋጃለን!"

"መልካም! ሻይ ይፈላልህ?"

"የለም አያስፈልግም። ደህና ይደሩ አባቴ!"

ምዕራፍ አስራ ስድስት

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ራሄል ብራና አስጎብኚ ድርጅት ፎቅ ሥር ሳምሶንን አወረደቸው።

"ስለ መቅደላዊት መልካም ዕድል!" ብላው ወደ ቤታ ስታቀና አርሱም "የሞቀ አልጋ ይጠብቅሽ!" አላትና ተሳስቀው ተለያዩ።

ሳምሶን ዘመናዊውን የብራና አስጎብኚ ድርጅት ስቴሽን ዋገን መኪና ከፍቶ ተደላድሎ ከተቀመጠ በኋላ ወደ መቅደላዊት ሁለት ጊዜ የስልክ ጥሪ አደረገ።

"እባክሽ ዛሬ ራት ልጋብዝሽ?"

"እግዜር ይስጥልኝ፣ በልቻለሁ።"

"ምናለበት እሺ ብትይ?"

"እንተስ ምናለበት እሺ ብትል።" ስልኩ ተዘጋ። ድጋሚ ደወለ።

"ምን ታደርግ? ካርድ የሚሞላው ድርጅቱ ነው።

"ነገ ወደ . . . መብረሬ ነው" አለ ድሬዳዋን ውጦ።

"መልካም በረራ።"

"ምናለበት የወጪ ብጋብዝሽ?"

"ስትመለስ" አለችው በተሰላቸ ድምጽ።

"እውነትሽን ነው?" አላት ደንግጦ።

"አዎን!"

"እወድሻለሁ!" ስልኩን ዘጋችው።

ሳምሶን መኪናውን አቁሞ በእግሩ እየሮጠና እየቦረቀ ወደ ቤቱ ቢሄድ ደስታውን ለመግለጽ ይበልጥ በተመቸው ነበረ።

**********//////////**********

ያፈት ዶክተር ሥራውብዙን በኮንትራት ታክሲ እስክ መኖሪያ ቤታቸው ከተከተላቸው በኋላ በቀጥታ ወደ አይቤክስ ሆቴል ከነፈ። ባለ ታክሲውን በሁለት መቶ ብር ሸኝቶ ሁለቱን ደረጃዎች ባንድ ርምጃ ወጣና የክፍሉን በር ከፍቶ ሲገባ ሰውነቱ ሽምቅቅ አለበት። በሩን ዘጋና ሰፊው አልጋ ላይ በጀርባው ተንጋሎ በሞባይል ስልኩ ደወለ።

"የት ነሽ?" አለ ቆጣ ብሎ።

"ምን አገባህ? ጠብቀኝ!" አለችና ዮዲት ስልኩን ዘጋችው።

**********////////**********

ራሄል የአፓርትመንቷን በር ከፍታ ስትገባ የሞባይል ስልኳ መጮህ ጀመረ። ከደስታዋና ከመቻኮሏ የተነሳ ስልኳን ከቦርሳዋ አወጥታ "ሄሎ ያሬድዬ!" ስትል እጅግ ደስ የሚል ቅላፄ ያለውና ረጂም የሴት ሳቅ ጆሮዋ ላይ እሸክካባት።

"ወይኔ ጉዴ . . . ! ማን ልበል?"

"አንቺ! ውነትም ይሄ ያሬድሽ የሳንፎርድ አዳራሽ ተገቢው ነው!" አለቻት እንደምንም ሳቋን እየታገለች።"

"ውይ በሞትኩት! ሶፊ! አፈር ያስበላሽ! እኔ እኮ ቁጥሩን ሳላይ..."

"ምንም አይደለም። እኛም አንድ ሰሞን የፍቅር ነገር ደንበር ገተር፣ ቀብገርገር ያደርገን ነበር። ለማንኛውም ፍቅር ይጥማል። ያፈቀረም ያገባል። ጋብቻ ከተመሠረተ በኋላ ግን ፍቅር ያቆምና ታሪክ ይጀምራል።"

"ጥሩ ፈላስፋ ሆነሻል ሶፊ። ምን አዲስ ነገር አለ?"

"የሚዜነት ጥያቄውን በክብር ተቀብያለሁ።"

"ቴንኪው! ሌላስ?"

"አዳራሹን አስፈቅጃለሁ።"

"ብራቮ ሶፊ!" ብላ ራሄል ስትጮህ ከደስታዋ ብዛት የተነሳ እውነትም አዳራሹን በቬሉ የምትዳክርበት ትመስል ነበር። በደስታ ላይ ደስታ እንዲሉም ልክ ስልኩን ዘግታ ስታስቀምጥ ያሬድ በሩን ከፍቶ ገባ።

**********////////**********

ያፌት አይቤክስ ሆቴል ደርሶ ለዮዲት ስልክ ሲደውልላት። እርሷ ካፌ ኢየሩሳሌም ከጌዲዮን ጋር ቢሮው ውስጥ በመነጋገር ላይ ነበረች። ውይይታቸውን ያቋረጠው የስልክ ጥሪ የያፌት መሆኑን ስታውቅ አበሳጫት። ለምን እንዳበሳጫት ግን አልገባትም። ሁኔታዋን ከገፅታዋ ያጤነው ጌዲዮን ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ጠረጴዛውን ዞረና ቀረባት። ዮዲት በስልክ የሚያናግራትን ሰው አመናጭቃ ስልኩን ስታስቀምጥ

ጌዲዮን ረገርም ፀጉሯን በእጁ እየዳሰሰ "አብረሽው ከምትሠሪው ሰው ጋር ስሜታዊ ግንኙነት ከፈጠርሽ ሥራው ይበላሻል!" አላት።

"ኡፍ! ልቀቀኝ!" ብላ እጁን ወዲያ ገፋችው። "ታዲያ አንተስ ለምን በስሜታዊነት ታካሺመኖለህ?"

"ምን ላድርግ? ልቋቋምሽ አልቻኩም።" አላት ወደ ወንበሩ እየተመለሰ።

ዮዲት ሲጋራዋን አቀጣጠለችና "ስማ ጌዲ!" አለችው። "እንደምታውቀው ይህ 'ቅርሳችን ይጠበቅ' የተባለው ቅርስ አስመላሽና ጠባቂ ተቋም ከተመሠረተ ምናልባት ከእኔ ዕድሜ በላይ ሊሆነው ይችላል። እኔ ድርጅቱን የተቀላቀልኩት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሳይኮሎጂ ተማሪ ሳለሁ ነው። በዐሥራ ዘጠኝ ሰማኒያዎቹ ውስጥ በቤተ—እሥራኤልነት ወደ እሥራኤል ከሄድኩ በኋላም በአባልነቴ ቀጥያለሁ። አሁን ደግሞ የ 'ዘመቻ መቅደላ' ዋና ተሳታፊ ሆኜ በዜና ወኪልነት ሽፋን መምጣቴን ታውቃለህ።"

"ኑዛዜ ነው? ወይንስ.....?" አላትና ከዮዲት ፓኮ ሲጋራ አውጥቶ ለኮሰ። ያልሰማችው መስላ ቀጠለች።

"እኛ የቅርሳችን ይጠበቅ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት አባላት ኦፐሬሽን መቅደላን የወጠነው ቅርሶቻችንን ለማስመለስ ብቻ ነው። ባይሳካልን እንኳን የሞከርነው ወጣ ያለ ተግባር ቅርስ የማስመለስ ጥረትን እና ትግልን በተመለከተ አዲስ ዐይነት ተጽዕኖ እና ትኩረትን ይፈጥራል ብለን እናምናለን።"

"ከዚያስ?" አላት ጌዲዮን።

"ያንተ የቤተ—እሥራኤሎች ማሕበር ደግሞ . . ."

"እንቺም ቤተ—እሥራኤል ነሽ እኮ!"

"ግን የማሕበራችሁ አባል አይደለሁም። ዋናው የማሕበራችሁ ዓላማ ኢትዮጵያ ውስጥ የቀሩትን ቤተ እሥራኤሎች መርዳት ነው። አሁን አሁን እንደማየው ግን ታሪካዊ ቅርሶችን እያሰላችሁና እያሰረቃችሁ ወደ እሥራኤል ታሸልካለላችሁ። ለምን ግን ጌዲዮን? ለምን በዚህ ተግባር ላይ ተሠማራችሁ? ይህን ተግባራችሁን የኢትዮጵያ መንግሥት ቢደርስበት እንደ አንድ ተቋም አዲስ አበባ ውስጥ የሚኖራችሁን ሕልውና አያሳጣችሁም?"

"ስሚ ዮዲት፣ በመጀመሪያ ደረጃ በቅርስ ሌብነት ላይ ስለ መሠማራታችን እርግጠኛ አትሁኚ። ይህ ፈጽሞ ሐሰት ነው። እኛ የኢትዮጵያን ቅርስ በመዝረፍ ተግባር ላይ ብንሠማራ ኖሮ ኦፐሬሽን መቅደላን ለመርዳትና የኢትዮጵያን ቅርሶች በማስመለሱ እደገኛ ተልዕኮ ላይ ለምን እንሳተፋለን?" አለና በዝምታ ጠበቃት። "መልስ ስጪኛ!"

"መልሱን ካንተ መስማት እፈልጋለሁ።"

"በጣም ጥሩ፣ እኛ ቤተ—እሥራኤሎች ባንድ ታሪካዊ አጋጣሚ እሥራኤላዊነታችንን ተቀዳጅተናል። አንቺንም ጨምሮ ማለቴ ነው። ነገር ግን እውነቱን እንነጋገር ከተባለ በጥልቁ ልቦናችን ውስጥ የተቀረፀውና ከሁለት ሺህ ዓመታት በላይ ያስቆጠረው ኢትዮጵያዊነት በአንዲት ጀምበር ተፋቀ ማለት ነው?"

"አይደለም!"

"በቃ፣ ስላልተፋቀ ብቻ ነው ኦፐሬሽን መቅደላ እንዲሳካ የምንረዳችሁ።"

"እናስ 'መጽሐፈ ጥበብ_ሕዋዊ ወ ምድራዊ' እጃችሁ ቢገባ ወደ ቱል አቪቭ ታሻግሩታላችሁ?"

"አንቺ በኔ ቦታ ብትሆኚ ምን ታደርጊያለሽ?"

"አቨር ማይ ዴድ በዲ!" አለችው።

"በአስከሬንሽ ላይ!" አለና ጧ! ብሎ ሳቀ። "እንግዲያው ገና አልበሰልሽም ማለት ነው። እንኪንስ አንድ ግለሰብ ይቅርና ጠንካራ መንግሥትም ቢሆን ቢያንስ በሕይወት ዘመኑ እንዴ በጽኑ የሚያምንበት መርሁን የሚያስጥሰው አስገዳጅ ሁኔታ ይከሰታል። ያኔ እንዳለየ ሆኖ እምነቱን ይሸርፍና ለአስገዳጅ ሁኔታ ያጎብድዳል። የኛ የቤተ—እስራኤሎች ማሕበርም ከዚህ ዕውነታ ሊያመልጥ አይችልም።"

"ስለዚህ መጽሐፈ ጥበብን የምናድንበት ዘዴና አማራጭ የለም ነው የምትለኝ?"

"እስራኤላዊነትሽን የዘነጋሽው መሰለኝ። ለማንኛውም መልሱ 'እምን!' ነው።"

ዮዲት እግሮቿን የጌዲዮን ጠረጴዛ ላይ ዘረጋችና ዘና ብላ ሲጋራዋን ማገች። "እሺ ወደ ሚከተለኝ ሰላይ ስንመጣ....."

ልክ ይህን ስትናገር በሩ ሁለቴ ተንኳኩቶ ተከፈተ። ሁለቱም ወደ በሩ ዞሩ። ኤፍሬም ወደ ውስጥ ገባና በሩን ዘግቶ በፀጥታ ቆመ።

"ታዲያስ ምን ፈለክ?" አለው ጌዲዮን።

"እ . . . ኤፍሬም ወደ ዮዲት አየት አደረገ።"

"ችግር የለም፣ ቀጥል" አለ ጌዲዮን"

"ዮዲት ከብራና አስጎብኚ ድርጅት ስትወጣ..." አለና ኤፍሬም ንግግሩን ሲጀምር እግሮቿን ከጠረጴዛው አወረደችና ኤፍሬምን አፍጥጣ ማየት ጀመረች።

".....በሁለት የኪራይ መኪኖች ከፊትና ከኋላ የተከራየችውን ታክሲ እየተከታተልን ሳለ ብዙም ሳንንገዝ የሚከተላትን መኪና ለየነው።"

"ማነው. . . ምንድ ነው?" ጌዲዮን ጠየቀ።

"የታርጋ ቁጥሩ ይሄው። የኪራይ ላንድ ክሩዘር ነው። መኪናውን የተከራየውና የሚያሽከረክረው ቤን ነው።"

"ይሄ ደደብ!" ዮዲት ተፈናጥራ ተነሳች።

"ቀስ . . . ቀስ! ተይው፣ አትናደጂ።" አለና ጌዲዮን ወደ ኤፍሬም ቀና ብሎ "እመሰግናለሁ መሄድ ትችላለህ።" አለው።

ኤፍሬም ወጥቶ በሩን ዘጋው።

"ለምን ይከተለኛል?" አለች ዮዲት ወዲህ ወዲያ እየተንጎራደደችና ሲጋራዋን እያቦነነች።

"ይሄ ካንቺ የሚጠበቅ ጥያቄ አይደለም። የሠለጠንሽ የሞሳድ ኤጀንት ነሽ። እንዴት ይህን ትጠይቂያለሽ?" ብሎ በፈገግታ ሲያያት ቆየና "በቃ! ጠርጥረውሻል ማለት ነው!" አላት።

"ለምን?"

"ያን መመለስ የሚችሉት እነርሱ . . . ቴል አቪቮች ናቸው።"

"ስለዚህ ኦፐሬሽን መቅደላም አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል ማለት ነው?"

ጌዲዮን ለጥቂት ሴኮንዶች ተክዞ ቆየና "አይመስለኝም" አላት።

"ለምን?"

"አየሽ ዮዲት። ዘመቻ መቅደላ ተሳካም አልተሳካ እስራኤል እና ሞሳድ በሽብርተኝነት ላይ ለሚያካሂዱት ፕሮፖጋንዳ ይረዳቸዋል። በተለይ ደግሞ ቢሳካ ለኤግዚቢሽን ከሚቀርቡት የብራና መጻህፍት ውስጥ የሚፈልጉትን 'ድርሻዬ ነው!' ይላሉ።

"ታዲያ ለምን ይከተሉኛል?"

"ከመስመር እንዳትወጪ! ኢትዮጵያዊነትሽ ሚዛን ደፍቶ ቅርሶቹን በሙሉ ይዘሽ እንዳትሰወሪ። "ሁሌም እየተከተልንሽ ነው።" የሚል ማስጠንቀቂያ ሊሰጡሽ ነው። እየሽ ሶዲት? ያንቺ ፊልድ ኦፊሰር ቤን ምንነቱና ማንነቱ ፍጹም ሳይታወቅ ሊሰልልሽ ይችላል። ሙያዊ ብቃቱም አለው። ነገር ግን እንደነ ኤፍሬም ዐይነት አማተሮች ለይተው እንዲያዩት አድርጎ 'በምስጢር' እንደተከታተለሽ ያስመስላል። ምክንያቱም እነ ኤፍሬም ለእኔ፣ እኔም ላንቺ ሪፖርት እንደምናደርግ ቤን አሳምሮ ያውቀዋል!"

"ብራቮ! ጌዲ!" አለችና ሲጋራዋን መተርኮሻው ላይ አጠፋች። "ይሄው ነው ምክንያቱ። አይደለም?"

"ይመስለኛል" አላት።

"ዘመቻ መቅደላ አደጋ ላይ አይደለም ማለት ነዋ። አይደል?"

"ይመስለኛል።"

"ዋናው ነገር የኦፐሬሽን መቅደላ ደህንነት ነው። ግፋ ቢል ምን ነበር እሱ? እ . . . መጽሐፉ ጥበብን አውጥቼ አቀብላችኋለሁ።"

"ቅድምም ያልኩሽ ይሄንኑ ነበር። አየሽ? ለኢትዮጵያዊነት ያለሽን ቀናኢነት የሚያስለውጥ አስገዳጅ ሁኔታ!"

"እናያለን!" አለችውና ተነሳች።

ምዕራፍ አስራ ሰባት

ከጧቱ 3:00 ሰዓት ላይ የሒልተን ሆቴል ቆይታ ሒሳቡን ዘግቶና ሻንጣውን በኮንትራት ታክሲ ጭኖ ወጣ። የታክሲውን ክላክስ የሰማው የባሕታዊው ታማኝ አገልጋይ በሩን ከፍቶ ወጣና የዶክተር አንዱዓለምን ሻንጣ ሲያወርድለት አንዱዓለም ለታክሲ እሽከርካሪው አንድ መቶ ብር ከፍሎ፣ የእጅ ቦርሳውን (ሳምሶናይት) እና ኮምፒውተሩን ይዞ ወደ ውስጥ ገቡ።

ልክ በረንዳውን ሲረግጡ የሳሉኑ በር ተከፍቶ "አንዱዓለም ደህና አደርክ?!" አለ ባሕታዊው። አገልጋዩ ሻንጣውን ከበሩ አጠገብ አስቀምጦ ሲወጣ ባሕታዊው በሩን ዘጉና ሶፋው ላይ ከአንዱዓለም ትይዩ ተቀመጡ። "ዶክተር ትንሽ ቁርስ ብጤ ተዘጋጅቷል።"

አንዱዓለም 'ማን ይሆን ያዘጋጀለት? ሲል አሰበና" እሺ አባቴ። ትንሽ ልቅመስ" አለ።

ሻንጣውን አስቀምጦ በፊት በር የወጣው አሽከር_ቦዲ ጋርድ በትሪ የተቀመጡ ዝርግና ጎድጓዳ ሳህኖችን ይዞ በጓዳ በር ገባ። ሳይጠራና ሳይታዘዝ ከባሕታዊው ጋር በመንፈስ የተነጋገረ ይመስል ቁርስ ይዞ በመግባቱ አንዱዓለም ተገረመ።

"በስመ አብ ወልድ ወ መንፈስ ቅዱስ . . ." ባሕታዊው ፀሎተ ቡራኬ ጀመሩ። አንዱዓለምም በፀጥታና በክበሬታ አንገቱን ሰበር አደረገ። ለነገሩ ለሽማግሌው ባሕታዊ ክበሬታ እንጂ እርሱ እንደ ሆነ ፀሎትና ቡራኬ የሚባሉ ነገሮችን መቼ እንደረሳቸው እንኳ ትዝ አይለውም።

"ማዕደ አብርሀምን የባረኩ ሥላሴ ማዕዳችንን ይባርኩልን!" ብለው ባሕታዊው ምግቡ ላይ ሲያማትቡ አንዱዓለም "አሜን" አለ።

"በል ዶክተር ተመገብ!" ባሕታዊው ማንኪያውን አንስተው በቅቤ የራሰውን ጨጨብሳ ወደ አፋቸው ሳኩ።

"በጣም የሚጣፍጥ ጨጨብሳ ነው" አለ አንዱዓለም።

"አገልጋዬ ነው ያዘጋጀው። በያም ወቅት የያም ምግብ ሲያዘጋጅ ባየህው! የሴት ወጥ ቤት የለኝም፣ ኖሮኝም አያውቅም።" አሉ ባሕታዊው።

"ይደንቃል። ግሩም ባለሙያ ነው። ሁለ ገብ!" አለ አንዱዓለም እያፈዘ።

"አምን በነገራችን ላይ ዶክተር! ሁላችንም ብንሆን ሁለ ገብ ሙያ ቢኖረን ይጠቅማል እንጂ አይጎዳም።"

"እምን አባ! እኛ ያበሻ ወንዶች ሀገራችን ውስጥ ስንኖር እኮ ነው ኩሽና አንገባም እያልን የምንተናጣው። ፈረንጅ ሀገርማ የቤት ሠራተኛ መቅጠር አይታሰብም።"

"መች አጣሁት። እኔስ ለዘመናት አውሮፓ ስመላለስ አይደል የኖርኩት? ዋናው ላወጋህ የምሻው ስለ ምግብ አዘገጃጀት ነው። እኛ ኢትዮጵያዊያን የራሳችንን ብቻ የሆኑ የምግብ ሰብሎችና የምግብ አዘገጃጀት ዘይቤዎች አሉን። ለሰውነት ብልቶቻችን እና ለጤንነታችን የሚውሉ ዕድሜንም የሚያራዝሙ የምግብ ዐይነቶች አሉ።" አሁን አንዱዓለም መላ አካላቱ ጆሮ ሆኗል።

"ለምሳሌ እኔን ተመልከት። ዕድሜዬ ስንት ይመስልሃል?" አንዱዓለም ለመገመት ሞከረ። ባህታዊውን ሲያውቃቸው ቀላል የሚባል ዘመን አልተቆጠረም። ሌላው ቀርቶ ሀ፡ሁ መቁጠር ሲጀምር ባሕታዊ ዝናቸው የገነነ ምሁር ባሕታዊ ነበሩ። "እኔ እንኳ አባቴ. . ምናልባት ከሃምሳ አምስት እስከ ስድሣ . . . ግን ቁመናዎን ላየና ለማያውቁዎት ቢበዛ ከሠላሳ አምስት እስከ አርባ ቢገምቱት ነው።"

"ልክ ብልሃል። ነገር ግን ባይገርምህ ሰባ ዓመቴን ከደፈንኩ አንድ ሳምንት አልፎኛል።

አንዱዓለም ክው ብሎ "ምን?" ሲል ጮኸ።

"እምን ሰባ ዓመት! ምስጢሩስ ምን መሰለህ? የአመጋገብ ሥርዓትና ምርጫ። ለማንኛውም እኔ ዘንድ የሚገኝ አንድ ጥንታዊ የምግብ ዝግጅት ወይንም ሞያ ልበለው? መጽሐፍ አለ። ይህን መጽሐፍ ከዘመቻ መቅደላ ከንውን በኋላ አሰጥሃለሁ። ወደ አማርኛ መልሰህ በትጉ ታዘጋጀውና ለወገኖቻችን አላትመን እናደርሰዋለን።"

"እጅግ በጣም ደስ ይለኛል። አባቴ። ሁላችንስ ብንሆን ረዥም ዕድሜ የቀን ተቀን ምኞታችን አይደል?"

"መልካም። አሁን ስለ የትርጉም ሥራህን እናውራ። የተቻለኝን ያህል ግዕዙን ተትርጉምህ ጋር እያስተያየሁ አነበበኩት። *መጽሐፍ ጥበብን* ስትተረጉም ዋና ወይንም አብይ የሆኑትን ጥበባት ስለምን ገደፍካቸው?" አሉና ባሕታዊው በነዚያ ሕሊናን ሰርስረው በሚገቡ ትናንሽ ዐይኖቻቸው ትኩር ብለው ተመለከቱት።

አንዱዓለምም አተኩሮ ሲያያቸው ቆየና "ለ ዲስ ኢንፎርሜሽን!" አላቸው።

ባሕታዊው በገጽታቸው ላይ በቅጡ የማይታይ ፈገግታ ሸ. . . ው! እያለ "እኔም የገመትኩት ይህንኑ ነበር።" አሉት።

"አምን አባቴ። ፈረንጆቹ የጥበበ መጽሐፋችንን ዘርፈው ምስጢሩን መፍታት ሲያቅታቸው አዙረው ለኛ ለባለቤቶቹ አቅርበው "ፍቱልን!" አሉ። እነርሱ ለምን ቀታሌ ብዙሃን (Mass destruction) የጦር መሣሪያዎቻቸውን ምስጢር ወደ አማርኛ ተርጉመው አይሰጡንም?"

"መልካም ብለሃል!" አሉ ባሕታዊው። "ነጮቹን ወይንም እንግሊዞቹን በተሳሳተ መረጃ (ትርጉም) አለፍናቸው እንበል። ይህንኑ መጽሐፍ እጅ ለማግባት በማነፍነፍ ላይ ያሉትን አሰራኤሎችስ እንደምን እንወጣቸው?"

"አምን እነርሱም ይህን የጥበብ መጽሐፋችንን ይፈልጉታል። ሕይወታችንን አደጋ ላይ በሚጥል ኦፐሬሽን ተእንግሊዞቹ ቀምተን ለሌላ ባዕድ የምንሰጥበት አንዳችም ምክንያት አይታየኝም። በዘመቻ መቅደላ ቢረዱንም ማለቴ ነው።"

"ታዲያ መፍትሄው ምንድን ነው?" አሉ ባሕታዊው።

"በጣም አስቢበታለሁ። ዘዴው ቀላል ነው።"

"ልስማዋ!" አሉ ባሕታዊው።

"በአጭሩ ለማስረዳት ኤግዚቢሽኑ ላይ ልዕልቲቱን፣ አምባሳደሩን እና ቅርሶቻችንን ካገትን በኋላ መጽሐፈ ጥበበን ለጊዜው እናስረክባቸዋለን። ምክንያቱም ለዘመቻ መቅደላ ስኬት ግዴታ የቤተ—አሰራኤሎቹ ድጋፍ ያስፈልገናል። ማለትም . . . የሠለጠነ ወታደራዊ የሰው ኃይል ድጋፋቸው ያሻናል።"

ባሕታዊው እንደ ድንጋይ ሙት በመለለ ዝምታ ያዳምጣሉ። ዶክተር አንዱ ዓለም ንግግሩን ቀጠለ።

"በቤተ አሰራኤሎች ድጋፍ ታግዘን ቅርሶቻችንን እጅ አግብተን እና የመጨረሻ መጠለያ ሥፍራቸው ካደረሰን በኋላ መጽሐፈ ጥበብን መልሰን እ... እ... እ... በ<u>ፊሊ ትራንስፖርቴሽን</u> እናመጣዋለን!"

ባሕታዊው ወደ ራት ዘመም አሉና . . . "በምን?" ሲሉ ጠየቁ።

"በደመና ጉዞ!"

"አንዱዓለም አስከሚያውቃቸው ድረስ ባሕታዊው ለመጀመሪያ ጊዜ ከልባቸው ተንከትክተው ሳቁና "ትርጉመ ቃላቱን ብቻ ሳይሆን ትርጉመ ጥበቡንም ተገንዝበሀዋል!" አሉት።

ምዕራፍ አስራ ስምንት

ዶክተር ሥራውብዙ የሁለቱን ፍቅ ደረጃዎች ሲወጡ ከወትሮ የተለየ አካላዊ ቅልጥፍናቸው የጨመረ ከመምሰሉም በላይ ፊታቸው በፈገግታ ተሞልቶ ነበር። የቢሮውን በር ክፍተው ሲገቡ ፀሐፊያቸው መቅደላዊት የሥራ ገበታዋ ላይ አቀርቅራ ነበር። ዛሬ ግን እንደሁሌው ቀና ብላ አላየቻቸውም። አረጋዊው ዶክተር በቀጥታ ወደ ጠረጴዛዋ ቀርበው፣ አገጯን ይዘው ቀና አደረጓትና ""ምነው የኔ ቆንጆ ዛሬ ሀላምታ የለም?" አሏት።

አንገቷን ዞር በማድረግ እጃቸውን ከፊቷ ላይ አስወገደችና ""ይሄ ቢሮ ውስጥ መኪሽም ይብቃ ብያለሁ!" አለቻቸው።

""ምን ተፈጠረ? ምን ሆንሽብኝ?""

"ምንም። አንተ እኮ ባለ ትዳርና ታላላቆቹ የሚሆኑ ልጆች አሉህ። ይህን የምስጢር ግንኙነት የጀመርነው ሥራዬን 'ሴክዉር' ለማድረግ ስል እንደ ነበር ታውቃለህ። አሁን ግን አንድ ወቅት ላይ ሊበቃን አይገባም ትላለህ?"

ዶክተሩ ግራ ተጋብተውና ደንግጠው ለጥቂት ሴኮንዶች ሲያዩዋት ከቆዩ በኋላ ድንጋጤያቸው ወዲያው ወደ ቁጣና የመበለጥ ስሜት ተለወጠ። "እምን እኔም እውቂዋለሁ! ጠርጥሪያለሁ! ምክንያትሽ ይገባኛል!" አሏት በንዴት እየተንቀጠቀጡ።

"የምን ምክንያት? ምኑን ነው ያወከው?" አለች መቅደላዊት ወንበሯን ደገፍ እያለች። በተራዋ ስጋት ወረራት።

"አውቂዋለሁ! ሳምሶን ከሚሉት ጎረምሳ ጋር መኪሽም ጀምረሻል። ከእርሱ ጋር የጀመርሽው ኦፊር' አለሽ። ቆይ እኔ ሥራውብዙ አይደለሁም! ባልሠራለት!"

መቅደላዊት ሳታስበው በሳት ጧ! ብላ ፈነዳች። ይኸኔ ዶክተር ሥራው ንዴታቸው ጠፋና ግራ ተጋብተው ተመለከቷት።

"እየህ?" አለች መቅደላዊት በጣም ተረጋግታ ዘና ብላ. . ." አየህ ዶክተር። አፊር ያለን እኔና አንተ እንጂ እኔና ሳምሶን አይደለንም። አንተ በትዳርህ ላይ የምታማግጠኝ ለወሲባዊ ጥማትህ እርካት የወጣት ሴት ገላ አስፈልጎህ ነው። እኔም አብራህ የማገጥኩት ... ታውቅ የለም? በጠፋ ሥራ የሥራዬን ዋስትና ለማረጋገጥ ስል ነው። አሁን ግን እግዚአብሔር ይመስገን ትምህርቴን አሻሽዬ ዲግሪዬን ይዣለሁ። አሁን ግን በቃ! ያንተ

ደሞዝ ባፍንጫዬ ይውጣ።" ብላ መትደላዊት ጠረጴዛዋን በጥፊ ጢ! አድርጋ መታችና ቦርሳዋን ብድግ አድርጋ ተነሳች።

በድንጉጥኛ ውርጅብኝ እና ውሳኔዋ የተደናገጡት አረጋዊ ዶክተር "ቆዩ! እንዴ ቆዩ! እባክሽ መትደላዊት አንዲት ትዕበት ብቻ አዳምጪኝ" እያሉ ተማፀኗት። መትደላዊትም በመሄድና ባለመሄድ መሃል እየዋለለች ቆመች።

"እባክሽ መቅዲ እንዴ ቁጭ በይ!"

"አልልም ይበቃኛል። የምትለውን በልና ልሂድበት!"

"እሺ! እሺ!" አሉ ዶክተር ሥራው እየርበተበቱ። "እየሽ መትደላዊት። እኔ ከጅምሩ የፊለኩሽ ለፍትወት ፍላጎቱ ወይንም ሌሰኛ ሆኜ አልነበረም። እሱማ እንዳንቺ ያሉ እጅግ ብዙ ወጣት ቆነጃጂትን በገንዘቤ መግዛት እችላለሁ። ግን እኔ ... መቅዲ .. እኔ አፈቅርሻለሁ።"

መትደላዊት እንደገና ጢ! ብላ ሳቀች። ወንበሯ ላይ ስትቀመጥ እንኳ ሳቋን አላቋረጠችም።

"እትሳቂ! እኔ እኮ ክልቤ ነው የማወራሽ። ደግሞ ክልቤ መሆኔን ላሳምንሽ? ጠብቂኝ! አሉና ወደ ውስጠኛ ቢሮአቸው ገሰገሱ። መትደላዊት 'ይህ ያበደ ሽማግሌ ምኑን ነው የሚያሳምነኝ?' እያለች ስታስብ ዶክተሩ ወረቀቶች ይዘው ተመለሱ።

"ተመልከቺ!" ጠረጴዛዋ ላይ ሰነዶቹን ጣሉላት። ተመልከቺ። ከባለቤቴ ጋር በሕጋዊ መንገድ ፍቺ የፈፀምኩበትና የንብረት ክፍፍል የጨረስኩበት የፍርድ ቤት ሰነድ ነው።"

"ታዲያ ምን ይጠበስ? ያንተ ዲቮርስ ለኔ ምኔ ነው?" አለች እጅግ ተገርማ።

"የማፈቅረው አንቺን ነው። እኩያሽ ባልሆንም አንቺም ታፈቅሪኛለሽ ብዬ እምናለሁ። ሚስቱን ፈትቼ ነፃ ሆኛለሁ። ተዝቆ የማያልቅ ሀብት አፍርቻለሁ። አሁን ደግሞ . . . ታያለሽ መትደላዊት። አሁን ደግሞ በቅርቡ ዐይንና ጆሮዎችሽ በፍፁም የማያምኑትን የንዋይ መአት ... ያውም በውጭ ሀገር ምንዛሪ እጄ ይገባል። ይህ ድርጅት ባንቺ ስም ይሠራል። በቅርቡ ለሃኒ ሙን (የጫጉላ ሽርሽር) ዓለምን እያዞርኩ አሳይሻለሁ። በውጭ ሀገር ባንክ በስምሽ አያሌ ገንዘብ ያውም በዶላር ገቢ ይሆንልሻል። ሰሞኑን ከባልደረቦቼ ጋር የጀመርነው አንድ ተልዕኮ ሲጠናቀቅ አንቺን የዓለም ባለቤት

የሚየደርግሽ ንዋይ አስጨብጥሻለሁ! ላንቺ ፍቅር ስል የገባሁበትን ነገር አታውቂም። እባክሽን መቅደላዊት አታበላሺው። ዕድሉን ሰጪኝና ለጥቂት ሳምንታት ብቻ ታገሺኝ!" አሏት እስሯ ተንበርክኩው እየተለማመጣት።

የመቅደላዊት አዕምሮ በብርሃን ፍጥነት እየተሽከረከረ ነገሮችን አያብላላ ነበረ። በመጨረሻም ቀና አለችና ፊቷ የብልጠት እንዲሁም የአሸሙር ስላቅ እየታየበት " እሺ ይሁን! ግን ሳምሶን ላይ የሰነዘርከውን የዛቻ ቃላት ትሰባለህ?"

"እምን መቅዲ! ምንም ዐይነት ጥቃት አላደርስበትም። ቃል እገባልሻለሁ።" አሏት በአዕምሮአቸው ደግሞ 'ብፈልግ እንኳን ሳምሶንን ዝንቡንም አ..ሽ ማለት አልችልም። እርሱ መመከትና መልሶ ማጥቃት የሚችል ፕሮፌሽናል የአየር ወለድ መኮንን ነው' እያሉ ያስቡ ነበር።

መቅደላዊት ፈገግ አለችና "እሺ! ይሁን" አለች።" አላውንቱ ዶክተር እጅግ ተደስተውና ዐይኖቻቸው እንባ አቅርረው "ቱንክ ዩ!" አያሉ ጉልበቷን ሲስሙ በሩ ተንኳኳ። ዶክተር ሥራውብዙ ከተንበረከኩበት እንደምንም ተውተርትረው ሲነሱ በሩ ተከፈተና የካፌው አስተናጋጅ የተለመደውን ቡና በፔርሙስ ይዞ ገባ።

"እንደምን አደራችሁ" አለና ፔርሙሱን የመቅደላዊት ጠረጴዛ ላይ አስቀምጦ ተመልሶ ወጣ። መቅደላዊት አሁንም በፍጥነት እያሰበች ነው። 'ይሄ ሽማግሌ ሰርቶ እስኪያካፍለኝ እጆቼን አጣጥፌ መጠበቅ የለብኝም።' "ዶክተር" አለቻቸው ዐይኖቿን እያስለመለመች። "አቤት የኔ ቆንጆ" አሉ ልባቸው እየቀለጠ። "እኔ...ታውቃለህ....የቅርስ ማስመለስ ጥረታችሁ እንዲሳካ አተባበራለሁ።" "እምን የኔ ፍቅር አውቃለሁ።"

"ግን አንድ ውለታ ብቻ ጠይቅየሃለሁ። 'መጽሐፈ ሕዋው' የተባለውን ጥንታዊ የስነፈለክ ብራና አስጥሻለሁ ብለህኝ አልነበረም? ታዲያ ለምን አታመጣልኝም?" አለችና ዐይኖቿን ይበልጥ እያስለመለመች ጉንጯቸውን በለስላሳና ውብ ጣቶቿ መደባበስ ጀመረች።

ሽማግሌው ዶክተር እንደ ቅቤ ቀለጡ። "የኔ ፍቅር፣ በጣም ብርቅዬ መጽሐፍ ቢሆንም ላንቺ ስል አውደ ርእዩ ሲያበቃ አውጥቼ አስረክብሻለሁ። ምን እንደሚያደርግልሽ ባይገባኝም!"

"እሱን ለኔ ተውልኝ" አለች እየደባበሰቻቸው። 'የሩሲያዎቹ ዶላር በሰለ!' አለች በሐሳቧ።

ዶክተር ሥራው ብድግ ብለው ወደ ቢሮአቸው እየተራመዱ "ስሚ መቅደላዊት" አላት። "ቀኑን ለተነገ ወዲያ አድርገሽ አንድ ደርሶ መልስ የጎንደር የአውሮፕላን ቲኬት እንዲሁም ሌላ ደርሶ መልስ ወደ ቴልአቪቭ ቲኬት አስመዝግቢልኝ።"

"የሁለቱም ጉዞ ባንድ ቀን?" አለች ግራ ተጋብታ።

"አዎን! እኔና አንቺ ዓለምን የሚያስጨብጠን ጉዞ አደርጋለሁ። ታዲያ ..." አሉና ምስጢረኝነቱን ለማሳየት ክንፈሮቻቸውን ገጥመው ልክ የሱሪያቸው ዚፕ እንደሚዘጉ ዐይነት በጣታቸው ምልክት አሳይዋትና ወደ ቢሮአቸው ገብተው በሩን ዘጉ።

**********//////////**********

የአሜሪካው የስለላ ተቋም ሲ.አይ.ኤ. የእንግሊዙ ኤም.አይ.ሲክስ እና የሩሲያው ኬ.ጂ.ቢ ለመረጃ አሰባሰብና ለስለላ ሥራ አስፈላጊና ወሳኝ የሆኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በምርምርና ጥናት እያመረቱ መጠቀም ከጀመሩ የሰነበተ ቢሆንም ይህ ብቻውን ዓለምን ለመቆጣጠር በቂ ሆኖ አላገኙትም።

ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ

ሳምሶን ከቀኑ ስድስት ሰዓት ላይ ድሬዳዋ አየር ማረፊያ ደርሶ ከአውሮፕላኑ ሲወርድ የተቀበለው የከረረ ፀሓይ ነበረ። ካነስተኛ ሻንጣው ጋር በታክሲ ተሳፍሮ ወደ ራስ ሆቴል ተጓዘ።

"ጤና ይስጥልኝ እህቴ!" አላት ተረኛዋን እንግዳ ተቀባይ።

"ጤና ይስጥልኝ" አለች ከፈገግታ ጋር። "ምን ልርዳዎት?"

"የመኝታ ክፍል መያዝ እፈልጋለሁ። ለአንድ ሳምንት ያህል።"

"የሚፈልጉት ያህል ቢቆዩ ደስተኞች ነን።" አለችና የመያዣቂያ ካርዱን ተቀብላ መመዝገብ ጀመረች። አስፈላጊው ፎረማሊቲ በጥቂት ደቂቃዎች ከተጠናቀቀ በኋላ ቁጥር 25 የተለጠፈበትን ቁልፍ አስረክባው "የሚፈልጉትን ነገር ካለ ሩም ሰርቪስ ማዘዝ ይችላሉ። መልካም ቆይታ" አለችው።

ሳምሶን ክፍሉ ገብቶ ሻንጣውን መሬት ላይ ጣለና አልጋው ላይ እረፊ ብሎ የሞባይል ስልኩን ቁጥሮች ነካካ።

"ሃሉ ሮበሌ!"

"ወርያ ሳምሶን! መጣህ?"

"አዎን አሁን ራስ ሆቴል ነኝ።"

"አሁን እኔ ይመጣል ጠብቀው።"

**********////////**********

ሳምሶን ገላውን በቀዝቃዛ ውሃ ከተለቃለቀ በኋላ ስስ የጥጥ ካናቴራ እና ቀለሙ የለቀቀ ጂንስ ሱሪ ለብሶ፣ የቆዳ ነጠላ ጫማ ተጫምቶ፣ ክፍሉን ቆለፈና ወደ ሎቢው ወረደ። የእንግዳ ማረፊያው ክፍል ውስጥ ጥቂት ሰዎች ይታያሉ። ሮበሌ ሲመጣ በቀላሉ ሊያየው የሚችልበትን ሥፍራ መርጦ ቀዝቃዛ ባቢሌውን እየተጎነጨ፣ ሲጋራውን እያጤሰና በተልቅ ስክሪን የሚተላለፍ የውጭ ዜና እያየ መጠበቅ ጀመረ።

ዜናው ሁሉ የጥፋት፣ የሽብርና የእልቂት ነው። 'እናንተ ፈረንጆች የምትፈልጉትን ያሸባሪነት ዜና በቅርቡ እኔም ልሠራላችሁ ነው!'

ይህን ሲያሰላልስ ስሙ ሲጠራ የሰማ መሰለውና ወደ 'ሬሴፕሽን' አቅጣጫ ተመለከተ። 'እሱ ነው?' አዎን አንድ ቀጠን፣ ረዘም ያለና ዕድሜው አርባ አምስት ዓመት

አካባቢ የሚገመት ሰው የራሴፕሽን ዴስክ አጠንብ ቆሞ....."አሁን ገባ! ሳምሶን የተባለ አንገዳ ይፈልጋል።" ሲል ሰማው።

ሮበሌ!" አለ ምሶን ከወንበሩ ብድግ ብሎ ወደ ሬሴፕሽን እያቀና።

"ወሪያ ሳምሶን!"

ሁለቱ ጓደኛሞች ተቃቅፈው ተሳላመ። የድሬዳዋ ተወላጆች ተለያይተው ሲገናኙ ሰላምታው፣ መጫጫኑ፣ መተራረቡ፣ መጠያየቁ፣ ሁሉ የተለመደ ባሕላቸው ነው። ሳምሶንና ሮበሌ ሎቢው ውስጥ ቀዝቃዛ ባቢሌ እየተጎነጩና ሲጋራቸውን እያጨሱ ለግማሽ ሰዓት ያህል በዝቅተኛ ድምጽ ሲያወሩ ቆዩና ስምምነት ላይ ደረሱ። ሳምሶን አስተናጋጅዋን ጠርቶ ሒሳቡን ከፈለና በሮበሌ መሪነት አብዛኛው የድሬዳዋ ከተማ ነዋሪ ቢያንስ በቀን አንዴ ወደ ሚጎበኘው ጫት ተራ በላጃጅ ተጓዙ።

ጫት ተራ የደረሱት በሰዓቱ ነው። ሰው፣ ፍየሉ፣ እብዱ ሁሉ ይተረማመሳል፣ ይነሰላል፣ ይጫጫኻል። ጠብደል ጠብደል ፍየሎች በገቢያተኛው መሃል እየተጋፉ የወደቀ ጫት ይቃርማሉ፣ የተሳነለት በየጥላው አረፍ ብሎ ያመነዥጋል።

ሳምሶን እንደ ድሬዳዋ ከተማ ተወላጅነቱ ብዙም የጫት ፍቅርና ልምድ ባይኖረውም አልፎ አልፎ ይቅማል። ሮበሌ ደግሞ ያለ ጫት ሌላ አስደሳች መዝናኛ እንደማያውቅ ሁኔታው ሁሉ ያመሰክራል። በሮበሌ ምርጫ ሁለት አቃራ ጫት ተገዛ። ዋጋውን ሳምሶን ከፈለ። 'አምን ቅረላችን ይጠበቅ ይከፍላል' አለ በሐሳቡ።

ከጫት ሽመታ በኋላ ባጃጅ ተሳፍረው መንገድ ጀመሩ። በጉዞአቸው ላይ ከናፍቆት ሠላምታና ከቤተሰብ ደህንነት ጥያቄዎች ያለፈ ነገር አላነሱም። በአብዛኛው የሱማሌ ብሔረሰብ ተወላጆች የሚኖሩበትና አፈቱላ በመባል የሚጠራው የከተማው ክልል ሲደርሱ ሮበሌ "እዚህ በካ!" አለና ባጃጁን አስቆመው። ሳምሶን ሒሳቡን ከፈለ።

ሮበሌ መንገድ ይመራል፣ ሳምሶን ይከተላል። ሮበሌ በመንገዱ ላይ ሠላምታ ለሚሰጡት የሠላምታ ምላሽ ቢሰጥም ከልቡ አልነበረም። እርሱ ገና አልቃመም። ከዚያም በላይ ምናልባት 'ጥሩ ቢዝነስ' ሊያሠራው የሚችል የዱሮ ጓደኛውን አግኝቷል።

አሁን መቀቱ እየገረረ ነው። የአፈቱላን አሸዋ አቋርጠው ከድንጋይና ከሲሚንቶ የተሠሩ አያሌ መኖሪያ ቤቶች ያሉበት ሠፈር ሲደርሱ ሮበሌ አንድ ገርበብ ያለ የብረት በር ገፋ አድርጎ ገባና "ፋጡማ! ፋጡማ!" እያለ ወደ ውስጥ ዘለቀ። ሳምሶንም ተከተለ።

ሮበሌ የቤቱን በር ከፍቶ "እቦ ሳምሶን ግባ! አንተ እንግዳ አይደለም! ፋጡማ! ሳምሶን መጣ። ምላ ቶሎ በይ!" አለና ነጠላ ጫማውን ወዲህና ወዲያ አሽቀንጥሮ ዙሪያውን የተነጠፈ ፍራሽ ላይ አረፈ። "ሳምሶን! ወላሂ። እንተ የሸዋ ሰው ሆኗል። ና! ውረድ።

የባሏን ጥሪ ገና ከደጅ ትሰማ የነበረችው ፋጡማ ወደ ሳሎኑ ገባች። ሰላምታዋ፣ ፈገግታዋና ደስታዋ ሁሉ ፍፁም ልባዊ ናቸው።

"እቦ ፋጡማ ምላ ቶሎ በይ!" አለ ሮበሌ።

ከውጭው አየር አኳያ ቤቱ ቀዝቃዛ ነው። የድራፍዋ ቤቶች አሠራር ባብዛኛው ሞቃቱን አየር የማለዘብ ባህሪ አላቸው።

ሳምሶን የቆዳ ነጠላ ጫማውን አውልቆ ወረደ። ፍራሹ በ "ጊ" ቅርፅ ተነጥፎ በንፁህ እንሶላ ተከሽኗል። ንፁህ ጪርቅ የለበሱ ትራሶች ዙሪያውን ተደርድረዋል። ሳምሶን ወደ "ቤቱ" መመለሱ ተማው።

በትሪ ላይ ንጹህ ብርጭቆዎች እና የውሃ ማቀዝቀዣ ተቀምጠዋል። ምናልባት እዚህ ሳሎን ውስጥ ዘመናዊ ተብሎ የሚጠራ የቤት ዕቃ ካለ ከወደ ጥግ የቆመው ፍሪጅ እና እነስተኛ ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠ ስልክ ብቻ ናቸው።

ሳምሶን እና ሮበሌ ከቀዝቃዛው ቋት በብርጭቆ ቀድተው እየጠጡ ሲያወጉ የሮበሌ ሚስት ፋጡማ የተጠቀለለ ላስቲክ እና የእጅ ውሃ የያዘች ትንሽ ልጅ አስከትላ ገባች።

"ሳምሶን እንደምን ነው?" ሃጫ በረዶ የመሰሉት ጥርሶቿና ፈገግታዋ ይማርካሉ። ከሮበሌ በአምስት ዓመት የምታንስ፣ የደስ ደስ ያላት ሴት ናት። ትንሿ ልጅ የያዘችውን ላስቲክ ፍራሹ ላይ አንጥፋና እጃቸውን አስታጥባ ስትወጣ ፋጡማም ተከተለቻት።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ፋጡማና ልጅቱ በትሪ እና በተለያዩ ጉድጓዳ ሳሕኖች ምግብ ይዘው ገቡ። ገበታው ፍራሹ ላይ ተሠራ። የተቀቀለ ሩዝና እንደ አሮስቶ የተጠበሰ የፍየል ስጋ፣ ቅቅል፣ በእንቁላል የተጠበሰና ማር የተቀባ ቂጣ . . . ሳምሶን ምራቁን ዋጠ።

"ወላሂ ሳምሶን! በሙሉ ካልበላ ነግሬያለሁ! "አለችው ፋጡማ። "እንተ የእማየ ምግብ ይበላል። ሮበሌ ያንተ እናት ይበላል። እንደዚህ ነው ያደጋችሁ።" አዎን እውነቷን ነው። ትላልቆቹ ነበሩ 'ይህ የክርስቲያን ያ የእስላም' እያሉ በምግብ የሚለዩት እንጂ በጎረቤት ልጆች መሃል ይህ ዐይነቱ ልዩነት አይታወቅም። ተው ቢባልም የሚለማ የለም። ፋጡማ ምግቡን አስተግናግዳ ወጣች። ሮበሌ "ቢስሚላሂ" ብሎ ሩዙን በእጁ አፍሶ አድቦልቡሎ ጎረሰና ሳምሶንን .. "ጀምር!" አለው።

ትሪ ሙሉ ሩዝ አጣርተው፤ ቃናውና መልኩ የሚያስደስተውን አሮስቶ ቆርጥመው መረቁ ተጠጥቶ፤ ወፈውም ከምግቡ እኩል እየተሰለቀ ምላ ተጠናቀቀ። 'ደግነቱ እኛ የድሬዳዋ ሰዎች ላስቲክ እያነጠፍን መመገባችን!' አለ ሳምሶን በሐሳቡ። የምግብ ዕቃ ተነስቶ ላስቲክ ተጠቅልሎ ገበታው (ፍራሹ) ከፀዳ በኋላ ሮበሌ ሜቱን አንስቶ አንዱን አቃራ ለሳምሶን አንዱን እራቱ አስቀመጠ። ወደ ሳምሶን ዞር አለና ..." ሃዬ ሳምሶን። ..." አሰው።

ሮበሌ ከዐማርኛ ተናጋሪዎች ጋር ሲሆን ያለ ዐማርኛ አያወራም። አሁን ግን በሶማሊኛ መናገሩ 'ወደ ሥራ እንግባ' ማለቱ እንደሆነ ለሳምሶን ግልፅ ነው። እናም ቁም ነገሩን ጀመሩ።

"እንደ ነገርኩህ አንዳንድ የጦር መሣሪያዎችን ለመግዛት ነው የመጣሁት።"

"ከታንክ በትስቀር የፈለከውን ታገኛለህ። ግን ወዴት ነው የምትወስደው?"

"አዲስ አበባ"

"እንዴት ያልፋል" አይከብድም?"

"ያ አይመለከትህም የኔ ችግር ነው!" አለ ሳምሶን የጫት ቀንበጡን ቀንጥሶ እየጎረሰ።

"እኔ ምንም አያገባኝም። አንተ ላታስብበት አልመጣህም። ምንድነው የምትፈልገው?"

ሳምሶን ለበርካታ ቀናትና ሳምንታት ቀን ተሌሊት ሲተነትን፤ ሲቆጥር፤ ሲያማርጥ ከርሟልና የሚፈልገውን ነገር ሁሉ በቃሉ አጥንቶታል። መዘርዘር ጀመረ።

ዓይነት	ብዛት
1. ኤ.ኬ.47. (ታጣፊ ክላሽ)	10
2. የ.ኤ.ኬ.47 ጥይት በካርታ	30
3. 9.ሚ.ሜ. ኡዚ	2
4. የ9ሚ.ሜ ኡዚ ካርታ	6
5. 9.ሚ.ሜ ማካሮቭ ሽጉጥ	5
6. የ9ሚ.ሜ ማካሮቭ ሽጉጥ በካርታ	15
7. ኤፍ 1 የእጅ ቦምብ	 20
8. 72 ሚ.ሜ የጦር ሜዳ መነፅር	2

አያንዳንዱን የጦር መሣሪያ ዐይነትና ብዛት ሳምሶን ሲጠራ ሮበሌ አንገቱን በአዎንታ ይንጥ ነበር። ሳምሶን ዝርዝሩን በቃሉ ተናግሮ ሲያበቃ ሮበሌ ለተወሰኑ ሴኮንዶች በፀጥታ

ላምሶንን እየተመለከተ ጠበቀው። ተጨማሪ የጦር መሣሪያዎች ትዕዛዝ ለመስማት የፈለገና ስምንት ብቻ መሆናቸውን በማወቁ ቅር የተሰኘ ይመስል ነበር።

"በቃ ይሄው ነው?" አለ በዐማርኛ።

"ለጊዜው ይሄው ነው። ምናልባት ተጨማሪ እፈልግ ይሆናል።" አለው ላምሶን በሶማሊኛ።

"ሁሉንም ማግኘት እችላለሁ። ላውንቸር እና ክባድ መትረየስ አትፈልግም? ምናልባት የምትፈልግ ከሆነ በክላሽ ወይንም በሽጉጥ ዋጋ ላገኝልህ እችላለሁ። ምክንያቱም ሁሉም ሰው የሚፈልገው የነፍስ ወከፍ መሣሪያ ስለሆነ የቡድን መሣሪያዎች ብዙም ገበያ የላቸውም።"

"ለምፈልገው ተግባር በጣም የሚያስፈልጉኝ ለጊዜው የነፍስ ወከፍ መሣሪያዎቹ ብቻ ናቸው። ምናልባት ዛሬ በስልክ ተጠያይቂ አንድ ፒ.ኪ.ኤም መትረየስ አንድ ላውንቸር እጨምር ይሆናል።"

"በቶሎ አላውቀኝ" አለ ሮበሌ።

"ስማ ሮበሌ!"

"ሃዬ!"

"ይህን ሁሉ መሣሪያ ለምን እንደፈለኩት አልጠየከኝም።"

"የኔ ሥራ መሸጥ ብቻ ነው። አንተ ለምን እንደፈለክው ታውቃለህ። አንድ ስህተት ከሠራህና እጅህ ከተያዘ በመጠየቅ የተካኑና የሠለጠኑ ሰዎች ይጠይቁሃል።"

ላምሶን ሳይወድ ላቀና "እሰን እውነትህን ነው። ለማንኛውም በ'ጠያቂዎች' እጅ እንደማልወድቅ እተማመናለሁ።"

"ኢንሻላህ!" አለና ሮበሌ የሞባይል ስልኩን ደወለ።

"ሃሎ! ወሪያ አንካሳ! አለ ሮበሌ። ሶማሌዎች ማንኛውንም ሰው በአካላዊ ጉደለቱ ወይንም በሌላ ቅፅል ስም ይጠሩታል። ነውር አይደለም።

"ሮበሌ ነኝ። ብቻህን እንድትመጣ። ብሎ ስልኩን ዘጋና ወደ ጫቱ ተመለሰ። ጨዋታቸው እንዴ በግለት ሌላ ጊዜ በለሆሳስ ቀጠለ። በዚህ መሃል ፋጡማ ሲኒዎች እና ትልቅ ፔርሙዝ ይዛ ገባችና ከነትሪው እፊታቸው አስቀምጣ "ላምሶን ሻሂ ጠጣ!" ብላ ወጣች።

የምርቃናው ግለት በጨመረ መጠን ሌሎች ያልታዩ ጥቃቅን ጉዳዮችን ሁሉ እያነሱ በጥልቀትና በዝርዝር ተወያዩ።

ምዕራፍ ሃያ

የዶክተር አንዱዓለም አውሮፕላን ከቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ተነስቶ በረራውን ሲጀምር ባሕታዊውን አስታውሶ ፈገግ አለ።

ዶክተሩ ስለ ሃይማኖት ግድ ባይኖረውም፤ ባሕታዊው በረንዳው ላይ የእጅ መዳፋቸውን ሲዘረጉለት፤ ሰውየው "ባሕታዊ" ናቸውና በክበሬታ እጃቸውን ተሳልሞ ነበር የተሰናበታቸው።

ዶክተር አንዱዓለም በሐሳብ ተውጦ በአውሮፕላኑ መስኮት ቁልቁል ወደ መሬት ተመለከተ። የሚወዳት ሀገሩን ቀይ አፈር አጥቦና የግብጽን በረሐ አያቋረጠ ወደ ሜዲትራኒያን ባሕር የሚጅመለመለውን አባይን በትካዜ ተመለከተው። ከፊት ለፊቱም አፍሪካ እና አውሮፓን የከፈለው ባሕር ተንጣሏል። ቀኑ ፀሓያማ፤ ሰማዩም ደመና አልባ ስለሆነ ትዕይንቱ እጅግ ያስደስታል። በመጠኑም ቢሆን ይህን አስደሳች ትዕይንት በሀዘን የበረዘበት የአባይ ነገረ ሥራ ነው።

"ታሪክን የሚጽፉት ሰዎች ብቻ ይመስለኝ ነበር።" አላት አንዱዓለም አጠገቡ የተቀመጠችውን መንገደኛ። ከ22 እስከ 25 ዓመት የሚሆናት ወጣትና ውብ ኢትዮጵያዊት ስትሆን በጉዞአቸው ላይ አልፎ አልፎ ትህትና ከተላበሱ ቃላቶች ያለፈ ብዙ አልተነጋገሩም። አንዱዓለም በንባብ ሲጠመድ ወሺታ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜዋን ያሳለፈችው ጆሮዋ ላይ ኢር ፎን ሰክታ ሙዚቃ እያዳመጠች፤ የተዋቡ ቅርፃማ እግሮቿን እያወዛወዘችና በጣም አጭር ቀሚሷን ዐሥራ ወደ ታች እየሳበች ነበር። ከአዲስ አበባ ካይሮ ድረስ መቁነጥነጥና ቁጭ ብድግ ማለት አብዝታ ነበር። ወደ ካይሮ ሲቃረቡ ግን መቁነጥነጧን በእጅጉ ቀንሳ ማራኪ ጭኖቿን በአጭር ቀሚሷ ለመሸፈን በመጣር "ቢዚ" ሆነች።

"ምን . . ማ..ለ..ት ነው?" አለችው በሚያማልል ድምጽ።

"የአባይ ወንዝ አቅጣጫ ወደ ሰሜን መሆኑ ቀርቶ ወደ ደቡብ ወይም ወደ ምሥራቅ ቢፈስ ኖሮ እስከ ዛሬ የተፃፈው የኢትዮጵያ ታሪክ ፍፁም የተለየ በሆነ ነበር።" አላት።

ያደራረበቻቸውን ውብ እግሮቿን ለማፍታታት ስትሞክር አጠገቧ ያኖረችውን የእጅ ሻንጣ ነካ አድርጋ ጣለችው። ደንገጥ አለችና አንስታ ከተቀመጠችበት ወንበር በላይ

ያለው መስቀያ ላይ አስቀመጠችው። ላምሶናይቷ ዶክተር እንዱዓለም ከያዘው ላምሶናይት ጋር ተመሳሳይ ነው። ልጅቷ ተመልሳ ተቀመጠችና "እኔ አላምንም! ወንዞችም ታሪክን የመሥራት ኃይል አላቸው ነው የምትለኝ?" አለችው ዐይኖቿን እያስለመለመች።

ልጅቱ ካይሮ ላይ ወረደች። አውሮፕላኑ ጉዞውን ወደ ለንደን ቀጠለ። ዶክተር እንዱዓለም ዘና ብሎ ሲጋራውን ለኮሰና . . . 'ጥሩ ሙከራ ነው' አለ። ተመሳሳይ ላምሶናይት ይዛለች። እንቅልፍ ሲያሸልበውና ካይሮን ሲቃረቡ እምሳያውን አስቀምጣለት ላምሶናይቱን ለውጣ ካይሮ ወረደች።

'ዘመቻ መቅደላ በታቀደለት መልኩ እየተንከባለለ ነው። ሞላድ ሆን ተብሎ የተዘጋጀለትን የመጽሐፈ ጥበብ ማሳሳቻ ትርጉም እጁ አስገብቷል።'

'ሞላድ ሆይ! አትስረቅ የሚለውን ቃል የሚያከብሩ ሁሉ ብዑአን ናቸው' ሲል እንዱዓለም አሰበና በሳቅ ፈነዳ።

ባጠገቡ የምታልፈው አስተናጋጅ ቆም ብላ . . ."የጎደለ ነገር አለ ጌታዬ?" ስትል ከማራኪ ፈገግታ ጋር ጠየቀችው።

"የለም የኔ እህት። ከቤቱ የኔ መስሎኝ የባለቤቱን ላምሶናይት ይገር መጣሁ። እሁን ስከፍተው ስጎትት ስጎትት የማያልቅ ስቶኪንግ አይቼ ነው የሳኩት።"

ሆስቴሷ ከልቧ እየሳቀች ጥላው ሄደች።

**********//////////**********

ያሬድ እና ራሄል የቤት ዕቃ የሚሸጥባቸውን ሱቆች እያሰሱ የዘመቻ መቅደላ አባላት በዚያ አዲስ በተከራዩት ቤት ውስጥ ለሚያደርጉት ቆይታ የሚያስፈልጓቸውን ቁሳቁስ ሁሉ ገዝተው ሁሉንም በመልክ በመልክ በየክፍሉ አደራጅተው ጨረሱ። ከመኝታ ፍራሾችና ልብሶች አስከ የምግብ ማብሰያና መመገቢያ ዕቃዎች፣ ከጠረጴዛና ወንበር አስከ አስቤዛና የንጽሕና መሣሪያዎች ... ምንም የቀረ ነገር የለም። ለጥቂት ላምንታት በአንድ ግቢ ውስጥ መሸጎ ለሚለነብት የዐሥራ አምስት ሰው ቡድኑን ያስፈልጋል፣ ይበቃል ያሉትን ድርጅት ሁሉ አስገብተው የላምሶንን ውጤት መጠባበቅ ያዙ።

ራሄል አፓርትመንቷን ለቃ ወደ ተከራየቸው ቤት በቋሚነት ስትገባ ያሬድም ተቀላቀላት።

**********//////////**********

ዶክተር ሥራውብዙ ከብዙ ማግባባትና መለማመጥ በኋላ መቅደላዊትን ዘመናዊ ራስቶራንት ውስጥ ራት ጋበሟት። የቀረቡት የፈረንጅ ምግቦች ግሩም ድንቅ ናቸው። እዋሽ ከሪስታል የወይን ጠጁም ጣፋጭና ለሁለቱም ቀለል ያለ መጠጥ ነው። ዶክተር ሥራው ደጋግመው የሚያወሩ በቅርቡ የሚቀዳጁትን የንዋይ ፀጋና ከፊታቸው የሚጠብቃቸው አዲስ የትንጦት ሕይወት ነው። መቅደላዊት ደግሞ ከሁሉም በፊት የምትጠይቀው ባለ ስድስት አሃዝ ገንዘብ በስሟ ባንክ ገቢ እንዲያደርግላት ነበር አበክራ ያሳሰበችው።

የወይን ጠጁ ጠርሙስ ባዶ ሲሆን ዶክተር ሥራው በጥያቄዋ ተስማሙና የቼክ ደብተራቸውን አውጥተው ጽፈው፣ ፈርመው አስረክቧትና "ነገ ማታ ወደ ቱል አቪቭ አበራለሁ። እስክመለስ ድረስ ረፍት ውጪ። ስመለስ ምን ይገርልሽ ልምጣ?" ሲሉ ጠየቋት።

"ምንም!"

ምዕራፍ ሃያ አንድ

"ወሪያ ሳምሶን። እንካላው ሲመጣ መሣሪያዎቹን ሂደን ታያለህ። ይዘታቸውን እያየህ መርጠህ ስትጨርስ የያንዳንዱን ዋጋ ከተስማማህበት ሒሳቡን ክፍለህ መጫን ብቻ ነው። ክፍያ ካሽ ነው።"

ይህን ሲናገር ከውጭ ድምጽ ተሰማ። "ሮበሌ! ፋጡማ!. . ." የግራ እግሩ ጉልበቱ እካባቢ ታጥፎ በጣም ያጠረው እንካላው ሰው ገባ። "ኪይፈክ" አለ በወረቢኛ።

"ሮመዳን ይህ ሰው ሳምሶን ይባላል። ተዋወቀው። እትክልትና ፍራፍሬ የሚገዛው እሱ ነው።" አለ ሮበሌ ከትውውቁ በኋላ። እንካላው ባዶው ፍራሽ ላይ ተቀመጠ። ወዲያው በሱማሊኛ ውይይቱ ተጀመረ። ሳምሶን የሚፈልጋቸውን የጦር መሣሪያ ዐይነቶችና ብዛት ሮመዳን ለእንግዳው በቃሉ ነገረው። ማስታወሻ አልያዘም ነበርና በሮበሌ፣ ባጠቃላይም በሱማሌዎች የአዕምሮ ማስታወስ ችሎታ ሳምሶን እንደ ጥንቱ ከመገረም ሊታቀብ አልቻለም።

እንካላው በእያንዳንዱ መሣሪያ ላይ ዋጋ ሲጠራ ሳምሶን ደግሞ ሒሳብ ማስላት ጀመረ። የጦር መሣሪያዎቹን ስም የሚጽፈው በኮድ ነበር። በቅጽበት ጊዜ ውስጥ የሚከለተው ነገር አይትወቅምና።

መጋዝ 15.00 (ክላሽ)

እንቁላል 20 (ቦምብ) . . . ወ.ዘ.ተ

ሳምሶን የመጨረሻውን ድምር ሠርቶ ቀና አለና የጻፈበትን ወረቀት መተርኮሻው ላይ አስቀምጦ እሳት ለኮሰበት። ተቃጥሎ ጥቁር አመድ ሆነ።

"የማይሆን ወሬ ነው የምታወራው!" አለው ሮመዳንን።

"የሚሆን ወሬ ነው።" አለ ሮመዳን ተኮሳትሮ። ተነስ እንሂድና መሣሪያዎቹን ተመልከት፣ ምረጥ፣ ካሽ ክፈል፣ ጭነህ ሂድ! በቃ ሌላ ወሬ አያስፈልግም።

"እናንተ የሸዋ ሰዎች ለዋጋ መከራከር በጣም ትወዳላችሁ። ዋሽንግተን ስትገቡ ሱፐር ማርኬት ውስጥ ዋጋ የተለጠፈበትን ዕቃ 'ቀንስ! ቀንሺ!' እንደምትሉ ሰምቻለሁ። ሃሃሃ!"

ሳምሶን ፈገግ አለና "እሺ ተነሱ እንሂድ። መጀመሪያ መሣሪያዎቹን እንመልከት" አለ። ሦስቱ ሰዎች የአፈቱላን ጉራንጉር እየተጠማዘዙ ዐሥር ደቂቃዎች ያህል ተጉዘው ከተን በሩ የተዘጋ አንድ አነስተኛ ግቢ ደረሱ።

"ወሪያ አብዱልፈታህ!" አለና ሮመዳን ሁለት ጊዜ አንደተጣራ በሩ ተከፈተና አንድ ቀጭን፣ ረዥምና ጢማቸው ተንዥርጉጎ በሂና የቀለመ አዛውንት ሰው በሩን በርገድ አድርገው "ግቡ!" አሉ።

ሦስቱ እንግዶች ተያይዘው ወደ ቤት ዘለቁ። ነጠላ ጫማ እያወለቁ ሁሉም ዙሪያውን በተነጠፉ ፍራሾች ላይ አረፍ አረፍ ሲሉ የቤቱ አባ ወራ አብዱልፈታህ የነበሩበት ፍራሽ ላይ ተደላድለው ተቀመጡ።

እንዲት መካከለኛ ዕድሜ ውስጥ የምትገኝ ሴት ተፈልቶ የቀዘቀዘ ወተት በጀበና ከነሲኒዎቹ አምጥታ ለሁሉም ቀድታላቸው እስክትወጣ ድረስ ወንዶቹ በጸጥታ ጠበቋት።

"መሣሪያዎቹን የሚገዛው ይህ ሳምሶን ነው" በማለት ሮበሌ ከቤቱ ባለቤት ከአብዱልፈታህ ጋር አስተዋወቀው። "አብሮ አደግ ጓደኛዬ ነው። ወንድሜ ማለት ነው። ወላሂ!" አለና ደንበኛው የሚፈልጋቸውን የጦር መሣሪያ ዐይነቶች ዝርዝር ለሐጂ አብዱልፈታህ አነበበላቸው።

"በሮበሌ በኩል የመጣና ከኔ ዘመዶች ጋር ያደገን ሰው የማላምንበት ምክንያት አይኖርም።" አሉና በሂና የቀለመ ሹል ጢማቸውን ጥቂት ሲጎነትሉ ቆይተው "የአያንዳንዱን መሣሪያ ዋጋ ነግረኸዋል?" ሲሉ ሮበሌን ጠየቁት። ሮበሌ መልስ ከመስጠቱ በፊት ሳምሶን ጣልቃ ገባ።

"የሮበሌን ዋጋ ሰምቻለሁ። በጣም ውድ ነው።"

"የለም ወላሂ ጥሩ ዋጋ ነው።"

ክርክሩና ሙግቱ ከአንድ ሰዓት ላላነሰ ጊዜ ተማሙቆ ቀጠለና ገገርና ሻጭ አንዱ ዝቅ፣ ሌላው ከፍ እያለ በመጨረሻም ሽማግሌውና ሳምሶን ዋጋ ቆርጠው ተስማሙ።

ኦፐሬሽን መቅደላ — በስራት አጥላባቸው

ዐይነት	ብዛት	ያንዱ ዋጋ	ድምር
ክላሽ ኤ.ኬ. 47	10	1000	10,000
የክላሽ ጥይት በካርታ	30	50	1,500
9. ሚ.ሜ. ኡዚ	2	1500	3,000
የኡዚ ጥይት በካርታ	6	100	600.00
9.ሚ.ሜ ማካሮብ	5	1 500	7,500
የማካሮቭ ጥይት በካርታ	15	25	375.00
ኤፍ1 የእጅ ቦምብ	20	10	200.00
72 ሚ.ሜ የጦርሜዳ መነፅር	2	500	1,000
		ድምር	23,975

"እነዚህ የጦር መሣሪያዎች በሙሉ በማንኛውም መንገድ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ንክኪ የላቸውም አይደል?" አለ ሳምሶን ወተታቸውን በድጋሚ ጠጥተው ሲያበቁ።

ሁሉም ባንድ ድምጽ መንጫጫት ጀመሩ። "ወሪያ ሳምሶን ወላሂ። እኔ ቃል አሰጣለሁ . . . እነዚህ መሣሪያዎች በሙሉ ከሶማሊያ መንግሥት ውድቀት በኋላ ወደ ኢትዮጵያ የተሰደዱ የሶማሊያ ተፈናቃዮች በዘረፋ ያመጧቸው ናቸው.....።" እና የመሳሰሉ ትረካዎችና ማረጋገጫ ከሦስቱም ሰዎች ከተሰነዘሩ በኋላ አሣውንቱ ሁሉንም ዝም አሰኙና "እንተ ሳምሶን!" አሉት"

"አቤት።"

ለመሆኑ የኢትዮጵያ መንግሥት ይህን ያህል መሣሪያ ቢጠፋበት እንደ ሶማሊያ መንግሥት ... 'ሽጣችሁ አካፍሉኝ!' የሚል መሰለህ?" ሲሉት ሳምሶን የተጎነጨው ወተተ ትን አስኪለው ድረስ በሳቅ ፈነዳ። በመጨረሻም መሣሪያዎቹን ለሳምሶን ለማሳየት ተነሱ።

አሁን ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሆኗል። የቤቱ ባለቤት አብዱል ፈታህ ሳምሶንን፣ ሮበሌን እና ሮመዳንን ወደ ጓሮ እየመሩ ወሰዷቸው። በግቢው ውስጥ የሰው ዘር የሚባል አይታይም። ወተት ያስተናገደቻቸው ሴት እንኳ ደብዛዋ የለም።

በሲሚንቶና በድንጋይ ከተሠሩ ሁለት ሰርቪስ ቤቶች መሃል አሣውንቱ አንዱን ክፍል ከፍተው መብራት አበሩና "ግባ ሳምሶን" አሉት። ሁሉም ገቡ። ክፍሉ ሙሉውን ምንጣፍ ተነጥፎበት ዙሪያውን ፍራሾች፣ ክፍራሾቹ በላይ ትራሶች ተነጥፎበታል። "ፍራሽና ምንጣፉን አንሱ!" አሉ ሽማግሌው።

ሮመዳንና ሮበሌ በቅልጥፍና ፍራሾቹን እያነሱ አንዱ ጥግ ላይ ከከመሩ በኋላ ምንጣፉንም ጠቅልለው ወደ ጥግ አኖሩት። ወለሉ ጣውላ ነው። አብዱል ራሺድ ጣታቸውን የአንዱ ጣውላ ቀዳዳ ውስጥ ጨምረው ጥቂት ካንጎዳጎዱ በኋላ ቀዳዳውን እንደያዙ ጣውላውን ወደ ላይ ብድግ አደረጉት። ሁለት ሜትር በሁለት ሜትር የሚያህልና ከውስጥ በኩል በማጠፊያ የተያዘ መስኮት ወደ ላይ ብድግ ሲል ሮመዳንም እገዛቸውና እስከ መጨረሻው ከፈተው። ከቤቱ ወለል አንስቶ ወደ ታች የሚወርድ የአጠና መሰላል ይታያል። የሳሉት መብራት እንደሚያሳየው ከሆነ መሰላሉ በርካታ የአግር ምልልሶችን ያስተናገደ ይመስላል። ሽማግሌው አብዱልፈታህ በመሰላሉ ወረዱና የምድር ቤቱን መብራት አብርተው ሳምሶንና ሮበሌ እንዲወርዱ ነገርዋቸው ሁለቱም ተከታታለው ሲወርዱ ከላይ ሮመዳን አንካሳው ከላይ ቀረ።

ሳምሶን ዙሪያውን ተመለከተ። ምድር ቤቱ አራት ሜትር በአራት ሜትር ሥፋት አለው። ግድግዳና ወለሉ በሲሚንቶ የተሠራ ነው። የታሸጉ ሲጋራዎች፣ ጥቅል (ጣቃ) ጨርቆች፣ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ተከምረዋል። በሌላው ማዕዘን ደግሞ አምስት ትላልቅ የብረት ሣጥኖች ተደርድረዋል። አዛውንቱ አብዱልፈታህ በጀለቢያቸው ላይ ከለበሱት የኮት ኪስ ውስጥ በርካታ ቁልፎችን አወጡና አያንዳንዱን ሣጥን መክፈት ጀመሩ። አርሳቸው ቁልፉን ቋ! አድርገው ይከፍቱና ወደ ሌላው ሣጥን ሲዞሩ ሮበሌ ቁልፉን ያላቅቅና የሣጥኑን ክዳን ይከፍታል።

ሳምሶን በመጀመሪያ ከተከፈተው ሣጥን ውስጥ ዐሥር ኤ.ኬ. 47 ታጣፊ ክላሺንኮቭ አውቶማቲክ ጠመንጃዎችን እያወጣ መሬት ላይ ደረደረ። ከዚያም እያንዳንዱን እየፈታ ከፈተሸ በኋላ መልሶ መግጠም ጀመረ። "ወላሂ! አስተማማኝ ናቸው! " ይሉታል አዛውንቱና ሮበሌ።

ዐሥሩ ጠመንጃዎች ተፈትሸው ሲያበቁ ሽማግሌው ሁለት ኡዚ አውቶማቲክ መሣሪያዎች አቀበሉት። አሁን ሳምሶን የስሜት መለዋወጥ በገጽታው ላይ ታየበት። የመጀመሪያውን እሥራኤል ሠራሽ 9 ሚ.ሜ ኡ.ዚ በተለየ ፍቅርና ስሜት እያገላበጠ ሲዳስሰው ቆየ። "ከምንም ነገር በላይ የምወደው መሣሪያ ይህ ኡዚ ነው" አላቸው።

"ወላሂ! በጣም ጥሩ አቶማቲክ!"

"ወላሂ! ምርጥ መሣሪያ!"

ሳምሶን ኡዚዎቹን እየፈታታ ፈትሾ ከገጠመ በኋላ ተመሳሳዩን ፍተሻ በሽጉጦች፣ በእጅ ቦምቦችና በጥይት ሜጋዚኖች ላይ በጥንቃቄ አደረገ። አጠቃላይ ቆጠራ አድርጎም ጨረሰ።

"ሃዬ ሳምሶን! መሣሪያዎቹ በሙሉ ጥሩ እይደሉም?" ሲል ሮበሌ ጠየቀው።

"እምን በጣም ጥሩ ናቸው። አሁን ወደ ክፍያና ርክክብ እንሂድ።"

"ክፍያ በሙሉ በካሽ ነው። ገንዘቡን ቆጥረህ ስታስረክብ መሣሪያዎቹን በሙሉ ትረክባለህ" አሉ ሽማግሌው።

"ነገ ልክ በዚህ ሰዓት።"

(ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ) መኪና ይዤ እመጣለሁ። መሣሪያዎቹን በሻንጣዎች ከፋፍለን እንደ ጫንን ወዲያው ሙሉውን ክፍያ በካሽ አስረክቤ ከሮበሌ ጋር እንወጣለን።"

"በቃ! ብቻህን ነው መኪና ይዘህ የምትመጣው?" ሲሉ አዛውንቱ በገረሜታ ጠየቁት።

"እምን! ብቻየን ነው የምመጣው። ሮበሌን እንኳንስ ለሃያ አምስት ሺህ ብር በሕይወቴም አምነዋለሁ።" አለ ሳምሶን። ሁለቱ አዛውንቱና ሮበሌ እጅግ ተደስተው ወላሂ እንተ ጥሩ ወንድማችን . . ." እያሉ ደጋጋመው አሞገሱት።

'ይህን መሣሪያ በገንዘብ ሸጦ መገላገል ለናንተ ከፍተኛ እፎይታ ነው!' ሲል አሰበ። 'ምናልባት ሽቀጡ ሌላ ዐይነት የኮንትሮባንድ ሽቀጥ ቢሆን ኖሮ . . . .'

"ነገ ማታ እዚህ አብረን እንመጣለን።" አለና ሮበሌ ሳምሶንን ተመለከተው።

"ትክክል!"

እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት ተኩል አብረው የቆዩት ሮበሌና ሳምሶን ነገ እኩለ ቀን ላይ ራስ ሆቴል ሊገናኙ ተስማምተው ተለያዩ። ሳምሶን ገላውን ታጥቦ፣ ራስ ሆቴል ያፈራውን እራት ተመግቦ፣ ሁለት ጠርሙስ ቢራውን ጨልጦ ወደ መኝታ ክፍሉ ገባ። አልጋው ላይ ገደም ብሎ ሲጋራውን እየማገ የመሣሪያ ግዢና ክፍያ፣ እንዲሁም የርክክብ ዕቅዱን በጥልቀት ፈተሸው። አንዳችም ለአደጋ የሚያጋልጥ እንክን አልታየውም። ይህ የመጀመሪያው ምዕራፍ ነው። ሁለተኛው ምዕራፍ የጦር መሣሪያዎቹን በደህና አዲስ አበባ ይዞ መግባት ነው። የጦር መሣሪያዎቹን የሚወስዱበትን መኪና ግዢውን እና የማስመሰያ ለውጥ ሥራውን ሮበሌ ሊጨርስለት ተስማምተዋል። ነገር ግን ዋጋው ..."

'ያኛውን ድልድይ ስንደርስ እናቋርጠዋለን!' አለና ሳምሶን መብራቱን አጥፍቶ ወደ እንቅልፍ ዓለም ነጎደ።

ምዕራፍ ሃያ ሁለት

ያልጋው ስፋትና ባዶነት ከአንቅልፏ አነቃት። በዳሰሳ ያጣችውን ለመፈለግ ዐይኖቿን ገልጣ ከጭሉን ቃኘችው። ያፈት በፒጃማው ላይ ትልቅ ፎጣ ያርቦ ምቹ ወንበር ላይ ተቀምጧል። ከፊት ለፊቱ የመልበሻ ጠረጴዛው ላይ ላፕ ቶፕ ኮምፒውተሩን አብርቶ አተርቅሮበታል። "ኡ . . .ፍፍፍ !" አለችና ስታዛጋ ያፈት ዞር ብሎ አያት። "የኔ ቆንጆ ነቃሽ?"

"አስበረድከኝ እኮ! ሲጋራ ለኩሰህ አቀብለኝ።" አለችው።

"እሺ የኔ ቆንጆ!" አለና ማርልበሮ ሲጋራ ለኩሶ መጣና ከንፈሮቿ መሀል ሰካላት። ሁለቱ በረኸሙ ሳበችለትና "ምን እየሠራህ ነው?" አለችው።

"ሄለኮፕተር እያበረረኩ!"

"የሲሙሌሽን ጦርነትን እየተዋጋህ ነዋ?" አለችው ፈገግ ብላ።

ያፈትም በተረፏ ፈገግ አለ። "ይሄ ኢንተርኔት የሚሉት ነገር ለሚጠቀሙበት ሰዎች አስደናቂ የመረጃ ውቅያኖስ ነው።"

"የምትፈልገውን ነገር በሙሉ አገኘህ?"

"የሚቀሩኝ ነገሮች አሉ።"

"ታዲያ ከየት ልትሞላው ነው?"

"ሁለት የአየር ኃይል ባልዳረቦችን ለማግኘት ስልክ ስደዋውል ቆይቼ አንዱን ዛሬ ለምሳ ቀጥሬዋለሁ።"

"በጣም ተጠንቀቅ!" አለችው እየሰጋች።

"ታስቢልኛለሽ?"

"እንክት!"

"በምን ታረጋግጪልኛለሽ?"

ሲጋራዋን ከሞዲኖው ላይ የተቀመጠ መተርኮሻ ላይ አጠፋችና አንሶላውን ገለጥ አድርጋ "ፒጃማህን ጣልና ማረጋገጫውን ላሳይህ!" አለችው። ያፈት ፒጃማዎቹን እና ፎጣውን ያወለቀበት ፍጥነት ምናልባት በ 'ጊነስ' ሪኮርድ መዝገብ ላይ የሚያስፍረው ሳይሆን አይቀርም።

**********//////////**********

የተባበሩት መንግሥታት (ዩ-ኤን) የሚሉ ፊደሎች ነጩ ቶዮታ ላንድ ክሩዘር መኪና ከፊት፣ ከግራና ቀኝ በሮቹ ላይ በለማያዊ ቀለም በጉልህ ተጽፎበታል። የራዲዮ መገናኛ አንቴናው በረጅሙ ተመሟል። ከኋላ ወንበር ላይ አንድ በጣም ትልቅና አንድ መካከለኛ መጠን ያላቸው ሻንጣዎች እንዲሁም ሁለት ትናንሽ የአንግት ቦርሳዎች ተቀምጠዋል። ከሹፌሩ አጠገብ ያለው ወንበር ላይ የመጠጥ ውሃ፣ አንዱ ሻንጣ ላይ አዲስና ትልቅ ብርድ ልብስ፣ የመኪናው ወለል ላይ ደግሞ የማርልቦሮ ሲጋራ ፓኬቶች ወዳድቀዋል። አዋሽ የፍተሻ ጣቢያ ላይ ሲደርስ ወታደሮች ምልክት አሳዩትና ዳር ይዞ መኪናውን አቆመ።

ወታደሩ ሠላምታ ሰጠውና "ለፍተሻ ቢወርዱልን ይመችዎታል?" አለው።

"ላምሶን ሲጋራ አውጥቶ እየለኮሰ "ማርልቦሮ ይመችሃል? ሲል ጠየቀው።

"ከምግብ በስተቀር ሌላ ሱስ የለብኝም!" አለ ወታደሩ።

"ሱሰኛ ባለመሆንህ የገዛሁትን የኮንትሮባንድ ብርድ ልብስ ልሸልምህ?" አለ ላምሶን ባውራ ጣቱ ወደ ኋላ ብርድ ልብሱን እያመለከተው።

ስምህን ማን ልበል?" አለ ወታደሩ።

"መቅደላ! ያንተስ ማን ይሰኛል?"

"ስምህ ደስ ይላል" አለና ወታደሩ ግራና ቀኙን ተመልክቶ በዝቅተኛ ድምጽ" ስሜ ብራና ነው። መልካም መንገድ!" አለው።

'የባሕታዊው እጅ ረኸቦም ነው' ሲል አሰበና በእፎይታ ተነፈሰ።

**********////////**********

ላምሶን በደስታ እንደማፏጨት እየቃጣው ከፍተሻ ጣቢያው ሁለት ኪሎ ሜትሮች ያህል ከራቀና አንድ ሊትር የላስቲክ ውሃ ከጨረሰ በኋላ ነበር ማርልቦሮ ሲጋራውን የለኮሰው።

በጣቱ የሲዲ ማጫወቻውን ተጫነው። 'መልካም ቅንብር ነው ባሕታዊው' ሲል እያሰበ ሙዚቃውን ጠበቀ።

"ና ገዳሙ....."ካሳ ተሰማ።

**********////////**********

ያሬድና ራሄል በጓደኛዋ ሶፊያ አስጎብኚነት የትምህርት ቤቱን አዳራሽና ቅጥር ግቢ ጎብኝተው ሲወጡ ከቀኑ አምስት ሰዓት ተኩል ሆኗል። የግቢው መውጫ በር ላይ ቆመው ሶፊያን ምላ ለመጋበዝ ደጋግመው ለመኗት። ሶፊያ ጊዜ እንደ ሌላት እና ምላ መያዟንም ተናግራ ይቅርታቸውን ከጠየቀች በኋላ "ሁለታችሁ በጣም የምትመጣጠኑ፣ የምታምሩና፣ የምትግባቡ ባለ ትዳር ይወጣችኋል። እኔ ስለናንተ በጣም ከልቤ ተደስቻለሁ። ለማንኛውም ይህ ኤግዚቢሽን ከተፈጸመ በኋላ የሠርጋችሁን ዝግጅት አሳምረን እንወጣዋለን።" አለቻቸው።

"በጣም ነው የምናመሰግንሽ።" አለ ያሬድ።

"በጣም! በጣም! እናመሰግንሻለን! ከነገ ወዲያ፣ ቅዳሜ ማለት ነው ምላ አብረን ነን። ቻው የኔ ቆንጆ!" ራሄል የልብ ጓደኛን ሶፊን ጉንጯ ላይ ላም አድርጋ ተሰናበተቻት።

**********//////////**********

"እሺ ያሬድ። እኔ ለቅርሳችን ይጠበቅ ማሕበር አባላት የስብሰባ ጥሪ ለማዘጋጀት ቢሮ መግባት አለብኝ። አንተስ አብረህኝ ትሄዳለህ?" አለችው የመኪናውን ማርሽ እየለወጠች።

"የለም እኔ ወደ ባሕታዊው ቤት ሄጄ የኦፕሬሽን መቅደላን የፕሮፖጋንዳ ፊልም ላዘጋጅ ነው የምውለው። ላፕ ቶፕ ይገዜ የወጣሁትም ለዚህ ነው።"

"መልካም። አሁን ባህታዊው ቤት አደርስህና እኔ ወደ 'ቅርሳችን ይጠበቅ' ቢሮ እሄዳለሁ። ስትጨርስ ከደወልክልኝ 'ፒክ' አደርግሃለሁ።"

"ውድ አገልግሎት ሰጠሽኝ ማለት ነዋ!"

"እስካሁንስ ያጓደልኩብህ አልግሎት አለ እንዴ?" አለችው ዐይኖቿን እያስለመለመች።

"የለም። ግን አንድ የመጨረሻ አገልግሎት እጠብቃለሁ።"

"ምን?" በጉጉት ዞራ አየችው።

"ዘመቻ መቅደላን ሰርቫይቭ አድርገሽ የልጆቼ እናት መሆን!"

ጭኑን በቀኝ እጁ ጣ! አድርጋ መታችውና "ዮ ካን ካውንት አን ሚ!" አለችው።

ምዕራፍ ሃያ ሶስት

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ንብረት የኾነውና የበራራ መስመር ቁጥር 627 የተመዘገበው ቦይንግ 767 አውሮፕላን ሁለተኛ ማዕረግ አብዛኛው ወንበሩ ተይሟል። ከመንገደኞቹ ብዙዎቹ ህበሾች መሆናቸው ዶክተር ሥራውብዙን አሳስቧቸዋል። ይህን የቴልአቪቭ ጉዞ አቅደው ሲነሱ ከመቅደላዊት በስተቀር ማንም ያወቀ የለም። የጎንደሩን በረራ ቲኬት ያስገዟት ለቴል አቪቭ ጉዞአቸው ሽፋን እንዲሆንላቸው ነው።

አውሮፕላኑ ከጧቱ 2:00 ሰዓት ዩቪድ ቤንጎሪዮን ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ አርፎ መንገደኞቹ ወረዱ። ዶክተር ሥራው ኮፊያቸውን ወደ ግንባራቸው አውርደው ሰፊ ጥቁር መነጽር አደረጉ። ጥራቱ የተጠበቀ ስስ ካኪ ሸሚዝና ሱሪ ለብሰው በጣም ስስ እና ጠፍጣፋ የቆዳ ጫማ ተጫምተዋል። የመካከለኛው ምሥራቅን የበጋ ሙቀት ተዘጋጅተውለት ነው የመጡት። አንዲት አነስተኛ በትከሻ የምትነገት ቦርሳ እና የእጅ ላምሶናይታቸውን ብቻ እንደ ያዙ ወደ ታክሲ ማቆሚያ አመሩ።

"ሰር ታክሲ?"

"ዩቪድ ሆቴል!" አሉትና የኋላውን በር ከፍተው ገቡ። መንገዳቸውን ሲጀምሩ ትራፊኩ ብዙም የተጨናነቀ አልነበረም። ጊዜው ፍልስጥኤማውያን በእሥራኤል መንግሥት ላይ 'ኢንቲፋዳ' ያቀጣጠሉበት ወቅት ቢሆንም ቴል አቪቭ ውስጥ አንዳችም የውጥረት ምልክት አይታይም።

የሆቴሉ ደጃፍ ላይ ታክሲው ሲቆም ዶክተር ሥራው የገንዘብ ቆጣሪውን ተመልክተው ባለ 50 ዶላር ኖት አውጥተው "ኪፕ-ዙ-ቼንጅ!" ብለው ለአሽከርካሪው ሰጡትና ወደ ሆቴሉ ገቡ። ሒሳቡ ሃያ ዶላር ነበር ። ዶክተር ሥራውብዙ ግን በታላቅ ደስታ ነው በርካታ ጉርሻ የሰጡት። ካሁን በኋላ የዚህ ዐይነቱን የቅንጦት ኑሮ መኖር እንደሚችሉ ከልብ አምነው ተቀብለውታል። 'ሺ ዓመት አይኖር!'

የአንግዳ መቀበያ ዴስክ ላይ ለሚሠራው ተረኛ አስተናጋጅ ፓስፖርታቸውን ከሰጡ በኋላ አስቀድመው ክፍል ማስያዛቸውን ነገሩት። "ላረጋግጥ" አለና ትሁቱ አስተናጋጅ ኮምፒውተሩ ከፈተሸ በኋላ "ልክ ነዎት ጌታዬ!" አለ በፈገግታ። "ክፍል ቁጥር 131 ተይዞልዎታል። ሁለተኛው ፎቅ ላይ ነው። መልካም ቆይታ ይሁንልዎት" አላቸው።

ዶክተር ሥራው ከአላንሱር ወጥተው ግራና ቀኝ ቁጥሮችን እያዩ ጥቂት ከተራመዱ በኋላ ቁጥር 131 ክፍልን ከፍተው ገቡና ከውስጥ ቆለፉት። ቦርሳዎቹን አስቀምጠው አልጋው ላይ አረፍ ካሉ በኋላ አንደ የራስጌውን ስልክ አንዱ የእጅ ሰዓታቸውን በጭንቀት መመልከት ጀመሩ። ብዙም ሳይቆይ አሥራኤላዊው ስልክ ጭንቀታቸውን የተረዳ ይመስል ጥሪ አሰማ።

"ሄሎ!" አሉ ዶክተር ሥራው።

"የሆቴሉ በር ላይ ጥቁር ሜርሴዲስ ይጠብቅዎታል። ጉብኝቱን ስለምናስጀምርዎ እባክዎን ቢመጡልን።"

ግራ ተጋቡ። 'የምን ጉብኝት?' ሳምሶናይትና ቦርሳቸውን ይዘው ወጡና ክፍላቸውን ቆልፈው በሊፍት ወደ ታች ወረዱ። ቁልፉን በፈገግታ የሰጣቸው እንግዳ ተቀባይ በፈገግታ ተቀበላቸው።

'ያው ሜርሴዲሱ!' ዶክተር ሥራው መኪናው ውስጥ ገብተው በሩን ከመዝጋታቸው መንገድ ጀምረዋል።

ኮኒላ በሩን የከፈተላቸው በሃምሳዎቹ ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኘው አስራኤላዊ እጁን ለሠላምታ ዘረጋ። "ካይም አባላለሁ ዶክተር ሥራው። እንኳ በደህና ወደ ቱል አቪቭ መጡ።" አላቸው። የኋላው መቀመጫ ከሹፌሩ በሚለይ መስተዋት ተዘግቷል። ካይም ተብዬው ወደ ሹፌሩ በጣቱ እየጠቆመ "ሳውንድ ፕሩፍ (ድምፅ የማያሳልፍ) መስተዋት ስለሆነ ያለ ስጋት ማውራት እንችላለን።" አላቸው።

"አሁን ወዴት ነው የምንሄደው?" አሉ ዶክተሩ። ካይም ጥያቄውን ችላ ብለው "ፓኬጁን ይዘዋል ጌታዬ?" አላቸው። ዶክተር ሥራው ግን አሁንም እርግጠኛ ስላልሆኑ መልስ መስጠት አልፈለጉምና "የምን ፓኬጅ?" ሲሉ ጠየቁት። ካይም ነኝ የሚለው አሥራኤላዊ ፈገግ አለ።

"ልክ ነዎት ጌታዬ! እንደርሶ ጠንቀቃና ብልህ ከሆነ ምሁር ጋር መሥራት እጅግ ያስደስታል። ራሴን ማስተዋወቅ ነበረብኝ።" አለና ስስ ጃኬቱን ገለጥ አድርጎ ሸሚዝ ኪሱ ላይ ያንጠለጠለውን መታወቂያ አሳያቸው። ኮሎኔል ካይም አኪባ። አሊያህ ቤት የሚል ጽሁፍ አነበቡ። አሊያህ ቤት 'ሞሳድ' በመባል የሚታወቀው የእሥራኤል የመረጃ ድርጅት የውጭ ሀገሮች ስለላ ክፍል ነው። ዶክተር ሥራው በመጠኑ እፎይታ ተሰማው።

"እምን ፓኪጁን ይዣለሁ። ነገር ግን መነጋገር የምፈልገው ከነባሩ ደንበኛዬ ጋር ነው!" አሉት።

"እምን ልክ ነዎት። እኔም የምወስድዎት ወደ ዋናው መሥሪያ ቤታችን ነው። የጠየኩዎት ለማረጋገጥ ብቻ ነውና አይቀየሙኝ።" አለ በትህትና።

ከዐሥራ አምስት ደቂቃዎች ጉዞ በኋላ የከተማው ዳርቻ ቁጥር 72 ጎዳና ላይ የሚገኝ አንድ ባለ 6 ፎቅ ሕንፃ ሥር ደረሱ። 'ሻሎም ኢምፓርት ኤክስፖርት' የሚል ማስታወቂያ የነኛው ፎቅ መግቢያ በር አናት ላይ በትልቁ ተጽፎበታል። ዶክተር ሥራው ፈገግ አሉና በልባቸው 'ሌቦች!' አሉ። ካይም ሐሳባቸውን ያነበበ ይመስላል። ምክንያቱም እርሱም በተራው ፈገግ ብሎ ጽሑፉን በጣቱ እየጠቆመ ... 'ለጥንቃቄ ያህል!' አላቸው። ሕንፃው ዙሪያውን በጣም በረኛም ግንብ ታጥሮ በተጨማሪም የኤሌክትሪክ አስተላላፊ ሽቦ ተገጥግጦባታል። ሜርሴዲሱ በሩ ላይ ሲደርስ ኡዚ አውቶማቲክ በደረቱ ያንጠለጠለና ዩኒፎርም የለበሰ ዘብ የመሰናክል ብረቱን ብድግ አደረገው። መኪናው ወደ ውስጥ ገብቶ ቆመ። ሌላ ዘብ በግራ እጁ ማስታወሻ ደብተር ይዞ መጣ። መጀመሪያ የአሽከርካሪውን የደረት ባጅ ካየ በኋላ ወደ ኋላው በር መስኩት መጣ። ካይም የበሩ እጀታ ላይ ያለውን ቁልፍ ተጭኖ መስታወቱን ወደ ታች አወረደው። ዘቡ ዘና አለና ኮረኔሉ ያንጠለጠለውን መታወቂያ ካየ በኋላ ወደ አንግዳው እያሳየ በዕብራይስጥ ቋንቋ ተናገረ።

ኮሎኔል ካይም አጭር ምላሽ ሰጠው። ዘቡም ራሱን በአምንታ ንጦ አሽከርካሪው ወደ ውስጥ እንዲያልፍ ምልክት ሰጠው።

ዶክተር ሥራውና ካይም ከመኪና ወርደው ሕንፃው ውስጥ የገቡት ራሱ በሚፈትሽ የኤክስ-ሬይ ማሽን ተፈትሸው ወደ አንግዳ መቀበያው ዴስክ አመሩ። ዴስኩ አካባቢ በጥቁር ቆዳ የተለበጠ ረዥም ሶፋና የቡና ጠረጴዛ አለ። ካይም ዶክተሩን . . . . " እባክዎን አረፍ ይበሉ!" ሲል በትህትና ሶፋውን ጠቆማቸው። ዶክተሩ መሰላቸትና ጭንቀት እየታየባቸው ቦርሳዎቹን ወለሉ ላይ አኖሩና ሶፋው ላይ አረፍ አሉ።

ኮሎኔል ካይም ላጭር ጊዜ ከአንግዳ ተቀባዩ ጋር ካወራ በኋላ መገበብ ላይ ሁለት ጊዜ ፈርሞ ወደ ዶክተር ሥራውብዙ መጣ። "ስለ አሰልቺው አንግዳ አቀባበላችንን ይቅርታ ያድርጉልን። የፀጥታ ችግር እንዳለብን ያውቃሉ" አለና አጠገባቸው እንደተቀመጠ አንዲት የወግ አጥባቂ አለባበስ (ኮት፣ ጉርድ ቀሚስ፣ አጭር ታክ ጫማ) የለበሰች ቢበዛ አርባ ዓመት የሚሞላት ሴት መጣች።

'ዶክተር ሥራው። እንኳ በደህና መጡ። ካሁን በኋላ እኔ አመራምታለሁ። እባክዎን ይከተሉኝ።" ዶክተር ሥራው ቦርሳዎቹን አንስተው ተከተሏት። በቀጥታ ሊፍት ውስጥ ይዛቸው ገባችና አንዱን ቁልፍ ተጫነችው። ወዲያው በሩ ከመዘጋቱ ሊፍቱ መንቀሳቀስ ጀመረ። ዶክተር ሥራው ግራ ተጋቡ። ምክንያቱም ሊፍቱ ወደ ታች የተንቀሳቀሰ ነበር የመሰላቸው።

ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላ ሊፍቱ ቆሞ በሩ ተከፈተ። ሴቲቱን ተከትለው፣ ውበት በሌለውና የመብራት ብርሃን ብቻ ባደመቀው ረዥም ኮሪደር ውስጥ በዝምታ ተጓዙ።

ዶክተር ሥራው ከመሬት በታች የተሠራ ሕንፃ ውስጥ እንዳሉ አሁን እርግጠኛ ሆኑ። 'ዕድሜ ልክ የሥጋት ኑሮ!' አሉ በሐሳባቸው። በመጨረሻም ምንም ዐይነት ቁጥር ወይንም ምልክት ያልተለጠፈበት በር ላይ ሲደርሱ ሴትየዋ የመታወቂያ ካርዷን በሩ አጠገብ የተለጠፈ አነስተኛ ራዲዮ የሚያክል መሣሪያ ውስጥ ጨመረችው። ከሁለት ሴኮንዶች በኋላ "ጢው!" የሚል ድምፅ አሰምቶ መታወቂያዋን ተፋላት። በሩም ተከፈተ። "ይከተሉኝ" አለችና መታወቂያዋን ይዛ ወደ ውስጥ ገባች።

**********////////**********

ዶክተር ሥራው ተከትለዋት ገቡ። ወደ ኋላ ዞር ባይሉና ምንም ድምጽ ባይሰሙም በሩ በራሱ መዘጋቱ ታውቋቸዋል። ይህ ክፍል አራት በአምስት ሜትር ያህል ስፋት ሲኖረው ሙሉውን ቡናማ ቀለም ያለው ምንጣፍ ተነጥፎበታል። መስኮት የሚባል ነገር ስለሌለው መብራቶቹ በርተዋል። ፊት ለፊት የሚታይ ትልቅ የጽሕፈት ጠረጴዛ ኋላ ምቹ የቆዳ ወንበር ላይ የተቀመጠውን አዛውንት ሰው ዶክተር ሥራው አስታወሱትና ፈገግ አሉ። "ፕፎሬሰር ሳብራይ! ሰላም አልሃለሁ።"

"ሻሎም ወዳጀ ዶክተር ሥራው!" አሉና አዛውንቱ ከመቀመጫቸው ተነስተው የዶክተር ሥራውን እጅ በመጨበጥ ደጋግመው ወዘወዙት። "ዶክተር ሥራው። በመምጣትህ ተደስቻለሁ። ግን የረባ ረፍት እንኳ ሳታገኝ እዚህ ድረስ ስላደከምንህ ይቅርታህን አለምናለሁ። እባክህን ተቀመጥ!"

ሁለቱም ወንበራቸውን ከያዙ በኋላ አይሁዳዊው ፕሮፌሰርና የሞላድ ባልደረባ እስካሁን ወደ ቆመችው ሴት ቀና አሉ። "ዳፍኔ! እባክሽን ዶክተሩ ቡና ይወዳል። ቀዝቀዝ መጠጥም ብታመጭልን!" አላት። ተመልሳ ወጣች። ነገር ግን ዶክተሩን ያስገረመው ለመውጣትም በመታወቂያዋ መጠቀሟ ነው።

"ከነበረብኝ የሥራ ብዛት አንፃር ወደ ቱል አቪቭ ለመምጣት ዘግይቻለሁ።" አሉ ዶክተር ሥራው።

"አምን አውቃለሁ ወዳጄ። ለመሆኑ ጥረትህ ተሳካ?"

"የተቻለኝን ያህል ሞክሪያለሁ። መቼም ጥያቄያችሁ ማለቂያ የለውምና ሁሉንም ማሳካት አይቻልም። ለማንኛውም ዋናውን ባይሆንም ኮፒውን አግኝቻለሁ።"

"መልካም ነው ወዳጄ" አሉ ፕሮፌሰር ሳብራይ። "እባክህን ልየው!"

ዶክተር ሥራው ሳምሶናይት ቦርሳውን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጠው ቁጥሮቹን እያዞሩ ከፈቱት። ሽማግሌው ሳብራይ ወደ ፊት ሰገግ ብለው ተመለከቱ። ዶክተር ሥራው በሁለት እጃቸው አንድ ዳጎስ ያለ የብራና መጽሐፍ አወጡና ፊቱን (አርእስቱን) ወደ ሳብራይ አዙረው አስቀመጡለት።

አይሁዳዊው ምሁር የንባብ መነጽራቸውን የአፍንጫቸው ጠርዝ ላይ ካስተካከሉ በኋላ . . . "አምን!" አሉ በጠራ የዐማርኛ ቋንቋ። "ይህ ብራና ዕድሜው ለጋ ነው።" እያሉ ብራናውን በትካዜ ሲዳስሱ ከቆዩ በኋላ "መጽሐፈ አስማት" አሉ።

"አምን መጽሐፈ አስማት ነው።" አሉ ዶክተር ሥራው። ይህ መጽሐፍ በ1520 ዓ.ም አካባቢ ነው ከዐረብኛ ወደ ግዕዝ የተተረጐመው። በ1860 ዓ.ም በአፄ ቴዎድሮስ ትዕዛዝ በደቡብ ጎንደር አስቱ የተባለች ቀበሌ ውስጥ ሁለተኛ ኮፒ እንዲገለበጥ ባዘዙት መሠረት የተፃፈ የዋናው ቅጂ ሲሆን አሪጂናሉ ባሁኑ ጊዜ ብሔራዊ ቤተ—መጽሐፍት ቤቶታችን ውስጥ በጥብቅ ይጠበቃል።"

"አውቃለሁ!" አሉ ሽማግሌው ፕሮፌሰር ሳብራይ። ለማንኛውም የጠየከው ዋጋ እጅግ ውድ መሆኑን የአንቲኩዊቲ ሚንስትራችን ነግሮኛል። ካንተ ጋር በሳንቲም መደራደር ቀላል አይደለም። አንተኮ ከነገደ ይሁዳ የባስክ ገብጋባ ነህ!" ዶክተር ሥራው ከልባቸው ሳቁ። ዶክተር ሥራው የሳብራይ የዐማርኛና የግዕዝ ቋንቋ ክህሎት ያስደንቃቸዋል።

"ምን ይደረግ ብለህ ነው። ይህ እኮ ከሼልፍ ላይ ብድግ አድርጌ የማመጣው የሊዮንዮሪስ ወይም የሲድኒ ሼልደን ልቦለድ አይደለም። የቦሌን ኤርፖርት ለማሳለፍ እንኳ አያሌ 'ፎርቹን' ከኪሴ መክፈል ነበረብኝ።"

"አውቃለሁ። ይገባኛል። ለማንኛውም የጠየቀውን ክፍያ ታገኛለህ ብዬ አምናለሁ። ግን ለ24 ሰዓት ያህል መጠበቅ ሊኖርብህ ነው። ለኦፕንቲኬሽን ምርመራ።"

ምዕራፍ ሃያ አራት

ሳምሶን "የተባበሩት መንግሥታት" ወይንም "UN" የሚል የሐሰት ሠሌዳና ጽሑፍ በተለጠፈበት ቶዮታ ላንድ ክሩዘር የጦር መሣሪያዎቹን ሞኖ አዲስ አበባ ከተማ ኮተቤ አካባቢ የተከራዩት ባለ ትልቅ ግቢ ቤት ካራገፈ በኋላ የመጀመሪያውና ጊዜ የማይሰጥ ተግባሩ የመኪናውን ድራሽ ከታሪክ ማሕደር መፋቅ ነበር።

ይህም ብዙ አስቸጋሪ አልነበረም። የመኪና "አራጆች" ባንዲት ጀምበር በታትነው የመሰዋወጫ ዕቃዎች መደርደሪያቸው ላይ ሰቀሉት። የቀረው የመኪናው የራዲዮ መገናኛ አንቴና ብቻ ነው። አራጆቹ ሊጠቅማቸው ወይንም ሊሸጡት ስለማይችሉ ሳይወስዱት ቀሩ። ያንቴናው ድራሽ አለመጥፋት ያሳሰባት ራሄል ከሳምሶን ጋር ክራር አተካራ ተያያዘች። "ጥቃቅን ስህተቶች ናቸው ታላላቅ ዘመቻዎችን የሚያከሳሹት!" ትላለች።

**********//////////**********

ግቢው ለልምምዱ ከፍተኛ አመቺነቱን አስመስክሯል። ኤግዚቢሽኑ የሚደረግበት ት/ቤትና ዙሪያ ገባው ሁሉ በአሸዋ ገበታ ተገንብቷል። የቅርሳችን ይጠበቅ ማሕበር አባላት ያፌት፣ ያሬድ፣ ሳምሶን፣ ዮዲትና ራሄል እንዲሁም ድጋፋቸውን ለመስጠት የተቀላቀሉት አራት ቤተ እስራኤላውያን ልምምዳቸውን ጀምረዋል። ቤተ—እሥራኤሎቹን ከቅርሳችን ይጠበቅ ማህበር አባላት ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋወቀችውና ያቀላቀለችው ዮዲት ናት።

"ሁላችሁም እንደምታውቁት በ1980ዎቹ ዓመታት መጀመሪያ አካባቢ ወደ አሥራ ስድስት ሺህ አካባቢ የሚገመቱ ቤተ—እስራኤላውያን ግዙፍ እና ምስጢራዊ በሆነ በአየር የማጓጓዝ ዘመቻ ወደ "ተስፋይቱ ምድራቸው" ተጓጉዘዋል። እኔም ከእነዚህ ተጓዦች አንዷ ነበርኩ። ዛሬም ድረስ ቤተ እስራኤሎችን ወደ ሀገራቸው እስራኤል የማፍለሱ ተግባር በአፈለል ቢቀጥልም ኢትዮጵያ ውስጥ የቀሩ ቤተ እስራኤሎችን ለመርዳት መንግሥታዊ ያልሆነ ግብረ ሰናይ ድርጅት መሥርተውና ጽሕፈት ቤቱን አዲስ አበባ ከፍተው . . . "

"የኤሌመንታሪ ትምህርት ቤት ታሪክ አስተማሪ መሰልሽ እኮ! ቁም ነገሩን ብቻ ተናገሪ!" ሲል ጌዲዮን አቋረጣት። ሁሉም ሳቁባት። "ኡፍ! አፍህን ዝጋ!" አለች ዮዲት ተናዳ።

"1ኛ፣ ጌዲዮን ታፈረ 2ኛ፣ ኤፍሬም ታፈረ (ወንድማማቾች) 3ኛ፣ ቢኒያም አየለ እና 4ኛ፣ እሸቱ ካሳ ዘመቻ መቅደላን በሕይወታቸውም ቢሆን ለማላክት ድግፋቸውን ሊሰጡን ከጎናችን ተሠልፈዋል!"

እያንዳንዳቸው ስማቸው ሲጠራ ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ ሠላምታ ሰጡ። ትውውቁ እንደተፈፀመ "እነዚህ ቤተ-እስራኤላዊያን ዛሬም ቢሆን "ማርጉርጉርነታቸውን" መቀየር ስላልቻሉ ነው ቅርሶቻችንን ወይንም ቅርሶቻቸውን ለማስመለስ ከጎናችን የተሠለፉት!" አለች ዮዲት ። ሁሉም በፈገግታ ተሞልተው ድምፅ የለሽ ጭብጨባ አወረዱ። ትውውቁ በዚህ መልኩ ተጠናቀቀ።

ቤተ-እስራኤሎቹ ወይንም ቱል-እቬቭ ከዘመቻ መቅደላ ትሩፋት ስለ ጠየቁት የብራና ክፍያ ግን ምንም ላይነሳ ቀረ።

አራቱ ቤተ—እስራኤላውያን ሀገራቸው ከፍተኛ ወታደራዊ ሥልጠና ሰጥታቸው በብሔራዊ ውትድርና አገልግለዋታል። ያፌት እና ላምሶን የተባ ወታደራዊ ክህሎት ያካበቱና በጦር ሜዳም ተፈትነው የቆሰሉ ወታደሮች ናቸው። የነዚህ ሰዎች ወታደራዊና ምሁራዊ ብቃት ደግሞ ምንም ዐይነት ወታደራዊ ሥልጠና የሌላቸው ያሬድና ራሄልን በቀላሉ ወታደራዊ ሙያን ለማስጨበጥ አስችሏቸዋል።

የአሸዋ ገበታው ዙሪያ ቆመው ዕቅዶችን ያጠናሉ። ድምፅ የለሽ (የማስመሰያ) የመሣሪያ ተኩስና ንቅናቄ ይለማመዳሉ። በዚህ መልኩ ቀኑን ሙሉ የጋራ ልምምዶችን ያደርጉና ከጥቂት ሰዓታት ረፍት በኋላ እንደ ገና የጨለማ ልምምዳቸውን ያካሂዳሉ። መግባባቱና መቀራረቡ የጋለ ነበር። ምግባቸውንም ተራ ገብተው እያበሰሉ ይመገባሉ። የመጨረሻው አስደሳችና አስከፊ ቀልድ የሚጀመረው ከእኩለ ሌሊት በኋላ ነበር።

"ያፌት እዚህ ተኛ!

"ዮዲት እዚህ ክፍል ግቢ!"

በያሬድና ራሄልም ተረቡ ይግላል። ከብሽሽቁ በኋላ ግን ወንዶችና ሴቶች በተለያዩ ክፍሎች ውስጥ ለሽ ብለው የድካም እንቅልፋቸውን ይለጥጣሉ።

ከሁለት ሣምንት ልምምድ በኋላ አራቱ ቤተ እሥራኤላውያን መበየጃ ማሽን፣ ቀለም መቀቢያ ማሽን (ኮምፕሬሰር)፣ አንድ ሚኒሻን ተሽከርካሪ ወደ ግቢው አምጥተው

የራሳቸውን ዝግጅት ጀመሩ። የቅርሳችን ይጠበቅ ማሕበር አባላት ስለ ተሸከርካሪዎቹ ምንጭ ምንም ነገር ሳይጠይቁ ቀሩ።

**********////////**********

ክብዙ ንትርክና ጭቅጭቅ በኋላ ሳምሶን መቅደላዊትን እንዲያያት በአብዛኛ ድምጽ ተወሰነለት። "እናንተ እንደምታስቡት አይደለም። እኔ ፕሮፌሽናል ለሆነ ጉዳይ ነው የምፈልጋት!" ሲል የዘመቻ መቅደላ አባላት በከፍተኛ የሳቅ ፍንዳታ ግቢውን ደበላለቁት።

ሳምሶን በሽቆና ተቆጥቶ የኮንትራት ታክሲ ፍለጋ ከግቢው ወጣ።

**********////////**********

ሳምሶን ቢሮውን ከፍቶ ሲገባ መቅደላዊት ሳታው ቀው ጮሃ ከወንበሯ ዘላ ተነሳችና ጠመጠመችበት።

"አንተ... የት ነው የጠፋኸው?"

"ፊልድ ወጥቼ!" አላት እርሱም አቅፎ ከሰማት በኋላ።

"ሌባ! እኔ የማላውቀው ፊልድ አለ እንዴ?"

"ይጠፋል ብለሽ ነው? ይልቅስ ዶክተር አሉ? ሠላም ልበላቸው።"

"ዶክተር ሥራው የለም፣ አሁን ወጡ።"

"መቅዲ! በጣም አምረሻል፣ ናፍቀሽኛል። አሁን የሥራ ሰዓት አብቅቷል፣ እንውጣና ጥሩ ራት ልጋብዝሽ።" አላት።

መቅደላዊት ቀና ብላ የግድግዳ ሰዓቱን ተመለከተችው። እጇ ላይ ምን ጊዜም ሰዓት ባይለያትም አሷ መቁጠር የምትወደው በግድግዳው ሰዓት ነው። የሰዓቱ ባክ ግራውንድ ስዕል የመቅደላው አንበሳ የዓፄ ቴዎድሮስ ምስል ስለሆነ ትወደዋለች።

"እውነትም ሰዓቱ ዐሥራ አንድ ተኩል ይላል።" አለችና ሳታቅማማ ቦርሳዋን ብድግ አደረገች።

**********////////**********

ሳምሶን መቅደላዊትን ለማሸነፍ ውድ፣ ምርጥ ራት እና የወይንጠጅ ብቻ አልነበረም ያስፈለገው። ፊልጋ ተረታችለት ማለቱ ይቀላል። ምክንያቱም አርሷም ፈልጋዋለች። ደጋግማ አስባበታለች። ደጋግማም ራሷን የጠየቀችው ጥያቄም ነው።

'በአርግጥ ሳምሶንን አፈቅረዋለሁ? ወይንስ ከሽማግሌው ዶክተር ማምለጫ ቀዳዳ ነው የምፈልገው?' ስትል ራሷን ደጋግማ ጠይቃለች። በተደጋጋሚ ያገኘችው መልስ ግን ከጥልቁ ልቦናዋ ውስጥ የመነጨ 'ታፈቅረዋለሽ. . . እንዳያመልጥሽ!' የሚል ማስጠንቀቂያ ነበር።

'ፍቅር ደርሶብኛል' የተሰኘውን የቆየ የጥላሁን ገሠሠ ሙዚቃ እያዳመጡ የከያኒውን ድምጽ፣ የሙዚቃ ቅንብሩን፣ የግጥሙን ስሜት ነኪነት በዝምታ ልጓም ሸብቧቸው ሲጓዙ ቆዩና ሙዚቃው ሲያበቃ መቅደላዊት ወደ ሳምሶን ዞረች።

"እንተስ ሁለት ሦስቱ ደርሶብሃል። እኔ ምን ቤት ነኝ?" አለችው። ሳምሶን ዞር ብሎ ሲያያት ዐይኖቿ እንባ አቅርረዋል።

"ፍቅር ተሞክሮ ባይኖረው ጥሩ ነው። ምክንያቱም የመጀመሪያ ፍቅር በየዋሕነት ላይ ተመሠረት ንፁህ ፍቅር ነውና ጣፋጭነቱ የዘለዓለም ነው። ለኔ ሁለተኛዬ ፍቅሬ ስለሆንሽ ምናልባት ሦስተኛና አራተኛም የማፍቀር እደጋ ሊያጋጥመኝ ይችላል።" አላት።

ግልጽነቱ አስገረማት። "የመጀመሪያ ፍቅርህስ"

"ዲቪ የሚሉት ሀገራዊ ሞት ገላገለኝ!"

ደንግጣ ለአፍታ ዝም አለችና "ከራት በኋላ አፈልግሃለሁ" አለችው።

ምግቡ ግሩም ነው። ነጭ ወይን ጠጃቸውን አጋጭተው ጨለጡት። ተሳሳቁ፣ በጠረጴዛው ላይ እጆቻቸውን ተሻሹ፣ ዐይኖቻቸውን አስለመለሙ። በመጨረሻም ወደ ሳምሶን ቤት በረሩ። ሳንድ ክሩዘሩ በዕድሜ ዘመኑ የዛሬውን ያህል የሮጠ አይመስልም ነበር።

**********//////////**********

አንድ ቶዮታ ቫን የኪራይ ግቢው ውስጥ አስገብተው ሥራቸውን ጀመሩ። አራቱ ቤተ— አስራኤላውያን ለኦፐሬሽን መቅደላ ስኬት እጅግ አስፈላጊ ነው ያሉት እና ከፍተኛ ገንዘብ የወጣበት ዝግጅት ነበረ።

የመኪኖቹ ሠሌዳና መብራቶች እንዲሁም የበር እጀታዎች በወረቀት ተሸፈኑ። የመበየጃ፣ የመቁረጫና የመቀቢያ መሣሪያዎች ሁሉ ቀርበው ግራና ቀኝ በመወደሪያ

(ስታንድ) የቆሙ ሁለት መብራቶች ፏ! ብለው በሩ። እናም መኪናውን ዚግዛጉን የማስቀየር ሥራ ተጀመረ።

**********////////**********

"ደክመሽ?" አላት መቅደላዊትን ከፍቅር ሥራ በኋላ።

"አልደክመኝም" አለችው ጠንካራና ጥይት የበሳሳው ደረቱ ላይ ተለጥፋ። እያንዳንዱን ጠባሳ በጣቶቿ እያሸች "ምንድን ነው? የት ነው የተመታህው?" እያለች ትጠይቀዋለች። በትዕግስት ይመልስላታል። "የፍልሚያ ጠባሳ ደስ ይላል" አለችው።

"ቢልም ባይልም ያለኝ ሀብት ጠባሳ ብቻ ነው" አላት።

"ያደለው ዓለምን እየዞረ በሀብት ላይ ሀብት ያካብታል። አንተ ግን ኢትዮጵያን እየዞርክ ጠባሳ ታከማቻለህ።"

"ማነው ዓለምን ዞሮ የበለፀገው?" አላት እየሳቀና እቅፍ አድርጎ እየሳማት።

"ዶክተር ሥራው።"

"እንዴት?"

"ዶክተር ሥራው ለገንዘብ ጥቅም ብዬ ያቀረብኩት ይመስለዋል። ግን እኔም የ"ዘመቻ መቅደላ" አባል መሆኔን ስለማያውቅ ገላዬን መስዋዕት አድርጌ ድርጊቱን ሁሉ መሰለል ጀመርኩ።"

"አውቃለሁ። ታዲያ ምን ዐዲስ ነገር አገኘሽ?" አለ ሳምሶን።

"ከቅርቡ እንኳ ወደ እሥራኤል . . ." ተረከችለት።

**********////////**********

ሳምሶን በማግስቱ ወደ ካምፕ ሲመለስ ዐይኖቹን ማመን አቃተው። ግቢው ጋራዥ መስሏል። ለሁሉም ሠላምታ አቅርቦ የቡድኑ ኮማንደር የሆነው ያፈትን ወደ ጎን ወሰደውና በምስጢር ያነጋግረው ጀመረ። ሁሉም ሥራውን እየሠራ ወደ ያፈትና ሳምሶን ይመለከታል። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አንድ ዐይነት መግባባት ላይ የደረሱ መሰሉ።

"ኢመርጅንሲ! አስቸኳይ ስብሰባ ሁላችሁም ወደ ቤት!" አለ ያፈት።

ምዕራፍ ሃያ አምስት

እነ ጌዲዮን የመጨረሻ የእጅ ሥራ ውጤታቸውን እየተመለከቱ ነው። ቶዮታ ሚኒ ቫኑ የተሟላ የማስመለያ ለውጥ ተደርጎበታል። 'ማዕከላዊ ፖሊስ' የሚል ጽሑፍ በጉልህ ለማያዊ ቀለም ተጽፎበታል። ሐሰተኛ የፖሊስ ታርጋ ተለጥፎበታል። መስታወት የሌለው አካሉ ውስጡን አያሳይም። የቀኝ በሩ ተንሸራታች ሲሆን ቅባት ጠግቦ በፍጥነት ይከፈታል፣ ይዘጋል።

የጋቢናው ወንበር አንድ ወጥ ሆኗል። ከአሽከርካሪው ሌላ ሁለት ሰዎችን ያስቀምጣል። ከጋቢናው ወንበር በስተኋላ ወለሉ ላይ 360 ዲግሪ የሚዞር መቆሚያ ተበይዶበታል። አንድ ሰው እዚህ ተሽከርካሪ ላይ ቆሞ በጣራው የፀሐይ መስኮት በኩል ብቅ በማለት 360 ዲግሪ እየዞረ መሣሪያ መተኮስ የሚያስችል መቆሚያ ነው። ሚኒ ቫኑ ውስጥ የነበሩት ወንበሮች በሙሉ ተነቃቅለው ተነስተው አሁን አያሌ ፖሊስ ዩኒፎርሞች፣ መለዮዎች፣ ጫማዎች፣ እና ቀበቶዎች እንዲሁም የማዕረግ ምልክቶች በካርቶን ተሞልተው ተቀምጠዋል። ኤፍሬምና ጌዲዮን እያንዳንዷን ጥቃቅን ቴክኒካዊ ለውጥና የማስመለያ ሥራ ከፈተሹ በኋላ የተሟላ ሥራ ለመሆኑ ተስማምተው ሙሉ በሙሉ በሽራ ሽፈኑት።

**********//////////**********

የዘመቻ መቅደላ ተሳታፊዎች አስፈላጊ ወይንም በቂ ነው ያሉትን ልምምድ በሦስተኛ ሳምንታቸው አጠናቀቁ። ይህ ልምምድ ተጀምሮ እስኪያበቃ ድረስ ማንኛውም አባል ከውጭው ዓለም ጋር የስልክ ጥሪ እንዳያደርግ ተከልክሎ ቆይቷል። በዛሬው ቀን ግን እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ጥሪዎች ብቻ እንዲደረጉ ከመፈቀዱም ሌላ አባላቱ ኦፐሬሽን መቅደላን በተመለከተ የመጨረሻውን ውይይት ለማድረግ ስብሰባ ሲቀመጡ ሁሉም ፊታቸው ላይ ይነበብ የነበረው የጉጉት ስሜት እና ያሳዩት የነበረው ሥነ—ምግባር እጅግ የተለየ ነበረ። ይህም ያለምክኒያት ከባሕታዊው ። ቀደም ሲል ራዔል ለአባላቶች ባስተላለፈችው ጥሪ መሠረት የቅርሳችን ይጠበቅ ማሕበር ስብሰባን ለማካሄድና ከሁለት ቀናት በኋላ ስለሚከበረው የአድዋ ድል በዓል አከባበር መግለጫ ለማውጣት በተለያዩ የመጓጓዣ ዘዴዎች ተጠቅመው ወደ ማሕበሩ ጽሕፈት ቤት ሲጓዙ ኤፍሬምና ሳምሶን ብቻ ግቢውን ለመጠበቅ ቀሩ።

የቅርሳችን ይጠበቅ ማሕበር መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት መደበኛ ስብሰባ በዋና ሥራ አስኪያጇ ራሄል ስብሳቢነት እና በድርጅቱ የቅጥር ፀሐፊ በወይዘሪት ሰናይት ቃሰ ጉባኤ ያዝንት ከቀኑ አሥራ ሁለት ሰዓት ተጀምሮ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ ተጠናቀቀ።

የማሕበሩ መሥራች ዶክተር ሥራውብዙ አየለ፣ ነባር እና ታዋቂ ከሆኑት አባሎች ያፈት፣ ያሬድ፣ እና ዮዲት ሲገኙ ማሕበሩን በገንዘብና በዕውቀት በመደገፍ የሚታወቁ ሌሎች ሠላሳ አባላትም ተሳትፈዋል። የዛሬው መደበኛ ስብሰባ ያተኮረበት ብቸኛ አጀንዳ በተለያየ ጊዜና አጋጣሚ ተዘርፈው ካገር የወጡ ቅርሶችን ስለማስመለስ ነው። ለአንድ ሰዓት ያህል ከተወያዩ በኋላ በአድዋ ድል በዓል ዋዜማ ምሽት ለመገናኛ ብዙሃን የሚለቀቅ ድርጅታዊ መግለጫ በማርቀቅ ስብሰባቸውን አበቁ።

"የቅርሳችን ይጠበቅ ማሕበር ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎችና ወቅቶች ተዘርፈው ከሀገራችን የወጡ ቅርሶቻችንን ለማስመለስ ከመንግሥታችን እና ከሌሎችም የሚመለከታቸው ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ተቋአማት ጋር በመተባበር ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ መቆየቱ ይታወቃል። ነገር ግን የጥረታችንን ያህል ተገቢውን ውጤት አግኝተናል ማለት አንችልም።"

ቅርስ በማስመለሱ ዘመቻ ተገኝቷል የምንለው ከፍተኛ አርኪ ውጤት ቢኖር መንግሥት የአክሱም ሐውልትን በማስመለስ ያስገኘው ውጤት ዋነኛው ነው። እስከ ዛሬ በባአዳን እጅ የሚገኙ ቅርሶቻችንን በተመለከተ ...

1. ቅርሶችን የማስመለሱ ጥረት በመንግሥት፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በኢትዮጵያ ወዳጆችና በታዋቂ ዜጎቻችን ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።
2. በውጭ ሃገር ዜጎችና ግለሰቦች እጅ የሚገኙ ቅርሶቻችንን በግዢ ለማስመለስ እንድንችል ማንኛውም የንግድ ተቋም፣ ባለ ሐብትና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ድርጅታችንን በገንዘብ እንዲረዳ ጥሪ እናደርጋለን።
3. ቅርሶቻችንን ሰርቀው በሚሸጡ ዜጎችና በድብቅ ከሃገራችን ለማውጣት በሚሞክሩ የውጭ ሀገር ዜጎች ላይ የሚጣለው ቅጣት ተሻሽሎ ከባድ የቅጣት ሕግ መደንገግ አስፈላጊ ስለሆነ በሕዝብ እንደራሴዎች በኩል ለምክር

ቤቱ ሐሳብ ማቅረብና ግፊት የማድረግ እንዲሁም የማግባባት ሥራ እንዲጀመር።

4. ሕዝባችን በተለይም ወጣቱ ትውልድ ታሪካዊ ቅርሶቹ የማንነቱ መለያ 'አሻራ' መሆናቸውን ተረድቶ እንዲንከባከባቸውና ለሚቀጥለው ትውልድ እንዲተላለፉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት። ይህን ኃላፊነት ሊያስገነዝብ የሚችል የትምህርትና የግንዛቤ ማዳበሪያ ጉባኤዎችና ጽሑፎችን ማዘጋጀትና ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችል ፕሮግራም በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት ትብብር እንዲዘጋጅ፤
5. ከትውልድ ወደ ትውልድ፣ በውርስ ተላልፈው በኢትዮጵያውያን ግለሰቦች እጅ የሚገኙ ቅርሶችን በባለቤትነት የያዙ ግለሰቦች በመልካም ፈቃደኛነት እንዲያበረክቱ የሚያስችል ሀገር አቀፍ የምዝገባ፣ የትምህርትና የቅስቀሳ ፕሮግራም እንዲዘጋጅ።

ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ላይ የነዚህ ውሳኔዎች ረቂቁ ተዘጋጅቶ ተጠናቀቀ። መግለጫውን የማሕበሩ ፕሬዝዳንት ዶክተር ሥራውብዙ እና ዋና ሥራ አስኪያጂ ራሄል የማሕበሩ ጽሕፈት ቤት ውስጥ በሚጠሩት ጋዜጣዊ መግለጫ አማካይነት የአድዋ ድል በዓል ዋዜማ ዕለት ይፋ እንዲያደርጉ ተወሰነ።

ምዕራፍ ሃያ ስድስት

ሁሉም እውደ ዓመትና ክብረ በዓላት በሁሉም ሰው ላይ ጥሎት የሚያልፈው የየራሱ ትዝታ አለው። የዘንድሮው የአድዋ ድል በዓለም በብዙ ኢትዮጵያውያን ሕሊና ውስጥ ለረኻም ዘመን የሚታወስባቸውን ሁለት ክስተቶች ጥሎ አለፈ። የመጀመሪያው ክስተት በዓሉ የተከበረው ቅርሶቹን በኃይል የማስመለስ አስደናቂ የአገታና ጠለፋ ተግባር ሊፈፀም ጥቂት ቀናት ብቻ ሲቀሩት በመኾኑ ብዙ ኢትዮጵያዊያን "አጥፍ ድል" ሲሉት አንዳንድ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ደግሞ *"ኢትዮጵያውያን የዘንድሮውን የአድዋ ድል በዓላቸውን ካከበሩት በኋላ የተዘረፉባቸውን ታሪካዊ ቅርሶች በኀይል በማስመለስ አንዱንና ታላቁን የድል በዓላቸውን ሁለት አደረጉት!"* እያሉ ዘገቡበት።

በዘንድሮው የአድዋ ድል በዓል ላይ ሁለተኛውን ትዝታ አትመው ያሰፉት ባሕታዊው ናቸው።

ከአፍ እስከ ገደፉ ጢም ብሎ በሕዝብ የተሞላው የአድዋ አደባባይ የተሰበሰበው ሕዝብ ክብረ በዓሉ ከተፈፀመ በኋላ እንደ ወትሮው ወዲያውኑ አልተበተነም። ላለ መበተኑ ምክንያት የኾነውም ለሕዝቡ የታደለች አነስተኛ ፓምፍሌት (በራሪ ወረቀት) ነበረች።

"የአድዋ ድል በዓልን ምክንያት በማድረግ በአራዳው ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በሚደረገው ልዩ መንፈሳዊ መልዕክት እና ፀሎት ላይ ይላተፉ!"

**********////////**********

"በስመ-አብ-ወልድ-ወ-መንፈስ ቅዱስ-አሀዱ አምላክ አሜን!" አሉ ባሕታዊው የቤተ ክርስቲያኑ አውደ ምሕረት ላይ ቆመው። በማይክራፎን የጎላው አስገምጋሚው ድምጻቸው በሕዝብ የተጥለቀለቀው አደባባይ ላይ እንደ ገደል ማሚቶ ያስተጋባል።

"እናንት ኢትዮጵያዊያን ወገኖቼ! በሀገራችሁም ሽነ በባዕዳን ምድር ላይ ቆማችሁ ታላቁን የአድዋ በዓል ስታስቡ አንድ የጎደለ ነገር መኖሩን አስታውሱ። ነፃነታችን ባይዘረፍም፣ ነፃነታችን ባይደፈርም የታሪክ፣ የአምነትና የማንነታችን አሻራ የሽኑ ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ቅርሶቻችን በተለያዩ ዘመናትና አጋጣሚዎች እየተዘረፉ ተግዘው በባዕዳን እጆች ወድቀዋል። ከዓፄ ቴዎድሮስ ሕልፈተ ሕይወት በኋላ በዙፋን የተቀመጡት ንጉሠ ነገሥት አፄ ዮሐንስ ለንግሥት ቪክቶሪያ "ከመቅደላ አምባ ከተዘረፉ

ቅርሶቻችን ውስጥ ‘ኩር ርእተ ርዕሱ’ የተባለው የክርስቶስን ስቅለት የሚያሳየው የተቀደሰ ስዕል ታገሬ በመጉደሉ ይህ ነው የማይባል ተፋልሶና ብጥብጥ ገጥሞናልና ሀገሬ ትረጋጋ ዘንድ ይህን የተቀደሰ ስዕላችንን ይመልሱልን!” ሲሉ በዓፉት ደብዳቤ ቅርሶቻችንን የማስመለስ የመጀመሪያው ዲፕሎሲያዊ ዘመቻና ትግል ተብሎ ይታወቃል። ደብዳቤያቸውም በዩኔስኮ “ያለም ሕዝብ ቅርስ” ተብሎ ተመዘግቧል። ባጼ ዮሐንስ የተጀመረው የመቅደላን ቅርሶች የማስመለስ ጥረት በኢትዮጵያውያን፣ በዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ ወዳጆቻችን እና በመንግሥትም ተጠናክሮ ይቀጥል!”

“ይቀጥል!!!” አራዳ ተናወጠ።

“ሕሮጌ ጨርቅ ከዚህ ሲጠቅሙት ከዚያ ይተረተራል እንዲሉ አንድ መቶ አርባ ዓመታት ሙሉ ቅርሶቻችንን ይመለሱ! እያለ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲማሰን የሦስት ሚሊዮን ዓመታት እናቱን፣ የኤደን ገነት ሔዋኑን፣ ድንቅነሽን ከመቃብሯ ተዘላለም ቤታ ቀስቅሰው ባሕር ማዶ አሻገሯት።”

ያራዳ ጊዮርጊስና አደባባይ በሃዘኔታ ጉምጉምታና በልቅሶ ናዳ ተናወጠ። ባሕታዊው እንደ ነጎድጓድ በሚያስገመግመው እንደበታቸው ቀጠሉ።

“እናንት ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ከእንግዲህ ወዲያ እንኳንስ አገራዊ በዓላትን ይቅርና የልጆቻችሁን ልደት እንኳ ስታከብሩ ‘አቤቱ ልዑል እግዚአብሔር ኾይ! ታሪካዊ ቅርሶቻችንን እና ድንቅነሽ እናታችንን ወደ ቤታቸው መልስልን!’ እያላችሁ ወልዩ! ለልጆቻችሁ የምታወርሱት ቅርስና የሦስት ሚሊዮን ዓመታት እናታቸው፣ ሔዋናቸው ጎደለዋልና!”

የአራዳ ጊዮርጊስ ቅጥርና የምኒልክ አደባባይ በሕዝባዊ እንባ ታጠበ፣ ራሰ። እንዳውም እንዳንድ የበዓሉ ታዳሚዎች እንዳሉት ከኾነ የአድዋ ድል በዓል እንደ ዘንድሮው ደምቆና ግሎ ተከብሮ አያውቅም ብለዋል።

ባሕታዊው “አሁን ፀሎታችንን አድርሰን እናሳርግ” ብለው የቀኝ እጃቸውን ጣቶች በመስቀል ቅርፅ ቀስረው ብድግ ሲያደርጉ አደባባዩ ዐጥ ረጭ አለ፣ በመቶ ሽህ ወይንም በብዙ ዐሥርተ ሺህ የሚቆጠሩ ራሶች ወደ መሬት አቀረቀሩ።

ፀሎትና ቡራኬው ተፈፅሞ ሕዝቡ በየአቅጣጫው መበትን ሲጀምር የመጀመሪያው ሠልፍ መንፈላዊ ዜማዎችን አያዜመ ተጓዘ። የጎላ ጎላ ግን ማን እንደ ገጠመው የማይታወቅ "ቅርላዊ ሙሾው" አያዜመ ተጓዘ።

ድንቅነሽ እናታችን
የሦስት ሚሊዮን ዓመታት ሐዋናችን
ትመለስልን ወደ ሀገራችን
ላይፈርስ የተፈጥሮ ቤትሽ
ድንቅዬ እናታችን ለምን አሻገሩሽ?
ድንቅነሽ እናታችን
ድንቅነሽ ሐዋናችን
ትመለስ ወደ ኢትዮጵያችን!!!

"ዕልልል! ዕልል!" እያለ፣ መልሱልን እያለ ወደ አሜሪካን ኤምባሲ ተመመ።

በግብጽ ኤምባሲ በኩል ያለፈው የአድዋ በዓል ታዳሚ ደግሞ . . .
እንኪንስ ድንቅ ነሽ እንኪንስ ብራናው

ባዕዳን ቀላቢው አባይም ቅርስ ነው!!! እያለ የግብጦቹን ደጃፍ አናወጠው።

ክፍል 2

ምዕራፍ ሃያ ሰባት

ኮሎኔል ሰናይ እና ሻለቃ ፍቅሩ የምርመራ ቡድኑ በተመሠረተ በሦላሳ ደቂቃ ውስጥ እና ጠለፋው ከተፈፀመ ከአርባ አምስት ደቂቃዎች በኋላ አገታና ጠለፋው የተፈጸመበት ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ደርሰው ከጣላፊዎቹ አፈ ቀላጤ ጋር ተገናኙ።'

ፊቱን አልሸፈነም። ኡዚውን ትከሻው ላይ አንጠልጥሏል። አራት የታጠቁ የፌዴራል ፖሊስ አባላት፣ ቀደም ሲል የተጋፈጡት ሁለት የደህንነት አባላት፣ የልዕልቲቱ አጃቢዎች መሪ የሆነው እንግሊዛዊ እና ሁለቱ ባለሥልጣናት ዙሪያውን ከበውት ቆሙ። እርሱ ግን ፍንክች የሚል ሰው አይመስልም።

"ያፈት አባላለሁ።" አላቸው።

"እኔ ኮሎኔል ሰናይ ነኝ። እርሱ ሻለቃ ፍቅሩ ይባላል። ሁለታችንም የፀረ ሽብር ክፍል ባልደረቦች ነን።"

ያፈት በምፀት ፈገግ አለ። "እ! ፀረ ሽብር። ተጨማሪ ሥራ ፈጠርኩላችኋ!" አላቸው።

ኮሎኔል ሠናይ ፈገግ አሉና ይህን ሥራ ብለህ ከምትፈጥርልን ቦዝነን ብንቀመጥ ይሻል ነበር።" አሉት።

"ፍላጎትዎ እንደዚያ ከሆነ ይህ . . ." ወደ አዳራሹ ዞረና... "ይህ የጠለፋና የአገታ ድራማ በሠላም የሚቋጭበትን መንገድ በጋራ እንፈልግና እንለያይ" አላቸው።

"እንለያይ? ቢያንስ ስድስት ወር እንኳን ሳላስርህ?

"እንዴት ስድስት ወር ብቻ? ያሸባሪነት ቅጣትን የሚቀንስ አዋጅ ወጣ እንዴ?" አላቸው እየሳቀ።

"አልወጣም። እንዳውም ተጠናክሮ ጨምሯል። ነገር ግን አንተና አሸባሪዎችህ ያገታችሁትን ሰው ሁሉ ለቃችሁ እጃችሁን ከሰጣችሁ የማስመሰያ ፍርድ ይፈረድባችሁና ከስድስት ወራት እሥራት በኋላ ትለቀቃላችሁ። ለዚህም መንግሥታዊ ማረጋገጫ አስጥሃለሁ።"

"በዚህች ዓለም ላይ ለዋስትናዬ ማረጋገጫ እየተሰጠኝ መኖር አልሻም። ማረጋገጫ ያሉትን እኔም ሆንኩ ባለዳረቦቼም አንፈልግም። እኛ የምንፈልገው ይህንን ብቻ ነው!" አለና ከማስታወሻ ደብተር ላይ የተገነጠለ ብጣሽ ወረቀት እጃቸው ላይ አስቀመጠላቸው።

ኮሎኔል ሰናይ ወረቀቱን ገለጡና ማንበብ ጀመሩ።

1. ልክ ከቀኑ ሰባት ሰዓት ላይ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ጋዜጠኞች የትምህርት ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዲገኙ፤
2. ከቀኑ ሰባት ሰዓት የምሳ፣ የመጠጥ ውሃ፣ የቡና እና ሌሎችም የታጋቾች የተለያዩ ፍላጎቶች ካሉ አቅርቦት እንዲጀመር። የምሳ አቅርቦት ከጋዜጣዊ መግለጫው በኋላ እንዲሆን። አራት በ12:00 ሰዓት ቁርስ ከጣቱ 1:00 ሰዓት።
3. ሠላሳ የመኝታ ፍራሾችና ሠላሳ የመኝታ ከረጢቶች ከምሳ በኋላ እንዲቀርቡ፤
4. ካሁኗ ደቂቃ እንስቶ አንድም የፀጥታ ሠራተኛ ወይንም ባልደረባ የትምሕርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዳይገኝ።
5. እኛን ለማነጋገር የሚፈልግ ባለ ሥልጣን የአዳራሹ ቢሮ ውስጥ ባለው መደበኛ ስልክ ብቻ እንዲጠቀም።

"በቃ ይሄው ነው?" አሉ ኮሎኔሉ ማስታወሻውን አንብበው ቀና አሉና።

"ዋናውን ፍላጎታችን ከጋዜጣዊ መግለጫው በኋላ እሰጥዎታለሁ። ላሁኑ ግን እዚህ ድረስ ደክመው ስላነጋገሩኝ በጣም አመሰግናለሁ።" ብሏቸው ፊቱን ወደ አዳራሹ ሲመልስ . . . "እንዴ ቆይ" አሉት።

"አቤት!"

"ልዕልቲቱ፣ አምባሳደሩና ሚኒስትራችን ላይ አንዳችም አደጋ እንዳይደርስ አስብበት።"

"እርስዎም የኛን ደህንነት አስቡበት" አላቸው። እጅግ ተከሳትሮ።

ኮሎኔሉ በእርጋታ ተመለከቱት። 'ይህ ሰው በጣም ፕሮፌሽናል፣ የቆረጠም ይመስላል።'

"ምናልባት . . ." አሉ ሻለቃ ፍቅሩ..... "የተነሳችሁበት ጉዳይ ከቅርሶቹ ጋር የተያያዘ ከሆነ የተከበሩ እንግዶቻችንን ማጉት አያፈልጋችሁም። ቅርሶቹ ብቻቸውን

ሆስቱጅ (መያዣ) መሆን ይችላሉና። ታጋቾችን ካሁኑ ብትለቱ ጥፋታችሁን ያቀለዋል። የሚዲያውን ትኩረት ለመሳብ ከሆነም አሁን የመላው ዓለም ትኩረት በናንተ ዜና ላይ ነው።" አሉት።

ያፈት ረዘም ላሉ ሴኮንዶች በዝምታ ሲመለከታቸው ቆየና "በእርግጥ ግምትዎ ሁሉ ትክክል ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ግባችንን ለመምታት ሆስቴጆቹ ያስፈልጉናል። አሁን . . ." አሰና ያፈት ፊቱን በፈገታ ሞልቶ "..... ሰዓቱ እየገፋ ነውና ወደ ምሳ ዝግጅት ብትሄዱ ጥሩ ነው!" ብሏቸው ትክሻው ላይ በማንገቻ ያንጠለጠለውን ኡዚ እያወዛወዘ ወደ አዳራሹ አመራ።

ኮሎኔል ሰናይን እና ሻለቃ ፍትሩን አጅበው የመጡት ፖሊሶች በሙሉ ጣታቸውን ቃታ ላይ አሳርፈው ወደ ኮሎኔሉ ተመለከቱ። ኮሎኔሉ ግን የሞባይል ስልካቸውን ከኪሳቸው እያወጡ አንገታቸውን በአሉታ በመወዝወዝ የፖሊሶቹን ጥያቄ አገዱ።

በመጡበት ላንድ ክሩዘር ተሳፍረው ከግቢው ሲወጡ ሻለቃ ፍትሩ በያዙት የእጅ ራዲዮ፣ ኮሎኔል ሰናይ ደግሞ በሞባይላቸው ግንኙነት ጀምረዋል።

"የአምባሳደሩን ፀሐፊ ወይንም የኤምባሲውን ሁለተኛ ሰው ባስቸኳይ ማነጋገር እፈልጋለሁ።" አሉ በጠራ እንግሊዘኛ።

"ኮሎኔል ሰናይ ከሀገር ውስጥ ሴኩሪቲ!"

በአምስት ሴኮንዶች ውስጥ መልስ አገኙ።

"ሄሉ ሚስተር ስሚት አባላለሁ። የኤምባሲው አንደኛ ፀሐፊ ነኝ። ምን ልርዳዎት?"

"የምስጥህን ቃል በትክክል በሥራ አንድታውለው።" የተከበሩ እንግዳችንን እና አምባሳደራችሁን ያገቱትን ሰዎች አነጋግሪያለሁ። የመጀመሪያው ጥያቄያቸው የምሳ የራትና የቁርስ ጥያቄ ነው። ምሳ ዛሬ በናንተ አቆጣጠር ከቀኑ 6:00 ራት በ12:00 ሰዓት ቁርስ ከጧቱ 7:00 ሰዓት። የታሸጉ የመጠጥ ውሃዎች፣ ቡና እና ሀላል የመኝታ ከረጢቶች እንዲሁም ሀላል የመኝታ ፍራሾች። እየሰማኸኝ ነው?"

"አዎን ጌታዬ?"

"ማስታወሻ እየያዝክ ነው?"

"እምን ጌታዬ!"

"ይህን ጥያቄያቸውን ወደ ኤምባሲያችሁ ያመጣሁት በሌሎች ችግሮች ላይሆን የተከበሩ ታላላቅ ዜጎቻችሁን የምገብ ፍላጎት ከማወቃችሁም በላይ ከኛ ይልቅ ኤምባሲያቸው ያዘጋጀላቸውን ምግብ በጥሩ እምነት ይመገባሉ ብዬ ስላሰብኩ ነው።"

"ትክክል ነዎት ጌታዬ። ፍራሽና የመኝታ ከረጢትን በተመለከተ ማድረግ የምችለውን አያለሁ። ለመሆኑ የስንት ሰው ምግብ ነው የምናቀርበው?"

"የሠላሳ።"

"ተቀብያለሁ!"

"አመሰግናለሁ!" አሉና ኮሎኔሉ ሌላ ስልክ መደወል ጀመሩ።

ሻለቃ ፍቅሩም የራዲዮ ግንኙነታቸውን ቀጥለዋል።

"የቡድን አባት ! ትሰማኛለህ?"

"ስድስቱም ቡድን የመገናኛና ራዲዮ መጠቀም ጀምሯል?"

"እምን ጌታዬ።"

"ተለዋጭ ኮዶች ተዘጋጅተዋል?"

"እምን ጌታዬ።"

"ውጭ!"

የመገናኛ ራዲዮናቸውን ኪሳቸው ከተው በሞባይል መደወል ጀመሩ።

"ሃሎ! ኢንስፔክተር። ግቢውን የከበቡት የጸጥታ ኃይሎች በሙሉ ከዙሪያው እንዲርቁና በስውር የደፈጣ ከበባ ብቻ እንዲያደርጉ እዘዝ። ከትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ጀምሮ እስከ 200 ሜትር ርቀት በሁሉም አቅጣጫ ወደ ትምህርት ቤቱ የሚወስዱ መንገዶች አሁኑኑ እንዲዘጉ። ማንም፣ ከተፈቀደለት ሰውና ተሽከርካሪ በስተቀር እንዳያልፍ።"

"ተቀብያለሁ" አሉ ከትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውጭ የነበረውን እንቅስቃሴ ይመራ የነበረው ኢንስፔክተር።

የሚጓዙበት መኪና መስፍን ሐረር መንገድን ተያይዞታል።

"ሃሎ! ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር።"

"እምን አነጋግሪያቸው ወጣሁ።"

"ጊዜያዊ ጥያቄ ነው። ለሠላሳ ሰዎች የምግብ የመጠጥና የመኝታ አቅርቦት። የምግቡን እና የመኝታ ጥያቄን ወደ ኤምባሲው አሳልፌያለሁ።"

"አይደለም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር። ልዕልቲቱ ከአምባሳደሩና ከቅርሶቹ ጋር የመጡት እንግሊዞች ቢያንስ የኤምባሲያቸውን ምግብ በተሻለ እምነት ይቀበላሉ ብዬ ስላሰብኩ ነው።"

ኮሎኔል ሰናይ ይህን ሲናገሩ የደሕንነት መሥሪያ ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ደርሰው ከመኪና ወርደው ወደ ቢሮአቸው እየተራመዱ ነበር። ሻለቃ ፍቅሩ ተነጥሰው ወደ ግምጃ ቤት አመሩ።

"እሺ! ፍራሹን ከራሳችን ግምጃ ቤት አወጣለሁ።"

"አዎን ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር። ይገባል የተባለውን የእንግሊዝ ምርመራ ቡድን የሚቀበልና ሊያዝን (አገናኝ) ሆኖ የሚሠራ ምክትሌን መድቤያለሁ። "

"እስካሁን የጠላፊዎቹን መሪ ብቻ ነው ያነጋገርኩት።"

"እሺ ሪፖርት አደርጋለሁ።"

ኮሎኔል ሰናይ ስልኩን ዘጉና ቢሮአቸው ገብተው የጠረጴዛውን ስልክ አነሱ። ሻለቃ ፍቅሩ ደግሞ ሌላ የመገናኛ ራዲዮ ኪሳቸው ጨምረው ወደ ኮሎኔል ሰናይ ቢሮ ገቡ።

ምዕራፍ ሃያ ስምንት

የጠለፋው ዜና እንደተሰማ የመላው ዓለም መገናኛ ብዙሃን ሁሉ አየተቀባበሉ ከአጥናፍ አጥናፍ አስተጋቡት። ዜናውን የሰሙ መንግሥታትም የተለያየ አቋም ያዙ። ከነዚህ ውስጥ የአውሮፓ ሕብረት፣ አሜሪካና እስራኤል ድርጊቱን በአሸባሪነት ለመፈረጅ ጊዜ አልወሰደባቸውም።

እንደ ተፈጥሮና ቅርስ ጥበቃ የመሳሰሉና መንግሥታዊ ያልሆኑ አንዳንድ ተቋማት ደግሞ "ድሮም ተናግረናል፣ ብለን ነበር. . . ." የመሳሰሉ ድምፀቶች ያላቸውን መግለጫዎች በመስጠት "የቅኝ ገዢዎች የቆየ ተንኮል የፈጠረው አገታ!" ሲሉ ተሳለቁ። "ቅርሳችንን መልሱልን! ለሚለው የተዘረፉ ሕዝቦች አቤቱታና ጩኸት አምነታዊ ምላሽ ሰጥተው ቢሆን ኖሮ ይህ አገታ ባልተፈፀመ ነበር።"

"ለመሆኑ ጠለፋው ከቅርሶቹ ጋር የተያያዘ ነው ትላላችሁ?" ተብለው ሲጠየቁ . . ." ሁኔታዎች የሚያመላክቱቱ እንደሱ ነው። ለማንኛውም ዛሬ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር እኩለ ቀን ላይ ወይንም በ10.00 ጂ.ኤም.ቲ. የጠለፋውን ምክንያት ከጠላፊዎቹ እንሰማለን።" የሚል መልስ ይሰጣሉ።

ከአሜሪካ መንግሥት የተሰጠው ፈጣን መግለጫ . . .

"ከመስከረም 11-2001 ዓ.ም ጥቃትና አልቂት በኋላ ሌላው ክባድ የአሸባሪነት ተግባር የአዲስ አበባው ጠለፋ ነው። እነዚህ አሸባሪዎች የተከበረችውን ልዕልት፣ ሚንስትሩን እና አምባሳደሩን ጨምሮ ያገቷቸውን ሰዎች ባስቸኳይ ለቀው እጃቸውን ካልሰጡ አስከፊ ውጤት ይኖረዋል። የኢትዮጵያ መንግሥት ያገሩን ጸጥታ ከአሸባሪዎች ለመከላከል በሚያደርገው ጥረትና አሁን የደረሰውን ያሸባሪዎች አገታ ለማክሸፍ በሚያደርገው ጥረት ሁሉ በሙሉ ኃይላችን ከጎኑ እንደምንሰለፍ እናረጋግጣለን።" የሚል መንግሥታዊ መግለጫ ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ይፋ ሆነ።

እንደ ቢ.ቢ.ሲ. ፣ ቪ.ኦ.ኤ. እና ሲ.ኤን.ኤን. የመሳሰሉት ታላላቅ የሚዲያ ተቋማትም የፖለቲካ ተንታኞችን፣ የሽብርተኝነት ኤክስፐርቶችን እና የቅርስ ጥናት ባለሞያዎችን በመጋበዝ በታለ መጠይቅ ላይ የተመሠረቱ ዘገባዎችን በማሠራጨት ተጠመዱ። በተለይም የእንግሊዝ የዜና አውታር ቢ.ቢ.ሲ. ታለ መጠይቅ ካደረገላቸው

ታዋቂ ምሁራን ውስጥ የኤደንብራ ዩኒቨርሲቲው ፕሮፌሰር ዴቪድ ኪምበርሊ አንዱ ናቸው.... ::

ቢ.ቢ.ሲ፡ "ሚስተር ኪምበርሊ:: የዊንድሶር ልዕልት ኢዛቤል አዲስ አበባ ውስጥ ታግተዋል:: በእንግሊዝ መንግሥት ከአንድ መቶ አርባ ዓመታት በፊት የተዘረፉ ቅርሶ በውሰት ወደ አዲስ አበባ ተልከው በጠላፊዎቹ እጅ ተይዘዋል:: አንድ ቡድን ወይንም ግለሰብ የተዘረፈውን ታሪካዊ ቅርሱን መልሶ ቢቀማ ወንጀል ነው ይላሉ?

ኪምበርሊ፡ "ይህ እንደ ተርጓሚው ይለያያል:: የለንደን ከተማን የፖሊስ ኢንስፔክተር ወይንም ፖለቲከኛ ብትጠይቃቸው ወንጀል ነው ሊሉህ ይችላሉ:: ምክንያቱም ቅድመ አያቶቹ ከአንዲት ጌላ ቀር እና ደካማ ሀገር የዘረፉትን ንብረት ተቀምቷልና:: እኔን ከጠየክኝ መልሱ "ወንጀል አይደለም!" የሚል ነው::"

ቢ.ቢ.ሲ፡ "እንዴት?"

ኪምበርሊ፡ "የኢትዮጵያ ወዳጅና የቅርስ ማስመለስ ጥረታቸው ደጋፊ የሆንን የታሪክና የቅርሳ ቅርስ ምሁራን በቅኝ ግዛት ዘመን ከኢትዮጵያ የዘረፍናቸውን ቅርሶች እንመልስላቸው የሚል ከፍተኛ ዘመቻና ቅስቀሳ ስናደርግ ሰንብተናል:: ሆኖም ግን አልተሳካልንም:: ቅርሶቹን ለባለቤቶቹ ሕዝቦች ከመመለስ ይልቅ "እናውሳችሁና በኤግዚቢሽን እዩት!" ብለን ሀገራቸው መዲና ድረስ ወስድንላቸው::"

"ታዲያ ይሄ ድርጊታችን አንዳንድ አገራቸውን የሚወዱ ሰዎች እና የሕዝቡን ቁጣና ቁጭት ቢያስነሳ ያስገርማል? አንተ (ጋዜጠኛውን) ከዚህ ስቱዲዮ ስትወጣ አንድ ሌባ ሰዓትህን ቀማህ እንበል:: በማግስቱ ቢሮህ ድረስ መጥቶ ሰዓትህን ላውስህና ጊዜን ቁጠር ቢልህስ? አየህ! የልዕልታችን እና የቅርሶቹም ዕጣ ፋንታ ካንተ ሰዓት ጋር ተመሳሳይ ነው::"

ቢ.ቢ.ሲ፡ "ተራ ሌብነትና አሸባሪነት ይለያያል::"

ኪምበርሊ፡ "አሸባሪነትን የፈጠርነው እኛው ራሳችን ነን:: የሕዝቦችን የማንነታቸው መለያ የሆኑ ቅርሶቻቸውን ከዘረፍን በኋላ 'እናውሳችሁ' ብለን አገራቸው ድረስ በመውሰድ ያሸበርናቸው እኛው ነን::"

ይህ ቃለ መጠይቅ እንግሊዛውያንን እና የሌሎች በርካታ ሀገሮች ዜጎችን በተለይም በቅኝ ግዛት ዘመን ቅርሶቻቸው የተዘረፉባቸውን ሕዝቦች አነሳሳቸውና ኃያላኑን

ዘራፊዎች' በመቃወም ታላላቅ ሰላማዊ ሰልፎችን አደረጉ። እነዚህን ከመሳሰሉት ሕዝባዊ ስብሰባዎች መሐል አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የተደረገው ሕዝባዊ ስብሰባ አንዱ ነበር።

መስቀል አደባባይ ስፍር ቁጥር በሌለው ሕዝብ ተሞልታል። የሀገር ውስጥና የውጭ ዜና ተቋማት ሰላማዊ ሰልፉን ከስፍራው በቀጥታ ስርጭት ለመላው ዓለም አስተላለፉት። ሕዝቡ በስብሰባው አስተባባሪዎች በኩል ለመንግሥት በላከው ደብዳቤ . . .

1. መንግሥት የተዘረፉ ቅርሶቻችንን ለማስመለስ የሚያደርገውን ጥረት አጠናክሮ ይቀጥል።
2. የእንግሊዝ ቅኝ ገዢዎች ከመቅደላ አምባ የዘረፏቸው ቅርሶቻችንን ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ ይመልሱልን።
3. አገታው በሰላም አልባት እንዲያገኝ ታጋቾቹ ተለቀው ቅርሶቻችን ይመለሱ፤ ለአጋቾቹም ምህረት ይደረግ።
4. ጠላፊዎቹ ሀገር ወዳዶች እንጂ አሸባሪዎች አይደሉም። አሸባሪው ጄኔራል ናፒዮር እና ወራሪ ጦሩ ነው።

በተለይም በቦምቤይ እና ካይሮ ከተሞች የተደረጉት ሕዝባዊ የተቃውሞ ሰልፎች ከሕዝብ ብዛትም ሌላ ቁጣና ረብሻ የተቀላቀለባቸው ነበሩ። የቅርሶቹ መዘረፍ ሳያንስ ዘራፊዎች "በውሰት" የማስጎብኘት ድፍረታቸው ያበላጨው በርካታ የካይሮና የቦምቤይ ሕዝብ የእንግሊዝ መንግሥት ኤምባሲዎችንና ተቋማትን በድንጋይ እስከ መደብደብ የደረሰ ታላቅ ተቃውሞ አሰማ።

**********/////////**********

በዚህ ሁሉ የሜዲያ ሰርከስ መሀል አንድ ሌላ ፊልም በዓለም ሜዲያዎች ተለቀቀ፡ ፊልሙ ተዘርፈው በተለያዩ አገሮች የሚገኙ የኢትዮጵያን ቅርሶች የሚዘክር እና የአዲስ አበባውን አገታ መንስኤና ምክንያት የሚያስተነትን የተዋጣለት የ20 ደቂቃዎች ዘጋቢ ፊልም ነበር። ፊልሙን በቀደምትነት ለለየር ያበቃው የእንግሊዙ ቢ.ቢ.ሲ ሲሆን ሌሎቹም እየተቀባበሉ ዋነኛውና ግንባር ቀደሙ ዜናቸው አደረጉት።

ባሕታዊው ቃለ ቡራኬ ሲሰጡ ዶክሜንታሪው ፊልም ይጀምራል። የተለያዩ ኢትዮጵያዊ የዱር አራዊትና ታሪካዊ ሥራዎችን እያስቃኘ በአውሮፓና በሌሎችም ሀገሮች

የተቀመጡ ቅርሶችን፣ በተለይም በለንደኑ ሙዚየም ውስጥ የተከማቹ ቅርሶችን ያስቃኝና በመጨሻም ከመቅደላ አምባ የተዘረፉትን እና ተመርጠው ወደ አዲስ አበባ "በውሰት" የመጡት ቅርሶች ላይ ባሕታዊ በጠራ እንግሊዝኛ ትንታኔ ይሰጡባቸዋል። "የእዜ ቴዎድሮስ ሹሩባ ለእንግሊዝ ሕዝብ የሚናረው ሥነ ልቡናዊ ፋይዳ ምንድን ነው? ዛሬም ደካማ ሀገሮችን ለመውረርና የመሪዎቻቸውን ሹሩባ ለመቁረጥ?" በሚል ጥያቄ የፕሮፖጋንዳ ፊልሙ ያበቃል።

ይህ የጠላፊዎቹ የተቀነባበረና በጥንቃቄ የተዘጋጀ አፓሬሽን ኃያላኑን መንግሥታት ቢያስደነግጥም የእንግሊዝን መንግሥት ያህል የደነገጠና በእነርሱ ቋንቋ (ፌስ-ሱዝ) ያደረገ ወይንም ሃረፍትን ያከናነበው አልነበረም። በዚህም የተነሳ የእንግሊዝ መንግሥት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በመተባበር የጠለፋውን ድራማ ለማክሸፍ ቆርጦ ተነሳ።

ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ

የለንደን ምዕራባዊ ክፍለ ከተማ (ዌስት-ኢንድ) ጻርቻ ላይ ባለ አራት ፎቅ ግራጫማ ሕንፃ ይገኛል። ምንም እንኳ የሕንፃው መግቢያ ላይ "ምሥራቃዊ የንግድ ክባንያ" የሚል ምልክት ቢለጠፍበትም ማንም የለንደን ከተማ ነዋሪ ይህ ሕንፃ የዝነኛውና እጅግ የሚፈራው "ኤስ.ኤ.ኤስ" የተባለው ልዩ ኮማንዶ ጦር ጠቅላይ መምሪያ መሆኑን ያውቃል።

ኤስ.ኤ.ኤስ ወይንም 'ስፔሻል-ኤር-ሰርቪስ' የተባለው ልዩ ኮማንዶ ጦር አባላት በከፍተኛ ደረጃ የሠለጠኑ፣ የዘመኑ ቴክኖሎጂ ያፈራቸውን የተራቀቁ የኤሌክትሮኒክስ እና የጦር መሣሪያዎች የታጠቁ ወጣት ኮማንዶዎች ናቸው።

የኤስ.ኤ.ኤስ ኮማንዶዎች በተለያዩ የዓለም ክፍሎች እየተዘዋወሩ በጥቂት የሰው ኃይል እጅግ ከፍተኛና አዳጋች የተባሉ አደገኛ ወታደራዊ ተልዕኮዎችን በስኬት የተወጡ ወይንም የተወጣ ጦር ነው።

የኤስ.ኤ.ኤስ አባላት ከሥራ ውጪ በየሥፍራው ተበታትነው ባሉበት ወቅት አንድ ዐይነት ድንገተኛ አደጋ ቢፈጠር ጠቅላይ መምሪያ ውስጥ የሚገኘው ተረኛ መኮንን አንድ የድንገተኛ አደጋ መጥሪያ መሣሪያ ያበራና ቁልፉን (በተን) ይጫነዋል። ይህን ጊዜ ሁሉም የኤስ.ኤ.ኤስ አባላት ወገባቸው ላይ የሚታጠቁትና በምንም ዐይነት ሁኔታ የማትለያቸው የማስጠንቀቂያ መሳሪያ ቢፕ! ቢፕ! ቢፕ! የሚል ድምጽ ታሰማለች። ቢፐር ተብላ ትጠራለች።

ይህች መሣሪያ ስትጮህ አባሉ ወዲያውኑ በጣቱ ተጭኖ ያጠፋትና ባስቸኳይ የሕዝብ ስልክ ወዳለበት ሥፍራ ሄዶ ወደ ጠቅላይ መምሪያው ይደውላል። ከሕዝብ ስልክ ውጪ ሌላ መጠቀም ፍጹም የተከለከለ ነው።

በዛሬው ዕለት 25 የኤስ.ኤ.ኤስ ኮማንዶ አባላት በተደረገላቸው የአስቸኩዋይ ጥሪ መሠረት ጠቅላይ መምሪያው ሕንፃ አራተኛ ፎቅ ላይ ለመሰባሰብ የወሰደባቸው ጊዜ ግማሽ ሰዓት ብቻ ነው። (ትራንስፖርት የተቸገረ አንድ አባል አንዱን ባለ መኪና በሽጉጥ አስገድዶ ጠቅላይ መምሪያው አካባቢ ከመድረሱ በፊት ከመኪናው ተገልብጦ በመውረድ ተሰውሯል።)

አራተኛ ፎቅ ውስጥ ሃያ አምስቱ ኮማንዶዎች ከመድረሳቸው አስቀድሞ የመጡ ሁለት አዛውንቶች ተገኝተዋል። አንደኛው 'መጥረቢያው' በሚል የቅፅል ስሙ ብቻ የሚታወቀው የሃምሳ አምስት ዓመቱ ኮሎኔል ስቲቨንስ የጦሩ አዛዥ ነው። ሙሉ የኤስ.ኤ.ኤስ ኮማንዶ ዩኒፎርሙን ለብሶ፣ ልዩ የኮማንዶ ሳንጃውን በማህደር ታጥቋል።

ከመጥረቢያው አጠገብ በ "ኢንግሊሽ ጀንትል ማን" አለባበስ የዘነጡት የ60 ዓመቱ አዛውንት አና የ'ግርማዊነቷ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ተቀምጠዋል።

"የተከበራችሁ ወጣት ልጆች!" አለ መጥረቢያው። "የውጭ ሴክሬታሪ ሚኒስተር ማክርቲን ተዋወቁ!"

ወጣት ኮማንዶዎች ራሳቸውን በሠላምታ ዝቅ አደረጉ። ማናቸውም ዩኑፎርምና መለዩ አልለበሱም።

"እንደምታውቁት በዛሬው ዕለት ከጥቂት ሰዓታታ በፊት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ አንድ የባሕል ኤግዚቢሽን በክብር እንግዳነት መርቃ ለመክፈት የተገኘችው ልዕልት ኢዛቤል በአሸባሪዎች ታግታ ተይዛለች። ሁኔታው በሠላም የማያልቅ ከሆነ የመጨረሻው መፍትሄ የኃይል አማራጭ ነው። ስለዚህ ዝግጅታችሁን አጠናቃችሁ ወደ አዲስ አበባ ትበራና በቅርብ ርቀት ላይ ሆናችሁ ትጠባበቃላችሁ።"

'መጥረቢያው' ወፍራም ሲጋራ ከመያዣው አውጥቶ ለኮሰ። ኮማንዶዎቹ በቆመበት ሲፍነከነኩና አዛገቡን በጉጉት ሲጠብቁ አስተዋላቸው።

'ለውጊያ ተልዕኮ ጓጉተዋል። ጥሩ ነው!' አለና በሐሳቡ "የእናንተን የአዲስ አበባ ተልዕኮ ካቢኒያችን እና የኢትዮጵያ መንግሥት ባስቸኳይ ስብሰባ ተነጋግረውበታል። የስምምነት ውሳኔም ላይ ስለተደረሰ ዛሬ ከሂትሮው አየር ማረፊያ ወደ አዲስ አበባ እንበራለን።"

ወጣቶቹ ኮማንዶዎች እጆቻቸውን ደረታቸው ላይ አጣምረውና እንደ ጅብራ ተገትረው ሁለቱን ባለሥልጣኖች ይመለከታሉ።

"እኔም የካቢኔውን መልዕክት ላቀብላችሁ እፈልጋለሁ።" አሉ አዛውንቱ ሚኒስትር ማካርቲ። "የናንተን ሥልጠና እና ብቃት ከማናቸውም ወታደራዊ ተቋም ልዩ የሚያደርገው በተለይ 'ሆስቴጆችን' ያለአንዳች ጉዳት ለማስለቀቅ የሠለጠናችሁ፤ እያሌ ስኬታማ ውጤቶችንም ያስመዘገባችሁ መሆናችሁ ነው። ዛሬም ወደ ምሥራቅ አፍሪካ

ተወርውራችሁ ልዕልት ኢዛቤልን እና እምባላደራችንን እንዲሁም ሌሎች ዜጐቻችን በሰላም ነፃ እንደምታወጡ ካቢኔያችንም ሆነ የግርማዊነቷ መንግሥት ሙሉ እምነታቸውን ጥለውባችኋል። ሌላ ላስታውሳችሁ የምወደው ጉዳይ በአዲስ አበባው ቆይታችሁ ከኢትዮጵያ ባለስልጣናትና የጸጥታ ኃይሎች ጋር ተባባራችሁ ትሠራላችሁ። መልካም ዕድል ይግጠማችሁ!" አመሰግናለሁ። ሚንስትሩ ኮማንዶዎቹን ተሰናብተው ሲነሱ የቦሩ አዛዥ 'መጥረቢያው' በሩን ከፍቶ ሸኝቷቸው ተመለሰ።

ሚኒስትሩ ከመውጣቱ ኮማንዶዎቹ በየአቅጣጫው ተበታትነው ትጥቆቻቸውን ማዘጋጀትና መሸከፍ ጀመሩ።

**********/////////**********

ከአራት ኪሎ በንግሥት ኤልሳቤጥ ጎዳና ጥቂት ተጉዘው የቀበናን ድልድይ ሻገር እንዳሉ የሚገኘው የሩሲያ ኤምባሲ የዛሪት (ንጉሳዊ) ሩሲያ፣ የኮሚኒስት ሩሲያ አሁን ደግሞ የሩሲያ ፌደሬሽን ቆንስላ ሆኖ ሲያገለግል ረዥም ዘመን ቢያስቆጥርም ኤምባሲው ውስጥ በዲፕሎማቲክ ሽፋን የተሰገሰጉት ስላዮች ስሞኑን በእጅጉ ሥራ የበዛባቸው ይመስላሉ። ከነዚህም የሩሲያ መረጃ ድርጅት ወኪሎች አንዱ ኒኮላስ ሞግዶቭ በአዲስ አበባ የሩሲያ መረጃ ድርጅት ዋና ወኪል ሲሆን የሸፋን ሥራው "የንግድ ግንኙነቶች ኃላፊ" የሚል ነው።

የመቅደላ ቅርሶች አውደ—ርእይ ሊከፈት ጥቂት ቀናት ሲቀሩት ሞግዶቭ ቢሮው ውስጥ ከሁለት ሩሲያውያን እና ከአንድ ኢትዮጵያዊ ጋር ምርጥ የኩባ ሲጋር ሽታው ከሚያስጎመጅ የየርጋ ጨፌ ቡና ጋር እየተጎነጨና እያጤሱ ስብሰባ ተቀመጡ። በርና መስኩቶች ግጥም ብለው ተዘግተው በመጋረጃውም ተሸፍኗል። መጨየም ይሄ የሁሉም ሰለላ ተቋማት እና የስለላ ወኪሎች መደበኛ ባሕርይ ቢሆን የኬ.ጂ.ቢ ግርፋ ሞግዶቭ ግን በጠንቃቃነቱ የተነገረለት ሰላይ ነው።

"ወይዘሪት መቅደላዊት" አለ ሞግዶቭ ያን ውድ የኩባ ሲጋር እየማገ። "ያመጣሽውን ዘገባ ተመልክቼዋለሁ። በዚህ ጉዳይ ላይ የምታውቂያቸው ባልደረቦቼ ባሉበት ብንነጋገር ቅር ይልሻል?"

መቅደላዊት ቡናዋን ፉት ብላ በስኒው ጠርዝ ላይ አንድሬይና....."ማን ነበር? አዎን ላምሶኖቭ' ላምሶኖቭን አየት አድርጋ ስኒዋን አስቀመጠች። "አይለኝም" አለችው።

"መልካም" አላት ሞግዶሽ በጠራ ዐማርኛ። "ብሪፖርትሽ ግልጽ እንዳደረግሽው ዶክተር ሥራው እንዳንድ ቅርሶችን ለሞላድ እያቀበለ ነው። ዐይነታቸውን ግን አላወቅሻቸውም። እኔ ግን ወደ ቴል አቪቭ ያሻገራቸውን ቅርሶች፣ በተለይም የብራና መጽሐፍት ካሉበት ቸርአስታቸውን በትክክል ማወቅ አሻለሁ። ገባሽ?"

"እምን።"

"መቅደላዊት። እኛም አንድ የብራና መጽሐፍ እንደምንፈልግ ነግረንሻል፣ 'መጽሐፈ ጥበብን' በጣም እንፈልጋለን። ኤግዚቢሽኑ ከመጠናቀቁ በፊትም ሆነ በኋላ ይህን የብራና መጽሐፍ በማናቸውም ዘዴ ተጠቅመሽ እጅሽ ማግባትና ለኔ ማቀበል አለብሽ። እኔ እንደማስበው ቀላሉ ዘዴ ሽማግሌውን ዶክተር በፍቅር አነሁልለሽ እንዲሰርቅልሽ ማድረግ ነው።" አለና ሞግዶሽ መቅደላዊትን በሽሙጥ ፈገግታ ዐየት አደረጋት። ፊቷ በሐፍረት ቀልቶ ዝም አለች።

"ከመጀመሪያውም" አለ ሞግዶሽ። "ከመጀመሪያውም መጠነኛ ሥልጠና ሰጥተን ከሽማግሌው ጋር ያጣበቅንሽ ዶክተሩ ለቅርሶቹ በጣም የቀረበና ለንዋይና ለወሲብ ክፍተኛ ፍቅር እንዳለው ስለምናዉቅ ነው።" መቅደላዊት አሁንም ፊቷ በሐፍረት ቀላ።

"እንቺም ብትሆኚ እንደ ወጣትነትሽና ክፍቅረኛሽ ሳምሶን ጋር ለሚጠብቅሽ ጣፋጭ ሕይወት በቂ ገንዘብ ያስፈልግሻል። እስከዛሬ ድረስ የቅርሳችን ይጠበቅና የብራና አስጎብኚ ደክሜንቶችን ኮፒ እያደረግሽ ስታቀብይኝ ከተከፈለሽ ገንዘብ ቢያንስ ከሃምሳ ከመቶ በላይ የሚሆን ገንዘብ፣ ያውም በዶላር ልከፍልሽ ተዘጋጅቻለሁ።" አለና ሞግዶሽ መቅደላዊትን መልከት አደረጋት። በጉጉት ምራቋን ዋጠች።

የዴስኩን መሳቢያ ሳበና በጣም ወፍራም ፖስታ አውጥቶ እፊቷ፣ ጠረጴዛው ላይ ጣለላትና "ምንም እንኳን ገና ውጠየታማ ምርት ባታስገኚም ለማበረታቻ ያህል ይቺን ሃምሳ ሺህ ብር ያዣት። በተረፈ ሕይወትሽን የሚለውጠውን ዶላር ለማግኘት ያንን እሮጌና ላገርሽ ምን ፋይዳ የሌው ብራና በርትተሽ አምጪልኝ። ተግባባን መቅደላዊት?" አለና በፈገግታ ተመለከታት።

"አዎን!" አለችው ፖስታዋን ወደ ቦርሳዋ እየከተተች።

"መልካም" አለ ሞግዶሽ ራሱን በመግባባት እየወዘወዘ። "ስብሰባችን አብቅቷል። በተለመደው መንገድ አንድሬይ ይሸኝሻል።"

ምዕራፍ ሰላሳ

መቶ አለቃ ሳሙኤል ሀብተማሪያም ከአለቃው ቢሮ እንደወጣ ቆሞ የሚጠብቀው ኮድ 2 ስቱሽን ዋገን ውስጥ በፍጥነት ገባና "ወደ ባሕል ሚኒስትር!" ሲል ሹፌሩን አዘዘው። ላንድ ክሩዘሩ ተፈትልኮ ከጸጥታ መሥሪያ ቤት ወጣና ዋናውን ጎዳና አቋርጦ ወደ ግራ በመታጠፍ ቁልቁል ከነፈ። ሳሙኤል ሲጋራውን እያቦነነ በገዘምታ ያስባል። 'በዚህ ሁኔታ (በጠለፋው) ውስጥ የውጭ ኃይሎች ፍላጎት ይኖር ይሆን? ጠላፊዎቹ እነማን ናቸው? ቅርሶችን በኃይል አናስመልሳለን የሚል 'የሞኝ አምነት' እንዴት አደረባቸው?' እነዚህን ጥያቄዎች እያብላላ ሁለት ሲጋራዎች ከፊጅ በኋላ ነበር የባሕል ሚኒስትር መሥሪያ ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ የደረሰው። ኮሎኔል ሰናይ በገቡለት ቃል መሠረት የሳሙኤልን መምጣት ያሳወቁ ይመስላል። ምክንያቱም ከሕንፃው መግቢያ ላይ ይጠብቃቸው የነበረ የምክትል ሚኒስትሩ ረዳት ወደ መኪናው ተንደርድሮ መጣና "መቶ አለቃ ሳሙኤል?" ሲል ጠየቀው።

"አዎን።"

"ምክትል ሚኒስትሩ እየጠበቁህ ነው። ተከተለኝ" አለው።

.....////////.....

የምክትል ሚኒስትሩ ቢሮ ከምቹ የቢሮ ዕቃዎች ይልቅ በታሪካዊ፣ ተፈጥሮአዊና ባሕላዊ ቅርሶች እንዲሁም ስዕሎች የተሞላ ሆኖ አገኘው። ምክትል ሚኒስትሩ ፊታቸውን ቅጭም አድርገው "መቶ አለቃ ሳሙኤል ተቀመጥ" "አሉና ወደ ረዳታቸው ሀረው "እባክህን ቡና አስመጣልን" አሉት።

"መቶ አለቃ የምታጨስ ከሆነ ማጨስ ትችላለህ። የታገቱትን የባሕል ሚኒስትራችንን በሰላም ታስመልስልናለህ ብዬ አምናለሁ። ሌሎቹንም እንግዶቻችንን" አሉ ሲጋራቸውን እየለኮሱ። ሳሙኤልም ዘና ብሎ ሲጋራውን ለኮሰና ጠበቃቸው።

"ለመሆኑ በምን መልኩ ነው ልረዳህ የምችለው? መቼም ወደ ባሕል ሚኒስትር የመጣህው ሽጉጥ ወይ የእጅ ካቴና ልትዋስ እንዳልሆነ ይገባኛል።"

ሳሙኤል ፈገግ አለ። "የመጣሁት ልዋስ ሳይሆን ስለተዋሳችሁት ቅርሳ ቅርስ ለማወቅ ነው።"

"ምንድነው ማወቅ የምትሻው?"

ሬዳታቸው ራሱ የቡና ፍንጃልና ሲኒዎች በትሪ ይዞ ገባና ለሁለቱም ከቀዳ በኋላ ማስታወሻ ደብተሩን ይዞ ከሚኒስትሩ በስተግራ ጥቂት ርቀት ላይ ተቀመጠ።

"እግዚብሽኑን ከለንደን ሙዚየም ጋር በመተባበር ማዘጋጀታችሁን ሰምኑን ከተደመጡ ያገር ውስጥ ሚዲያዎች ተረድቻለሁ። የለንደን ሙዚየም እና የባህል ሚኒስትር ብቻ ናችሁ ስምምነቱን የተፈራረማችሁት? ዝግጅቱን ያዘጋጃችሁት?"

"እኛ (የባህል ሚኒስትር)፣ የለንደን ናቹራል ሂስትሪ ሙዚየም፣ የቅርሳችን ይጠበቅ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ..." ሳሙኤል በፍጥነት እየመዘገበ ያዳምጣል።

"ቅርሳችን ይጠበቅ ነው ያሉኝ?"

"አዎን"

"ምን ዐይነት ድርጅት ነው?"

ከብዙ ዓመታት በፊት በኢትዮጵያውያን የተመሠረተና ቅርሶቻችንን ተዘርፈው ከተወሰዱበት ሀገር ለማስመለስ፣ በሀገር ውስጥ ያሉትንም አሰባስቦ፣ ዋስትናቸው እንዲጠበቅ ለማድረግ የሚጥር መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋም ነው።"

"ሥራ መሪዎቹና አስታፉስ?"

"ዋና ዳይሬክተሩ ወይንም ፕሬዝዳንቱ ዶክተር ሥራውብዙ አየለ የተባሉ በአ.አ. ዩኒቨርሲቲ ለረጅም ጊዜ ያስተማሩ ምሁር ናቸው። ባሁኑ ጊዜ 'ብራና' የተባለ አስጎብኚ ድርጅት ባለቤት ናቸው። የቅርሳችን ይጠበቅ ዋና ሥራ አስኪያጅ ራሄል ግዛው የተባለች የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ መምህር ናት . . . "

መቶ አለቃ ሳሙኤል ቀና ብሎ ምክትል ሚኒስትሩን እያቸውና ወዲያው ማስታወሻው ላይ አቀረቀረ።

"ሌሎችም ከለንደን ሙዚየም የመጡ አስተባባሪዎች አሉ። ያፈት ናህ። የቀድሞው መንግሥት አየር ኃይል ባልደረባና የመንፈሳዊ (የሃይማኖታዊ) ሰዕሎች ምሁር፣ ያሬድ መልካሙ የታሪክ....."

"ጌታዬ! እነዚህን ሰዎች በትርብ ያውቋቸዋል?"

"አዎን መቶ አለቃ። እዚህ ያሉት ዶክተር ሥራውብዙና ራሄል፣ እንዲሁም ያፈትና ያሬድ ከለንደን እየተመላለሱ መሥሪያ ቤታችንን እና የብራቲሽ ሙዚየምን በማደራደር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል።" አሉና መቶ አለቃ! በነገራችን ነሩ አዘ

አውቶማቲክ ያንጠለጠለውና ካዳራሹ እየተኮሰ የወጣው የእጋቾቹ መሪ ያፌት ከለንደን ይመጡ ከነበሩት አስተባባሪዎች እና የቅርሳችን ይጠበቅ ማሕበር አባላት አንዱ መሆኑን አውቀሃል?

ሳሙኤል ቀና ብሎ አያቸው። ፊቱ ላይ ግን አንዳችም ለውጥ አይታይም። ጥያቄያቸውን እንዳልሰማ አለፈውና "አዲስ አበባ በውሰት የመጡትን ቅርሶች ዝርዝር እና የቅርሳችን ይጠበቅ ማሕበር አባላትን ስም ዝርዝር በጣም እፈልጋለሁ። ሊያገኙልኝ ይችላሉ?" ሲል ጠየቀ።

"እባክህን ዝርዝሩን ለመቶ አለቃ ሳሙኤል ስጠው!" ሲሉ ረዳታቸውን አዘዙት። ለውየው ወዲያውኑ ወደ አለቃው የፋይል ካቢኔት ሄደ አንዱን መሳቢያ ሳበው። ምክትል ሚኒስትሩም ላፕ-ቶፕ ኮምፒውተራቸውን ነካ-ነካ አድርገው "ይሄው። ዝርዝሩ እዚህም አለ።" ከማለታቸው ረዳታቸው አንድ ፋይል አወጣና የቅርሶቹን ዝርዝር የያዘውን ሰነድ ለመቶ አለቃው አቀበለው።

"አመሰግናለሁ። ሃርድ ኮፒው ይሻለኛል!" አለ ሳሙኤል።

"ኤግዚቢሽኑን ከለንደን ወደ አዲስ አበባ ለማዛወር ከፍተኛ ተሳትፎ ያደረጉት የቅርሳችን ይጠበቅ ማህበር አባላት ዝርዝርም ይሄውልህ።" አሉ ምክትል ሚንስትሩ።

"አመሰግናለሁ። ሃርድ ኮፒው ይሻለኛል።" አለና ሳሙኤል ሰነዶቹን ከሚንስትሩ ረዳት እጅ ተቀበለና ቡናውን እንኳ ሳይጨርስ ብድግ ብሎ ወደ በሩ አመራ።

ምክትል ሚኒስትሩ ተገርመው "በቃ ይሄው ነው? መሄድህ ነው?" አሉት።

"አዎን መሄድ አለብኝ። አመሰግናለሁ!"

ሳሙኤል ሁለቱን ደረጃ በአንድ እርምጃ አፈፍ አያለ ቁልቁል ወረደ። "ወደ ቅርሳችን ይጠበቅ ጽሕፈት ቤት። የት እንደሆነ ታውቃለህ?" ሲል አሽከርካሪውን ጠ!ቀው።

"እንዴታ! አዲስ አበባ ውስጥ የማላውቀው ቦታና ድርጅት የለም።"

'ሥራህ አይደል?' አለ ሳሙኤል በልቡ።

**********//////////**********

አሜሪካን ኤምባሲ ግቢ ውስጥ አዲስ በተገነባው ሕንጻ ምድር ቤት ውስጥ ሦስት ሰዎች ስብሰባ ተቀምጠዋል። ሁለቱ እዚሁ የኤምባሲው ስታፍ አባላት ሲሆኑ ዕድሜው በዐርባዎቹ መጀመሪያ የሚገመተው ክላርክ በ ንግድ ግንኙነት አታሼነት የተሰመ የሲ.አይ.ኤ ኃላፊ ሲሆን ባልደረባው ዴቪስ ደግሞ በባሕል ግንኙነት የሥራ እርእስት የተሸፈነ የታላቁ ስለላ ተቋም ባልደረባ ነው። ሦስተኛው ሰው ለዚሁ ስብሰባ ላንግሌይ ቪርጂኒያ ከሚገኘው የሲ.አይ.ኤ. ጠቅላይ መምሪያ የተላከው የሠላሳ ዘጠኝ ዓመት ዕድሜ ያለው ዶክተር ሬይ ብራድፎርድ ነው።

የዓለማችን ግዙፉን የስለላ ተቋምት፣ ሲ.አይ.ኤ. የሩሲያው የስለላ ድርጅት ////////////////////እና ሌሎቹም ከሚያከናውኗቸው ከፍተኛ ጥናትና ምርምሮች ውስጥ ዋነኛውና እጅግ ጥብቅ በሆነ ምስጢር የሚረባረቡበት ጉዳይ የጥንታዊ ሀገሮች፣ ሥልጣኔዎች፣ ባሕሎች፣ እና ሕዝቦችን የቆዩና ሊጠፉ የደረሱ ምስጢራዊ ዕውቀቶችን መሰብሰብሰብ፣ መመርመር፣ ምስጢራቸውን መፍታትና ዓለምን በበላይነት ለመቆጣጠር ወደሚያስችል ቁሳዊ መሣሪያነት መቀየር የቀን ተሌሊት ሕልማቸውና ጥረት—ግረታቸው ነው። ዶክተር ሬይ ብራድፎርድ ደግሞ በ ኤሶቴሪክ ወይንም ጥቂቶች ብቻ የሚያውቁት ምስጢራዊ ዕውቀት፣ ኦከልት ወይንም ምትሃታዊ፣ ረቂቅ፣ እና መንፈሳዊ ጥበባትን በተመለከተ ከበርካታ ሀገሮች የተሰበሰቡ ጥንታዊ መጽሐፍትን በመመርመር የተካነና የተጠበበ የሲ.አይ.ኤ ወኪል ነው።

"እስከ ዛሬ ድረስ ተኝታችኋል ማለት እችላለሁ። የጥንታዊና ምስጢራዊ ዕውቀቶች መገኛ የሆነችው ኢትዮጵያ ውስጥ እስከ ዛሬ ድረስ ኦፐሬሽን አለመጀመራችሁ ድክመት ነው። ጀርመኖች፣ እንግሊዞች፣ ሩሲያውያን.....ሌላው ሁሉ ቀርቶ አዲሷ የምጣኔ ሀብት ኃያል ቻይና እንኳን ሳትቀር የኢትዮጵያን ጥንታዊና ምስጢራዊ ጥበባት እያሰሱ በመዝረፍ ብዙ ቀድመውናል። ስለዚህ በቅርቡ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሊዘጋጅ የታቀደውን የጥንታዊ ቅርሶች ኤግዚቢሽን መነሻ በማድረግ ማድረግ የሚገባችሁን ኦፐሬሽን አሳውቃችኋለሁ.....።"

**********////////**********

ምዕራፍ ሰላሳ አንድ

ከሁሉም ዘርና የምድር ገጽ የተሰባሰቡት የመገናኛ ብዙሃን ወኪሎች፣ ዘመናዊ የድምጽና የምስል መቅረጫዎች፣ እጅግ ዘመናዊና በሳተላይት የሚታገዙ ዜና ማሠራጫ መሣሪያዎች በአንግሊዝ ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ተገጥግጠዋል። የኢትዮጵያ መንግሥት የጸጥታ ኃይሎችም በሲቪል አለባበስና በተለያዩ የማስመሰያ ሽፋኖች (በተለይም በጋዜጠኛነት) ስብሰባውን ታድመዋል።

የመላው ዓለምና ያገር ውስጥ ጋዜጠኞች ካሜራዎቻቸውን ከዋናው በር ጀምሮ ባለው ሰፊ የአስፋልት ግቢ ውስጥ ደርድረውና አዘጋጅተው የጠላፊዎቹን መግለጫ በጉጉት ይጠባበቃሉ። የታገቱት ክቡራን ወደሚገኙበት አዳራሽ የሚወስደው መንገድ በረጅም ገመድ ተከልሏል። እዚህ ክልል ላይ ብቻ ዩኒፎርም የለበሱና የላስቲክ ዱላ ብቻ የያዙ አራት ፖሊሶች ቆመዋል።

በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ልክ ከቀኑ ሰባት ሰዓት ላይ የአዳራሹ በር ተከፈተና ወገቡ ላይ በማህደር ሽጉጥ የታጠቀ፣ በመካከለኛ ዕድሜ ውስጥ የሚገኝ ሰው ጋዜጠኞቹ ወደ ተሰበሰቡበት ሥፍራ በእርጋታና በራስ መተማመን ስሜት እየተራመደ መጣ። የካሜራ መብራቶች ተብለጨለጩበት። ቪዲዮ ካሜራዎች ቀረጻ ጀመሩ። ታጣቂው የስብሰባው ሥፍራ ላይ ሲደርስ ግራ ቀኙን ከተመለከተ በኋላ አታክልት የተተከለበት አጭር የድንጋይ ግንብ ላይ ወጥቶ ቆመ። ግቢው ጸጥ ረጭ አለ።

"የተከበራችሁ!" ሲል ንግግሩን ጀመረ።

**********////////**********

"አንበሳ 1 ሰማዕከል። መቶ በመቶ 'ሳይቴ' ውስጥ ገብቷል። ግንባሩ ላይ ነኝ ላንሳው?" ሲል ራሱ ላይ ባጠለቀው መነጋገሪያ (ሄድ ፎን) የጸረ ሽብር ኮማንዶው በሹክሹክታ ተናገረ። የጠለፋው ድራማ በተጀመረ አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያ ጸረ-ሽብር ኮማንዶዎች ከትምህርት ቤቱ ፊት ለፊት የሚገኘውን አንድ ሕንፃ አራተኛ ፎቅ ተቆጣጥረው አትርበው በሚያሳዩ መነጽሮች (ቴሌስኮፒክ ሳይት) በተገጠመላቸው ዘመናዊ ጠመንጃዎች አዳራሹንና ግቢውን እየቃኙ ጠላፊዎቹን ሲቆጣጠሩ ቆይተዋል።

አሁን እንደ ሐውልት ቆሞ መናገር የጀመረው የያፈት ግንባር ላይ ያለመው ኢትዮጵያዊ ስናይፐር (አልሞ ተኳሽ) ዐይኑን መስቀሉ ላይ፣ ጣቱን ምላጩ ላይ አሳርፎ እንደኛ ደረጃ ምላጭ ከገደለ በኋላ (የጠመንጃውን ምላጭ ግማሽ በግማሽ መጫን). . . . "ገብቷል ላንሳው?" ሲል በጉጉት ጠየቀ። "ተው!" የሚል መልስ መጣለት። ኮማንዶው በረጅሙ ተነፈሰና ከጠመንጃው ቴሌስኮፕ ላይ ቀና አለ።

ያለቃና የኮማንዶ የራዲዮ ግንኙነት የሚሰማቸው ሌሎች የጸረ ሽብር ኮማንዶዎችም ቀና ቀና አሉ. . .።

**********/////////**********

የመቶ አለቃ ሳሙኤል አዕምሮ በከፍተኛ ፍጥነት እያሰበ ነው። መኪናው ወደ ቅርሳችን ይጠበቅ ማሕበር ጽሕፈት ቤት በከፍተኛ ፍጥነት ሲከንፍ የሞባይል ስልኩን አወጣ።

"ሃሎ ኮሎኔል ዘገየ። የሚፈልጉትን የቅርሳችን ይጠበቅ ማሕበር አባላት የስም ዝርዝር አግኝቻለሁ።" አለና የስም ዝርዝሩን እንብቦ ሲጨርስ በዝምታ ሲያዳምጥ ቆይቶ ዋና ዋናዎቹ መሥራቾች እና አባላት ያዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ባልደረቦች ናቸው። ከዚያ መጀመር ይችላሉ።" አላቸው።

"ተቀብያለሁ!" አሉ ሌ/ኮ ዘገየ።

"በነገራችን ላይ . . . የሰንደኑ የምርመራ ቡድንስ?"

"መንገድ ላይ መሆኑ ተነግሮኛል።"

"እመሰግንዎታለሁ!"

**********/////////**********

የባሕታዊው መኖሪያ ቤት ሳሎን ውስጥ በባሕታዊው ጥሪ መሠረት አባላቱ በሙሉ ለስብሰባ ተገኝተዋል።

"ምናልባት" አሉ ባሕታዊው ቃለ ቡራኬያቸውን እንዳበቁ....."ዘመቻ መቅደላን በተመለከተ ምናልባት የመጨረሻው ሊሆን ለሚችለው ውይይት ጥሪዬን አክብራችሁ እዚህች ደሳሳ ጎጆዬ ስለተገኛችሁ ልዑል እግዚአብሔር ይባርካችሁ።"

"አሜን!"

የባህታዊው አገልጋይና አጃቢ በዝርግ ላህን ላይ ሲኒዎችን እና የሻይ ጀበና ይዞ ገባና ከቡና ጠረጴዛው ላይ ካኖረ በኋላ ከወደ ጥጉ ብቸኛ ወንበር ላይ ተቀመጠ። ራሄል ከወንበሯ ተነስታ ሻዩን በስኒዎች ቀድታ፣ ለባልደረቦቿና ለባሕታዊው ካደለች በኋላ የራሷን ይዛ እስክትቀመጥ ሁሉም በዝምታ ተሸብበው ጠበቋት። ለአንድ ደቂቃም ያህል ቤቱን የቃት—ቃት ድምጽ ሞላው።

"ተአያሌ ዓመታት በፊት የመሠረትነው 'ቅርላችን ይጠበቅ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት' ግብና ዐላማው በተለያየ ዘመን ተዘርፈው ወደ ባዕዳን ሀገራት የተወሰዱ ቅርሶችን ማስመለስ፣ በሀገር ቤት በየአድባራቱና ገዳማቱ ተበታትነው የሚገኙትንም የገንዘብ ድጋፍ በማሰባሰብ መጠበቅና መንከባከብ፣ ሲቻልም ወደ ብሔራዊ ቤተ—መዘክር ማሰባሰብ እንደሆነ የምታውቁትና የለፋችሁለት ዐላማው ነው። ይህ ጥረትና ግረታችን በነገው ዕለት ዐዲስና የተለየ መንገድን ተከትሎ እንዲራመድ ለማስቻል ሁላችሁም ቆርጣችሁና ታጥቃችሁ ተነስታችኋል....." አሉና አባሉትን በዙር ተመልከተው ቀጠሉ።

"ያለማችሁት፣ ያለምነው እንዲሳካልን ከልቤ ጸልያለሁ። ከፉ እንዳይነካችሁ ከልቤ ጸልያለሁ....."

"ምነው አባ! ጸሎት ብቻ?" ዮዲት ነበረች የባሕታዊውን ንግግር ያቋረጠችው። ባለደረቦቿ በሙሉ በግልምጫ ሲያነሷት ባሕታዊው ግን እንዳችም ስሜታዊነት አልታየባቸውም።

"አባ! ጸሎት ብቻ ምን ይረባል? ጥይት ተከላካይ ድግምት የለምት እንዴ?"

የኦፕሬሽን መቅደላ አባላት በሙሉ ክቅጽበታዊ ድንጋጤያቸው ሲያገግሙ ቤቱን በሳቅ ፍንዳታ ናጡት። ባሕታዊው እንኳ ሳቃቸውን ሊገቱ የቻሉት በትግል ነው።

"እየሸ" አሏት ሳቃቸውን ሲያበቁ....."ፈረንጆቹ ምንድነው እሱ.....እምን ቡሌት ፕሩፍ አልባሳት (ጥይት ተከላካይ ልብስ) የሠሩት ትናንት ነው። እኛ ሀበሾች ግን ከጥንት እንሰቶ የራሳችን ጥንታዊና ረቂቅ መከላከያ አይኖረንም ብለሽ ታስቢያለሽ? ታስባላችሁ?" አሉና ዙሪያውን ተመለከቷቸው። መልስ የሰጣቸው የለም፣ አርሳቸውም አልጠበቁም። ወደ ዮዲት መልከት ባሉ ቁጥር ቀልጿና ግልጽነቷ እየታሰባቸው ፈገግ ከማለታቸው በስተቀር የገጽታቸውን መቀጨም ላስተዋለ ሰው እኒህ ሰው በጥልቁ ሕሊናቸው ተቀብሮ የኖረ ዕውነት እንደሚያወሩ አይጠራጠርም።

"ከከብቶቻችሁ መሃል አንዱ ቢጠፋ ማድረግ ያለባችሁ ደ አንዱ "አዋቂ" በመሄድ እንድ ወይንም ሁለት ብር መክፈል ነው። በማግስቱ ወይንም ማታዉኑ አህያችሁ ወይንም በራያችሁ በጅቦች ለሃጭ ታጥቦ ይመጣላችኋል፣ አውሬ እንኳ የማያስበላ መከላከያ አለ ማለቱ ነው። በድንበር ዙሪያ የሰፈረውን ሰራዊታችንን የጥይት መከላከያ፣ በተለምዶ አባባል "ድግምት" ብናለብሰው የየትኛው ኃያል መንግሥት ወራሪ ያሸንፈዋል? ይህ የማይሆን ብላችሁ አታስቡ! አጊዜው ሲደርስ ይደረጋል!"

የዘመቻ መትደላ አባላት ላያዉቁት ባንድድነት ጭብቸባውን አቀለጡት። "መቼም ያገሬ ደብተራ የማይተበትበው ጉድ የለም!" አለች ዮዲት። ባሕታዊውን ቸምሮ ሁሉም በሳቅ ፈነዱ። "ወቸ ጉድ!" አሉ ባሕታዊው እየሳቁና ራሳቸውን በአግራሞት እየወዘወዙ።

"ለነገሩ" አለ ሳምሶን ሳቁን እየታገለ....."የፊረንጆቹ ጥይት ተከላካይ ጃኬት እኮ ዘመናዊ ድግምት ነው!"

"አያችሁ ልጆቼ" አሉ ባሕታዊው ቀልድና ስላቁ ሲለሰልም ጠብቀው። "ማንኛውም ሥልጣኔ፣ ስጥንቶቹም ይሁን ዘመናውያኑ፣ ሁሉም በሚሠሩት ስህተት ይጠፋሉ፣ ይወድቃሉ፣ ከታሪክ መዝገብም ይፋቃሉ። ሥልጣኔን እና ዕውቀትን ጨብጠው የነበሩ ቀደምት ኢትዮጵያውያን ዝርያዎቻችንም ዕውቀታቸውን ምስጢራዊ አድርገው በጥቂቶች እጅ ብቻ በመያዛቸው ብዛትና ብቃት፣ እንዲሁም ጥራት ያለው ዐዋቂ ሕዝብ ሲያፈሩ ስላልቻሉ ሀገራዊ ሥልጣኔያችን ከውጭ ጠላቶችና ከውስጥ መሰሪዎች ሊከላከለን ባለመቻሉ ወደቅን። ለሌሎች ሲያካፍሉት የሚባዛ ዕውቀት ብቻ እኮ ነው! ዛሬ ቅርሶቻችንን ለማስመለስ ቆመናል። ነገ ደግሞ ቅርሶቻችንን ውስጥ የተቀበረውን እምቅ ዕውቀት አውጥተን ለሕዝባችን በማካፈልና በማሰራጨት እናድጋለን እንበለጽጋለን።"

"እዚህ ላይ አንድ ነገር ብጠይቅም ወዳለሁ.....ከይቅርታ ጋር።" ያቋረጣቸው ዶክተር አንዱዓለም ይፍረደው ነበር ።

"በጀ፣ ምን ይሆን?" አሉ ባህታዊው።

"ለነገሩ ጥንታዊና ምሥጢራዊ ዕውቀቶችና ጥበቦች እንደነበሩን እውነት ቢሆንም እነዚያ በጥቂት ሰዎች እጆች፣ በተለይም በቤተ ክህነት ሰዎች እጅ የነበሩ ዕውቀቶችና ጥበቦች ከዛሬው ዓለም ጋር በቴክኖሎጂና በምጣኔ ሀብት ተፎካካሪና እኩያ ሊደርጉን ይችላሉ?"

ባሕታዊው ፈገግ አሉ። አንዳንድ ጥርጣሬና እምነት ማጣትን የመሳሰሉ ነገሮች ግልጽ እንዲሆኑ እንጂ ዶክተሩ በቀደምት እና ረቂቅ ዕውቀቶቻችን ኃያልነት ከልቡ እንደሚያምን ባሕታዊው በጽኑ ያምናሉ።

"ይቅርታ አባ! ሊጋራ ማጤስ ፈልጋለሁ። ከባሕታዊ ቤት እንጂ ገዳም ውስጥ አይደለንም እኮ!" በዮዲት ንግግር የዘመቻ መቅደላ አባላት የሳቅ አሮምታ ሲያወርዱ ባሕታዊውም ፈገግ ብለው...."ሱስኛች ብታጤሱ ቅር አይለኝም አሉ። ቤቱ ወዲያውኑ በትምባሆ ጢስ መታጠን ሲጀምር የባህታዊው ታማኝ አገልጋይ ብድግ ብሎ አጠገቡ ያለውን መስኮት ከፈተው።

"አንዱዓለም ጥሩ ቁም ነገር ጠይቀሃል" አሉ ባህታዊው። "ድርቅ ቢሆን ወይ የዝናም እጥረት ቢገጥመን እና ዝናሙን ማዝነብ ከቻልን ድርቅና ረሃብን አስወገድን ማለት አይደለም? ይሄስ በምግብ ራሳችንን አስችሉ እንዲያውም የምግብ ሰብሎችን ወደ ውጭ በሸጥ ባለጸጋ አያደርገንም?"

"ያደርገናል! ያደርገናል!" ያንድ ሁለት አባላት መልስ ተሰማ።

"የመድኃኒት እጽዋቶቻችንን በስፋት ዘርተንና አምርተን ብንጠቀምባቸው ለመድኃኒት የምናወጣውን ብዙ እጅግ ብዙ ዶላር አናድንም? ዛሬ ፈረንጆቹ ፈውስ ያጡለት ሕማም ብዛት ዐይነቱ ብዙ ነው። በኛ ሀገር እንዲህን ሁሉ በሽታና ህመሞች የሚፈውሱና ሳይንስ የማያውቃቸው በርካታ ዕጽዋት ሞልተዋል። ከነዚህ ዕጽዋት መድኃኒቶችን በኢንዱስትሪ ደረጃ ብናመርትና ለውጭ ገበያ ብንሰድ ሐብታምና ኃያል እንሆንም። ሕንድና ቻይናን፣ በተለይም ሕንድን ብንመለከት ከባሕላዊ መድኃኒቶች ምን ያህል ተጠቃሚ እንደሆኑ ማየት በቻልን።"

የዘመቻ መቅደላ አባላት በከፍተኛ ተመስጦ ባሕታዊውን እያደመጡ ነው ከተባለ ዶክተር ሥራውብዙ አየለ ግን መላ አካላቸው ጆሮ ብቻ ሆኗል ማለት ይቻላል።

"እኔ በተለይም በቤተ ክህነት ሰዎች ብቻ ተይዞ ስለነበረው ጥንታዊና ምስጢራዊ ዕውቀትና ጥበብ ማለት የምፈልገው ነገር አለ።" አለች ራሄል። ዐይኖች ሁሉ ወደርሷ ዞሩ።

"ሰዎችን ለመጉዳት፣ አንደርቢ አያሉ በድንጋይ ለመደብደብ፣ ጠላትን በውጋት ወይንም በሌላ ሕመም ለመግደል.....ወዘተ የሚውል ዕውቀት አንዴት ዕውቀት ተብሎ ይጠራል?"

"እየሽ ራሄል" አሉ ባሕታዊው እጅግ ተገርመውና ቁጣ ገጽታቸውን ወደርሷ አዙረው...."አልፍሬድ ኖቤል....." ገና ስሙን ሲያነሱት ራሄል ፈጣ ብላ ራሷን መወዝወዝ ጀመረች። "ኖቤል ዳይናሚትን የፈለሰፈው የድንጋይ ናዳን በቀላሉ ለመናድና የሰዎችን ድካም ለማቅለል ነበር። ነገር ግን ሰዎች ዳይናሚትን ሰዎችን ለመፍጀት አዋሉት።"

"ዕውቀታችንን ለበጎም ለመጥፎም ልናውለው እንችላለን" አለ ያሬድ ታልቃ ገብቶ። "ያም ሆኖ ግን ሀገራችንን ወደ ኢንዱስትሪያዊ ሀገርነት ሊያዘልቅ የሚችል ጥንታዊ ዕውቀት አለን ይላሉ?"

"እንዴታ!" አሉ ባሕታዊው በትጽበት። *"በመጽሐፉ ጥበብ ወይንም 'ጥበበ አዕባል' የተዘረዘሩ የከበሩ ደንቢያ ማዕድናትን በኢንዱስትሪ ደረጃ ማልማት የማንችልበት ምክኒያት የለም። በመጽሀፉ ዝንዝዋዋ የተጠቀሱ ሥነ—ከዋክብት ጥበባትን የማንካንበት ሰበብ አይኖርም። ምናልባት ሁላችሁንም የሚያሳስባችሁ በኢንዱስትሪ ወደ ኋላ መቅረታችን ይመስለኛል። ግን ኢንዱስትሪዎች የተፈጥሮን ሚዛን እንደሚያዛቡና ከሁሉም በላይ ሰዎች ከተፈጥሮ ጋር ያላቸውን መስተጋብር እንደሚቀርጠው ማወቅ ቀላል ነው። ርዕደ—መሬት ከመከሰቱ በፊት የቤትና የዱር እንስሳት አስቀድመው የሚሸሹት በኢንዱስትሪ የተመረተ ጫማ ስለማይጫሙና የሰው ልጅ ያጣውን የአዋር ራዳርነት እንስሳቱ ስላላጡት ነው። ይህን ስል ጫማ ወይንም ኢንዱስተሪ አያሻንም ማለቴ ሳይሆን....."* አሉና ዙሪያውን መቃኘት ሲጀምሩ ዮዲት ጣልቃ ገብታ ጨረሰችላቸው።

"ዕጸ—ደብዳቤ ወይንም ዕጸ—ፈውስን ወደ መድኀኒት ኢንዱስትሪነት፣ ጥበበ አዕባልን ወደ ማዕድን ኢንዱስትሪነት መለወጥ እንችላለን እያሉ ነው?"

"አዎን ዮዲት እንደርሱ ማለቱ ነው።"

"ጥቂት የምለው አለኝ" አለ ዶክተር አንዱዓለም።

"ከአንድ መቶ ዐርባ ዓመታት በፊት "ፀሐይ ካይጠልቅባት ኢምፓዬር" የመጡት የእንግሊዝ ጦር ወራሪዎች ያንን ደረቱን የሰጠና ቀጥ ብሎ የቆመ ተራራ በመድፍ ቅንቡል

ሲደበድቡትና ሲያቃጥሉት በዐይነ ሕሊናዩ ይታየኛል። የዘመኑ ቴክኖሎጂ ያፈራቸውን ከባድና ቀላል የጦር መሣሪያዎችን የታጠቀው፣ በወታደራዊ ሳይንስና ዲሲፕሊን የሠለጠነው እና በጀኔራል ሰር ሮበርት ናፒየር የሚታዘዘው የእንግሊዝ ጦር ዓፄ ቴዎድሮስና ከእርስ በርስ ጦርነትና ከክዳት የተረፉ ጥቂትና ታማኝ ወታደሮቻቸውን ብቻ ይዘው የመሸገብት የመቅደላ ተራራ ግርጌ ሥር እስኪደርሱ ድረስ አንዳችም ተቃውሞ አልገጠማቸውም ነበር። እንዳዉም ዓፄ ቴዎድሮስን በሚቃወሙ ኢትዮጵያውያን የጦር መሳፍንቶች እየተመሩ ነበር የመጡት። እንግሊዛውያን እስረኞችን ለማስፈታት የተደረጉ ድርድሮች ከሸፉ በኋላ የናፒየር ጦር በመድፎች እሳት አምባው አቃጥሎ እነዚያን ጥቂት የሀበሻ አንበሶች ድል ለማድረግ ቻለ። ከዚያም አምባውን ሙሉ በሙሉ አቃጥሎና ቅርሶቻችንን ሙልሞ አድርጎ ዘርፎ እንዳመጣው ያላንዳች መሰናክል ወጣ።"

"ታሪክ 101!" ሲል ያሬድ ተሳለቀ። እንዱዓለም ፈገግ አለና ቀጠለ።

"የዛሬዎቹ እንግሊዛውያን አያቶቻቸው የዘረፏቸውን ቅርሶቻችንን ለምን ወደ ሀገራችን መከለሰው አመጧቸው? የሚል ጥያቄ ሲነሳ የተሰጠው መልስ.....'በሕዝባዊ ተቃውሞ ምክኒያት አውደ—ርእዩን ለንደን ላይ ማዘጋጀት ስላልተቻለ' የሚል ነው። እኔ ግን ከዛም በላይ የሆነ ምስጢራዊ ምክኒያት አለ እላለሁ። ይሄውም እነዚህ ቅርሶች በተለይም ምስጢራዊ ጠበባትን የያዙት የብራና መጽሐፍቶቻችን እውነተኛ ኃይል፣ የሚኖራቸው ወይንም ኃይል የሚያገኙት ረቂቁን መንፈሳዊ ኃይል ከምታመነጨው እና ከተፈጠሩባት ምድራቸው ነው። ነገር ግን ለአንድ ተኩል ምተ ዓመት ያህል ካገራቸው በመራቃቸው መንፈሳዊና ረቂቅ ኃይላቸውን አጡ። እናም ምክኒያትና ሰበብ ፈልገው እንደገና የቀድሞ ኃይላቸውን ለማደስ ወይንም 'ቻርጅ ለማድረግ' ልበለው? በኤግዚቢሽን ከለላ ወደ አዲስ አበባ አመጧቸው!"

ትንፋሻቸውን ውጠው በአግራሞት የሚያደምጡት አባላቱ ከአግራሞታቸው የተነሳ ጥያቄም ሆነ አስተያየት እንኳ መሰንዘር ተሳናቸው።

**********//////////**********

"እምን እንዱዓለም የሚነግረን ለያንዳንዱ ባትሪ የራሱ ቻርጀር እንደሚያሻው ሁሉ እዚህ የተፈጠሩት ኢትዮጵያዊ ቅርሶች ቻርጀራጀራቸው ሀገራቸው ናት ነው የሚለን" አሉና ባሕታዊው ጥቂት ቆዝመው ቀጠሉ። "ይህ ነገዘላ መነኩሴ አሰለቸን ላትሉኝ ነገሬን

ቀርቅቤ ላብቃ" አሉ ባሕታዊው እጅጉን ቆዝመውና ያን የፍየል የመሰለ ሹል ጺማቸውን ወደታች እየነነተሉ። እስካሁን ድረስ አንዲትም ቃል ሳይተነፍሱና ሐሳባቸውን ሳይገልጹ በዝምታ እያደመጡ ማስታወሻ ይዥሩ የነበሩት ዶክተር ሥራውብዙ ማስታወሻ ደብተራቸውን ዘግተው በንቃት ባሕታዊውን ማድመጥ ጀመሩ። የቤቱ አባላት በሙሉ ከቀድሞው በበለጠ ትኩረት ማድመጥ ጀመሩ።

"ከወጣትነትና የተማሪነት ዘመናችሁ አንስቶ፣ እንዲሁም በሙያዊና የእምነት ሥፍራዎች ተዋውቀን፣ በዓላማና ግብ ተዋህደን፣ ክፉና በጎውን አብረን አሳልፈን የነገው ዘመቻ መቅደላ ላይ ደርሰናል። ዘመቻ መቅደላ "የመቅደላ ትሩፋት" ነው። የዛሬ አንድ መቶ ዐርባ ዓመት ከመቅደላ አምባ በእንግሊዝ ወራሪ ጦር የተዘረፉብንን ታሪካዊ ቅርሶች ነገ በኃይል ለማስመለስ ቆርጠን ተነስተናል። ዝግጅታችንንም አጠናቀናል። ቀሪው ያምላካችን ፈቃድ ብቻ ነው። ከዓመታት በፊት 'የቅርሳችን ይጠበቅ ማህበርን' ስንመሠርት ግቡ ወደ ባዕዳን ሀገሮች በጦር ዘረፋና በስርቆት የተጋዙብብን በርካታ ቅርሶች በዲፕሎማሲያዊ ትግል ማስመለስ ነበር። ሆኖም ግን የነገውን ዐውደ—ርእይ ተከትሎ የተፈጠሩ ዐዳዲስ እውነታዎች ሲከሰቱ እናንት ወንድሞቼና እቶቼ ነገሮችን መዝናችሁና ተንትናችሁ ስታበቁ ከጉልበት ሌላ አማራጭ የለንም!' ስትሉ ወሰናችሁ'። ምንም እንኳን ኃይልና ጉልበት ለደካማ መነኩሴ ምርጫው ባይሆኑም አዛሬ ውሳኔያችሁ ላይ ለመቆም ያበቃኋችሁ እኔ ነኝና አብሬያችሁ ቆሜያለሁ።"

የዘመቻ መቅደላ አባላት በሙሉ ከወንበራቸው ተንስተው ለባሕታዊው የጋለ ጭብጨባ አወረዱላቸው።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ቤቱ ጸጥ አረጭ ሲል....."አሁን ጸሎት አስማና አበቃለሁ" አሉ ባሕታዊው።

**********//////////**********

ምዕራፍ ሰላሳ ሁለት

የኤግዚብሽኑ አዳራሽ ውስጥ በጦር መሣሪያ ታግተው የተያዙት በሙሉ የስዕልና ቅርፃ ቅርጽ ትዕይንት የተዘጋጀበት መድረክ ላይ እንዲሰበሰቡ ተደርጓል። ልዕልት ኢዛቤል፣ የእንግሊዙ አምባሳደር ፒተር ክላይፍ እና የኢትዮጵያ ባሕል ሚኒስትር አቶ ኢብራሂም ከማል መድረኩ ላይ ጎን ለጎን በሦስት ወንበሮች ተቀምጠዋል። ሦስቱ የለንደን ሙዚየም ባልደረባ እንግሊዛውያን እና ሁለቱ የልዕልቲቱ አጃቢዎች ደግሞ የመድረኩ ጠርዝ ላይ ተቀምጠው አግሮቻቸውን ወደ ታች ወለሉ ላይ አሳርፈዋል።

ልዕልት ኢዛቤል በጓንት የተሸፈነ ሌባ ጣታቸውን ምልክት በማሳየት ዮዲትን ጠሯት።

"ግን አይ ሄልፕ ዩ? (ልረዳም እችላለሁ?)" ስትል ዮዲት ልዕልቲቱን ቀርባ ጠየቀቻቸው።

"ቡናችሁ በጣም ጣፍጦኛል። ከምንም ነገር በፊት ይህን ቡና ስላስመጣሽልን አመሰግንሻለሁ። አንድ ነገር ልንገርሽ? ይህ ቡና ከመምጣቱ በፊት ነፃ ለቀሽኝ ቢሆን ኖሮ በጣም ይቆጨኝ ነበር!"

ዮዲት ሳትወድ ፈገግ ከማለቷም በላይ የልዕልቲቱ አርጋታና በራስ መተማመን ስላስደነቃት በሐሳቧ 'ሺ ሀገ ነርቭ!' አለች።

"የተከበሩ ልዕልት! ስለ ቡና ለመወያየት እንዳልጠሩኝ አውቃለሁ።" አለች ዮዲት።

"የጠራሁሽ ይህ የሽብር ሥራችሁ ተቀባይነት የሌለው ውግዝ ድርጊት ስለሆነ አሁኑኑ እንድትለቁን ልመክርሽ ነው።"

"እናንተ ቅርሶቻችንን የዘረፋችሁበት ድርጊትስ ተቀባይነት አለው? ውግዝ አይደለም?" አለች ዮዲት ደሟ ፈልቶ።

"ቀዝቀዝ በይ . . . እ . . . ማን ብዬ ልጥራሽ?"

"ዮዲት!" አለች አሁንም በቁጣ።

"ዮዲት! ቆንጆ ስም ነው። መቼም ከእነዚያ ስፍር ቁጥር ከሌላቸው የቅድመ ታሪክ ንግሥቶቻችሁ የአንዷ ስም መሆን አለበት?"

"ብዙም ከእውነታው አልራቁም። ከብዙ ምዕተ ዓመታት በፊት በሰሜን ኢትዮጵያ የቤተ እሥራኤሎችን አመጽ የመራች፣ ክርስቲያናዊውን መንግሥት የገለበጠችና ለብዙ ዓመታት የገዛች የነፃነት መሪ ነበረች።"

"እ! በጣም አስደናቂ ነው!" አለች ልዕልቲቱ።

"ምኑ ነው ያስደነቀሽ?"

"ስሟን ከነ አመጻኛነቱ መውረስሽ?"

ዮዲት ጧ! ብላ በሳቅ ፈነዳች። የሁለቱ ውይይት ወዴት ያመራ ይሆን እያሉ ሲጨነቁ የነበሩት እንግሊዛውያዊው አምባሳደርና ሚንስትሩ አቶ ኢብራሂም አብረው ሳቁ።

"የተከበሩ ልዕልት። በጣም ቀልደኛ ነምት።"

"እመሰግናለሁ።"

"እሸባሪ አይደለሁም።"

"ሆንሽም አልሆንሽ የጀመርሺውና የያዛችሁት አደገኛ ጨዋታ የማይሳካና መጨረሻው የማያምር መሆኑኑ ላስጠነቅቅሽ እወዳለሁ።"

"ምን ማለትም ነው ልዕልት? የኤስ.ኤ.ኤስ ኮማንዶዎቻችሁ ያስጥሉናል ብለው ያምናሉ?" አለች ዮዲት ቆጣ ብላ።

"ጥያቄው ያስጥሉናል ወይንም አያስጥሉንም አይደለም። እኔ ልነግርሽ የሞከርኩት አይሳካላችሁም! ስል ነው።"

"እኔ ደግሞ በጣም ላረጋግጥልዎ የምወደው. . ." አለችና ዮዲት ወደ ልዕልቲቱ ጆሮ አፏን አስጠግታ....."ይሳካልናል። ምክኒያቱም ልዕልትነትዎም ይተባበሩናል!" አለቻቸው።

"እንዴት?" አሉ ልዕልት በመገረም።

ዮዲት ማስረዳት ጀመረች።

**********//////////**********

አንድ ሜትር ተኩል ያህል ከፍታ ያለው አበቦችና ሌሎችም የተዋቡ ዕፅዋት የበቀለበት ግንብ ላይ የቆመው ያፈት ከእምስት ሜትር ርቀት ጀምረው ከፊቱ የተኮለኮሉትን የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጋዜጠኞች በርጋታና በጸጥታ ሲቃኝ

ከጋዜጠኞቹ በስተኋላ ከሚገኘው የግቢው ዋና በር በኩል ሦስት ሰዎች በቀጥታ ወደ ስብሰባው ሥፈራ ሲመጡ ተመለከተ። ሁለቱ ሰዎች ቀደም ሲል ኮሎኔል ሰናይ እና ሻለቃ ፍቅሩ ሲሉ ራሳቸውን ያስተዋወቁት ሲሆኑ ከመሃላቸው የሚራመደውን እና አነስተኛ የሰነድ ማሕደር የያዘውን ሰው ግን አያውቀውም። 'ይህ ሰው ከርዕሰ ብሔሩ የተላከ ዋናው ተደራዳሪ መሆን አለበት' ሲል አሰበ።

**********////////**********

"የተከበራችሁ ጋዜጠኞችና የመንግሥት ባለሥልጣናት!" ሲል ንግግሩን ጀመረ። ግቢው ወዲያውኑ ጸጥ ረጭ አለ። እጅግ ዘመናዊ የምስልና የድምጽ መቅረጫዎች ሥራቸውን ከመጀመራቸው የያፈት ምስልና ድምጽ ለመላው ዓለም በቀጥታ መተላለፍ ጀመረ።

"እኔና ባልደረቦቼ አሸባሪዎች አለመሆናችንን ለማሳመን የምናገረው አይኖረኝም። እኛ የምንጠይቀው አንድና አንድ ጥያቄ ብቻ ነው። ቅርሳችንን መልሱልን!"

ያፈት ይህን አለና የለበሰው ሳፋሪ ጃኬት ኪስ ውስጥ እጁን ከቶ አንድ ጥቁርና አነስተኛ ገመድ የመሰለ ነገር አውጥቶ ወደ ላይ ከፍ በማድረግ ለካሜራዎቹ እንዲታይ ካደረገ በኋላ..... "ይህ የምትመለከቱት ከአንድ መቶ አርባ ዓመታት በፊት የሰር ሮበርት ናፒዮር ጦር የመቅደላን አምባ በወረረበት ጊዜ ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ሕይወታቸውን ሲያጠፉ የእንግሊዝ ወታደሮች ከራሳቸው ላይ ቆርጠው የወሰዱት የጀግናው ንጉሣችን ሹሩባ ነው።"

"ለመሆኑ ይህ የሀበሻው ንጉሥ የጸጉር ሹሩባ ለእንግሊዞች ምናቸው ነው?

**********////////**********

ከትምህርት ቤቱ ፊት ለፊት የሚገኘው ሕንፃ ላይ ያደፈጡት ሁለት አልሞ ተኳሾች (ስናይፐር) አቅርቦ የሚያሳይ መነፅር በተገጠመበት ዘመናዊና ኃይለኛ ጠመንጃዎቻቸው ያፈት ላይ አልመው አጠገባቸው የቆመውን የአለቃቸውን ትዕዛዝ ይጠባበቃሉ። የሻለቃ ማዕረግ ያለው አለቃቸው በያዘው የመገናኛ ራዲዮ በገባታና በምስጢር ቃላት ካወራ በኋላ ""በተጠንቀቅ ጠብቁ!"" አላቸው።

ዩኒፎርም የለበሱ የፖሊስ ሠራዊት አባላት ከግቢው ውጭ ያለውን አነባበቢ ተቆጣጥረው ከተፈቀደላቸው ጋዜጠኞችና ባለሥልጣናት በስተቀር ማንም ወደ ግቢው እንዳይዘልቅ አግደዋል።

**********////////**********

የተሰበሰቡት ጋዜጠኞች ጥያቄ የማቅረብ ዕድል ለማግኘት እጆቻቸውን አነሱ።

ቪ.ኦ.ኤ- "ልዕልቲቱና የታገቱት ሰዎች በምን ሁኔታ ላይ ይገኛሉ?"

ያፌት- "ሁሉም በመልካም ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ። በቀረበላቸው ቡና እየተዝናኑ ነው።"

ቢ.ቢ.ሲ.- "ያቀረባችሁት የቅርሳችን ይመለስ ጥያቄ ቢመለስ እንኳ ከቅጣት እናመልጣለን ብላችሁ ታምናላችሁ?"

ያፌት- "ይህ የኛ ችግር ብቻ ነው።"

የኢትዮጵያ ራዲዮ- "አሁን ከያዛችሁት የቅርስ ማስመለስ መንገድ የተሻለ ዘዴና አማራጭ አልነበራችሁም?"

ያፌት- "እኛ የቅርሶችና የታሪክ ባለሞያዎች ነን። ይህ ሙያችን በፈጠረው አጋጣሚ ሁሉ የተዘረፉ ቅርሶቻችንን ለማስመለስ አታካች ጥረቶችን አድርገናል። የማይናቁ ስኬቶችንም አግኝተናል። አሁን የተያዘው "ቅርሶቻችሁን እናውሳችሁና አይታችሁ መልሱ!" የሚሉት የንቀት ጨዋታ ግን ከግፈኝነት በላይ የዘለለ ወንጀል ነው!" (ያፌት ይህን ጥያቄ የመለሰው በዐማርኛ ቋንቋ ነበር።)

ኤ.ኤፍ.ፒ- "እነዚህን ቅርሶች በኃይል ብታስመልሱ እንኳ የት እናስቀምጣቸዋለን ብላችሁ ታስባላችሁ?"

ያፌት- "ካሁን በኋላ የዘራፊ መንግሥታት እጆች የማይደርሱበት ሥፍራ!"

የተሰበሰቡት ጋዜጠኞች ሳቁ። ከሦስቱ የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት በስተቀር። ያፌት ከዚህ በኋላ የተለያዩ አምስት ጥያቄዎችን መለሰና. . ."ለዛሬው ይበቃናል! እዚህ ተገኝታችሁ ስላነጋገራችሁኝ አመሰግናለሁ።" ብሎ ከቆመበት ሥፍራ ሊወርድ ሲል . . .

"ከዚህ ሥፍራ ቅርሶቹን ይዛችሁ ለመውጣት የሚያስችለውን ዋናውን ጥያቄያችሁን ያቀረባችሁ አይመስለኝም!" ሲል የፊረንሳይ ዜና ወኪል ጠየቀ።

"አሁን ያልከውን ጥያቄ በተመለከተ ነገ ልክ በአሁኑ ሰዓት እዚህ ስፍራ መግለጫ ስለምንሰጥ ብትገኙልን እናመሰግናለን።" አለና ከግንቡ ላይ ዘሎ ወረደ። ወደ አዳራሹ መንገድ ሲጀምር የእጅ ካሜራዎችና የድምጽ መቅረጫዎችን የያዙ ጥቂት የባሕር ማዶ ጋዜጠኞች ገደቡን በማለፍ እየተንጫጩ ያፈትን መከተል ጀመሩ። ፖሊሶቹ በትግል እና በማግባባት መለሷቸው። ሦስቱ ባሥልጣኖች ብቻ ያፈትን ሲከተሉ ፖሊሶቹ አሳለፏቸው።

**********////////**********

ከኋላው የእግር ኩቴዎች ቢሰሙትም ካዳራሹ የአምስት ሜትር ርቀት ብቻ ሲቀረው ነው ያፈት ፊቱን አዙሮ የቆመው። አዳራሹ በግማሽ ሜትር ስፋት ብቻ ተከፍቶ ኤ.ኬ 47 አውቶማቲክ ጠመንጃ የያዘው ሳምሶን አጠገብ ሲደርስ ቆመ።

"እርስዎን ማን ልበል?" ሲል ከኮሎኔል ሰናይ እና ከሻለቃ ፍቅሩ መሃል የቆሙትን በመካከለኛ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ሰው ጠየቃቸው።

"ግርማይ በርሄ እባላለሁ። የጠቅላይ ሚኒስትሩ ልዩ ረዳት ነኝ። እዚህ የመጣሁት የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩን መልዕክት ላደርሳችሁና ይህ የጀመራችሁት የሀገራችንን መልካም ገጽታ የሚያጠፋ ተግባር በሠላም የምንፈታበትን መንገድ ከናንተ ጋር ተነጋግረን ለመቋጨት ነው።"

"ይህን ችግር ለመፍታት እዚህ ድረስ በመድከምዎ አመሰግንዎታለሁ።"

"ጠቅላይ ሚንስትሩ ይህን ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመቋጨት ከካቢኔያቸው ጋር አስቸኳይ ውይይት ካደረጉ በኋላ ይህን የመፍትሄ ሐሳብ ልከዋል" አሉና ባለሥልጣኑ በማህተምና በፊርማ የደመቀ አፊሺያል መንግሥታዊ ደብዳቤ አቀበሉት።

**********////////**********

"የኛ ካቢኔ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ቅርሶቻችንን ለማስመለስ ያደረገውን አታካች ጥረቶችና ያገኛቸውን ቀላል የማይባሉ ስኬቶች ታውቃላችሁ ብዬ አምናለሁ። ነገር ግን ይህ አሁን የፈፀማችሁትና እጅግ የተከበሩ እንግዶቻችንን ያገታችሁበት ተግባር ከወንጀልና ከሽብር ተግባር አንዲት ጋት እንኳን ዝቅ እንደማይል አበክራችሁ ታውቃላችሁ ብዬ አምናለሁ። ዛሬ በውሰት ወደ አገራችን የመጡትን እና በናንተ እጅ የወደቁትን ቅርሶች እዚሁ ለማስቀረት ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት

በማድረግ ላይ ሳለን የናንተ የኃይል ጣልቃ ገብነትን ጥረታችንን በማክሸፍና ያገራችንን መልካም ገፅታ በማበላሸቱ አዝነናል። የሆነው ሆኗል። በኛ በኩል ይህ ክስረት በሠላም እንዲያበቃ . . .

1. በቅድሚያ የያዛችኋቸውን ታጋቾች በሙሉ ያለአንዳች ጉዳት ለረዳቱ አንድታስረክቡ።
2. ያላንዳች ቅድመ ሁኔታ እጃችሁን ለመንግሥት እንድትሰጡ።
3. ይህን ያለማወላወል ከፈፀማችሁ እስከ ዛሬ ቅርሶቻችንን ለማስመለስ ያደረጋችሁትን 'ሕገ-ወጥ' ጥረት ግምት ውስጥ በማስገባት፣ እንዲሁም ሕጉን የመተርጎምና የማስፈፀም ግዴታ ስላለብን ብቻ በጣም አነስተኛ ቅጣት ተቀብላችሁ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በምሕረት የምትወጡበትን መንገድ የምናመቻች ለመሆናችን ቃል እንገባላችኋለሁ።

ፊርማ አለው

ማህተም የማይታይ

ያፌት ደብዳቤውን አንብቦ ቀና አለና ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ረዳት የሽሙጥ ፈገግታ እያሳየ "ይህን የክቡር ጠቅላይ ሚንስትር የመፍትሄ ሐሳብ ከባልዳረቦቼ ጋር ከተወያየሁበት በኋላ መልሱን በነገው ዕለት በምንለጠው ጋዜጣዊ መግለጫ አሳውቅዎታለሁ። ደብዳቤውን ይቀበሉኝ!" አለና መንግሥታዊውን ደብዳቤ ለባለስልጣኑ ዘረጋላቸው።

"ከባልደረቦችህ ጋር አሳይተህ ልትወያይበት ትችላለህ።" አሉት።

"አመሰግናለሁ!" ብሎ ያፌት እጅ ነሳ።

"የታላቋ ብሪታኒያን ልዕልትና አምባሳደሩን፣ እንዲሁም አምስቱን እንግሊዛውያን ምኞት በሌለው አያያዝ እስከ ነገ ማቆየቱ ከፍተኛ በደልና አደጋ ማድረስ ይሆናል። ስለዚህ የምክራችሁን ውጤት ቢበዛ በሁለት ሰዓታት ውስጥ ብታሳውቀኝ መልካም ነው። ከትምህርት ቤቱ ፊት ለፊት የሚገኘው ሕንፃ ውስጥ ጊዜያዊ ቢሮዬን ከፍቻለሁ። በስልክም የማያቋርጥ ግንኙነት ልናደርግ እንችላለን።"

"እሞክራለሁ ጌታዬ። ለማንኛውም የነገው ፕሬስ ኮንፈረንስ እንዳይስተጓጎል!"

"ከሁለት ሰዓት በኋላ!" አሉና አቶ ግርማይ ወደ ኋላ ዞረው መንገድ ጀመሩ። ያፌት በፈገግታ ሸኛቸው።

ምዕራፍ ሰላሳ ሶስት

መኪናው ከመቆሙ መቶ አለቃ ሳሙኤል ሹፌሩን "ተከተለኝ!" አለና የፎቁን ደረጃዎች በሩጫ መውጣት ጀመረ። ሦስተኛው ፎቅ ማረፊያ ላይ ሲደርስ ቆም ብሎ የቢሮዎቹን የስም ዝርዝር የተግፈበትን ሠሌዳ ማየት ጀመረ። "ቅርሳችን ይጠበቅ" ቢሮ ቁጥር 105 የሚል በር ከፊት ለፊቱ ሲያይ ትንፋሹን ዋጠና። የግራ ጎኑን በቀኝ እጁ ጻሰስ አድርጎ ማካሮቭ ሽጉጡ መኖሩን ካረጋገጠ በኋላ በዝግታ እርምጃ ወደ በሩ ሄዶ ጎላ ባለ ምት ሦስት ጊዜ በሩን ሲያንኳኳ አሽከርካሪው ፖሊስም ጥቁር ማካሮቭ ሽጉጡን አቀባብሎ ከበሩ ስር አደፈጠ።

ጥቂት ጠበቀ። እንደገና ኃይሉን ጨምሮ ደጋግሞ በሩን መታው። ምንም መልስ የለም። ወደ አሽከርካሪው ዞሮ "ይህንን በር መስበር እንችልም?" ሲል ጠየቀው።

"መስበር እንችላለን። ግን .. መቶ አለቃ ... የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ይዘሃል?"

ሞባይል ስልኩን አወጣና ቁጥሮች መታ።

"ሃሎ ኮሎኔል። የቅርሳችን ይጠበቅ ማሕበርን የመፈተሻ ትዕዛዛ ከፍርድ ቤት ለማውጣት ጊዜ የለኝም። ረዳት መርማሪዎችን ቢልኩልኝ? አመሰግናለሁ።" አለና እንደገና ሌላ ስልክ መታ።

"ኮሎኔል ዘገዬ፣ እኔ ቅርሳችን ይጠበቅ ማሕበር ነው ያለሁት። ወደ ብራና አስጎብኚ ሊሄዱልኝ እና . . ."

"እሺ አመሰግናለሁ።" ስልኩን ዘግቶ ኪሱ ጨመረና ጥቁር ማካሮቭ ሽጉጡን አቀባብሎ በሰደፉ በሩን ደጋግሞ በኃይል መታው። ምንም ምላሽ የለም። "ስበረው" አለና ከበሩ ላይ ገለል ብሎ ቆመ። ግዙፉ አሽከርካሪ ወደ ኋላው አምስት እርምጃዎች ያህል አፈግፍጎ እንደ ተዋጊ በሬ የቀኝ ትከሻውን አስቀድሞ በሩ ላይ ተወረወረ።

ሳሙኤል የበሩን መሰበር ወይንም የሹፌሩን በግጭቱ መጎዳት ነበር የጠበቀው። ነገር ግን ሌላ ያልጠበቀው ነገር ተከሰተ። ሹፌሩ በሩን ለመስበር በተወረወረበት ቅፅበት ከውስጥ በኩል በሩ በድንገት ወለል ብሎ ተከፈተ። እናም እንደ ኮርማ የተወረወረው ሹፌር እንደ ትንታግ እየሾረ ወደ ቢሮው ሰተት ብሎ ገባ። ወዲያው ሌላም ያልተጠበቀው ነገር ተከሰተ። የቀለጠ ሉሉታ ከውስጥ በኩል ተሰማ። በሹፌሩ ሁኔታ ሳቅ ጀምሮት

የነበረው ሳሙኤል ባልጠበቀው ኡኡታ ተደናግጦ ሽጉጡን በሁለት እጆቹ ወድሮ ተንደርድሮ ሲገባ ኡኡታው ጨምሮ ሕንፃውን እናወጠው።

"ዝም በይ! አይዞሽ ፖሊሶች ነን!" አለ ሳሙኤል የመታወቂያ ካርዱን በግራ እጁ እያወጣ። አላመነችውም። እንደ አዲስ መጮህ ስትጀምር ዘሎ አፏን በግራ እጁ አፈነው።

"ፖሊስ ነኝ! ዝም በይ!" እንደብራቅ ጮኸባት።

ወዲያውኑ ፀጥ አለች። "አይዞሽ። እኔ ፖሊስ ነኝ። ነይ እዚህ ወንበር ላይ አረፍ በይ።" እየገፋፋ የእንግዳ መቀበያው ወንበር ላይ አስቀመጣት።

የሳሙኤል ሹፌር ከቢሮው የውስጥ ግድግዳ ጋር ተጋጭቶ ነበር የቆመው። አሁንም ሽጉጡን ይዟል።

"እንቺ ማን ነሽ? በሩን ለምን አልከፈትሽም?" አለና ወደ ሹፌሩ ዞሮ የውስጠኛውን ቢሮ ፈትሽ!" አለው። ሹፌሩ በሩን ከፍቶ ገባ።

"እኔ ፀዳለ ነኝ የጽዳት ሠራተኛ።"

"ደጋግሜ በሩን ስደበድብ ለምን አልከፈትሽም?"

"እንቅልፍ ጥሎኝ ነበር።" አለች እየተርበደበደች። "እትዬ ሰናይት እና እትዬ ራሄል ሲዘገዩ ፈራሁና ከውስጥ በሩን ዘግቼ ሶፋው ላይ አረፍ ብዬ ስጠብቅ . .."

"ሰናይት ማን ናት?" ሳሙኤል አቋረጣት።

"የቅጥር ጸሐፊዋ።"

በዚያች ቅጽበት ከበስተጀርባው የእግር ኮቴና "ምንድነው? ምን ተፈጠረ?" የሚል ድምፅ ተሰማው።

የጽዳት ሠራተኛዋ "እትዬ ሰናይት!" ብላ እንደገና ማልቀስ ጀመረች።

**********////////**********

በኤር-ባስ- ኩባንያ የተሠራው C-130-A 'አቪየተር' የተባለ የሮያል ኤር-ፎርስ ወታደራዊ አውሮፕላን ከለንደን በቀጥታ በረራ ቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ደረሰ። ኤስ.ኤ.ኤስ ልዩ ኮማንዶ ጦር በዓለም ዙሪያ ለሚያደርገው ተልዕኮ ታልሞ የተገነባ ስለሆነ ከ150-160 ሰዎችን የሚይዙና ተዘርግተው መኝታ የሚሆኑ ምቹ ወንበሮች፣ ለቀዶ ጥገና ጭምር የሚያገለግል የሕክምና ክፍል ያለውና በሦስት አብራሪዎች፣ በሦስት ሐኪሞች፣

በአምስት የምግብና መስተንግዶ ሠራተኞች፣ በሁለት የራዳርና የግንኙነት ቴክኒሽያኖች የተደራጀ እጅግ ዘመናዊ አውሮፕላን ነው።

'አቪዮተር' ቦሌ ሲያርፍ ሠላሳ የኤስ.ኤስ ኮማንዶዎችን እና አምስት የስኮትላንድ ያርድ ፖሊስ መርማሪዎችን ይዞ ነበር።

ሌ/ኮሎኔል ዘገየና የጠቅላይ ሚኒስትሩ ልዩ ረዳት አቶ ግርማይ በርሄ እንዲሁም የእንግሊዝ ኤምባሲ ዋና ጸሐፊ ቡድኑን ከተቀበሉት በኋላ ወዲያውኑ መንግሥት ባቀረባቸውና ምንም ዐይነት መለያ ባልተለጠፈባቸው አሥር ዘመናዊ ሚኒባስ ተሽከርካሪዎች ከነ ሙሉ ትጥቃቸውና መሣሪያዎቻቸው ተሳፍረው፣ ከፊት ሞተረኛ ፖሊስ መንገድ እያስከፈተላቸው በከፍተኛ ፍጥነት ወደ እንግሊዝ ኤምባሲ ገሰገሱ።

**********/////////**********

"ወይዘሮ ሰናይት" አለ ሳሙኤል። "የቅርሳችን ይጠበቅ ማሕበር አባል ነሽ?"

"አይደለሁም፣ እኔ የቅጥር ጸሐፊ ነኝ። እዚህ ሥራ ከጀመርኩ ሁለት ዓመት ሆኖኛል።"

ሰናይት ወንበር ላይ ተቀምጣ ከተረጋጋች በኋላ ነበር መቶ አለቃ ሳሙኤል ቃለ መጠይቁን የጀመረው።

"የድርጅቱ ቋሚ አባላት እነማን ናቸው?"

"ዶክተር አንዱ ዓለም ይፍረደው፣ ወይዘሪት ራሄል፣ ያሬድ መልካሙ፣ ያፌት ኖህ፣ ዮዲት . . . የተባሉት ናቸው። ሌሎች ቢያንስ በጠቅላላ ጉባኤ ላይ ብቻ የሚገኙ በርካታ አባላት አሉ። ዝርዝራቸውን ልሰጥህ እችላለሁ።"

"እባክሽን!"

ሰናይት ከወንበሯ ተነስታ የፋይል ካቢኔቱን ከፈተችና አንድ እነስተኛ ሰነድ አምጥታ ሰጠችው።

ዶሴውን እየገለጠ ለአሥር ደቂቃዎች ያህል ተመለከተና "ያልነገርሽኝ መረጃ አለ። ለምጠይቅሽ ጥያቄ ያልተሟላ መልስ ከሰጠሽኝ መረጃ ከፖሊስ በመሸሸግ የሕግ ጥሰት ትጠየቂያለሽ።" አላት።

"የዘነጋሁት የድርጅቱ መሥራች የሆኑት ባህታዊው እኔ ከመቀጠሬ በፊት ከንቁ ተሳታፊነት የተገለሉ ስለሆነ ነው። በዝና ብቻ ነው የማውቃቸው።"

"አሁን የት ነው የሚኖሩት?"

"እኔ አላውቅም::"

"ሌላ የረላሽው የለም?::"

"እ ... ይቅርታ! ሳምሶን ኃይሌ የሚባል የብራና አስጎብኚ ድርጅት ሹፌር አለ:: እርሱም የቅርሳችን ይጠበቅ ማሕበር አባልና ተሳታፊ ነው::"

"እዚህ ቢሮ ውስጥ ሰሞኑን ስለነበሩት እንቅስቃሴዎች እስቲ አንድ በአንድ አስረጅኝ::"

ሰናይት በረጅሙ ተረከችለት:: እርሱም በፀጥታ እያዳመጠ ማስታወሻ ሲጭር ቆየና አንድ ቦታ ላይ አስቆማት:: "ወይዘሮ ሰናይት! ወይዘሮ ራሄል ሰሞኑን ከመኖሪያ አፓርትመንቷ ሌላ አዲስ ቤት ተከራይታለች ነው የምትይኝ?"

"አዎን የኪራይ ውሉን የዘጋጀሁት እኔ ነኝ:: እትዬ ራሄል እንደነገረችኝ በቅርቡ ልታግባ ስለሆነ ሰፋ ያለ ቤት ያስፈልገኛል ብላ ነው ቤቱን የተከራየችው::"

"የቤት ኪራይ ውሉ ኮፒ አለሽ?"

"ሰነዱን ኮምፒውተሬ ላይ 'ሴቭ' አድርጌዋለሁ::"

"እባክሽን ፕሪንት ታደርጊዋለሽ?"

ሳኤል የኪራይ ውል ቅጹን ተቀብሎ ከቢሮው ወጣና ኮሪደሩ ላይ ሆኖ ስልክ ደወለ::

"ኮሎኔል፣ ሰናይ እባክዎን አንድ ድጋፍ ሰጪ የምርመራ ቡድናችን አሁን ወደምሰጥዎት አድራሻ ወይንም ቤት ባስቸኳይ ይላኩና ቤቱ ውስጥ የተገኙ ሰዎችና ማናቸውንም መረጃ ሁሉ በቁጥጥር ስር እንዲያውሉ፣ ሌላ ቡድን ደግሞ ብራና አስጎብኚ ድርጅትን እንዲፈትሽ ይዘዙልኝ::"

"አመሰግናለሁ::" ስልኩን ዘጋና ወደ ቢሮው ተመለሰ::

"ወይዘሮ ሰናይት:: የባሕታዊውን ቤት በእርግጥ አታውቂም?"

"እንኳንስ ቤታቸውን መልካቸውንም አላውቀውም::"

"የስንት ልጆች እናት ነሽ?"

"የሁለት::"

"ዕድሜያቸው?"

"አስርና አሥራ ሁለት ዓመት" አለች እንባ እየተናነቃት።

"እዚሁ እቢሮሽ ትቼሽ ብሄድ አትጠፊም?"

"ለምን ብዬ? እኔ ልጆቼን ማሳደግ የምፈልግ ተቀጣሪ ሠራተኛ ነኝ። ወንጀለኛ አይደለሁም። አልሸሽም።"

"በጣም ጥሩ። እንደ ተለመደው ዛሬም ምን ጊዜም መደበኛ ሥራሽ ላይ ትቆያለሽ። ስፈልግ በአካል ወይ በስልክ አናግርሻለሁ። እስከዚያው የባሕታዊውን ወሬ ለማፈላለግ ሞክሪ። በተጨማሪም አንቺን እና ቢሮውን በስውር የሚጠብቁ የደህንነት አባላት መኖራቸውን አትርሺ።"

ሰናይት በእሽታ ራሷን አወዛወዘች።

**********//////////**********

የእንግሊዝ ኤምባሲ ግቢ አንድ ሰፊ የእንግዶች መቀበያ ቤት ውስጥ ተሰብስበዋል።

"የተከበራችሁ የስኮትላንድ ፖሊስ ያርድ ምርመራ ቡድን አባላት። እንዲሁም የኤስ-ኤ-ኤስ ጦር አባላት። አሁን በኛ በኩል አስፈላጊ የተባሉትን ዝግጅቶች ሁሉ ስላጠናቀቅን እና አገታው ከተፈፀመበት ትምህርት ቤት ፊት ለፊት በጥቂት ሜትሮች ርቀት ላይ የሚገኘውን ባለ አራት ፎቅ ሕንፃ ስላስለቀቅንላችሁ አሁኑኑ ወደዚያው እንንቀሳቀሳለን።" በማለት የጠቅላይ ሚኒስትሩ ልዩ ረዳት አሳወቁ። የኮማንዶውና የምርመራ ቡድኑ አባላትም ወደተባለው ሥፍራ ተነቃነቁ።

**********//////////**********

ይህ ቡድን ከትምህርት ቤቱ ፊት ለፊት ያለው ሕንፃ ላይ በሠፈረ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ዝግጅቱን ጀመረ። የእንግሊዝ ፖሊስ የፀረ ሽብር ምርመራ አባላት ሁለተኛው ፎቅ ላይ ጊዜያዊ የምርመራ ቢሮ ሲከፍቱ የኮማንዶው አባላት ደግሞ የመጨረሻው ፎቅ ላይ እጅግ ዘመናዊ የሆኑ የመገናኛና የስለላ መሣሪያዎቻቸውን ማስተካከል ጀመሩ። ይህን ካጠናቀቁ በኋላ ኮሎኔል ዘገዬ ከፎቅ ወርደው ፍራሽና የመኝታ ከረጢቶችን የጫነው መለስተኛ ካሚዎን እንዲሁም የእንግሊዝ ኤምባሲን ፎርድ መለስተኛ አውቶቡስ እየመሩ ወደ ትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ዘለቁ።

ምዕራፍ ሰላሳ አራት

የሰሜን ስኮትላንድ ደጋማና ተራራማ ወረዳ ውስጥ የተገነባው ካስል የሦስት መቶ ዓመታት ዕድሜውን ሊያከብር ጥቂት ሳምንታት በቀሩት በዚህ ወቅት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የልዕልት ኢዛቤል እና የቅርሶቹን ባልታወቁ "ውዳቂና ኋላ ቀር" ፍጡራን መታገት ምክንያት በማድረግ ሰር ዶይል ኦ ሱሊቫን በእርሱ አባባል "ያስቸኳይ ጊዜ" እንግዶቹን በማስተናገድ ላይ ነው።

ካስሉ ከአሥር ሺህ ካሬ ሜትር በላይ ስፋትና ወርድ ባለው መሬት ላይ ከተራራው ወገብ ጥቂት ዝቅ ብሎ ነው የተገነባው። በዚህ ሰፊ የኦ-ሱሊቫን ርስት ውስጥ ወንዝ፣ ጥቅጥቅ ያለ ደን፣ አነስተኛ ሃይቅ፣ እና ባካባቢው ነዋሪዎች በፍርሃትና በሹክሹክታ የሚወራለት "የሰይጣን ማምለኪያና ሰብአዊ መስዋዕት ማቅረቢያ" ቤተ-አምልኮንም ይዟል።

ሰር ዶይል ኦ ሱሊቫን ዕድሜው ሰባ አምስት ዓመት፣ ፀጉሩ እንደ ዛገ ብር ሸብቶ የወየበ፣ ቁመቱ ወደ 2 ሜትር የሚደርስና ወቅታዊው ባለ ርስት ነው። "ይህ ካስል ብቻ አይደለም ርስቱ" ይላሉ በቅርቡ የሚያውቁት ሰዎች መላዋ ዓለም ርስቱ ናት!"

ኦ-ሱሊቫን ከአንድ ሺህ ዓመት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረውና 'ስከል -ኤንድ-ቦን' (አፅምና የራስ ቅል) የተባለው እጅግ ምስጢራዊ፣ ፀረ-ክርስቶስ እና ዓለምን ለመቆጣጠር የተነሳ ድርጅት መሪ ስለመሆኑ ብዙ ብዙ ተጽፏል፣ ተነግሯል። ከሚፃፍለትና ከሚወራለት ብዛት አንፃር የዚህ ሰውና የድርጅቱ ነገር "አፈ ታሪክ ወይንም ተረት ተረት" ለመሆን የተቃረበ ይመስላል።"

ተረት ተረት ላለመሆኑ ማስረጃው ይህ የዛሬው 'ያስቸኳይ ጊዜ' ስብሰባ ነው። የተንጣለለው "አንቲክ" ሳሎን ውስጥ የማንደጃው እሳት ግው ብሎ ነዶ ክፍሉን አሙቆታል። ሰፊውና ረጂሙ የገበታ ጠረጴዛ አናት ላይ የተቀመጠው ሽማግሌውና አስፈሪው፣ አፈ ታሪኩ ኦ ሱሊቫን ነው። የጥንታዊ 'ፍሪማሶን' ወይንም የመካከለኛው ዘመን ጦረኛ መሣፍንት (Kinght Templar) ሙሉ የጦር ልብስ ነው ለብሷል።

ከርሱ በስተቀኝ የእንግሊዝ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ጸሐፊ (ሚንስትር) ሚስተር ማካርቲ ተቀምጠዋል።

ከሚንስትሩ ፊት ለፊት የተቀመጠው የተባበሩት መንግሥታት የባህል፣ የሳይንስና የትምህርት ድርጅት "ዩኔስኮ" ዳይሬክተር፣ አሜሪካዊው ማክስ ጎድፍሬይ ነው። ከርሱ ጎን የተቀመጠው የብሪቲሽ ናቹራል ሂስትሪ ሙዚየም ዳይሬክተር ፕሮፌሰር ፍሊፕ ቱይለር ነው። ከፕሮፌሰሩ ትይዩ የተቀመጠው ደግሞ በወግ አጥባቂ አለባበሱና ካፋ በማይለያት ፒፖው የሚታወቀው የኤም.አይ.ሲክስ (የእንግሊዝ ዋነኛውና የውጭ የስለላ ተቋም) ምክትል ዳይሬክተር ሰር ዳላስ ፍሬድ ነው።

'ይህን ሁሉ ምግብ ሊበሉት . . .እ . . ልንበላው ነው የቀረበው?' ሲል ፍሪድ በሐሳቡ ራሱን ሲጠይቅ ነበር።

አምን ምግቡ ተበላ . . ዕድሜው ብዙ የሆነው ውድ የወይን ጠጅ ተከፍቶ በየመለኪያቸው ተንቆረቆረ።

'የእሳቱ ብርሃን ወይን ጠጁ ላይ ሲያርፍ ቀለሙ በጣም ይቀላል' ፕሮፌሰር ፍሊፕ ያስባል። 'የሰው ደም ይመስላል።'

"እናንተ ሕፃናት!" አለና አዛውንቱ ኡ-ሱሊቫን በጥንታዊ ሠይፉ ሰደፍ የገበታ ጠረጴዘውን ደለቀው። 'የሰው ደም' የተቀዳባቸው የወይን መለኪያዎች ተንገዳግደው ሲቆሙ የተረጨው የወይን ጠጅ የገበታ ጠረጴዛ ልብሱን በደም ቀለም በከሉት። እንግዶቹም በድንጋጤ ከወንበራቸው ዘለሉ።

አዛውንቱ ባለፀጋ በሳቅ እሸክካ። "እናንተ ደደቦች! አሳሞች! ከብዙ መቶ ምዕተ ዓመታት ጀምሮ ስናስሳቸው፣ ስናነፈንፋቸው ኖረን በብዙ ጥረትና መስዋዕትነት እጃችን ያስገባናቸውን ብርቅና ድንቅ የብራና መጽሐፍት "እናውሳችሁ" ብላችሁ በእነዚያ አራዊቶች እጅ ውስጥ ጣላችሁት!" አለና መለኪያውን አንስቶ በአንድ ትንፋሽ ጨለጠው።

"ዛሬ እዚያ ያምልኩት ቤት ውስጥ ለመስዋዕት የተዘጋጀውን የአሥር ዓመት ሕፃን ለቅቂ እናንተን ነበር መስዋዕት ማድረግ የሚገባኝ!" አለና እንደ ድንጋይ ሙት በመሰሉና ቀለማቸው በጠፉ ዐይኖቹ አንድ በአንድ ተመለከታቸው። 'ጥሩ ነው። ሽንታቸውን ፓንታቸው ላይ ሲለቁት ተቃርበዋል!'

"እናንተ አሳሞች!! ቅርሱን ለምን፣ እንዴት . . . ወደ ኢትዮጵያ ላካችሁት? የሚል ደደብ ጥያቄ አልጠይቃችሁም። መልሳችሁ ደደብ እንደሚሆን አውቀዋለሁ። ቃሌ

አንድ ብቻ ነው! እነዚያን የብራና መጽሐፍት መልሳችሁ አምጧቸው። እዚህ . . . እኔ ዘንድ!"

ሁሉም በፀጥታ እንገታቸውን ደፉ።

ከመንግሥታት በስተጀርባ ሆነው መንግሥታትን እያሽቆጠቆጡ ያዛሉ፣ መሪዎችን ባሻቸው ሰዓት ያስቀምጣሉ፣ ይጥላሉ ከሚባልላቸው ድርጅቶች አንዱን "አጽምና የራስ ቅል" የተባለውን ምስጢራዊ ድርጅትን የሚመራው ሰር ኦ. ሱሊቫን ብድግ ብሉ ጥንታዊውን ሠይፉን ወደ ላይ ሲቀስር ሁሉም ተነስተው ወደ ላይ እንጋጠው በፀጥታ ቆሙ። ሽማግሌው የዓለም ገዥ እንግዶቹ በማያውቁት ጥንታዊ ቋንቋ ድግምት የመሰለ ንግግር (Ritual) ማነብነብ ጀመረ።

**********//////////**********

"ሃሉ! አሰ ዶክተር አንዱዓለም።

"የስኮትላንዱ ጸረ ክርስቶስ ጀምሯል። 'መጽሐፈ-ጥበብ'ን ገፅ 85 ላይ ግለጥና ድምፅ ሳታሰማ በለሆሳስ "መክታ-ዘ-መናፍስትን" ሰባት ጊዜ ድገም!" አለና ደዋዩ ስልኩን ዘጋው።

ዶክተር አንዱዓለም የባሕታዊውን ድምጽ አውቆታል መልዕክቱም ገብቶታል። እዚህ ስፍራ ላይ የተፋጠጡት ኮማንዶዎችና ቅርሳቸውን ለማስመለስ የተነሱ ዜጎች ብቻ አይደሉም። እዚህ ሥፍራ፣ እዚህ አዳራሽና በዙሪያው የተፋጠጡትና ሠይፍ የተማዘዙት የበጎና የክፉ መናፍስትም ናቸው።

አንዱዓለም ለትዕይንት የመጡት ብራናዎች ወደ ተደረደሩበት ሄደና "መጽሐፈ-ጥበብን" ገፅ 85 ላይ ገለጠው። ታሱንም ለመድገም ተዘጋጀ። የመከላከያ ድግምቱን ከመጀመሩ በፊት የባሕታዊው የቆየ ንግግር ትዝ አለው።

'እነዚህ የእንሽላሊት ዝርያዎች (ፊረንጆች) የሚፈልጉት ሀገራችንን የቅኝ ወይም የእጅ አዙር ቅኝ ተገዢ ማድረግ ብቻ ይመስልሃል? አይምሰልህ። ከሀገራችን የሚፈልጉት በጣም ረቂቁ ምስጢር አለ። በጀመሪያው የመስቀል ጦርነት ቅድስቲቱ ከተማ (ኢየሩሳሌም) ጎድ ፍሬይ በመራው ጦር ከተያዘች በኋላ እዚያችው እየሩሳሌም ውስጥ ጎድፍሬይ የመሠረተው ምሥጢራዊ ድርጅት ስሙን እየለዋወጠና በመላው ዓለም የንግድ፣ የፖለቲካ፣ የጦር፣ የሃይማኖት ያስተዳደር፣ መዋቅሮች ውስጥ ድሩን እያደራ ልክ እንደ

ካንሰር በሽታ ተሰራጭቶ ባሁኑ ዘመን 'ስውሩ የዓለም ገዢ' መሆኑኑ ታውቃለህ። እነዚህ ምስጢራዊ እና ኃያላን ባለፀጎች (illuminati) ኃይላቸውን የሚያደረጁት የገንዘብና መንግሥታዊ መዋቅሮችን በመቆጣጠር ብቻ አይደለም። ይልቁንም እኔ፣ አንተ፣ ምድሪቱ፣ ተፈጥሮ... ባጠቃላይ ሥነ—ፍጥረት የሚገዛበትን መንፈሳዊና የተቀደሰ ኃይል ሁሉ.....በ.....በ.....በመዝረፍ ልበለው? የራሳቸውን ኃይል ማዳበሪያ ያደርጉትና ለእኩይ ፍላጎታቸው ማስፈፀሚያ ያውሉታል።'

ዶክተር አንዱዓለም ገፅ 85 ላይ እጁን አሳርፎ እና የባሕታዊውን ንግግር እያስታወሰ ቀና ብሎ ልዕልት ኢዛቤልን ተመለከታቸው። ባለ 'ሰማያዊ ደም' የሚባለው የእንግሊዝ ንጉሣዊ ቤተሰብ በሙሉ፣ ልዕልት ኢዛቤልን ጨምሮ የዚህ ምስጢራዊና አምልኮ ባዕድ አራማጅ ድርጅት ቀንደኛ አባላትና የበላይ መሪዎች መሆናቸውን ያውቃል።

"መጽሐፈ ጥበብ" ገጽ ሰማኒያ አምስት ላይ ቀኝ እጁን አሳርፎ ልዕልቲቱን ሲመለከታቸው ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የነበራቸው የሰውነት መልክና ገጽታ እየተለወጠ . . . እየተለወጠ ከአንገታቸው በላይ ያለው ገፅታ ወደ እንሽላሊትነት የለወጠ መሰለው።

ዶክተር አንዱዓለም ከሰመመን ዐይነት ራእዩ ብትት ብሎ ባነነና የገፅ ሰማንያ አምስትን 'ኃይለ ሆሄያት' መድገም ጀመረ። ገና የመጀመሪያውን መነባነብ (ሪቹዋል) ከመድገሙ የስኮትላንዱ እርኩሰት ረቂቅ ኃይል እና ሕዋዊው ቅዱስ ኃይል (መፍትሄ ሥራይ) በላዩ ላይ፣ በዙሪያው፣ ባዳራሹ አካባቢ አየር ላይ ሠፍሬው የሞት—ሽረት ትግላቸውን ሲፋለሙ ይሰማው ጀመረ።

'እነዚህ ዓለምን በጭብጣቸው ውስጥ አውለው ለመቆጣጠርና ለመግዛት የተነሱ ጥቂት ሰዎች ያብዛኛዎችን ሀገሮች መንፈሳዊ ኃይል ዘርፈውና ተቆጣጥረው ሰራሳቸው ኃይል ማበልፀጊያ አድርገውታል። አሁን የቀራቸውና ለመቆጣጠር ያስቸገራቸው ኢትዮጵያ ውስጥ የሰፈፈውና ይህችን ጥንታዊት ሀገር የሚጠብቀው የተቀደሰ መንፈሳዊ ኃይል ብቻ ነው.....።'

ዶክተር አንዱዓለም በጣም... በጣም... በዝግታ፣ እያንዳንዷን የግዕዝ ፊደል በጣቱ እየቆጠረ፣ በዝግ አንደበቱ ሲደግም ከባህታዊው ማብራሪያ ባሻገር የስኮትላንዱ እርኩሰ መናፍስት (ኔጋቲቭ ኢነርጂ) ተጽእኖ ካዳራሹ ሕዋው ውስጥ ቀስ በቀስ በተሸናፊነት ሲገፍ ተሰማው።

**********//////////**********

ሽማግሌው ሰር ኦ' ሱሊቫን ድግምቱ ምትሃቱን ከጨረሰ በኋላ ሰውነቱ ዝሎና በላብ ተዘፍቆ እየተንዘፈዘፈ ጥንታዊ የፋርስና የሮማ ነገሥታት የመሰለ ዙፋኑ ላይ "ዘፍ!" ብሎ ተቀመጠ። በዙሪያው ቆመው ሲያመልኩ የነበሩት የዓለማችን ግዙፋንም በእኩይ መንፈስ እንደተወረሩ በየወንበራቸው ተከትለውት 'ዘፍ' አሉ።

"አልቻልኩትም! አልቻልኳቸውም!" አለና በጥንታዊውና የቀደምት ክርስቲያናችን ደም በጠገበው ሠይፉ ጠረጴዛውን ጠለዘው።

"ያንን የተረገመ ባሕታዊ መንፈስ አልቻልኩትም። እነዚያን በየ ዋሻውና በየጫካው መሸገው ላገራቸው የሚፀልዩ መነኮሳት እና ሼካዎችን መንፈስ (ፖዚቲቭ ኢነርጂ) አልቻልኩትም። እዚያ አዳራሽ ውስጥ ያሉትን አጋቾች ለማድከም መንፈሴን ስልክ እነርሱ ወዲያውኑ ያን ጥንታዊና ኃይለኛ መንፈላቸውን አዳራሹ ውስጥ አስፍፈው ድል ነሱኝ!" አለና ሽማግሌው በዚያ የሙት ዐይኖቹ አገልጋዮቹን ሰርስሮ አያቸው። "ትሰማለህ የታላቋ ብሪታኒያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር? ትሰማለህኛለህ የግርማዊነቷ ሰላይ?"

ሁሉቱ ባለሥልጣናት አንገታቸውን እንደቀለሱ "አዎን! ታላቅነትዎ!" አሉ።

"እነዚያን ቁሻሻና የተረገሙ አጋቾች፣ ቢያስፈልግ ከነ ታጋቾቹ ገድላችሁና ፈጅታችሁ ብራናዎቼን እንድታመጡ! ልዕልቲቱም ብትሆን መስዋዕት ትሁን! በእናሳ ዝርያዎች እጅ ከወደቀች እርሷም ብትሆን አትረባንም፣ አታስፈልገንም!"

ምዕራፍ ሰላሳ አምስት

ዶክተር አንዱዓለም ከስኮትላንዱ አርኩሰት ጋር በባሕታዊው አትኩሮተ ሕሊና እና በ "መጽሐፈ-ጥበብ ሐዋዊ ወ ምድራዊ" እየተረዳ ካደረገው የመንፈስ ጦርነት ባሸናፊነት ብትት ብሎ ሲባንን መላ አካላቱ በላብ ተዘፍቆ እየተንዘፈዘፈ ነበር። ዐይናቹን ሲገልጥ ከልዕልት ኢዛቤል ዐይኖች ጋር ተፋጠጠ። 'ይህች ሴት ሬፐታይል እንጂ የሰው ዘር አይደለችም' የሚል ጩኸት አዕምሮው ውስጥ አስተጋባ። ዴቪድ አይክ የተባለው ዝነኛ ተመራማሪ ጸሐፊ "የእንግሊዝ ንጉሣውያን ቤተሰቦችና ምሥጢራውያኑ የዓለማችን ገዥዎች (ሴክሪት ሶሳይቲስ- ካባልስ) በደረታቸው ተሳቢ (ሪፕታይልስ) ናቸው ..." በማለት የማይናቁ መረጃዎችን የተነተነበት 'And the truth shall set you free' የተሰኘ መጽሐፍ ትዝ አለውና 'እውነትም እንሽላሊት መስላለች' አለ ዶክተር አንዱዓለም ወደ ልዕልቲቱ እየተራመደ። አጠገባቸው ሲደርስ ልዕልት ኢዛቤል መላ አካላታቸው ተንቀጠቀጠ።

"ዶክተርዬ፣ ከልዕልት ጋር አንድ ዲያሎግ ይዘን ነበር።" አሉት ዮዲት ቡና ቀድታ እየሰጠችው።

"ምን ዐይነት?" አለና ቡናውን ተቀብሎ ፉት! አለው።

"ዶክተር!" አሉ ልዕልቲቱ ጣልቃ ገቡና። "ዮዲት በጣም ትምክህተኛ ናት። 'የብራና መጽሐፍቶቻችን የተራቀቁ የጥንታዊ ሥልጣኔ ቴክኖሎጂ ምሥጢሮችን ይዘዋል። እኛ ኢትዮጵያውያን ከናንተ የበለጠ የሠለጠን ነበርን.....' ትላለች። ታዲያ ሥልጣኔያችሁን ምን ዋጠው? በእርግጥ ሥልጡናች ከነበራችሁ የቴክኖሎጂያዊ ሥልጣኔያችሁ ቅሬት የታለ? ሃውልት ብቻ!" አሉ ፈገግ እያሉ።

'ፈገግ ስትል ደግሞ ፍውም አባብ መሰለች' አለና ዶክተሩ ቅፍፍ አለው። 'ዮዲት ግን የልዕልቲቱ መለወጥ አልታያትም' እያለ አሰበና ፈገግ ብሎ

"ክብርት ልዕልት . . ." አለ ልዕልቲቱ አጠገብ የነበረ ታሪካዊ ቅርስ በርጩማ ላይ ቁጭ እያለ።

"የኛ ሥልጣኔ እንደናንተ ቁሳዊ ሥልጣኔ ባለመሆኑ አልሠለጠናችሁም ማለትዎ ስህተት ነው። አንድ ምሳሌ ላሳይዎ . . ." አለና ወደ ዮዲት ዘወር ብሎ "መጽሐፈ ዣንሻርዋ ቀዳማዊ እና መጽሐፈ ሔኖክ (ቅጂ ብራና) አምጭልኝ" አላት።

ዮዲት ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሁለቱን ብራናዎች ይዛ መጣች። ዶክተሩ ብራናዎቹን ወለሉ ላይ አስቀመጠና ከሁለቱም ድርሳናት ውስጥ የሚፈልጋቸው ገጾች ላይ በጥንቃቄ ገልጦ ከለየ በኋላ ወደ ልዕልት ኢዛቤል ቀና አለ።

"ክብርት ልዕልት ኢዛቤል። የናንተ ዘመናዊ፣ 'ሳይንሳዊ' እና ቁሳዊ የቴክኖሎጂ ግሥጋሴና ሥልጣኔ መሆኑን፣ የእኛ ግን ጥንታዊ፣ በጥቂት ጠቢባን ብቻ የሚታወቅ ዕውቀት (esoteric) እንጂ ቁሳዊ ሥልጣኔ እንዳልሆነ ሲናገሩ ሰማሁ። በዚህ አባባልዎ ማዘን ሲገባኝ አላዘንኩም። ምክኒያቱም እናንተ 'ሥልጡን' አውሮፓውያን ጥንታዊና ቀደምቱን ዕውቀታችንን በእደባባይ እያጥላላችሁ፣ እየኮነናችሁ፣ እና ጠቢቡን ሁሉ 'መናፍቅ (Heretic)'እያላችሁ በእደባባይ፣ ከነሕይወቱ በእሳት በምታቃጥሉበት ጊዜ እንኳ የኛን ምስጢራዊና ረቂቁ ዕውቀት ስትዘርፉና ስትመራመሩበት ኖራችኋል።" አሰና ትክ ብሎ ካያቸው በኋላ "ጀምስ ብሩስን ብጠቅስልዎ ለሌብነታችሁ ጥሩ ማስረጃ አይሆንም?" ሲል ጠየቃቸው። ፊታቸው በሀፍረት ወየበ እንጂ መልስ አልሰጡትም።

"ዜጋችሁ ጀምስ ብሩስ የአባይን ምንጭ ለመፈለግ ሳይሆን ይህንን የምትመለከቹውን መጽሐፈ ሔኖክን ለመስረቅ ነው ወደ ኢትዮጵያ የመጣው። አምን ተሳክቶለትም ሰርቆ ወስደው። ይህ የሚመለከቱት ብራና ብሩስ የሰረቀው የኦሪጂናሉ 'መጽሐፈ ሔኖክ' ነው።"

"መጽሐፈ ሐየኖክ የተጻፈው በሔኖክ ኢትዮጵያዊ ነው። ሔኖክ በጠፈር ውስጥ እየተጓዘ፣ እናንተ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ከፀሓይና ጭፍሮቿ ባሻገር መገለል ያልቻላችሁትን እርሱ ከነሕይወቱና በሙሉ አካሉ አስትራል ትራቭል ተጠቅሞ ህዋው አቋራጭ ጉዞ በማድግ የጠፈር ምርምር ያካሂድ ነበር። እግዚብሔርም ማብራሪያ፣ መግለጫ፣ ትምህርት ይሰጠው ነበር። አምላክ ሔኖክን የሚያናግረው ሕዋው ውስጥ በበተናቸው አልፋ አዕላፍ ከዋክብቱ አቀማመጥ እየጻፈለት ነበር።"

አሁን ልዕልቲቱ መላ አካላታቸው ጆሮ ሆኖ በተመስጦ እያዳመጡት ነው።

"የናንተ ታላቁ አስትሮ ፊዚሲስት ማን ነበር ስሙ? ያ ሽባው!" አለ የሽሙጥ ፈገግታ እያሳያቸው። "እምን! ስቲፈን ሃውኪንግ እና እጅግ በተራቀቁ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎችና ሱፐር ኮምፒውተር ጭምር የታገዙት ሌሎቹም ሳይንቲስቶቻችሁ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ያልደረሱበትን የሥነ— ከዋክብት ምስጢር የኛው ሔኖክ ከብዙ፣ በጣም ብዙ ምዕተ ዓመታት በፊት የከዋክብቱን፣ የሥነ—ምሕዋር ምስጢራቸውን መርምሮና አውቆ ዕውቀቱን በመጽሐፈ ሔኖክ ትቶልን አልፏል።" አሰና አንዱዓለም ጥቂት ቆዘመ።

"አምን እንደምታውቁት አውቃለሁ። የናንተ ጀምስ ብሩስ ከደቡብ ኢትዮጵያዊ የዝዋይ ሐይቅ ገዳማት ሰርቆ የወሰደውን 'መጽሐፈ ሔኖክ' ሊመራመርበት የከረመው ጆሃንስ ኬፕለር የ'ሶላር ሲስተም ግኝት' ባለቤት መሆኑን አወጀ!"

አንዱዓለም ይህን ሲናገር ልዕልቲቱ የ"ተግባባን" ዐይነት ፈገግታ አሳዩት። እርሱም ፈገግ አለ።

የሁለቱን ውይይት እንግሊዛዊው አምባሳደርና የባሕል ሚንስትሩ አቶ ኢብራሂም ከማል በዝምታና በተመስጦ ያዳምጡ ነበር።

"ለመሆኑ" አሉ አምባሳደሩ። "የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን የሠሩት ንጉሥ ላሊበላን ለመርዳት የመጡ አውሮፓውያን መሆናቸውን አታምንም?"

"ለመሆኑ" አለ ዶክተር አንዱዓለም። "ለመሆኑ እናንተ አውሮፓ የሠራችሁትን የኒውክሊዮር ኃይል ማመንጫ ለምን ኢትዮጵያ ውስጥ አልሠራችሁትም?" አምባሳደሩ ትከሻቸውን ነቀነቁ ዝም አሉ።

"ከስምንት መቶ ዓመታታ በፊት 'ፍሪሪማሶን፣ ናይት ቴምፕላርስ ወዘተ ተብለው የሚጠሩት ምስጢራዊ ድርጅቶች በዓለማችን የሥነ ጥበብ ታሪክ ያልታዩትን የላሊበላ ሕንፃዎች ሀገራቸው ሳያንጹ አዚህ አቢሲኒያ የሚገነቡበት ምን ዐይነት አሳማኝ ሪዝን፣ ሱጂክ አለምት?" ሲል አምባሳደሩን ጠየቃቸው። መልስ ለመስጠት አልቃጡም።

"እነ አልበርት አነስታይን እና ሌሎችም ሊቃውንቶቻችሁ የአንቲ ግራቪቲ ምሥጢርን ለማግኘት በተለይም 'ዙፊላደልፊያ ኤክስፐርመንት' ተብሎ በሚታወቀው የምርምርና መከራ ፕሮጀክታቸው ላይ ታላቅ ውድቀት እንደገጠማቸው ይክዳሉ?. . . መልካም! ተፈጥሮን ከሚገዙትና ከሚመሩት አራት ተፈጥሮአዊ ኃይሎች አንዱ የሆነው የስበት ኃይል (ግራቪቴሽናል ፊልድ) የኛ ሊቃውንቶች ከተረዱትና ድል ከመቱት ብዙ ምዕተ—ዓመታት ተቆጥረዋል። ፖልተርጂስት፣ እኛ 'አንደርቢ' አንለዋለን። ድንጋይና ሌሎች ክባድ ቁሶች የመሬትን የስበት ኃይል አሸንፈው ወደ አየር እንዲነሱና እንዲወረወሩ ማድረግ ለእኛ ሊቃውንቶች እና ክለርጂስ (የቤተ—ክህነት ባልደረቦች) እጅግ በጣም ቀላል ሳይንስ መሆኑን አያውቁም?"

አምባሳደሩ፣ ክቡር ሚኒስትሩና ልዕልቲቱ በአንድነት፣ በአምንታ ራሳቸውን ወዘወዙ።

"እናንተ" አለ ዶክተር አንዱዓለም. . . " ከኢትዮጵያም ሆነ ከሌሎች ጥንታዊ ሥልጣኔ ሰፍኖባቸው ከነበሩ ሀገሮች ጥንታዊ የብራና ጽሑፎቻቸውን የምትዘርፉት እንደምትሉት 'For safe Keeping (አስተማማኝ ጥበቃ)' ለማድረግ አይደለም። በውስጣቸው የሠፈረውን አያሌ ጥንታዊ ዕውቀት ለመጨበጥ እንደሆነ ቢያንስ እኔና እናንተ ልንክካድ አንችልም።"

ይሄኔ አምባሳደሩና ልዕልቲቱ የመግባባት ዐይነት አይታ ሰረቅ አድርገው ተያዩና ሁለቱም "ክብራችን ተነካ!" የሚል ትርጓሜ ያለው የሃፍረት ቅላት ቀሉ።

"እባክሽን ዮዲት። ይህን ድንቅ ቡናችሁን ቅጂልኝ!" አሉ ልዕልቲቱ።

ምዕራፍ ሰላሳ ስድስት

መቶ አለቃ ሳሙኤል ሞባይሉ እጁ ላይ ነዘረው። "ሃሎ! ሻለቃ ፍቅሩ" አለ።

"አሁን ብራና አስጎብኚ ድርጅትን ፈትሼ መውጣቱ ነው። ስሜት የሚሰጡ ዶክሜንቶችን አግኝቻለሁ። ብታያቸው ጥሩ ነው።"

"እሺ ጌታዬ! እዚያው ጠብቁኝ መጣሁ።"

ሻለቃው የዶክተር ሥራውብዙ ጠረጴዛ ላይ ዶክሜንቶቹን ዘርግተው ሲጠብቁት ደረሰ።

"ሳሙኤል ይህን ተመልከት" አሉት ገና ከመግባቱ።

"ይህን ቢሮ ለመፈተሽ የመጡት ኮሎኔል ዘገየ መስለውን ነበር።" አላቸው።

"ዘገየ ከሰንደን የገባውን መርማሪ ቡድን በመቀበል ቢዚ ስለሆነ አኔን ላከኝ።"

ሳሙኤል ራሱን በአዎንታ ወዘወዘና ሰነዶቹን ማገላበጥ ጀመረ።

1. በመቅደላዊት ስም በርካታ ገንዘብ ከእሥራኤል ወደ ስዊዘርላንድ ባንክ 'ዋየር' የተደረገበት (የተላወረበት)
2. በዶክተር ሥራውብዙ እና መቅደላዊት ስም የተገዛ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የደርሶ መልስ ትኬት ደረሰኝ፣ ወደ በርን ስዊዘርላንድ።
3. ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ወደ ሌሎች ሁለት የግል ባንኮች የተላለፈ በርካታ ገንዘብ ደረሰኝ . . .

"ይህ በጣም ጠቃሚ ነው!" አለ ሳሙኤል ሻለቃውን እየተመለከተ "ሻለቃ። ለመሆኑ ባሕታዊው በሚል ስም ብቻ የሚጠራውን የቅርሳችን ይመለስ ሥራቹን መነኩሴ ያውቁታል?"

ቀና ብለው ሳሙኤልን ለትጽበት ጊዜ አዩትና ዐይኖቻቸውን ባዶው አየር ላይ ተክሉ። በፀጥታ ጠበቃቸው።

"አላውቀውም።" አሉት።

"አመሰግናለሁ" ብሎ ሊወጣ ሲል "ወዴት ነው ሳሙኤል?" አሉት እርሳቸውም እየተነሱ።

"ወደ ኮተቤ የኪራይ ቤት።"

"መልካም። ካሁን በኋላ ከምርመራ ቡድኑ ጋር ግንኙነት ማድረግ ሲኖርብህ በተንቀሳቃሽ ራዲዮንህ ተጠቀም። ምክንያቱም ንግግራችን እና እንቅስቃሴያችን ሁሉ በማዕከላዊ ምርመራ ዶክሜንትድ መሆን አለበት።"

"እሞን ሻለቃ!" አላቸውና ሲጋራውን እየለኮሰ የፎቁን ደረጃዎች ወረደ። "ወደ ባንክ!" አለው አሽከርካሪውን።

ሹፈሩ 'ምላ ሰዓት አልፎ አራት ሊደርስ እኮ ነው' ሲለው አሰበና ተወው።

**********////////**********

አጋችና ታጋቾች ከሚገኙበት ትምህርት ቤት ውጭ በጥቂት መቶ ሜትሮች ርቀት የሚኘውን ሕንፃ የተቆጣጠሩት የኤስ.ኤ.ኤስ እና የኢትዮጵያ ፀረ—ሽብር ኮማንዶዎች መሣሪያዎቻቸውን ተክለው ጨርሰዋል። አቅርበው የሚያሳዩ ኃይለኛ ባይኖኩላሮች፣ ባለ ቴሌስኮፒክ ሌንስ ካሜራዎች፣ የቪዲዮ ካሜራዎች፣ ከርቀት ድምጽ የሚሰበስቡና የሚያጸምጡ ልዩ መሣሪያዎች . . .። ተዋጊና መቺ ኮማንዶዎቹም ትጥቆቻቸውን ዝግጁ አድርገዋል። እንግሊዛውያኑ ኮማንዶዎች አጫጭር እና ኃይለኛ 'ብራውኒንግ' አውቶማቲክ ጠመንጃዎች ከድምጽ ማፈኛ (ሳይለንሰር) እና ቴሌስኮፒክ ሳይት ጋር፣ ብራውንግ ሽጉጥ፣ ባለ አሥራ ሁለት ኢንች የኮማንዶ ሳንጃ፣ ባለ ኢንፍራሬድ ጨረር የሌሊት መመልከቻ (ናይት ስኮፕ)፣ እና ራስ ላይ የሚጠለቅ የመገናኛ ራዲዮኖችን ታጥቀዋል።

የአድዋ ክፍለ ጦር ፀረ—ሽብር ኮማንዶዎች ደግሞ ኤ.ኬ 47 አውቶማቲክ ጠመንጃ፣ ሳንጃ እና የእጅ ቦምቦችን ታጥቀው 'ይህ ሁሉ ቅራቅንቦ ሽክም ምን ያደርግላቸዋል?' እያሉ በፈረንጆቹ የትጥቅ ብዛትና ዐይነት ይገረማሉ። የመጨረሻው ፎቅ ላይ የሚገኝ አንድ ሰፊ ክፍል ውስጥ የስፖንጅ ፍራሾችና ብርድ ልብሶችን አንጥፈው ማረፊያ አድርገውታል። ምግብ፣ ትኩስ ቡና፣ ውሃና ሌሎችንም አቅርቦቶች የእንግሊዝ ኤምባሲ ለእንግሊዞቹ፣ መከላከያ ለአድዋ ኮማንዶዎች ያቀርባሉ።

አራተኛው ፎቅ ላይ የሠፈረው አንድ የመቶ (30 ሰው) የኢትዮጵያ የፀረ-ሽብር ኮማንዶ ጦር በመቶ አለቃ ጋሻው የሚታዘዝና አያሌ አውደ ውጊያዎች ላይ የተፈተነ ጦር ነው። 'እነዚህ ፈረንጆች ይህ ሁሉ የተራቀቀ መሣሪያ ምን ያደርግላቸዋል? አዚና ክላሽ ብቻ ለታጠቁ ጥቂት ሰዎች?' እያሉ ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው ያወጋሉ።

**********////////**********

ከቀኑ አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ አዳራሹ ውስጥ የሚገኘውን መደበኛ ስልክ ያነሳው ያፈት "አቶ ግርማይ? " በማለት ያላንዳች መቅደም ጠየቀ። "አዎን አቶ ያፈት ግርማይ ነኝ። የአስተዋይነት ምላሻችሁን እየጠበቅን ነው።"

"ክቡር ሆይ! አዝናለሁ። የመጨረሻውን መደራደሪያ የምናቀርበው በነገው ዕለት ነው። አሁን የራት ሰዓት መድረሱን ላስታውስዎ እወዳለሁ። በተጨማሪም ከፊታችን የሚገኘው ሕንፃ ውስጥ የሠፈሩት የኤስ.ኤ.ኤስ እና የኢትዮጵያ ኮማንዶዎች አጥፊ እና ጀብደኛ ርምጃ እንዳይሞክሩ ይታዘዙ። ያለዚያ የልዕልቲቱን የራስ ቅል በዝርግ ትሪ ላይ አልክልዎታለሁ!" አለና ግንኙነቱን ዘጋው። የርዕስ ብሔሩ ልዩ ረዳት ግርማይ በርሄ ስልኩን የጨበጠው እጃቸው በላብ ሲርስ ተሰማቸው። የያፈት አራዊታዊ ማስፈራሪያ በሕሊናቸው እየታያቸው ዐይኖቻቸውን ጨፈኑና "አንተ ጀብደኛ ውሻ። ዋጋህን.....ዋጋችሁን ታገኛላችሁ!" ሲሉ በውስጣቸው ዛቱ።

**********/////////**********

ሌ/ኮሎኔል ዘገዬ፣ ሻለቃ ፍቅሩ፣ መቶ አለቃ ላሙኤል እና ረዳቶቻቸው ያቀናበሩትን የምርመራና የክትትል ሥራ (ኢንቪስቲጌሽን) ይዘው ከምሽቱ 1:00 ሰዓት ላይ ኮሎኔል ሰናይ ቢሮ ውስጥ ተሰብስበዋል። ይህን የምርመራ ውጤት ለማዳመጥና ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሪፖርት ለማድረግ አቶ ግርማይ በርሄም ተገኝተዋል።

አጫሾች ሲጋራቸውን ለኩሰዋል። የቡና ወዳጅ የሆኑትም በኩባያ ቀድተው ይጎነጩታል።

"ዘገዬ፣ ካንተ ብንጀምርስ?" አሉ ኮሎኔል።

"ላሙኤል የሰጠኝን የስም ዝርዝር ለረዳቶቼ በማስተላለፍ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተነስተን በኢሚግሬሽን እና በተለያዩ ክፍለ ከተማ አስተዳደሮች በመዘዋወር የተጠርጣሪዎቹን ፐርሰናል ፕሮፋይል እና አይደንቲቲት (ማንነት) አዘጋጅተናል። በዚህም መሠረት ይህን በከተማችን ውስጥ በዐይነቱ የመጀመሪያው የሆነ የእገታና የጠለፋ ወንጀል የፈፀሙት . . .

1. *ዶክተር ሥራውብዙ አየሁ* ዕድሜ ሃምሳ አምስት ዓመት፡ ከአንድ ወር በፊት የሁለት ልጆቹን እናት በሕግ የፈታ፣ የመጀመሪያ ዲግሪውን በታሪክ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በፓሌኦ አንትሮፖሎጂና በቅርስ ጥበቃ እስከ ፒ.ኤች.ዲ ሆላንድ የተማረ። ለአሥር ዓመታት ያህል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

በመምህርነት ያገለገለ። ባሁኑ ጊዜ 'ብራና አስንብኚ' የተባለ ድርጅት ባለቤት። የቅርሳችን ይጠበቅ ድርጅት መሥራችና ፕሬዝዳንት።

2. *ዶክተር አንዱዓለም ይፍረደው* ዕድሜ አርባ ሁለት ዓመት። በታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ እስክ ፒ.ኤች.ዲ ኤደንብራ ዩኒቨርሲቲ። ባሁኑ ጊዜ በለንደን ናቹራል ሂስትሪ ሙዚየም የምሥራቅ አፍሪካ ቅርሶችን ጠባቂና ተመራማሪ። የቅርሳችን ይጠበቅ ማህበር ቋሚ አባልና ኤግዚቢሽኑን አዲስ አበባ ላይ ለማዘጋጀት ከፍተኛውን ድርሻ የተጫወተ።

3. *ወይዘሪት ራሄል ግዛው* ዕድሜ ሠላሳ ዓመት። በታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። በትርስ ጥበቃና ጥናት ሁለተኛ ዲግሪዋን ከኤደንብራ ዩኒቨርሲቲ። ባሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ መምህርትና የቅርሳችን ይጠበቅ ማሕበር ዋና ጸሐፊ።

4. *ያሬድ መልካሙ* ዕድሜ ሠላሳ አምስት ዓመት። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪ። ሁለተኛ ዲግሪ ከኤደንብራ ዩኒቨርሲቲ። በለንደን የተፈጥሮ ታሪክ ሙዚየም የምሥራቅ አፍሪካ ተመራማሪ። የተዘረፉ የኢትዮጵያ ቅርሶችን ለማስመለስ ባደረገባቸው ጥረቶች የሚታወቅ። ይህን ኤግዚቢሽን ከባሕል ሚኒስቴር እና ከቅርሳችን ይጠበቅ ማህበር ጋር በመተባበር አዲስ አበባ ላይ ለማዘጋጀት ያስቻለና የቅርሳችን ይጠበቅ ቋሚ አባል።

5. *ያሬት ናሀ* ዕድሜ 37 ዓመት። አሥራ ሁለተኛ ክፍል በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት። የኢትዮጵያ አየር ኃይል ውስጥ በተዋጊ ሄሊኮፕተር አብራሪነት ያገለገለና በአርስ በአርስ ጦርነት ወቅት ቆስሎ ከሠራዊቱ የተገለለ። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በስዕልና ሥነ ጥበበ የመጀመሪያ ዲግሪ። ሁለተኛ ዲግሪውን በተመሳሳይ ሙያ ከፈረንሣይ አገር የጨረሰና በኢትዮጵያ ሃይማኖታዊ ስዕሎች ላይ ስፔሻያላይዝ ያደረገ። የጠለፋው ወንጀል እስከተፈፀመበት ጊዜ ድረስ በተማረበት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት በማገልገል ላይ የነበረና የቅርሳችን ይጠበቅ ማሕበር ቋሚ አባል።

6. *ሳምሶን ኃይሉ* ዕድሜ ሠላሳ አራት ዓመት። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በድሬዳዋ ከተማ ናተር ዳም ትምህርት ቤት የጨረሰ። በኢትዮጵያዊ አየር ወለድ ሠራዊት በመቶ ሻምበልነት ማዕረግ ያገለገለና በአርስ በርስ ጦርነቱ ወቅት

ቶስሎ ከሠራዊቱ የተገለለ። ባሁኑ ጊዜ በብራና አሰንብኘ ድርጅት በአሰንብኘ ሾፈርነት የሚሠራ። የቅርላችን ይጠበቅ ማሕበር መደበኛ አባል።

7. *ወይዘሪት ሶዲት ሙሴ* ወይንም በአሥራኤላዊነት ፓስፖርቷ ሶዲት ሞሼ ዕድሜ ሠላሳ ሁለት ዓመት። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን በጎንደር ከተማ ፋሲለደስ ትምህርት ቤት የተማረች። ስለ ወላጆቿ እስካሁን ምንም ማወቅ አልተቻለም። በዘመቻ ሰለሞን ወደ እሥራኤል ሀገር የተወሰደች። ዜግነት ያገኘችና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የእየሩላሌም ፖስት ዜና ወኪል ሆና የተመደበች።

ሌተናንት ኮሎኔል ዘገየና ረዳት ቡድናቸው ያቀናበረው የምርመራ ሪፖርት ተነቦ ሲያበቃ አቶ ግርማይ በርሄ ነበሩ የመጀመሪያውን አስተያየት የሰነዘሩት።

"አብዛኛዎቹ የታሪክ ምሁራን መሆናቸው ያመሳስላቸዋል።"

"አምን ይህ ባክ ግራውንድ ያመሳስላቸዋል. . ." አሉ ኮሎኔል ሰናይ። "ጥቂቶቹም የማይናቅ ወታደራዊ ሥልጠናና ተሞክሮ አላቸው።" አሉ አክለው።

"በተለይም . . ." አለ ሳሙኤል። "በተለይም የያዬት ተዋጊ ሄሊኮፕተር አብራሪነት በጣም አላስቦኛል። ምናልባት በነገው ዕለት በሚያቀርቡት ጥያቄ ውስጥ ተዋጊ ሄሊኮፕተር ይቅረብልን የሚል ጥያቄ ሊካተትበት ይችላል። ስለዚህ . ." አለ መቶ አለቃ ሳሙኤል ወደ አቶ ግርማይ እየተመለከተ። "ምናልባት ሄሊኮፕተር ከጠየቁና መንግሥት ለማቅረብ ከተገደደ . . .እ. .እ. .አንድ ሄሊኮፕተር ይዘጋጅና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ባለሙያዎቻችን ሄሊኮፕተሩ ውስጥ የማዳመጫና ማስተላለፊያ መሣሪያዎች በስውር ቢጠመዱበት . . .::"

"ልክ ነህ!" አሉ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ረዳት። "አይሆንም ከማለት ይሆናል ብለን ብንዘጋጅ ይሻላል።" አሉና ማስታወሻ ያዙ።

"ፍቅሩ! አንተስ እጅህ ከምን?" አሉ ኮሎኔል ሰናይ።

ሻለቃ ፍቅሩ "እህህ..." ብለው ጉሮሮአቸውን አፀዱ። በእጃቸው ማስታወሻ አልያዙም።

"እነዚህ ወንጀለኞች የተጠቀሙባቸውን የጦር መሣሪያዎች ምንጭ ለማረጋገጥ ባደረግነው ጥረት ሮመዳን ሮበሌና ሐጂ አብዱል ራሽድ የተባሉ ሰዎችን ድሬዳዋ ከተማ ውስጥ በቁጥጥር ስር አውለናል። የሕገ ወጥ መሣሪያዎቹ ዋነኛ አዘዋዋሪ ሐጂ አብዱል ሲሆኑ የጦር መሣሪያዎቹና መሣሪያዎቹ ወደ አዲስ አበባ የገቡበት መኪና (ቶዮታ ስቴሽን ዋገን) ከመንግሥት አልባዋ ሶማሊያ ተዘርፈው በድብቅ ድሬዳዋ የገቡ ናቸው። እነዚህን የጦር መሣሪያዎች በህሽ የገዛውና ወደ አዲስ አበባ ያጓጓዘው የድሬዳዋ ከተማ ተወላጅና የቀድሞው

የአየር ወለድ ሰራዊት ባልደረባ ላምሶን እንደሆነ ከተያዙት ተጠርጣሪዎች ቃል ለመረዳት ችለናል። እነዚህ አጋቾች የታጠቁት ከፍተኛውና አስጊው የጦር መሣሪያ ታጣፊ ክላሺን ኮቭ እና ኤፍ ዋን የእጅ ቦምቦች ብቻ ናቸው።"

"የጦር መሣሪያዎቹን ያጓጓዘውን መኪና በተመለከተ . . ." አሉና ሻለቃ ፍቅሩ ወደ ላሙኤል መልከት አድርገው ዝም አሉ።

"አምን አለ ላሙኤል።" መኪናውን አሽባሪዎቹ የተከራዩት ቤት (ሴፍ-ሃውስ) ውስጥ ቅሪቱን ማለት እችላለሁ ... አግኝተነዋል። የሩቅ ርቀት መገናኛ አንቴናውን እና አዕሙን . . አ . ሻሊውን አግኝተናል።"

"ሌላስ?" አሉት ኮሎኔል ሰናይ።

"ቤቱን የጠለፋውን ተግባር እስከፈፀሙበት ዕለት ድረስ የመደበቂያ፣ የመለማመጃ፣ እና የመደራጃ ምሽግ አድርገው ተጠቅመውበታል። የቤቱ ባለርስት የሆኑትን ባልቴትም አግኝተን ላምሶንና ራሄል እንደተከራዩዋቸው በሰነድ ማስረጃ አረጋግጠውልናል።"

የዶክተር ሥራውብዙን የፋይናንስ እና የንብ እንቅስቃሴም ተከታትያለሁ። የቅጥር ጸሐፊውን የወይዘሪት መቅደላዊትንም እንደዚሁ። ከአሥራ አምስት ቀናት በፊት ጀምሮ መቅደላዊት በባንክ አካውንቷ በርካታ ገንዘብ፣ በተለያየ ጊዜ እስከ ግማሽ ሚሊዮን ብር ገቢ ተደርጎላት እንደገና ዊዝድሮው። አድርጋዋለች ወደ ስዊዘርላንድ የደርሶ መልስ አየር ቲኬት ገዝታለች። ባሁኑ ጊዜ ካገር ለመውጣቷ ማስረጃ ባይገኝም የቦሌ አየር ማረፊያ ላይ ቁጥጥር እየተደረገባት ነው።"

"ዶክተር ሥራውብዙም በቅርቡ ወደ እሥራኤል ተንቡ ተመልሷል። የሀገር ውስጥ የፋይናንስ ሰነዶቹ የሚያሳዩትም አንድ ዐይነት ሕገ ወጥ ትራንዛክሽን ውስጥ የተዘፈቀ መሆኑን ነው። ይህ ሰው በቅርስ አስመላሽነትና ጠባቂነቱ ባደባባይ ቢታወቅም ውስጥ በሹክሹክታ 'የታቦት ሌባ' እየተባለ ይታማል።

የመረጃ ዘገባው፣ ትንታኔውና ውይይቱ ለሦስት ሰዓታት ያህል በጥልቀት ተከናወነ። የምርመራ ቡድኑ አባላት የሚቀጥለውን ስትራቴጂ ለማጥናትና ለመንደፍ እዚያው፣ የኮሎኔል ሰናይ ቢሮ ውስጥ ሲቀሩ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ረዳት ደግሞ የምርመራ መገገቡን ግልባጭና ባጭሩ ያቀናበሩትን ሪፖርት ሸክፈው ወደ አለቃቸው ቢሮ ከነፉ።

ምዕራፍ ሰላሳ ሰባት

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከምሽቱ 3:30 ላይ በጽሕፈት ቤታቸው ውስጥ ካቢኒያቸውን ሰብስበው ረዳታቸው የሚያቀርቡላቸውን የምርመራ ሪፖርት ያዳምጣሉ።

". . . . በታሪክ የመጀመሪያ .. . .።"

"ቆይ!አንዴ!" አሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ።

"ሰፋ ያለውን ዲቴክቲቭ ስቶሪ ተወውና ስለ ጠላፊዎቹ ያለህ ተጨባጭ መረጃ ምንድነው?"

ረዳቱ ሌሎች ገጾችን ከገላለጡ በኋላ "አጠቃላይ መረጃው ይሄውና። አስካሁን ባለን መረጃ የጠላፊዎቹ የሰው ኃይል ብዛት ሰባት ነው። አንድ ሰፊ የኪራይ ግቢ ውስጥ ካደረጉት ወታደራዊ ልምምድ በስተቀር ፕሮፌሽናል የሆነ ወታደራዊ ልምድ ያላቸው አንድ የቀድሞው መንግሥት ተዋጊ ሄሊኮፕተር አብራሪና አንድ የአየር ወለድ ኦፊሠር ብቻ ናቸው። የታጠቁትን የመሣሪያ ዐይነት በተመለከተ አውቶማቲክ የእጅ መሣሪያዎች፣ ሽጉጦችና የእጅ ቦምቦች ናቸው።

"ያፈት የተባለው የጠላፊዎቹ አፈ ቀላጤ ነገ ከቀኑ 7:00 ሰዓት ላይ በጠራው የፕሪስ መግለጫ ላይ ጥያቄዎቻቸውን ይፋ እንደሚያደርግ ገልጿል። የመረጃ ትንታኔዎቻችን እንደሚጠቁሙት ከሆነ ያፈት ቀደም ሲል የተዋጊ ሄሊኮፕተር አብራሪ ስለ ነበረ ቅርሶቹን ጭነውና ታጋቾቹን ሰብለዊ ጋሻ አድርገው፣ ወደ መጨረሻው መሸሸጊያ የሚያመልጡበት ሄሊኮፕተር ይጠይቃል ተብሎ ይገመታል።"

"የፀረ—ሽብር ኮማንዶ ኤክስፐርቱ ኮሎኔል አሰፋ የግቢውንና ያዳራሹን አጠቃላይ ፕላን ካጠና በኋላ በተመረጡ ጥቂት ኮማዶዎቹ አዳራሹን 'ስቶርም' በማድረግ (ድንገተኛ ጥቃት በመሰንዘር) ቢበዛ በአስር እና አሥራ አምስት ደቂቃዎች ውስጥ ድንገተኛና ፈጣን የኮማንዶ ጥቃት በመሰንዘር ታጋቾቹን ያለ አንዳች ጉዳት ነፃ የማውጣት ዕድሉ ዘጠና አምስት ከመቶ እንደሚደርስ አረጋግጦልናል።"

"እኔ እንደማምንበት . . ." አሉ የመከላከያ ሚኒስትሩ። "ለዚህ መሰሉ የኪሳራ ወቅት የሠለጠኑት ኮማንዶዎቻችን ታጋቾቹን የማስለቀቅ ስኬታቸው አስክ ዘጠና ፣ ምስት ከመቶ የሚደርስ ነው። የኤስ-ኤ-ኤስ ኮማንዶ አዛዦም አመቺ ሥፍራ ላይ ሆ/ኒው፡

የአዳራሹ ሞዴል በአሸዋ ዝታ ተሠርቶ ከእኛ ኮማንዶዎች ጋር በጋራ የማጥቃት ልምምድ እንዲያደርግ ፈቃድ ጠይቋል።"

"ልምምዱን በመረጣችሁት ሥፍራ በጋራ እንድታደርጉ ፈቅጃለሁ።" አሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ። "ዋናውና በጣም ያሳሰበኝ ነገር የአምስት ፐርሰንት ያለመሳካት ጉዳይ ነው። ጥቃት ከተሰነዘረ በኋላ ያቺ አምስት ፐርሰንት ወደ ጠላፊዎቹ ካደላች ሊታረም የማይችል ጥፋት ውስጥ ልትጥለን ትችላለች። ስለዚህ ምን የምታቀርቡት ሐሳብ አለ?" ሲሉ የካቢኔ አባሎቻቸውን ተራ በተራ እየቃኙ ጠየቁ።

የካቢኔው አባላትም እያንዳንዷን ጥቃቅን ነጥብ ሁሉ እያነሱና እየጣሉ ለአንድ ሰዓት ተኩል ያህል አበጥረው ከተወያዩበት በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አጭር ውሳኔዎቻቸውን እና ትዕዛዛቸውን ለረዳታቸው በመስጠት የምሽቱ ያስቸኳይ ጊዜ ስብሰባ ተጠናቀቀ።

1. አዳራሹ እና የግቢው ሞዴል ተሠርቶ የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ኮማንዶዎች በጋራ የማጥቃት ልምምድ እንዲያደርጉ።
2. የጠላፊዎቹ አፈ ቀላጤ ጋዜጣዊ መግለጫ በሚሰጥበት ወቅት የእንግሊዝና የእኛም ኮማንዶዎች በሪፖርተርነትና በሌላም ሽፋን የፕሬስ ኮንፈረንሱ ላይ ተቀላቅለው ማጥቃት የሚችሉበትን አመቺ ቅዕበት በንቃት እንዲጠብቁ።
3. እኔ የምርመራው ኮማንድ ለዐረ—ሽብር ኮማንዶ መሪዎች በራዲዮ መገናኛ ትዕዛዝ ካልሰጠ በስተቀር በናዕዱም ማጥቃት እንዳይሰነዝሩ።
4. አመቺ ሁኔታ ካልተፈጠረ የሚወሰዱ ተለዋጭ እርምጃዎችን የምናላውቀው የጠላፊዎቹ የመጨረሻ ፍላጎት (ዲማንድ) ከተሰማ በኋላ ነው።

ይህን ትዕዛዝ ለረዳታቸው ካስጨበጡ በኋላ የሰላማዊ ድርድሩን ቀዳዳ እስከ መጨረሻው ለጠቀሙበት ወሰኑ።

". . . ለተዘረፉ ቅርሶቻችን ያላችሁን ቀናኢነት ብናደንቅም አላማችሁን ለመተግበር የተጠቀማችሁበት የኃይል ተግባር የሀገራቱን የእንግዳ ተቀባይነትና የሕዝቦቿን የጨዋነት ባሕል የሚጻረር፣ ደረጃቸው እጅግ የከበረ እንግዶቻችን ላይ የተፈፀመ ኢ-ሰብአዊ ወንጀል መሆኑን ተረድታችሁ ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ

ታጋቾቹን ብትለቁና እጃችሁን በሠላም ብትሰጡ ቀደም ሲል የገባንላችሁ እጅግ ለስላሳ የማስመሰያ ቅጣትና ከጥቂት ወራት በኋላም ነፃ የመሆን ዕድላችሁ እንደተጠበቀ በድጋሚ አረጋግጥላችኋለሁ።"

"ለማንኛውም ..." አሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ደብዳቤው ላይ ፊርመው ለረዳታቸው እየሰጡ። "ለማንኛውም ይህን ደብዳቤ ራስህ አንብበህለት ወይንም አስነብበህው ብትመልሰው መልካም ነው። ምክንያቱም የፕሬስ ሰዎች እጅ ከገባ ዳሜጂንግ (ጎጂ) ውጤት ሊመጣብን ይችላል።"

አቶ ግርማይ አለቃቸውን ተሰናብተው ወጡ።

**********////////**********

ጊዲዮን ኤፍራም፣ ቢኒያም እና እሸቱ ካፌ ኢየሩሳሌምን በአድሳት ሽፋን ከዘጉት አንድ ሳምንት አስቆጥሯል። የማስመሰያ ለውጥ የተደረገበት የፖሊስ ቫን ግቢው ውስጥ በሸራ ተሸፍኖ ቆሟል።

አራቱ ቤተ—እሥራኤላውያን ሙሉ የፖሊስ ደንብ ልብስ ለብሰው የእጅ መሣሪያዎቻቸውን ዝግጁ አድርገው ጊዲዮን ቢሮ ውስጥ ተቀምጠዋል። ሁሉም ከጉጉት በስተቀር አንዳችም የውጥረት መንፈስ አይትይባቸውም። ጊዲዮንም ሲጋራ እያጨሰ ሰዓቱን ደጋግሞ ያያል።

**********////////**********

ከለንደን አዲስ አበባ የገባው የምርመራ ቡድን እና የልዕልት ኢዛቤል ቦዲ ጋርዶች ሾላ በሚገኘው የእንግሊዝ ኤምባሲ ቅጥር ግቢ በተዘጋጀላቸው ልዩ ክፍል ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሰየሙት ልዩ የምርመራ ቡድን እስክ አሁኗ ሰዓት ድረስ ያመረተውን የመረጃ ክምር (በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉሞ የተዘጋጀውን ቅጂ) ሲያጠኑ ሲመረምሩና ሲተነትኑ ካመሹበት በኋላ ለንደን ለሚገኘው አመራር በኮድ የታሰረና ዲጂታል ሲግናል በሳተላይት መገናኛ መሣሪያ የሴኮንድ አንድ ሺህኛ በሆነ ፍጥነት አስተላለፉ።

"ያለ ሀፀፃቹ ጣልቃ ገብነት የኤስ -ኤ-ኤስ ኮማንዶዎቻችን ታጋቾቹን የማስለቀቅ በታታቸው 99.9 ፡ (ዘጠና ዘጠኝ ነጥብ ዘጠኝ ከመቶ) እንደሚሆን ተማምነናል።"

**********////////**********

የሸላ፣ የቀበና የግንፍሌ እና ያካባቢው ነዋሪዎች ከእንግሊዝ ኤምባሲ ግቢ ምግብና መጠጥ ለታጋቾቹ የሚያመላልሱትን አንድ ኮድ 03 ቫን እና አጃቢው ሆኖ የሚከተለውን አንድ ቶዮታ የፖሊስ ቫን ከተላመዷቸው ውለው አድረዋል። ልክ ከምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ አራት ፖሊሶችን የያዘው ቫን ከፊት እየቀደመ፣ ኮር ዲፕሎማቲክ 03 ቫን እየተከተለ ትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ዋና በር ላይ ሲደርሱ ተቆጣጣሪው የፖሊስ ኢንስፔክተር አስቆማቸው። በመጀመሪያ የፖሊሱን ቫን ቀጥሎም ምግብና መጠጥ የታጨቀበትን የዲፕሎማቲክ ቫን እያስከፈተ ከተመለከተ በኋላ ወደ ግቢው አሳለፋቸው።

**********////////**********

"ነገ ሳኒት ቁርስ የሚያደርሰውን ቫን ተጠቅመን አዳራሹን እንድናጠቃ ይፈቀድልኝ።" ሲል መጥረቢያው ለኤምባሲው ዋና ጸሐፊ በልዩ ራዲዮን ጥያቄ አቀረበ። ጸሐፊውም ጥያቄውን ወዲያውኑ ለጠቅላይ ሚንስትሩ ረዳት በስልክ አስተላልፉት።

ጠ/ላይ ሚንስትሩ ከመክላከያ ኤታማጆራቸው ጋር ተመካክረው "ጊዜው ገና ነው፤ ሰ ,ታልም አደገኛ ነው!" የሚል መልስ ሰጡ።

ምዕራፍ ሰላሳ ስምንት

ያፈት ልክ ከቀኑ ሰባት ሰዓት ትናንት መግለጫ የሰጠበት ግንብ ላይ ወጥቶ ቆመ። ግቢው እጅግ ዘመናዊ መቅረጸ ምስልና መቅረጸ ድምጾችን በያዙ ያገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጋዜጠኞች ጢቅ ብሎ ተሞልቷል። አከንባሎ የመሳሰሉ የሳተላይት ዲሻቸውን ሆድ ዕቃ ወደ ሕዋው አነጣጥረው የዘረጉ የቀጥታ ስርጭት መኪናች ግቢው ውስጥ ቆመዋል። ቴክኒሺያኖቹ ዝግጁ ሆነው የአሸባሪዎቹን መሪ እየጠበቁ ነው። ዩኒፎርም የለበሱና ቁጥራቸው ከዐሥር የማይበልጥ ፖሊሶች የተከለለውን ሥፍራ ማንም ሰው እንዳያልፍ ይቆጣጠራሉ።

እንደተለመደው ኮሎኔል ሰናይ፣ ሻለቃ ፍቅሩና አቶ ግርማይ በርሄ ከጋዜጠኛው መንጋ በስተጏላ ራቅ ብለው ያፈትን ይመለከታሉ።

'ዙሰን' የሚል የዜና ወኪል ባጁ ደረቱ ላይ ያንጠለጠለ አንድ አውሮፓዊ ጋዜጠኛ ወደ ሦስቱ ባለ ሥልጣናት ሊጠጋ ፖሊሱ ሊያስቆመው ሞከረ።

"ተወው አሳልፈው!" አሉ አቶ ግርማይ።

"ሰር! አለ ጋዜጠኛ የተመለከው 'መጥረቢያው'። ይህንን ባስታርድና አዳራሹ ውስጥ ያሉትን አሸባሪዎች ቢበዛ በአምስት ደቂቃዎች ውስጥ መደምሰስ እንችላለን። በጣም ዝግጁ ነን። ይህ ሰው መግለጫውን መስጠት ሲጀምር እኔም የማጥቃትና ድምሰሳ ውጊያ ልጀምር።" አላቸው።

"ይህን ትዕዛዝ መስጠት የሚችሉት ሁኔታውን 'ላይቭ' የሚከታተሉት ጠቅላይ ሚንስትራችን ብቻ ናቸው። አሳቸው ካዘዙ ወደ አንተ አስተላልፋለሁ። እስከዚያ አርፈህ ተቀመጥ!" ሲሉ ተኮሳትረው መለሱት።

**********////////**********

"ጤና ይስጥልኝ !" ሲል በፀማርኛ ሠላምታውን አቀረበና በነጠረ የእንግሊዞች እንግሊዘኛ ንግግሩን ቀጠለ። የቀጥታ ሥርጭት ሳተላይቶችም ወዲያውኑ ያፈትን በመላው ዓለም አየር ላይ ማሠራጨት ጀመሩ።

"ያቀረብነው ጥያቄ 'ቅርሶቻችንን መልሱ!' ነበረ። ሆኖም ዘራፊው አካል ንብረታችንን ሊመልስ አልቻለም። ዓለም አቀፉ ማሕበረሰብም ሊያስመልስልን አቅም የለውም።" አለና እንግሊዞች ከአንድ መቶ ሃምሳ ዓመታት በፊት ከዓፄ ቴዎድሮስ አስከሬን ራስ ላይ ቆርጠው የወሰዱት ፀጉራቸውን ከፍ አድርጉ እያሳየ "ዛሬ እኔ ሕያው ከሆነችው የእንግሊዝ ልዕልት ራስ

ላይ ወራሪን ወይንም አንገታ ላይ ያንጠለጠለችውን ከቅኝ ተገዢዋ ሕንድ የተዘረፈውን ዝነኛ የአልማዝ ሀብላን በጥሩ ብውስያው የሚከለክለኝ አለ?"

ይህን ጊዜ የጋዜጠኛ ባጅ ያንጠለጠለው የኤስ.ኤስ ኮሎኔል 'መጥረቢያው' ተናዶ 'ዩ ዶር ተች ሽር (ልትንካት ብትቃጣ!) ሲል ጥርሶቹን ገጥሞ ዛተ።

"እውን የሚከለክለኝ የለም። ግን አነሳሳችን የሰው ንብረት ለመዝረፍ ሳይሆን የራሳችንን ንብረት በጎይል ለመውሰድ ነው። አድርገንዋልም። አሁን የቀረን ንብረታችንን ይዘን መሄድ ነው። ይህን በሰላም እንድናደርገው ከተፈለገ በቅድሚያ ጋዜጠኛ ተመስለው የሚርመሰመሱት የእንግሊዝና የኢትዮጵያ ኮማንዶች እጆቻቸውን ወደ ቃታቸው እንዳይልኩ አስጠንቅቃቸዋለሁ። ይህን ካልኩ በኋላ እነዚህን ጥያቄዎች አቀርባለሁ።

1. ባለ ሁለት ቱን ችሎታ ፎርክ ሊፍት ከነ አፕሬተሩ። (የጦር መሣሪያ ያልታጠቀ) አለ ያፈት ከፈገግታ ጋር።
2. ሰበረራ (ለሥራ) ዝግጁ የሆነ ኢም 30 ሄሊኮፕተር ከነአብራሪው
3. "ሦስተኛ....." አለ ያፈት ከፈገግታ ጋር። "የተከበሩ ልዕልት ኢዛቤል የጉዞ ባለደረባችን መሆናቸውን ከግንዛቤ ጨምሮ የኢትዮጵያ መንግሥት የአየር ላይ መንገዳችንን ከማናቸውም መሰናክሎች ነፃ... እደግመዋለሁ... ነፃ እንዲያደርግልን!"

"እነዚህ በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከሌሊቱ 6:00 ሰዓት ወይንም እንዲቀርቡልን እንጠይቃለን። ይህ ያማንዳችን (ጥያቄያችን) በሰዓቱ ካልተሟላ . . ." አለና ያፈት ፊቱን ቅጭ አድርጎ ባለ ዘጠኝ ሚሜ ኡዚውን በቀኝ እጁ ከፍ አድርጎ ለመላው ዓለም ተመልካቾች አሳየ።

.....//////.....

ከዚህ ቀኖሎ ጋዜጠኛው ሁሉ እየተንጫጫ ጥያቄዎችን ለማቅረብ እጁን ወደ ላይ ሰቀለ። ያፈት ዙሪያውን ቃኝና አንዱን የባሕር ማዶ ጋዜጠኛ በጣቱ ጠቆመ።

አለን (ከሲ.ኤን.ኤን)፡ "ከዚህ ተነስታችሁ ወዴት ነው የምትጓዙት?"

ያፈት፡ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ጣና ገዳሞች።

ጂም ሚለን (ቪ.አ.ኢ)፡ አንጋፋዎቹ ልዕልት ኢዛቤል እና አምባሳደሩ ከዕድሜና እስካሁን ከያረሰባቸው መሳሳቶል አንፃር ይህን ተጨማሪና የግዳጅ ጉዞ ይቋቋመዋታል?"

ያፈት፡ "ይቋቋመዋታል።"

ተስማ (ከኢትዮጲያ ራዲዮ)፡ "የማንስትራችን እና የሌሎች አንግሊካውያን ታጋቾች ይዞታ ምን ያመስላል?"

ያፌት "ሁሉም በመልካም ጤንነት ላይ ይገኛሉ።"

ጀነ ግራን (ክታይምስ)፡ "የልዕልቲቱ ጤንነትስ?"

ያፌት "ይህንን ልዕልት ኢዛቤል ራሷ ብትነግራችሁስ?"

ግራን፡ "ማለት?"

"ማለት" አለና ያፌት ኑዚውን ወደ ላይ ቀና አድርጎ ምላጩን ሲጫነው አንድ ጥይት ፈነዳ።

የምስልና የድምጽ መሣሪያዎችን የያዙ ሪፖርተሮች የያፌትን ድርጊት ለመቅረጽ ተረባረቡ። የላተላይት መገናኛ የተጠመደባቸው ተሽከርካሪዎችም ይህንን 'ሴንሲሽናል' ዜና በቀጥታ ለመላው ዓለም ማሠራጨታቸውን ቀጠሉ።

ያፌት የጥይት ተኩስ ሲያሰማ የአዳራሹ በር ካንድ ሜትር ስፋት በማይበልጥ ሽረር ብሎ ተከፈተ። የዜና ወኪሎች በሙሉ መሣሪያዎቻቸውን በቀጥታ ወደ አዳራሹ አዞሩ።

የዊንድሶር ልዕልት ኢዛቤል ከአዳራሹ ወጡና ወደ ያፌት አቅጣጫ አመሩ። አለባበሳቸው እንደ ትናንቱ ነው። የተሰወጠ ነገር ባይኖርም በጣም መጠነኛ መሳሳቆል ይታይባቸዋል። መላ ስውነታቸውን እንደ እንጨት ቀጥ አድርገው፤ ዐይኖቻቸውን ጋዜጠኞቹ ላይ ተክለው፤ በራስ መተማመን ስሜት ወደ ፊት ሲራመዱ ከጎልፍ ጨዋታ የምትመለስ ወይዘሮ እንጂ በጦር መሣሪያ የታገቱ ታጋች አይመስሉም ነበር። ጋዜጠኞቹንም ሆነ የመላውን ዓለም ተመልካቾች ያስገረመው ነገር ልዕልቲቱ ወደ ጋዜጣዊ መግለጫው ሥፍራ ሲመጡ ያጀባቸው እንድም ታጣቂ ያለመኖሩ ጉዳይ ነው።

**********//////////**********

ልዕልት ኢዛቤል ያፌት የቆመበት ያታክልት ግንብ ስር ሲደርሱ ፊታቸውን ወደ መላው ዓለም አዙረው ቆሙ። ለጥቂት ሴኮንዶች ያህል የፕሬሱን ማሕበረሰብ ቃኘት ቃኘት አድርገው . . . "ሌይዲስ ኤንድ ጀንትል ሜን!" በማለት ጀመሩ።

"በመላው ዓለም የተለያየ ጠርዝ ላይ ሆናችሁ ይህንን ትዕይንት የምትከታተሉ ሁሉ! እኔና አምባሳደር ክላይፍ፤ የተከበሩ የኢትዮጵያ ባሕል ሚኒስትርና ሌሎች አምስት እንግሊዛውያን ዜጎቼ 'ቅርሶቻችንን መልሱ!' በሚሉ ኢትዮጵያዊያን ታጣቂዎች ከፍላጎታችን ውጭ በጦር መሣሪያ ታግተን እዚያ..... የምትመለከቱት አዳራሽ ውስጥ ከታጎርን በርካታ ሰዓቶች ተቆጥረዋል። እኔ እንደ አንዲት የሠለጠነ ሀገር ዜጋነቱ ትክክለኛ ጥያቄም ቢሆን በጦር መሣሪያ ኃይል የማስፈጸም ድርጊትን አልቀበልም፤ አላምንበትም።"

"ነገር ግን ግን እዚያ አዳራሽ ውስጥ ባሳለፍኳቸውና ምቾት በጎደላቸው፤ ማለቂያ የለሽ በሚመስሉ ሰዓታት ውስጥ ራሴን ደግሜ ደጋጋሜ የጠየኩት አንድ ጥያቄ አለ። 'ከአንድ

ተኩል ምዕተ ዓመታት በፊት ከአቢሲኒያ ምድር ቅድመ አያቶቹ የዘረፏቸው ታሪካዊ፣ ሃይማኖታዊና ሌሎችም ቅርሳቅርሶች ለኛ ለአንግሊዛውያን ምናችን ናቸው?"

**********////////**********

የልዕልቲቱን ንግግር በተጥታ ሥርጭት ስኮትላንድ ካስሉ ውስጥ ተቀምጠ የሚከታተለው ሽማግሌውና ስውሩ የዓለም ገዢ ሰር ዶይል ኦ ሱሊቫን የልዕልቲቱን ንግግር ሲሰማ ደሙ ፈልቶ ጠረጴዛውን በጥንታዊው ሠይፍ ሰደፍ ጠለዘውና "አንቺ አንሸላሊት! እነዚያ ብራናዎች የመጨረሻዎቹ

ኃይል አመንጪ መሣሪያዎች ናቸው እኮ!" ሲል እንደ ብራቅ ጮኸ።

**********////////**********

'ፑር ኢዛቤል!" አለ ዊስት ሚኒስትር አቤይ ቢሮው ውስጥ ዜናውን የሚከታተለው የእንግሊዝ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር። "ምስኪን ኢዛቤል! ይህን የምትናገሪው አስፈራርተውሽ ነው። የብራናዎቹን ምንነት ካንቺ በላይ የሚያውቅ የለም!" አለ።

**********////////**********

"ለምንስ ነው እስክ ዛሬ ድረስ ቅርሶቹን ለባለቤቱ ሕዝብና መንግሥት ያልመለስነው? ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ አላገኘሁም። እኔ የታላቋ ብሪታኒያ ልዕልት ኢዛቤል አያት ቅድመ አያቶቹ ከኢትዮጵያ ከዘረፏቸው ቅርሶች ጋር በሌብነት በመታገቱ ክልቤ አፍራለሁ። ይህ የአገታና ጠለፋ ተግባር ያለ አንዳች ጉዳት በሠላም እንዲያበቃ ወደ አምላኬ ጸልያለሁ። የሚመለከታቸው የኢትዮጵያና ብሪታኒያ ባለሥልጣናትም የአስተዋይነት ውሳኔያቸውን እንዲሰጡ እጠይቃለሁ! አመሰግናለሁ!" አሉና ፊታቸውን ወደ አዳራሹ አዙረው መንገድ ጀመሩ።

ልዕልቲቱ አዳራሹን ዘልቀው መግባታቸውን ያረጋገጠው ያፌትም "አመሰግናለሁ!" አለና ከአጭሩ የአትክልት ካብ ላይ ዱብ ብሎ ወደ አዳራሹ አመራ። የጋዜጠኞች ጫጫታና ሁካታ የተመላበት ጥያቄ ምላሽ አጣ።

**********////////**********

"ጋዜጠኞችን በሙሉ ከግቢ አስወጡ!" ሲሉ ኮሎኔል ሰናይ በራዲዮናቸው አጭር ትዕዛዝ ከመናገራቸው ዩኒፎርም የለበሱ ፖሊሶች እየገፋፉና በትህትና እየለመኑ ጋዜጠኞችን ከትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ አስወጡ።

ያዳራሹ በር ላይ ያፌት ከሦስት ባለ ሥልጣናት ጋር ተፋጦ ቆሟል።

"ያቀረባችሁትን ጥያቄ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ካቢኔ ቀርቦ ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ እንተ ካስቀመጥከው የጊዜ ገደብ በላይ ይወስዳል። በተጨማሪም ያሉን ጥቂት የጦር ሄሊኮፕተሮች አዲስ አበባ ውስጥ ሥራ የላቸውም። በጣም በጣም ርቀው ድንበር ጥበቃ ላይ መሆናቸውን አትርሳ!"

"እኔም የቀድሞ ፓይለትና ውስጥ አዋቂ መሆኔን አይርሱ!"

"በአሁኑ ጊዜ እንኳንስ ፓይለትነትህን የራስ ቅልህ ላይ ያለውን የፀጉር ብዛትም አውቃለሁ!"

"የኢትዮጵያ የስለላ ተቋሞች ከዚህ ያለፈ ብቃት እንዳላቸው እኔም አውቃለሁ።"

"አሁንም የመጨረሻና ያስተዋይነት ጥያቄያቸውን ልከውልሃል!" ብለው አቶ ግርማይ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ደብዳቤ ሰጡት።

"ይህንን የምህረት ደብዳቤ ጣና ገዳም ስንደርስ ውሳኔ እንሰጥበታልን። ለማንኛውም እኩለ ሌሊት ላይ እንገናኝ!" አለና ወደ አዳራሹ ገባ።

የጠላፊዎቹን መግለጫ ሲያበቃ ጠቅላይ ሚንስትሩ ወደ ልዩ ረዳታቸው ዞሩና "ይህ ውሳኔዬ በተሰጠኝ ልዩ ሕገ—መንግሥታዊ ሥልጣን በግሌ የሰጠሁት ውሳኔ ነው። ዛሬ ማታ ማጥቃቱ ይፈጸም። ነገር ግን ከጠላፊዎቹ በኩል ጠንካራ መቋቋም ከታየ ወይን በታጋቾቹ ላይ አደጋ የሚያደርሱ ከሆነ ወዲያውኑ ማጥቃቱ እንዲቆም!"

"ተቀብያለሁ!" አሉና ረዳቱ በጥድፊያ ከጠቅላይ ሚንስትሩ ቢሮ ወጡ።

ምዕራፍ ሰላሳ ዘጠኝ

"ይህን የጠሰፋና እገታ ወንጀል ለማክሸፍ የምንችለው ከአጋቾቹ በስተጀርባ ያለውን ስውር መሪ ስንይዘው ነው።"አለ ሳሙኤል አለቃው ያቀበሉትን ቡና ፉት አለና።

"የግያታያ መሪ አለ ብለህ ታስባለህ?" አሉ ኮሎኔል ሰናይ።

"አዎን! ባሕታዊው ነው ብዬ አምናለሁ። የዚህን፣ ጎስት (መናፍስት) መነኩሴ ታሪክ ለመቆፈር ሞክሪያለሁ። ባሁኗ ቅፅበት የት እንዳለ አይታወቅም።"

"ደጠቅመናል የምትለውን ፍንጭ ሁሉ ቆፍር። ነገር ግን ጊዜ እየከዳን ስለሆነ ቁፈራህን ከዶግ ወደ ኤክስካቫተር ለውጠው!"

"ኮሎኔል! እኔም ልጠይቅዎት ያሰብኩት ይሄንኑ ነበር!"

"ምኑን? ኤክስካቫተር?" አሉ ተገርመው።

"አዎን። የፖሊስ አውሮፕላን!"

"ምን ልትሆን?"

"ቀድሜ ወደ ሰሜን መብረር አለብኝ።"

"ይህ የሚሆን አይደለም። ያሉን የፖሊስ አውሮፕላች ለሰፕላይ ሥራ በረዋል።"

"ግዴታ መብረር አለብኝ!"

ኮሎኔል ሰናይ በቀጥታ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር በስልክ ካወሩ በኋላ ዘንና አንድ ፎክር አውሮፕላን መደበኛ ጉዞዋን ሰርዛ ቻርተር እንዲደረግልህ ጠይቀዋል። ግን ሳሙኤል!"

"አቤት!"

"የምታደርገውን ነገር እወቅ! ያለዚያ ከአሁለ ሌሊት በኋላ አኔም አንተም ሥራ ፈላጊዎች እንደምንሆን አትጠራጠር!"

**********//////////**********

ኤፍሬምና ባልዳረቦቹ የፖሊስ ዩኒፎርም ለብሰው፣ ትጥቆቻቸውን ዝግጁ አድርገው፣ ስንቅ አቀባዩን የእንግሊዝ ኢምባሲ ቫን ቀድመው እያጀቡ ወደ እንግሊዝ ትምህርት ቤት ከነፉ። የቀበና አደባባይን በግማሽ ክብ ዞረው ወደ ቀኝ የሚታጠፈውን ሰፊ እና ዘመናዊ ጎዳና ሊያያዙት ጌዲዮን ወደ አሽከርካሪው ወንድሙ ኤፍሬም ዞሮ "አቁምልኝ!" አለው። በድንገት ፍሬኑ የተረገጠው የፖሊስ ሚኒ ባስ የዋይታ ድምጽ

አለምቶ ቀጥ ሲል ከኋላ ይከታተላቸው የነበረው ኮድ 03 የዲፕሎማቲክ ተሽከርካሪም ቆመ።

"ሃምሳ አለቃ!" አለ ጌዲዮን በጋቢናው መስኮት ወጣ ብሉና ትከሻው ላይ የለጠፋቸውን የኢንስፔክተር ማዕረግ ኮከቦች ለሞተረኛው ትራፊክ እንዲታዩ አድርጎ።

"አቤት አለና የትራፊክ ፖሊሱ ሰላምታ ሰጠው።

"ከፊት ቅደምና አጅበን። ወደ እንግሊዝ ትምህርት ቤት!" የትራፊክ ፖሊሱ ቀልጠፍ ብሎ ፈጣንና ዘመናዊ ሞተሩን አስነስቶ፣ መብራት እያብለጨለጨ፣ ሳይረኑን እያስጮኸ ቀደማቸው። ተከተሉት።

**********/////////**********

ዮዲት የፕሬስ መግለጫው ላይ ተሳትፈው የተመለሱት ልዕልት ኢዛቤልን "በመልካም ፈቃድዎ ላደረጉት ንግግር በጣም ነው የማመሰግንዎት!" አለቻቸው።

"የተናገርኩትን መናገሬ የናንተ መጠቀሚያ አያደርገኝም!" አሉ ልዕልቲቱ።

ዮዲት እኚህን ፍንክች የማይሉና በራሳቸው የሚተመማኑ ልዕልት በልቧ እያደነቀች "ቡና?" አለቻቸው።

ለታገቱት ሰዎች በሙሉ ቡና ካደለች በኋላ "ክቡራን! ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ራት ይቀርባል!" አለቻቸው።

**********/////////**********

የቅጥር ግቢው በር ላይ ዘብ የቆሙት ፖሊሶች በፖሊስ ሞተረኛና በፖሊስ መኪና ታጅቦ የመጣውን የእንግሊዝ ኤምባሲ መኪና አላለፉት። ሁለቱ ሚኒ ባሶች በቀጥታ ወደ አዳራሹ ሲያመሩ ጌዲዮን ሞተረኛውን "ከዚህ መመለስ ትችላለህ! አመሰግናለሁ።" አለው።

በቅድሚያ ምግብና መጠጥ የያዘው ኮ.ዲ.03 የእንግሊዝ ኤምባሲ ቫን የኋላ ተከፋች በሩን ወደ አዳራሹ በር አስጠግቶ አቆመውና አሽከርካሪው ወርዶ የኋላውን በር ከፈተው። አራቱ ፖሊሶች ታጣፊ ክላሺንኮቭ ጠመንጃቸውን ይዘው ወደ በሩ ተጠጉ።

አዳራሹ በር ላይ የቆመው ተረኛ ዘብ ሳምሶን የሰዎቹን ማንነት ካረጋገጠ በኋላ በሩን በሁለት ሜትር ሰፋ ከፈተው። ከውስጥ ያሬድና ራሄል የምግብ ማቅረቢያ

ተሽከራካሪዎችን እየገፉ ወደ መኪናው ቀረቡ። የመጣው ንጉሣዊ ምግብና መጠጥ አንድ በአንድ በጋሪዎቹ እየተጫነ ወደ አዳራሹ ገባ።

የኤምባሲው መኪና ጭነቱን አራግፎ ስፍራውን ሲለቅ ጌዲዮን ኤፍሬምን "ቀጥል" አለው።

የፖሊስ ሚኒ ቫኑ ወደ ኋላ እየተጠጋ.....እየተጠጋ መጥቶ የአዳራሹን በር ለመንካት አንድ ሜትር ሲቀረው ቆመ።

"ዋት ዘ ሄል ኢዝ ጎይንግ ኦን?" (ምን እየሆነ ነው?) አለ መጥረቢያው በለሆላስ ድምጽ አጠገቡ ላለው ስናይፐር። የአዳራሹን በር በግልፅ የሚያሳይና ሃያ ሜትሮች ርቀት ላይ የሚገኝ የትምህርት ክፍል ውስጥ ፀሥር የብሪታኒያ እና ፀሥር የኢትዮጵያ ኮንማዶ ጦር አባላት ሰፊ የትምህርት ክፍል ውስጥ አድፍጠዋል።

ኤፍሬምና ጌዲዮን የፖሊስ ሚኒ ቫኑን የኋላ በሮች ግራና ቀኝ ሲከፍቷቸው በሮቹ ካዳራሹ በር ጋር ገጠሙ። ያዳራሹ በር በሁለት ሜትር ያህል ስፋት ተከፍቷል። እሁን በቫኑ እና በአዳራሹ መሃል የሚከናወነው ነገር ለአድፋጭ ኮማንዶዎቹ አይታያቸውም።

"እጅግን ይስጡኝ።" አለ ኤፍሬም። ባሕታዊው የቀኝ እጃቸውን ዘረጉለትና በቀስታ ክቫኑ ሲወርዱ ዮዲት "ዌል ካም ፋዘር!" ብላ በፈገግታ እጃቸውን ይዛ እየመራች ወደ ውስጥ ወሰደቻቸው። ዶክተር ሥራውብዙም በጌዲዮን ድጋፍ ክቫኑ ወረዱና ወደ አዳራሹ ዘለቁ። ግራ መጋባትና የጭንቀት ገጽታ ይታይባቸዋል። "ይፍጠኑ ጌታዬ!" አለ ኤፍሬም።

"እነዚህን ሳጥኖች ማውረድ አለብኝ። እግዙኝ።" አለ የባሕታዊው ታማኝ አገልጋይ። የተለመደውን ካኪ ኮትና ሱሪ ከጥቁር ቆዳ ጫማ ጋር ለብሶ ኤኬ.54 ክላሺን ኮቭ ጠመንጃ በጀርባው አንግቷል።

"ቶሱ! ፍጠኑ!" አለ ሳምሶን። ኤፍሬምና ጌዲዮን አንዱን የእንጨት ሳጥን ግራና ቀኝ ይዘው ወደ አዳራሹ ሊያስገቡ ሳምሶንና የባሕታዊው ጠባቂ ሁለተኛውን ሳጥን አውርደው ወደ አዳራሹ አስገቡ። ሳጥኖቹ በጣም ክባድ ለመሆናቸው ከተሸካሚዎቹ ሁኔታና አቋም ያስታውቀል። ይህ ከተከናወነ በኋላ ዶክተር አንዱዓለም "ማረጋገጥ ከፈለክ ክፍተህ ማየት ትችላለህ።" አሉና አንድ ትልቅ ሳምሶናይት ቦርሳ ለጌዲዮን አቀበሉው።

"አመሰግናለሁ። ሁለታችሁንም አምናችኋለሁ። መልካም ዕድል!" ብሎ ወደ ቫኑ ገሠገሠ። ሁለቱ የኤፍሬም ባልደረቦች ይህ ሁሉ ሲከናወን ታጣፊ ክላሺን ኮቫቸውን አቀባብለውና መጠበቂያዎቹን ለቀው ግን አፈሙዛቸውን ወደ ታች፣ እንደ ዋሣ አንጠልጥለው አንዱ ከቫኑ በስተግራ ሌላው በስተቀኝ አካባቢውን በንቃት ይጠብቁ ነበር።

ጌዲዮን "ይህን ይዛችሁ ግቡ!" ብሎ ሳምሶናይቱን ለቢኒያም አቀብለውና በፍጥነት ቫኑ ውስጥ ተከታታለው ገቡ። ጌዲዮን ወዲያውኑ በሮቹን ሲዘጋቸው ከውስጥ በኩል ተቆለፈ። ጌዲዮን ወደ አዳራሹ ፊቱን መልሳ የሚፈልገው ሰው ያለ ይመስል ሊቃኝ ከሮዲት ጋር ተያዩ። በጣም ፈጣን፣ የቅፅበት ታህል ብቻ ጊዜ የወሰደች የዐይን ጥቅሻ አሳየችው። መልስ አልሰጠም። ፊቱን አዙሮ ጋቢናውን ከፍቶ ገባ።

**********/////////**********

ኤፍሬም መኪናውን አስነስቶ ወደ ግቢው መውጫ በር ሲነዳና የመኪናው ከሰላ ሲገልጥላቸው አድፋጭ ኮማንዶዎቹ የጠበቃቸው ዕይታ በአንድ ስንዝር ስፋት ብቻ የተከፈተው በር ላይ ታጣፊ ክላሹን ቁንጮቹ ላይ አጋድሞ ሲጋራ የሚያጨሰውን ተረኛ ዘብ ሳምሶንን ብቻ ነበር የተመለከቱት።

**********/////////**********

የ"ኦፐሬሽን መቅደላ" አባላት እዚህም እዚያም በተንተን ብለው የተለያዩ ተግባሮች ላይ ተሰማርተዋል። ዮዲት ማካሮቭ ሽጉጧን ወገቧ ላይ ታጥቃ፣ ያጭር ርቀት መገናኛ ራዲዮ ይዛ ከልዕልቲቱ ካምባሳደሩ እና ከባሕል ሚንስትሩ ጋር ታወራለች። ዶክተር አንዱዓለም የብራና መጽሐፍቱን ከሰነድ ጋር እያስተያየ ቆጠራ የሚያደርግ ይመስላል። ያፌት፣ ሳምሶን እና ያሬድ አውቶማቲክ ጠመንጃዎቻቸውን ይዘው ያዳራሹን በሮችና መስኮቶች እየተዘዋወሩ ይቆጣጠራሉ።

ራሄል ለታጋሎች ቡና እየቀዳች ታዳርሳለች። ድንገት ያዳራሹ ደቡባዊ ግድግዳ ሲቦደስ የተሰማው ፍንዳታ ታጋችና አጋቾችን ከተቀመጡበትና ከቆሙበት በድንጋጤ ቢያዘልላቸውም ዮዲት የወሰደችው ቅጽበታ እርምጃ ግን በባልደረቦቿ ብቻ ሳይሆን በታጋቾቹም አድናቆትን ሳያሰጣት አይቀርም።

ያዳራሹ ግድግዳ ከጣራው ጥቂት ዝቅ ብሎ ምንነቱ ባልታወቀ ፈንጂ ከመቦደሱ በተከታታይ ሁለት የጢስ ቦምቦች በተቦደሰው ክፍተት ገብተው ሲፈነዱ አዳራሹ በጢስ መታፈን ጀመረ። ከድንጋጤያቸው ያገገሙት ያፌት፣ ያሬድ፣ ሳምሶን እና ራሄል አውቶማቲክ ጠመንጃዎቻቸውን ወድረው በሮችና መስኮቶችን በመያዝ የጥይት ዝናም በየክፍተቶቹ ወደ ውጭ ማርከፍከፍ ጀመሩ።

ከሁሉም ቀድማ የተንቀሳቀቸው ግን ዮዲት ነበረች። ፍንዳታውን ተከትሎ አዳራሹ በጢስ መታፈን ሲጀምር ዮዲት ወገቧ ላይ የታጠቀችውን ማካሮቭ ሽጉጥ በፍጥነት መዛ በማውጣት መጠበቂያውን ለቀቀችና በቀጥታ ልዕልት ኢዛቤል ግንባር ላይ ስትደግን ልዕልቲቱ ያላንዳች ፍርሃት ረጋ እና ፈገግ ብላ ዮዲት እየቻት።

ሦስቱ የለንደን ሚውዚዬም እንግሊዛውያን፣ አምባሳደሩ፣ እና የኢትዮጵያ ባሕል ሚንስትር በያሉበት ሥፍራ ላይ ግማሹ በደረቱ ኩሺ ሲተኛ ሌላው በየጠረጴየዛው ስር ከለላ ሲወሽቅ ሁለቱ የስኮትላንድ ያርድ ፖሊስ ባልደረቦች ግን ዐይኖቻቸውን ወዲህ ወዲያ እያቅበዘበዙ ወደ ለዕልቲቱ መራመድ ሲጀምሩ ሳምሶን ኤ.ኬ 47 አውቶማቲክ ጠመንጃውን እንደወደረ ተንደርድሮ መጣና.....“ጌት ባክ.....! ላይ ዳውን! (ተመለሱ፣ ወለሉ ላይ ተጋደሙ)" ሲል በጩኸት አዘዛቸው።

ዐይኖቹ ገዳይ እሳት ይፈኝጥቹ ስለነበረ ሳያቅማሙ ታዘዘዙት።

ያፌትና ያሬድ አሁንም ባዳራሹ ፀባብ ክፍተቶች ወደ ውጭ እየቶኩሱ ነው። ሳምሶን ደግሞ ልዕልት ኢዛቤል እና የእንግሊዙ አምባሳደር ላይ ታጣፊ ክላሹን ደግኖ ሲቆም ዮዲት ጥቂት ራቅ ብሎ ጠረጴየዛ ላይ ወደ ተቀመጠውና ከመንግሥት ባለ ሥልጣናት ጋር ግንኙነት ወደሚያደርጉበት መደበኛ ቴሌፎን ልዕልቲቱን በአፈ ሙዝ እየነዳች ወሰደቻቸው። “አሁን የማዝዎትን ከፈጸሙይህን በምቾት የተጠበቀ ሰውነትዎን ከዘጠኝ ሚሊሜትር ጥይት ያድናሉ!" አለችና ስልኩን አንስታ ቁጥሮችን መምታት ጀመረች።

“ዮዲት! ቶሎ ከመንግሥታችሁ ባለ ሥልጣናት ጋር አገናኚኝ" አሉ አስገራሚ እርጋታ የሚታይባቸው ልዕልት ኢዛቤል።

**********//////////**********

ከአዳሩሹ ውጭ ጨለማን ተገን አድርገውና በኢንፍራ ሬድ (በጨለማ የሚላይ መነጽር) እየታገዙ ወደ አዳራሹ በማጥቃት ስልት መንቀሳቀስ ጀምረው የነበሩት የኤስ.ኤስ ኮማንዶዎች ካዳራሹ ውስጥ የገጠማቸው የአውቶማቲክ መሣሪያዎች ተኩስ ያልጠበቁት ከመሆኑም ሌላ ሁለት ባልደረቦቻቸው እንዱ እግሩ ላይ ሌላው ክንዱ ላይ በጥይት ተመተው መጠነኛ ቁስል ስለደረሰባቸው ፀራት ባልደረቦቻቸው ማጥቃቱን አቁመው ቁስለኞቹን ወደ ኋላ ለማግለል ተገደዱ። አሁንም ካዳራሹ በሮች የተኩስ ውርጅብኝ ይንጣጣባቸው ስለነበር መጠጋት አልቻሉም። ጆሮው ላይ በተለጠፈው ራዲዮ እያዳመጠ አፉ ላይ በቀረበው መናገሪያ ይጫጫህ የነበረው 'መጥረቢያው' "ባክ አፍ! ወደ ኋላ ተመለሱ!" ሲል ለባልደረቦቹ በራዲዮኑ ተናገረ። ሁሉም ጆሮአቸው ላይ በተለጠፈው መገናኛ ስለሰሙት በትዕዛዙ /መሠረት ወደ ኋላ ማፈግፈግ ሲጀምሩ ጨለማን ተገን አድርገው አዳራሹን ከበስተ ጀርባ በመስኩቶቹ በኩል ለማጥቃት አቆብቁበው ይጠባበቁ የነበሩት የአድዋ ክፍለጦር ጸረ ሽብር ኮማንዶዎችም ተመሳሳይ ትዕዛዝ ስለደረሳቸው ወደ ኋላ መመለስ ጀመሩ።

**********/////////**********

"እዎን ዮዲት ከጠቅላይ ሚንስትሩ ረዳት ከግርማይ በርሄ ጋር ነው የምታወሪው።"

"በጣም ጥሩ" አለች ዮዲት። "አሁን ከርስዎ ጋር የማውራት ፕሮግራም አልያዝኩም፤ ልዕልቲቱን ያናግሩ!" አለችና የስልኩን እጀታ ለልዕልት ኢዛቤል አቀበለቻቸው።

"ሚስተር በርሄ? አሁን የማወራዎት አውቶማቲክ መሳሪያዎች እናቴ ላይ ተደግነውብኝ ነው። አምባሳደራችን፣ ሚንስራችሁ እና ሌሎቹም ታጋቾች በተመሳሳይ አደጋ ሥር ናቸው። እኛን ለማስጨረስ ካልፈለጋችሁ ይህንን የጀመራችሁትን ኃላፊነት የጎደለው ወታደራዊ ጥቃት አቁሙ!" ልዕልቲቱ ይህን ከመናገራቸው ዮዲት ትከሻዋ ላይ በማንገቻ አንጠልጥላው የነበረውን ዘጠኝ ሚሊሜት ፀዚ አቀባብላ በርካታ ጥይቶች በልዕልቲቱ አናት ላይ ተኮሰች። ልዕልት ኢዛቤል ስልኩን ወለሉ ላይ ጥለው፤ ምድራዊ የማይመስል ጩኸት ጮሁና ወለሉ ላይ ወደቁ።

"ዮዲት! ዮዲት!" ዮዲት ስልኩን አነሳችው። "አቤት የተከበሩ!" ድምጿ የፈዝ ቅላጼ ነበረው።

"ዮዲት! የኃይል ትዕዛዝ ማን እንደሰጠ አላውቅም። ለማንኛውም አስቆመዋለሁ። ነገር ግን ታጋሎቹ ላይ ቅንጣ እንኳ ጉዳት ብታደርሱ....." ዮዲት ሳታስጨርሳቸው ስልኩን ዘጋችው።

"ቀድሞውንም ተናግሬ ነበር!" አሉ ከንዴታቸው ብዛት ካናታቸው እንፋሎት የሚወጣው ጠቅላይ ሚንስትር። ይሄን እርምጃ ለመውሰድ የወሰንው ካቢኔያችንን ሳናማክር ነው። የገፋፋችሁኝም እናንተ ናችሁ። አጋቾቹ ጥቃት ቢከፈትባቸው ሊወስዱ የሚችሉት እርምጃ አሁን እበክረነረ ተገንዝበናል። ካሁን በኋላ ጥቃት ከከፈትን ወደ የማንልበትን የመጨረሻውን አመቺ አጋጣሚ እስክናገኝ ድረስ መጠበቅ አለብን! ገባችሁ?" አሉና አቶ በርሄን፣ የአድዋ ክፍለጦር አዛዥን፣ ያገር ውስጥ ጉዳይ ሚንስትራቸውን እና የእንግሊዝ ኤምባሲውን ወኪል አሳ በሚተፉ ዐይኖቻቸው ተመለከቷቸው። ሁሉም በአዎንታ ራሳቸውን ወዘወዙ።

በተረፈ ያሁኑ የጥቃት ትዕዛዝ የተሰጠው አፈሻል ባልሆነ (የካቢኔው ይሁንታ የሌለበት) ዘይቤ ነው። ስለዚህ ከፕሬሱና ከሕዝብ ጆሮ ተሰውሮ ይጠበቅ!

**********////////**********

ምዕራፍ አርባ

የቦሌ አየር ማረፊያ የደህንነት ኃላፊው በጣም አነስተኛ የመንገድ ቦርሳ ብቻ የያዙትን ቂስ እየመራ የኤሌክትሮኒክስ መፈተሻውን እና የመንገደኞች መቆጣጠሪያውን ካለለፋቸው በኋላ ከፊት ቀደም እያለ "ኮሎኔል ሰናይን ያውቋቸዋል አባቴ?" ሲል ጠየቀ። መልስ የለም። "አባ . . ." አለና ወደ ኋላው ሲዞር ግድግዳ ላይ የተንጠለጠለው በጣም ትልቅና ዘመናዊ ቴሌቪዥን ላይ አፍጥጠው አየ።

የደህንነት ኃላፊው ተገርሞ ወደ አባ ተመለሰና የሚመለከቱትን መመልከት ጀመረ። የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ዜና ነው።

".....እነዚህን ጥንታዊና ታሪካዊ የብራና መጽሐፍትና ሌሎችንም በርካታ የታሪክ ቅርሶች ለብሔራዊ ቤተ—መጽሐፍት በስጦታ ያበረከቱት አባ ጥበበ ሥላሴ እንደተናገሩት . . ."

በቴሌቭዥኑ መስኮት አያሌ የብራና እና ሌሎችም የታተሙ መጽሐፍት በሳጥንና በየጠረጴዛው ተከምረው ይታያሉ። ስለጦታው ለጋሽ የሆኑት ዕድሜያቸው ከስድሳ ዓመት በላይ የሚገመት ባሕታዊ ስለ ስጦታቸው ያወራሉ። ዜናውን በቴሌቪዥን የሚከታተሉት ቂስ አዕምሮአቸው በብርሃን ፍጥነት ሕዋውን እየቀዘፈ ያስባል።

"አባቴ! አባቴ . . ."

ቂሱ እጃቸውን የልብስ ተከህኗቸው ኪስ ውስጥ ከተቱና ሞባይላቸውን ሲያወጡ የደህንነት ባለሥልጣኑ ተገርሞ መመልከት ቀጠለ።

"ሄሎ ኮሎኔል ሰናይ። "

"ኤርፖርት ቼክ ፓይንት ላይ የኢ.ቴ.ቪ ዜና እያየሁ ነው።"

"አዎን ፍተሻውን ያለ ችግር አላልፎኛል . . . እኔ ስሙኝ። ጊዜ የለንም። የሰዓቱ ዜና የሚያላየው ለብሔራዊ ቤተ መዛግብት አያሌ የብራና መጻህፍትን የለገሱ መኩሴ . . . ወይንም ባሕታዊ ነው። "

"የዜናውን ቅንጫቢ እንደ ሰማሁት . . . አባ . . . ማንትስ . . . በቅርስ ስብስብና ጥበቃ፣ ካገር የወጡ ቅርሶችን ለማስመለስ ባደረጓቸው ጥረቶች የሚታወቁ . . .ናቸው።"

"ገባኝ! ገባኝ!" አሉ ኮሎኔሉ።

"ይህን ሥጦታ ያበረከቱበትን ቤት ማግኘት ቀላል ነው። አባክዎን ይህ ባሕታዊ ድራሹን ሳያጠፋ ድረሱበት!" አሉና ቁሉ ሞባይላቸውን ዘግተው ኪሳቸው ውስጥ ከተቱ።

"አባቴ!" አለ እጅግ የተገረመው የፀጥታ ሰው።

"ኧ. . .አቤት !" አሉ ቁሉ።

"ይከተሉኝ አባክዎን።"

ሰንዞ ዝግጁ ሆኖ ወደሚጠብቃቸው ፎክር መራቸው። ቻርተር ይደረጋል የተባለው አውሮፕላን ከአየር መንገዱ ጋር በተደረገው ንግግር የመንገደኞችን ንብ በፍፁም መሰረዝ የማይቻል መሆኑ ስለተገለፀ በምሽቱ አውሮፕላን ለመብረር ተገደዱ።

**********////////**********

የቀበናን ድልድይ ይዞ፣ በሺ ሰማንያ መሥመር ግንፍሌን፣ እንዲሁም በምኒልክ ሆስፒታል ወደ ሳንፎርድ ትምህርት ቤት ባለው ክልል ውስጥ የሚገኙት ነዋሪዎች ሰሞኑን የተከሰተው ድርጊት መኖሪያ ቀዬአቸውን የመላው ዓለም የትኩረት ማዕከል ስላደረገላቸው የተደሰቱ ባይጠፉም አብዛኛዎቹ ነዋሪዎች ግን . . ." ማለፍ ክልክል ነው . . . ወዴት ነው? . . . በዚህ ውጡ . . . በዚያ ግቡ . . ." የሚለው የፖሊስና የጸጥታ ኃይሎች ግርግርና ወከባ አስመርሯቸዋል። የፖሊስ ተሽከርካሪዎች ሳይረን ጩኸትም የቀን ተሌሊት ሙዚቃቸው ሆኗል።

ይባስ ብሎ የምሽቱን ሰማይ የሚንጠው የዛሬውን ድምጽ "ለየለት መሰል!" እያሉ የተኙት ተነስተውና የተነሱትም ተሯሩጠው በመውጣት፣ ወደ ሰማይ ማንጋጠጥና በስጋት መመልከት ጀመሩ።

**********////////**********

ግዙፉና ጥቁሩ፣ አስፈሪው፣ ተዋጊ ሄሊኮፕተር የጨለመውን ሰማይና አካባቢውን በነውጠኛ ድምፁ እየናጠና ዐይን የሚያጥበረብረውን መብራቶቹን ፏ! አድርጎ የትምሕርት ቤቱን ቅጥርና አካባቢ እሽኮለሌ ይዞርበት ጀመረ። ከትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢና ውጭ ደግሞ አምቡላንሶችና የፖሊስ ተሽከርካሪዎች ሳይረናቸውን እያጮኹና መብራቶቻቸውን ብልጭ ድርግም እያረጉ ዙሪያ ገባውን ወረውታል።

ቀን ጋዜጣዊ መግለጫ የተካሄደበት የግቢው ማዕከላዊና ሰፋ ያለ አስፋልት ላይ የቆመ አንድ የፀጥታ ሠራተኛ ኃይለኛ የእጅ ባትሪውን ወደ ሰማይ ቀስሮ ብልጭ ድርግም፣

ብልጭ ድርግም፤ እያደረገ ለሄሊኮፕተሩ አብራሪ ሲግናል (ምልክት) መስጠት ጀመረ። ረጂም አጭር . . . አጭር . . . ረጅም ብልጭታዎች። እነዚህን ቀላል ሲግናሎች የሚመለከተው ፓይለት ወደነጥብና ሰረዝ (. -) ቀጥሎም ነጥብና ሰረዞቹን ወደ ኤ.ቢ.ሲ.ዲ ሆሄያት እየለወጠ መልዕክቱን በማንበብ አቅጣጫውን ያስተካክላል።

ወደ ግራ . . . ቀኝ . . .። ከጥቂት ደቂቃዎች 'ማኑቨር' በኋላ በመጨረሻ ግዙፉን ሄሊኮፕተር በትክክል የግቢው መካከለኛ ሥፍራ ላይ አሳረፈው። ሄሊኮፕተሩ ካረፈ ከሁለትና ሦስት ደቂቃዎች በኋላ አንድ በባትሪ ኃይል የምትሠራ ባለ ሁለት ቶን ችሎታ 'ፎርክ ሊፍት' ግቢውን ዘልቃ ስትገባ ዩኒፎርም የለበሰው ተረኛ ፖሊስ ተቆጣጠሪ እየመራ ወደ አዳራሹ በር ወሰዳት።

ሳምሶን ፖሊሱን "እመሰግናለሁ። ተመለስ!" አለውና የማሽኗን ኦፐሬተር "ግባ" ብሎ በሩን ከፈተለት። ፎርክ ሊፍቷ ገባች።

**********//////////**********

"አሁን ወርቃማ ጊዜ ነው!" አለ መጥረቢያው ከራስ ቅሉ ላይ ጠልቆ ማዳመጫው ጆሮው ላይ፤ መናገሪያው አፉ አጠገብ በተለጠፈ የመገናኛ መሣሪያ።

"ጠብቅ። ምንም አክሽን እንዳትወስድ!"

"አሁን ወይንም መውጣት ሲጀምሩ እንምታቸው!" አለ ካሎኔል አሰፋ።

" ትዕዛዝ ላንሰጥ ተኩስ እንዳትከፍት!"

የአበሻና የፈረንጅ ኮማንዶዎች በየማዕዘኑ አድፍጠውና ኩሼ ተኝተው በጉጉትና በንቃት ያለቆቻቸውን ምልክት ይጠብቃሉ። ፎርክ ሊፍቱ ትላልቅ ሣጥኖችን በሹካ መሰል ብረቶቹ ጭኖ ወደ ሄሊኮፕተሩ፤ ያን መሬት አኑሮ እንደገና ወደ አዳራሹ፤ እየተመላለሰ በአምስት ዙር ወደ ሃያ የሚጠጉ ሣጥኖችን ሄሊኮፕተሩ ሥር ከመረ።

ልዕልቲቱ፤ አምባሳደሩ ሚኒስትሩ፤ ሦስቱ የለንደን ሙዚየም ባልደረቦች እንግሊዛውያን እና ሁለቱ የልዕልት ኢዛቤል አጃቢዎች በቅደም ተከተል፤ በያፌት ያሬድና ሳምሶን የጦር መሣሪያ አፈሙዝ ተከበው ከአዳራሹ ወጡና አምስት ሜትር ርቀት ላይ ሲደርሱ መሬት ላይ እንዲቀመጡ ታዘዙ። ትዕዛዙን ፈፀሙ። ሦስቱ ታጣቂዎች በታገቱት ሰዎች ከለላ ስር ተቀምጠው መሣሪያዎቻቸውን ደገኑባቸው።

አሁን የአዳራሹ መብራቶች በሙሉ ጠፍተው አንድ አነስተኛ መብራት ብቻ መድረክ ላይ በርቶ ደብዘዝ ያለ ብርሃኑን ይፈነጥቃል።

"እዚህ ተቀመጥ!" አለች ዮዲት ዶክተር ሥራውብዙ ላይ ማክሮብ ሽጉጧን ደግና። ጂንስ ሱሪ በቡት ጫማ፣ ከላይ ጥቁር ጃኬት ለብሳ ጥቁር የሹራብ ቆብ አናቷ ላይ አጥልቃለች። አዚ ትከሻዋ ላይ፣ ሁለት የእጅ ቦምቦች ደግሞ በቀበቶ ወገቧ ላይ ታጥቃለች።

"ለምን?"አሉ ዶክተር ሥራው ዐይንና ጆሮዋቸውን ማመን አቅቷቸው።

ዮዲት በጸጥታ ኃይሎች መካከል በተለይም የምርመራ አባላቱ በአዳራሹና በአካባቢው የሚያደርጉትን የግንኙነት ልውውጥ ትከታተልበት የነበረውን ራዲዮ መድረኩ ላይ ያለው ጠረጴዛ ላይ አኑራዋለች። አረንጓዴው መብራቱ አልፎ አልፎ ብልጭ ድርግም ይላል።"

"ቁጭ በል!" ስትል አንባረቀችባቸው።

አዛውንቱ ዶክተር እየተንቀጠቀጡ ተቀመጡ። ፍርሃት እና ድንጋጤ ያቸውን ለመደበቅ ያደረጉት ጥረት አልተሳካላቸውም።

"ባህታዊው ወደ ራሄል መራመድ ሲጀምሩ ዮዲት ግራ እጇን ብድግ አድርጋ . . ." ይህ በኔና በሥራው መሃል ብቻ ነው። ይመለሱ!" አለቻቸው። ያቺ አማላይቷ ዮዲት አሁን አራስ ነብር መስላለች። ባሕታዊው ራሳቸውን ነቅንቀው ከመድረኩ በመውረድ በዝምታ ወደ በሩ ሲያመሩ ዶክተር አንዱዓለም አንገቱን ሰብሮ ተከተላቸው።

"ምንድነው ነገሩ! የት ነው ትታችሁኝ የምትሄዱት?" አዛውንቱ ዶክተር በሚለቀጥጥ ጩኸት ዋይታቸውን ለቀቁት።

"ዝም በል። ሺት!" አለች ዮዲት።

"ምነው ዮዲት? ምን ነካሽ? ምን በደልኩሽ?" አሉ ልቅሶ እየዳዳቸው።

"አንተ ተባይ! አኩይ!" አለ ክላሺኑን አቀባባሉ ዶክተሩ ላይ የወደረውና ሽበት የወረረው የባሕታዊው አገልጋይ።

ድሮም አይወዱትም፣ ድሮም ይፈሩታል። እንኳንስ አፈሙዝ ደግኖባቸው መልኩ እና ሁኔታው ብቻ ሲቀሩቸው ኖሯል። የዶክተር ሥራውብዙ አየለ አዕምሮ 'ከታሪክ ማሕደር' የተሰኘ ዶክመንታሪ ፊልም የከፈተ ይመስል ወደ ቆየ ዘመን በሐሳብ ነጎዱ።

"ስንቱን ቅርስ ሸጥከው . . ቸበቸብክው!" አለች ዮዲት በጥላቻ እየተንገሸገሸች። "ባሕር ማዶ ያለውን ስናስመልስ፣ አገር ቤት ያለውን እያነፈነፍክ ስትሸጥ ኖርክ። ስንት፣ ለማን፣ የት፣ በስንት እንደሸጥክ ዝርዝሩን ከሀ እስከ ፐ ልነግርህ እችላለሁ። እኔም ሆንኩ ከኔ በፊት የነበሩትና ያሉት የቅርሳችን አባላት ሌብነትህንና ስስትህን ታግሰውት ኖሩ። ያሁኑ ግን እጅግ ፀያፍ መከራህ ነው!"

"እንቺ ሴት ምንድነው የምታወሪው . . . !" እየተንዘፈዘፉ ሙሁና ከመቀመጫቸው ሊነሺ ሲሉ ቡት ጫማ ባጠለቀችበት ቀኝ እግሯ አፍ. . .ንጫቸው ላይ ስትመታቸው ተመልሰው ወንበሩ ላይ . . . ከነወንበሩ ተያይዘው በጀርባ ወለሉ ላይ ተዘረሩ። ቆይው ቀና አሉና በተሸበሩ ዐይኖቻቸው ዮዲትን እየተለማመጡ ካፍንጫቸው የሚወርደውን ደም አንዱ በእጃቸው አንዱ በኮታቸው መጥረግ ጀመሩ።

"እምን! ዓመታትን በፈጀ ጥረትና ልፋት ለዚህ ኤግዚቢሽን የመጣውን ብርቅ መጽሐፍ ልትሸጥ? ስሜን ኢትዮጵያ ምናምን ብለህ ቱል አቪቭ አልበረርክም? አናውቅም? ለምን ሄድክ? የኢየሩሳሌምን ገዳም ልትሳለም?" አለችና ዮዲት ከ.....ት! ብላ ሳቀች።

"አብዳለች ማለት ነው!" አሉ ሽማግሌው በፍርሃት እየራዱ።

"ያንተ የቱሪስት አስጎብኚ ንግድ ሥራ መነሻ ካፒታሉ የእሮጌው ወርቅ አይደለም?"

ዶክተር ሥራው 'እሮጌ' የሚለውን ቃል ሲሰሙ አመድ የተነሰነሰበት ጉበት መሰሉና.....ሊስቱ ተቃረቡ።

ምዕራፍ አርባ አንድ

'እንዴ? አልዘጋሁትም?' አሉ ቂሱ። አጠገባቸው የነበረው መንገደኛ ዞር ብሉ አያቸው።

ቦርሳቸውን ከፈቱና የመገናኛ ራዲዮናቸውን አወጡ። ይህ ኤስ.ኤስ.ቢ (ሲንግል ሳይድ ባንድ) የሩቅ ርቀት ራዲዮ በእጅ የሚይያዝና ኃይለኛ ባትሪ የሚጠቀም ነው። ቂሱ ሳያጠፉት ቀርተው ነው አሁን ድምጽ ያሰማው።

"የት ነው ትታችሁኝ የምትሄዱት!" ድምጹ ጠፋና ቆይቶ "ምነው ዮዲት?" የሚል ጩኸት አሰማ።

ቂሱ ከወንበራቸው እመር! ብለው ተነሱ። "አስተናጋጅ! . . . አስተናጋጅ!"

"አቤት! ምነው!" አለች የተደናገጠችው ሆስቴስ በጥድፊያ እየመጣች። ከቂሱ ወንበር ወደ ኋላ ርቆ የተቀመጠ አንድ መንገደኛ ብድግ አለ። እጁ ኮቱ ውስጥ ወደ ሽንጡ ገብቷል።

"አቤት አባቴ!" ምን ችግር አለ?" አለች ሆስቴሷ።

"ቶሎ በይ! ኮኮ ፒቱን አስከፍቼልኝ! ካፒቴኑን ባስቸኳይ ማነጋገር አለብኝ!" አሉ አባ ደረታቸው አካባቢ እጃቸውን ሰደው የመታወቂያ ባጅ እያወጡ።

ሆስቴሷ ጠጋ ብላ መታወቂያቸውን አየችው። የአባን ፊት ለማየት ቀና ስትል ዐይኖቿ በአግራሞት ተጎልጉሰው ሲወጡ የጉድጓዳቸው ጫፍ ላይ ደርሰዋል።

"መቶ አለቃ ሳሙኤል ኃብተማርያም!" አለች ጮሃ።

"አዎን እህቴ። ልዩ መርማሪ ሳሙኤል።"

"ኮክ ፒት እንኳ ማስከፈት አልችልም። ያውም ለመንገደኛ! በጥውም ክልክል ነው!"

"የሰሞኑን.....የዛሬውን የአገታ ወንጀል ሰምተሽ የለ?"

"አዎን። ነገር ግን ከአየር መንገዳችን ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም።"

"ልክ ነሽ። ግን የአየር መንገዳችሁን ዕርዳታ መንግሥት ይፈልጋል።"

ከጓላቸው ተነስቶ ቆሞ የነበረው ሰው አሁን ቂሱ አጠገብ ደርሶ ንግግራቸውን በዝምታ እያዳመጠ ነው። እጁ አሁንም ሽንጡ አካባቢ ነው።

"እባ እስቲ መታወቂያዎን!" አላቸው።

ሳሙኤል አላመነታም ወዲያው አቀበለው። የበረራ ደህንነት ሠራተኛው (እንቲ ሃይ ጃኮር) እንዳች ስሜት አይነበብበትም። "ሌላ ማረጋገጫ አለህ መቶ አለቃ?" አለው።

"እምን ኮሎኔል ሰናይን ወይንም የጠቅላይ ሚንስትሩ ረዳት አቶ ግርማይን . . እ. . እ. አምን! ወይንም የቦሌ ሴኩሪቲ ኃላፊው አቶ አያሌውን ኮንታክት አርገህ ማረጋገጥ ትችላለህ።"

ሰውየው ሳሙኤልን እየተመለከተ ጥቂት ቆዘመና ሆስቴሷን ወደ ኮክፒቱ በር ከወለዳት በኋላ በለሆሳስ ያወራት ጀመረ። በመጨረሻም ራሷን ነቀነቀችና በሩ ላይ ኢንተር ኮም ቁልፍ ተጫነች።

"ካፕቴን ሞገስ . . .። እሷ ስትጨርስ የበረራ ደህንነት ሠራተኛው ተተካ። "እምን ካፕቴን....."

በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ካፕቴኑ በሩን ከፍቶ ብቅ አለ። "ምን ልርዳዎት . . . መቶ አለቃ?" አለ በጣም እየተገረመ።

ሳሙኤል በዝርዝር አስረዳው። ካፕቴኑ ጥቂት አለብ አድርጎ" ሴኩሪቲ፣ ፈትሸው!" ሲል እንቲ ሃይ ጃኮሩን አዘዘው።

"ምንም ነገር አልያዝኩም" አለ ሳሙኤል።

"መፈተሽ አለብኝ!" አለ የደህንነት ሠራተኛው።

"ቀጥል" አለ ሳሙኤል።

ካፕቴን ሞገስ ቂሱን....እ.....መቶ አለቃውን "ተከተለኝ!" አለና ወደ ኮኮ ፒቱ ገባ።

ከብዙ ሙከራ በኋላ በአቪየሽኑ የግንኙነት ማዕከል ሥር ከኮሎኔል ሰናይ ጋር ተገናኘ።

"ኮሎኔሌ! ስንት የመገናኛ ራዲዮ ነው ቡድናችን ውስጥ የተሠራጨው?"

"ስድስት።"

"ምድቦችን ይንገሩኝ።" ኮሎኔሉ ነገሩት። "ሌላ ትርፍ ራዲዮ፣ ሰባተኛ ያወጣ ሰው አለ?"

"እ. . . አዎን! ፍቅሩ ሌላ ራዲዮ አውጥቷል። አሁን ትዝ አለኝ!" የኮሎኔል ሰናይ ድምጽ አሁን ገና እንደ ሠይፍ የሰላ መሰለ።

"ጠላፊዎቹ እነ ዮዲት ራዲዮኑ ደርሷቸዋል! ግንኙነታችንን ሲከታተሉ ቆይተዋል። አሁንም እየተከታተሉ ነው። የግንኙነት ፍሪኩዌንሲ ባስቸኳይ ቀይሩ? ሻለቃ ፍቅሩንም . . ." አለ ሳሙኤል ሳግ እየተናነቀው "በቁጥጥር ሥር አውሏቸው!"

መልስ የሰጠው አልነበረም። "ኮሎኔል፣ ይሰሙኛል?" አለ።

"አምስት ባምስት።"

"ከአዘዞ አየር ማረፊያ የሚጠብቀኝ መኪና ከነአሽከርካሪው ይዘዙልኝ።"

"አዘዞ ምን ትሠራለህ?"

"የድራማው የመጨረሻ ተውኔት ከዚያ የሚጀምር ይመስለኛል!"

**********////////**********

የጠቅላይ ሚኒስትሩ ዐይኖች ነበልባል የሚተፉ መስለዋል። የወታደራዊ ደህንነት ኃላፊው ጀነራል ድንበሩ ያቀረቡላቸውን መረጃ ሲመለከቱ በቁጣ ቢጦፉም ድምፃቸው ግን ዝግተኛና የተረጋጋ ነበረ። ትርፋማ የቢዝነስ ሥራዎችን የሚያወሩ አንጂ ነርቭ የሚነካ ሀገራዊ ውጥረት ላይ የሚወያዩ አይመስሉም።

"የኤስ.ኤ.ኤስ ጦርና የስኮትላንድ ያርድ መርማሪዎች አዲስ አበባ እንዲገቡ የፈቀድነው ካለን ግንኙነትና የተከሰተውን የሽብር ድርጊት ገምግመን ነው። እዚህ መረጃ ላይ የምመለከተው ነገር ግን የሠለጠነ ሀገርና መንግሥት አስተሳሰብ ያልሆነ ነገር ነው። እጠቅሰዋልሁ 'አጋች ታጋቾችን ሁሉንም ደምስሳችሁ የብራና መጽሐፍቱን ብቻ . . .' ይልና ከእንግሊዝ መንግሥት ለኤስ.ኤ.ኤስ ጦር አዛዥ እጅግ ውስብስብ በሆነ ኮድ ታስሮ የተላለፈው መልዕክት የጥቂት፣ የተመረጡ ብራናዎችን አርዕስት ከጠቀሰ በኋላ . . . 'እነዚህን ብራናዎች ብቻ ተቆጣጥራችሁ በመያዝ ሌሎቹን ቅርሶች ለአበሾቹ ተውላቸው!' ይላል።

የካቢኔው አባላት በሙሉ በድንጋጤ ተውጠው በዝምታ ጠቅላይ ሚኒስተሩን ተመለከቱ። "የምትሉት ነገር አለ?"

መልስ የለም። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ ረዳታቸው ዞሩ።

"ግርማይ"

"አቤት?"

"የፀረ ሽብር ኮማንዶ አዛዣችንን አገናኝኝ።"

አቶ ግርማይ የሞባይል ስልካቸውን አወጡና ደወሉ። ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላ "ጠብቀኝ!" ብለው ስልካቸውን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አቀበሏቸው።

"አሠፋ!"

"አቤት?"

"ለእንግሊዞቹ አሁን ትዕዛዝ አስተላልፋለሁ። አንተና ጦርህ የምታደርጉት ይህንን ነው። ፈረንጆቹ በአዳራሹና በአጋቾቹ ላይ ጥቃት የሚከፍቱ መሆናቸው በማያሻማ ሁኔታ ካረጋገጥክ በተመቸህ ወታደራዊ መንገድ አስቁማቸው!"

"ተቀብያለሁ የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር!"

ምዕራፍ አርባ ሁለት

"የምስጢራዊ ዕውቀት(esoteric) ባሕር የሆኑት ጥንታዊ የብራና መጽሐፍቶቻችን የንዘብ ብቻ ሳይሆን የረቂቅ ኃይል ምንጮች መሆናቸውንም ታውቃለህ አለችና ዮዲት በቀኝ እጇ ማክሮቭ ሽጉጧን ይዛ በግራ እጇ ማርልቦሮዋን ልምጥጥ አድርጋ ስባ ጢሱን ዶክተር ሥራው ፊት ላይ አቦነነችው። የሲጋራ ጢስ እንደማያወዱ ታውቃለች። አውቃም ስታጥናቸው ኖራለች።

"ይህን የአባቶቻችን ምስጢራዊና ጥንታዊ ዕውቀት የሚያስጨብጥህ መስሎህ ያንዱዓለምን የትርጉም ሥራ ለመስረቅና ለማሰረቅ ሞክርክ። ነገር ግን ያልተረዳኸው ምስጢር ምን መሰለህ ዶክተርዬ?" አለች እያሾፈች። "ምስጢሩ እንድታውቀው ስለፈለክና ስለ ሸመደድከው ብቻ አይታወቅህም!"

ዶክተር ሥራው ከዕድሜያው በአሥር ዓመት ያረጁ መሰሉ። ዮዲት ሲጋራውን ጥላ በቡት ጫማዋ ረግጣ አጠፋችውና ማክሮቧን ወደ ደረታቸው አቀናቸው።

"ምን ልታደርጊ ነው?" አሏት ዐይኖቻቸው በፍርሃት ተጎልጉለው።

"ያንተ ወንጀል ያገራችንን ቅርሶች ለባዕዳን መቸብቸብ ብቻ አይደለም። ቅርስ ፍለጋ ሊረዱን ቁፋሮ ላይ ላባቸውን ያንጠፈጠፉ ገበሬዎችንም የቆፈሩት ጉድጉድ ውስጥ በጅምላ ረሽኖ እስከ መቅበር የሚደርስ አረመኔያዊ ተግባር ነው። ብላ በሚያስፈራ ጥላቻ ተመለከተችውና ለመሆኑ ያ ክንደ ንቅሳታሙ ቆፋሪ ይረሳሃል?" አለች።

"አይረሳኝም። ግን . . . ግን . . . ምን ልታደርጊ ነው?" አሏት።

"ልገድልህ ነው?"

"ለምን?"

"የነዚያ ምስኪን ገበሬዎች የደም ጩኸት ስለጠራህ!" አለችና በጣም በርጋታ፣ በቀዝቃዛ ስሜት የሽጉጧን ቃታ አራት ጊዜ ተጫነችው። ከቆፋሪዎቹ መሀል ክንደ ንቅሳታሙ ወላጅ አባቷ ለመሆኑ አልነገረችውም። ምክንያቱም ይህ ተራ ግለሰባዊ ብቀላ አይደለም። ለውዲቱ ሀገሯ ደህንነት መውሰድ ያለባት ምዕራፍ፣ የቅጣት እርምጃ እንጂ። ዮዲት መሬት ላይ የተደፋውን በድን አካል ዞር ብላም ሳታይ ያንድ ሜትር ብቻ ክፍተት ባለው በር ስትወጣ "ፍጠኝ!" አለና የባሕታዊው አገልጋይ በሩን ስቦ ዘጋው። የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ኮማንዶዎች የዮዲት ተከታታይ አራት ተኩሶች አልተሰማቸውም።

የሄሊኮፕተሩ አስገምጋሚ ድምፅ እንኪንስ የሽጉጥ ጥይት የእሳተ ጎመራ ድምጽም ይውጣል።

ኮማንዶዎቹ በተለይም እንግሊዞቹ ፊታቸው ላይ ባጠለቁት ሰፊ የኢንፍራሬድ መነጽር (ናይት ስኮፕ) አጋችና ታጋቾች ችምችም ብለውና መሬት ላይ ተኮልኩለው ይታዩዋቸዋል። "ለምን?" አለ መጥረቢያው በንዴት። "በዚህ ቅፅበት እያንዳንዱን አሸባሪ ግንባሩን በጥይት መፍለጥ ስንችል ለምን ትከለክሉናላችሁ?" በማለት በተደጋጋሚ እፉ ላይ በተሰጠፈችው 'ማውዝ ፒስ' በሹክሹታ ወተወተ።

"በታጋቾቹ ሕይወት ላይ ላለ መቆመር!" አሉት አቶ ግርማይ።

አጋቾቹ በሙሉ የታጋቾቹን ሰውነት እንደ ሰብአዊ ጋሻ ተከልለው በጥድፊያ ሄሊኮፕተሩ ስር ደረሱ። ልዕልቲቱን በማስቀደም፣ አምባሳደሩን በማስከተል ካሳፈሯቸው በኋላ አምስቱን እንግሊዛውያን እና ክቡር ሚኒስትሩን ቅርሶቹን በያዙት ሳጥኖች ዙሪያ ክብ አቆሟቸው።

"አባቴ ይቀጥሉ!" አለ ያፌት። ባሕታዊው በድጋፍ ሄሊኮፕተሩ ላይ ከወጡ በኋላ ያፌት ተሳፈረና "አንዱዓለም ቀጥል!" አለው። ዶክተሩ ወጣ። ለባሕታዊው አገልጋይ ምልክት ሰጠው። ተከተለ። ቀጥለውም ያሬድና ሳምሶን ሲወጡ ሄሊኮፕተሩ ስር ዮዲት ብቻ ቀረች።

ያፌት የሄሊኮፕተሩ በር ላይ ቆሞ "ቀጥል! እንላ" አለው የፎርክ ሊፍቱን አፐሬተር። ሁለት ቶን ክብደት በሚሸከሙ ሹካዎቹ ሳጥን ሰቅስቆ ሲያነሳ . . . ከፍ ሲያደርግ . . . ሄሊኮፕተር ላይ ሲያርፍ . . . ውስጥ ያሉት እያነሱ ወደ ባዶው ሥፍራ ሲከምሩ፣ ሲደረድሩ፣ በዚህ ዐይነት ርብርብ ሃያ የታሸጉ ሳጥኖች በሦላሳ ደቂቃዎች ውስጥ ተጫኑ።

የመጨረሻው ሳጥን ሄሊኮፕተሩ ላይ ካረፈ በኋላ ያፌት አፐሬተሩን "መሄድ ትችላለህ! አመሰግናለሁ!" አለው።

"በቃ ይሄው ነው? የቀረ የለም?" ሲል ጠየቀ አፐሬተር ኮማንዶው።

"የቀረህ እኛን መግደል ነበረ። ለዛሬ አይሠራም። ቻው!" አለው ያፌት።

ኦፐሬተሩ አሳት በሚተፉ ዐይኖቹ ያፌትን ገላመጠውና አጠገቡ ወደ ቆመችው ዮዲት ፊቱን መለስ አደረገ። ግንባሩ ላይ ኡዚ ደግናበት ተመለከተ።

ፈገግ አለና "ከዚህም በላይ አስፈሪ ከሆኑ አፈሙዞች ጋር ተፋጥጫለሁ። ቻው" አሳትና ማሽኑን እያሽከረከረ ከግቢው ወጣ።

የሄሊኮፕተሩ ቀዛፊዎች (ፕሮፔለር) በፍጥነት እየተሽከረከሩ፣ ድምፁም ግቢውን ናጠው። ንፋሱም ዮዲትን ይወዘውዛት ጀመር።

"ዮ. . . ዲ. . .ት! ውጪ?" ሲል ያፌት ጮኸና እጁን ዘረጋላት።

**********//////////**********

ሄሊኮፕተሩ ምድር ከመልቀቁ የአበሻና የፈረንጅ ኮማንዶዎች በሁለት ምድብ ተከፍለው አንደኛው ምድብ በኮሎኔል አሰፋ መሪነት ወደ አዳራሹ ሲሮጥ፣ ሁለተኛው የኤስ.ኤ.ኤስ ኮማንዶ ቡድን በ'መጥረቢያው መሪነት ሄሊኮፕተሩ ወደ ነበረበት ገላጣ ሥፍራ በሩጫ ተፈተለከ።

"እናንተን እንዴት ለቀቋችሁ?" አለ መጥረቢያው ታግተው ከነበሩት የልዕልቲቱ ጠባቂዎች አንዱን።

"ምናልባት 'ፔይ ሎድ' (ሙሉ ጭነት) እንዳይበዛባቸው ይሆናል" አለ አንደኛው እንግሊዛዊ ታጋች እና የቅርስ ባለሙያ እያፌዘ።

"ክቡር ሚኒስትር እርስዎ ደህና ነዎት?"

"አይ አም ኦኬ!" አሉት ሚንስትሩ።

መጥረቢያው የአምስቱን እንግሊዛውያን ታጋቶች እና የሚንስትሩን ደህንነት አረጋግጦ በሁለት ዘመናዊ አቡላንሶች ካሳፈራቸው በኋላ አምቡላንሶቹ በሁለት የፖሊስ ላንድ ክሩዘሮች ታጅበው ሳይረኖቻቸውን እያስጮሁ ግቢውን ለቀው ወጡ።

አዳራሹ ውስጥ ቀድሞ የገባው የፀረ ሽብር ኮማንዶ ቡድኑ አዛዥ ኮሎኔል አሠፋ ነው። የዶክተር ሥራውብዙን በድን አካል በደም ኩሬ ተነክሮ አገኘው። ወደ ወታደሮቹ ዞር ብሎ "የአዳራሹን በር ዝጉና ጠብቁ! ማንም እንዳይገባ!" ብሎ የመገናኛ ራዲዮኑን ተጫነው።

እንግሊዛውያን ኮማንዶዎቹን አስከትሎ አዳራሹ በር ላይ የደረሰው አዛዣቸው መጥረቢያው በሩ ላይ በኢትዮጵያውኑ ኮማንዶዎች እንዲቆም በመደረጉ ፊቱ በንዴት ላምባ መስሎ ይጮህ ገባ።

"ኋይ?!"

"ኮሎኔል አሰፋ ረጋ ብሎ ግራ እጁን የመጥረቢያው ትከሻ ላይ ጣል እደረገና "ክራይም ሲን ኢንቪስቲጌሽን!" አለው። "የወንጀል ሥፍራ ምርመራ ስለምናደርግ ማስረጃዎች እንዳይጠፉ!"

በኃይል ጥሶ መግባት እንደማይችል ሲረዳ መጥረቢያው ፊቱን አዙሮ አሥር እርምጃዎች ያህል ካዳራሹ ራቀና "ኢትስ አንብሊቨብል! (የማይታመን ነው) አሁን ምን ማድረግ አለብን?" ሲል በልዩ ራዲዮኑ ሹክ አለ።

"ቀዝቀዝ በል!" አለው የእንግሊዝ ኤምባሲ አንደኛ ጸሐፊ እና የአምባሳደሩ ረዳት። "አሁን ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ልዩ ረዳት ከአቶ ግርማይ በርሄ ትዕዛዝ ደርሶኛል። ለናንተም ይደርሳችኋል። የኤስ.ኤ.ኤስ እና የኢትዮጵያ ኮማንዶዎች ወደ ቦሌ ኤርፖርት በአስቸኳይ ትንቀሳቀሳላችሁ!"

"ለምን?"

"በኛ (በኤስ.ኤ.ኤስ) አውሮፕላን ትሳፈሩና የጠላፊዎቹን ዱካ ወደ ሰሜን ትከተላላችሁ!"

ከአሥር ደቂቃዎች በኋላ ቦታው የደረሱት የማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ ፖሊሶች ወዲያውኑ አዳራሹ ውስጥ የወንጀል ሥፍራ ምርመራቸውን (ክራይም ሲን-ኢንቪስቲጌሽን) ጀመሩ። የጣት አሻራዎች በጥንቃቄ ተለቀሙ፤ አስከሬኑና አዳራሹ በርካታ ፎቶ ግራፎች ተነሱ፤ የወዳደቁ ጥቃቅን ነገሮች ሁሉ በጥንቃቄ እየተለቀሙ በፕላስቲክ ከረጢቶች ታሸጉ።

ምዕራፍ አርባ ሶስት

ልዕልቲቱና የእንግሊዙ አምባሳደር፣ ቅርሶቹ የታሸጉባቸው ሣጥኖችና ባልደረቦቹ በሙሉ መሳፈራቸውን ካረጋገጠ በኋላ ወደ አብራሪው ዞረና "ያፌት" እባላለሁ!" አለው። "የጠሰፋው መሪ እና የዚህ በረራ አዛዥ ነኝ። ምናልባት ሰሞኑን በመገናኛ ብዙሐን ፊቴን ሳታየው አትቀርም።"

"መቶ አለቃ ገረመው እባላለሁ።" አለው አብራሪው እጁን ለሠላምታ እየዘረጋለት። ያፌትም ሳያመነታ ጨበጠው፡

"እምን መልክህን በቴሌቪዥን ዜናዎች ደጋግሜ ተመልክቼዋለሁ። ምንም እንኳ የሰራኸው አክሽን ፊልም ባያምርም!"

ያፌት በአብራሪው ስላቅ በንዴት ፈገግ አለ።

"እምን የሠራሁት ፊልም ላያስደስትህ ይችላል። ነገር ግን ከዚህች ደቂቃ ጀምሮ እያንዳንዷን ትዕዛዜን በትክክል ካልፈፀምክ የፊልሙ ፍፃሜ ከምትገምተው በላይ አሰቃቂ ይሆናል!"

"መጥፎ አክተር ብትሆንም አዳምጥሃለው!"

"ልታታልለኝ አትሞክር!" አለ ያፌት ፊቱን የበለጠ አኮሳትሮ፣ ድምፁን እንደ መቃብር ቅዝቅዝ አድርጎና ትክ ብሎ እየተመለከተው። "ልታታልለኝ ከሞከርክ ያለማወላወል አስከፊ እርምጃ እወስድብሃለሁ። በነገራችን ላይ በመቶ አልቅና ማዕረግ የተዋጊ ሄሊኮፕተር አብራሪ እንደ ነበርኩ ሳሳውቅህ እወዳለሁ!"

አብራሪው ለመጀመሪያ ጊዜ የስሜት መለዋወጥ በገፅታው ላይ ታየበት። ይህ እንደ ተራ ወንጀለኛ ገምቶት የነበረው ሰው እንደ እርሱ በተመሳሳይ ሙያ ውስጥ ያለፈ መሆኑን ሲረዳ በቀላሉ ሊያሞኘው እንደማይችል ተረዳ።

"ወዴት ነው የምንበረው?" ሲል በለሆሳስ ጠየቀው።

"ወደ ሰሜን ጎንደር!" አለ ያፌት።

**********//////////**********

መቶ አለቃ ሳሙኤል አዘዞ አየር ማረፊያ ከወረደ በኋላ ባደረገው የራዲዮና የሞባይል ስልክ ግንኙነቶች አማካይነት አጋች እና ታጋቾችን የያዘው ሄሊኮፕተር ወደ ሰሜን ጎንደር አቅጣጫ መብረሩን ለመረዳት ቻለ።

በቂስነቱ ወይንም በለበሰው ልብስ ተከሀኖ ከሌሎቹ መንገደኞች በቀላሉ ሊለየው የቻለው የፖሊስ ላንድ ክሩዘር አሽከርካሪ ያለችግር አገኘው።

"አባቴ እርስዎን ልረዳ ታዝዣለው።" አለው።

"እሺ አመሰግናለሁ" አለ ሳሙኤል ግንባሩን እንደ ተዋጊ በግ ባሰገገበት ፖሊስ ሁኔታ ግራ እየተጋባ። ሳሙኤል ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላ ነገሩ ተከሰተለትና ፊገግ አለ። ለካስ ፖሊሱ ሳሙኤል እውነተኛ ቂስ መስሎት እንዲያላልመው ነበር ፊቱን ያስጠጋው። ሳሙኤል የመታወቂያ ባጁን አወጣና ዐይኖቹ ሥር አስጠግቶለት "ይህን ላላልምህ?" አለው።

ፖሊሱ መታወቂያውን አተኩሮ እየና ከመጠን በላይ ተገርሞ "ወይኑ ነው አባ . . . እ . .. መቶ አለቃ?" ሲል ጠየቀው።

"ወደ ዋልድባ።"

"ምን?"

"አዲ አርቃይ፣ ዋልድባ!"

ግዙፉና ጥቁሩ ሄሊኮፕተር ጥርት ያለውን፣ በከዋክብት የተንቆጠቆጠ የምሽት ሰማይ እየሰነጠቀ፣ ቋሚ በሆነ ከፍተኛ ፍጥነት እየከነፈ ነው። ያፌት እና ሳምሶን ያለመታከት አብራሪውን በዐይነ ቁራኛ እየተቆጣጠሩት ነው።

ባሕታዊው እና ዮዲት ደግሞ የታሸጉ ሣጥኖች ላይ ጎን ለጎን ተቀምጠው በለሆሳስ ያወራሉ። አጠገባቸው ሌላ ሳጥን ላይ የተቀመጡት ልዕልት ኢዛቤል፣ ዶክተር አንዱዓለም እና ያሬድ በፀጥታ በራሳቸው ሐሳብ ተጠምደዋል። የሚበሩበት ከፍታ ያስከተለው ቅዝቃዜ ሁሉንም ማስቸገሩ በግልጽ ይታያል።

"ኧረ ባዛኙቱ! ይህን ትምባሆሽን ተይኝ!" አሉ ባታዊው።

"አባ የሱስ ነገር ሆኖብኝ እኮ ነው።" አለች ሲጋራዋን እየማገች። ጭውውታቸውን ለሰማው ሰው ሁለቱም በጣም የቀረበ ግንኙነት፣ ምናልባትም ዝምድና ብጤ እያጡም ብሎ ሊገምት ይችላል።

"አባ! አንዳንድ ጊዜ እናንተም ያችን ነገር ታጫጭሳላችሁ የሚል ሀሜታ ይናፈሳል እኮ!"

ባሕታዊው ሳይወዱ ፈገግታ ፈነጠቀባቸውና "ምን ታደርጊዋለሽ ዮዲትን አንዳንደ በዋልድማም ይዘፈናል! ይባላል እኮ" አሏት።

ሄሊኮፕተሩ የጨለመውን ሰማይ እየሰነጠቀ በመጨረሻ ፍጥነቱ እየበረረ ነው። ዮዲት ከፊት ለፊቷ ደም የመሰለችውን ደማቅ ጨረቃ በትካዜ ስትመለከት ቆየችና ወደ ባሕታዊው ዞረች። "በቀይ ጨረቃ ሌሊት ቀይ ደም ማፍሰሴ ታወሰኝ።" አለቻቸው።

"ላስቆምሽ ባለመቻሌ አዝናለሁ። የሆነው ሆኗል። ነገር ግን ዋናው አላማሽ ጥቁር ደም ወይንም በቀል አይደለም። የተነሳሽበት አላማ የምትወጂያት ሀገርሽን የታሪክና የእምነት ቅርሶች ማስመለስ፣ መታደግ መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን።"

"እሱማ ነው። ግን ለግል በቀል ስል ነው ወይ ያደረኩት? በማለት ውስጤን ስፈትሽ ነበር።"

"እና ሀሊናሽ ምን መልስ ሰጠሽ?"

"ቅንጣትም ፀፀት የለበትም። ዋናው ግቤ የአገሬን ቅርሶች ከጠላቶች ወይንም የኢትዮጵያዊነታችን ጠላት ከሆኑት ሊበች መታደግ ነው።"

"ጎሽ ዋናው የሀሊና ነፃነት ነው። መሃላችን ለግል በቀል ስትይ እንዳደረግሽው የሚያምን አንድም አይኖርም። ትክክል የመሰለሽን ነገር አድርገሻል። አሁንም ቀጥይበት። ይህን የፀና አላማሽን ከግቡ ለማድረስ የቀረሽ በጣም ጥቂት እርምጃዎች ብቻ ናቸው። ለማንኛውም እግዜር ያንዛሽ።" አሉና ባህታዊው የቀኝ እጃቸውን ዘረጉላት። ዮዲት "አሜን" ብላ እጃቸውን እንደ መስቀል ተሳለመችውና "ግን እኮ አይሁድ ነኝ" አለቻቸው ፈገግ እያለች።

"የሁላችንም ፈጣሪ አንድ አይደለም እንዴ?" አሏት እሳቸውም ፈገግ ብለው።

**********//////////**********

ከጎንደር ከተማ በስተሰሜን አንድ መቶ ሰባ ሰባት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከዋናው አውራ ጉዳና በስተ ግራ የአዲ አርቃይ ከተማ ትገኛለች። ከከተማዋ ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ደኑን እና በረሃማውን ምድር እያቋረጡ ወደ ተከዜ አቅጣጫ ሲጓዙ የዋልድባ ገዳም ይገኛል። በጣም ጥንታዊ ገዳም ነው። የገዳሙ መነኮሳት ስለ ምናኔያቸው፣ ስለ ቅርሶቻቸውና ገለልተኛ ስለሆነው መንፈሳዊ ሕይወታቸው በእጅጉ ቀናኢ

ከመሆናቸው የተነሳ አንድም ጎብኚ፣ በተለይም የውጭ ሀገር ጎብኚዎች ዝር ባይሉባቸው ይወዳሉ። ደግነቱ ቦታው ለዘመናዊ ትራንስፖርት አመቺ አይደለም።

የዛሬው ቀን ዓመታዊ ንግሥ በዓል የሚከበርበት ቀን ቢሆንም ከወትሮው በተለየ መልኩ ሥፍር ቁጥር የሌለው ሕዝብ (ምእመናን) ተገኝቷል። ቅዳሴ ዝማሬና ሥርአተ ጸሎቱ ሌቱን ሙሉ ሲከናወን ያድራል። ሌላም አከባበር ነበር። አውቶማቲክ የጦር መሣሪያ በታጠቁ ሰዎች የታጀቡና በባትሪ ድንጋይ የሚሠራ የድምጽ ማጉያ የያዙ መነኩሴ ለተሰበሰበው ምዕመናን "ትምሕርት" ያሰማሉ። ስብከቱ ያተኮረው ለየት ባለ ርዕስ ጉዳይ ላይ በመሆኑ የብዙዎችን ቀልብ ስቧል።

"ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ቅርሶቻችን ተዘርፈው ባዶ እጃችንን አጨብጭበን ከመቀመጫችን በፊት እንጠብቃቸው! "ሕዝበ ክርስቲያን ከንፈሩን ይመጣል። "የተዘረፉ ቅርሶቻችንም ቢሆኑ ሁሉም ወደ ተቀደሰችው ሀገራችን እንደሚመለሱ ትንቢት ተነግሯል!" ዕልልታው ይቀልጣል። "ይህ የእግዚአብሔር ቃል ነውና ትንቢቱ ቶሎ ይፈፀማል!" ሕዝበ ክርስቲያን እንባውን እያፈሰሰ፣ መሬት እየሳመና እልልታውን እያቀለጠ ደስታውን ይገልፃል።

በድንገት አካባብቢን የሚንጥ ድምፅ ተሰማና ሕዝበ ምዕመናን ፊቱን ወደ ሰማይ አቀና። መነኩሴው ዐይናቸውን ከንጋት ፀሐይ ጨረር በእጃቸው እየከለሉ ወደ ሰማይ ሲመለከቱ ቆዩ።

"ተመልከቱ!" አሉ። "የአምላክን ፈቃድና ሥራ ተመልከቱ! አሁን ስናወሳቸው የነበሩት ቅርሶቻችን ደረሱ! የምሥራች! አምላክ ይመስገን!"

እልልታውና ሆታው ምድሪቱን አደባለቃት። የአውቶማቲክ መሣሪያዎች ተኩስ ሜዳ፣ ሸለቆና ተራራውን ሁሉ ናጠው።

ግዙፉና ጥቁሩ አስፈሪ ሄሊኮፕተር መሬት አርፎ ቀስ በቀስ ሞተሩ ፀጥ አለ።

"በሉ ጎበዝ! አሁን የተመረጣችሁት ብቻ ተከተሉኝ። የተቀደሱ ቅርሶቻችንን ተሸክመን ወደ ተዘጋጀው ሥፍራ እንጓዝ!"

አንድም ግር ግር አልተነሳም። ነገሩ ሁሉ አስቀድሞ ከፍተኛ ዝግጅትና የቅስቀሳ ሥራ የተከናወነበት ለመሆኑ ያስታውቃል። ከአካባቢው በጥንቃቄ የተመረጡ አንድ መቶ አርሶ አደሮችና ጠንካራ ቀላውስቶች ከሕዝቡ መሃል ወጣ ወጣ ብለው በመነኩሴው ዙሪያ

ቆሙ። ቁጥራቸው ከመጀመሪያዎቹ የማያንስ ዘመናዊ አውቶማቲክ መሣሪያዎችን ያነገቡ ስሜነኛ ታጣቂዎችም መነኩሴውን ተከትለው ወደ ግዙፉ ሄሊኮፕተር ገሰገሱ።

**********/////////**********

ባሕታዊው እና ዶክተር አንዱዓለም ከሄሊኮፕተሩ ሥር ቆመው የሚራገፈውን ጭነት ይቆጣጠራሉ። በአሥር ሰው እና በአንድ የጎበዝ አለቃ (መንገድ መሪ) ለተዋቀረው ቡድን ባሕታዊው በሣጥን የታሸጉትን ቅርሶች አከፋፍለው ጨረሱ። እነዚህ ምድቦችም ቢያንስ በአሥርና ከዚያም በላይ በሚሆኑ ታጣቂዎች ታጅበው ገላጣ ሜዳ ላይ በመሠለፍ የጉዞ ትዕዛዝ እየተጠባበቁ ነው። በዚህ መልኩ ዝግጅቱ ያላንዳች ግርግር እና ችግር በፀጥታ በቅልጥፍና ተከናወነ።

ዮዲት ከልዕልት ኢዛቤልና ከእንግሊዙ አምባሳደር ጋር ጥላ ሥር ቆማ ታወራለች። ልዕልቲቱን ወበቃማው አየር የበለለ ቲማቲም አስመስሏቸዋል። ያለማቋረጥ ፊታቸውን በባርኔጣቸው ያራጋግባሉ። አምባሳደሩ የታሸገ የላስቲክ ውሃ ለልዕልቲቱ ሰጥተው የራሳቸውን ይጎነጫሉ። ያሬድ፣ ራሄል፣ ያፌትና የዋልድባው መነኩሴ በግራር ዛፍ ጥላ ሥር ተቀምጠው ያወጋሉ።

"ይህ ምዕራባዊ ባሕል ወይንም አዲሱ አሥራኤላዊነትሽ ይመስለኛል አጢያሽ ያደረገሽ" አሉ ልዕልቲቱ የዮዲትን አጢያሽነት በሚያወግዝ ድምፀት።

"የለም ተሳሳተዋል" አለች ዮዲት። "በዘመቻ ሰለሞን ወደ እሥራኤል ከመሄዴ በፊት ገና የኮሌጅ ተማሪ በነበርኩበት ዘመን ነው ማጨስ የጀመርኩት። በወቅቱ በእርስ በርስ ጦርነት ትታመስ የነበረችው ሀገሬ ኢትዮጵያ ሁኔታና ዕጣ ፈንታ በእጅጉ ያሳሰበኝ ነበረ። ለዘመናት በጭቆና ቀንበር ሥር ከወደቀ እምነትና ሕብረተሰብ መገኘቴም ረፍት ይነሳኝ ነበረ። "የተስፋይቱ ምድር" ናፍቆትና ምኞትም ያስጨንቀኝ ነበረ። እናም አጢያሽ ሆንኩኝ።

"ስፕሊት ፐርሰናሊቲ?" አላት አምባሳደሩ።

"ልትሰው ትችላለህ። ሲጨቁንህ የኖረ አገዛዝን እና የጭቆና ፋብሪካ የሆነችውን የትውልድ ሀገርህን ለይተህ ማየት፣ እየመጣ ካለው አዲሱ አስራኤላዊነት ጋር መፋጠጥ፣ ስንጥቅ ወይንም ተደራራቢ ስብዕናን ቢጭንብህና ማንነትህን ቢያምታታብህ አያስገርምም።"

"ታዲያ ለምን እዚህ . . . ዘመቻ መቅደላ ነው የምትሉት? ውስጥ ለምን ተካፈልሽ?"

"ንብር ሻጉንጉርጉርነቱን ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊነቱን ሊፍት ይቻለዋልን?" አለች ዮዲት። ልዕልቲቱ ፈገግ አሉ።

"የሁለት ሺህ ዘመን ኢትዮጵያዊነት በእሥራኤል ፓስፖርት ያውም ባንድ ጀምበር የሚሸረሸር ነገር አይደለም። ኢትዮጵያዊ ስለሆንኩ ከዘመቻ መቅደላም በላይ በሆነ ተልዕኮ ይህችን ሀገር ባገለግልና ሕይወቴንም ብሰዋላት ደስ ይለኛል። እዩ ክብርት ልዕልት? ብትጨቁንም፣ ብታበለፅግ ወይ ብታደኸይ ሀገር ሀገር ናት!" አለች ዮዲት ድምጿ በስሜት እየጋለ።

ረዘም ላሉ ሴኮንዶች ልዕልቲቱ በዝምታ ቆዘሙ።

"እምን ዮዲት፣ በዚህች አጭር ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያዊነትሽን ከተግባርሽና ከአኗኗንሽ ማየትና ማረጋገጥ ችያለሁ። አንቺና ቤተ—እስራኤላዊት ያልሆነችው ኢትዮጵያዊቷ ራሄል ምን ልዩነት አላችሁ?" ምንም! የሌላ አገር ዜግነት ፍለጋው የመጣው የእምነት ነፃነትን ለማስከበር ይመስለኛል።" አሉ ልዕልቲቷ ዮዲትን እንደ ጀግና ትክ ብለው እየተመለከቱ።

ዮዲት ከጥቂት ቀናት በፊት ከጌዲዮን ጋር ያወሩትን ተያያዥ ሀገራዊ ጉዳይ በእዝነ ልቦታዋ መከለስ ጀምራ ነበር። በወቅቱ ጌዲዮን በ"ዘመቻ ሰለሞን" ወደ ተስፋይቱ ምድር ከገባሁ በኋላ ለሁለት ሺህ ዓመታት ስንናፍቀው የኖርንለትን እስራኤላዊት ብንቀዳጅም አዲሱ እስራኤላዊነቴ ከነባሩ ኢትዮጵያዊነቴ በላይ በውስጣዊው ነፍሴ ጠልቆ ሊሰርፅ አልቻለም" ብሏት ነበር።

"እምን ልዕልት ኢዛቤል" አለች ዮዲት ከሐሳብ ባቡር ላይ ወርዳ። "እምነቴን በነፃነት ለማራመድና ከድህነት ለማምለጥ ወደ ተስፋይቱ ምድር ተሰደድኩ እንጂ የሁለት ሺህ ዓመታት ጥልቀት ያለውን ኢትዮጵያዊነቴን ከሥሩ አልነቀልኩትም! ኢትዮጵያዊነትን ወደ መካከለኛው ምሥራቅ "ኤክስፖርት" አደረኩ እንጂ ኢትዮጵያዊነትን ከደሜ ውስጥ አላወጣሁትም!"

"ለማንኛውም . . ." ሲሉ ልዕልቲቱ ዮዲት ከሐሳቧ ባነነችና ፊቷን ወደ ልዕልቲቱ መለሰች። "ለማንኛውም እንቺንም ሆነ የዘመቻ መቅደላ ባልደረቦችሽን ከልቤ አደንቃችኋለሁ፣ አከብራችኋለሁ። ምንም እንኳን አሸባሪዎች ብትሆኑም።"

ሦስቱም ከልባቸው ተንከትክተው ሳቁ። በተሰይ የልዕልቲቱ ፊት በደማቅ ፈገግታ ደምቆ በርቷል።

"አሸባሪዎች እያሉን ለምን?" አለች ዮዲት።

"የተነሳችሁበት ዓላማ ቀላልና ተራ የአሸባሪ ተግባር አይደለም። ሰብዓዊ ፍጡርን በጦር መሣሪያ አግታችሁ በመያዝ ራንሰም (የገንዘብ ክፍያ) አልጠየቃችሁም። ይህን አስቸጋሪ ተልዕኮ ለመፈፀም ያነሳሳችሁ ወይንም ያነሳሳሽ ያገራችሁን ፕራይስለስ (በዋጋ የማይተመኑ) ቅርሶች ለማስመለስ ያላችሁ የነደደ ሀገራዊ ፍቅር ብቻ ነው። በቁርጠኛነት የተወጣችሁትም ከዚህ ሌላ አማራጭ ስላልነበራችሁ ነው። ለዚህ ነው ደስታዬን እና አክብሮቴን ልገልፅልሽ የተገደድኩት።"

ዮዲት ፈገግ እያለች መገላቸው ያላፈራት ይመስል አንገቷን ሰበር አደረገች። ግን ብዙም ሳትቆይ አንገቷን ቀና የሚያደርግ ድምፅ ሰማች። ሁለት የጦር ሄሊኮፕተሮች አድማሱን እየሰነጠቁ መጡና የመጀመሪያውን ሄሊኮፕተር በርቀትና በስፋት አንዳሞራ ከዞሩት በኋላ ሁለት መቶ ሜትር ርቀት ያህል በሚገኝ ገላጣ ሥፍራ ላይ ተራ በተራ አረፉ።

ባሕታዊውና ዶክተር አንዱዓለም ጭንት የማከፋፈሉን ሥራ አብቅተው ምድብተኞቹን በቅደም ተከተል እያሰሰፉ ነው። ወደ አዲስ መጪዎቹ ሄሊኮፕተሮች ዞር ብለው የማየት ስሜት እንኳ አላሳዩም። እነ ያፌትና ዮዲት ግን በፀጥታ ሄሊኮፕተሮቹን እየተመለከቱ ነው።

ከሦስቱም ሄሊኮፕተሮች እጅግ ዘመናዊ መሣሪያዎችን የታጠቁ፣ በድምሩ ቁጥራቸው ስልሳ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን እና እንግሊዛውያን ኮማንዶዎች በቅልጥፍና እየዘለሉ በመውረድ በሄልኮፕተሮቹ ዙሪያ ቦታ ቦታ ይዘው ቁጭ፣ ቁጭ አሉ።

ምዕራፍ አርባ አራት

የአድዋ እና የኤስ.ኤ.ኤስ ኮማንዶዎች ወደ ሰሜን ከመንቀሳቀሳቸው በፊት ይህን ቡድን በበላይነት ይዘው የሚዘምቱት አቶ ግርማይ በርሔ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ መመሪያና ትዕዛዝ ተቀብለው ነበር።

"ይህን ክራይስስ ለመፍታታ የሚያስችል፣ ለጠላፊዎቹ የምትሰጠው 'አጥንት' (የመደራደሪያ ሐሳብ) ይህ ነው።"

"ታዛኘር ነኝ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር!"

"ልዕልቲቱን እና አምባሳደሩን እንደዚሁም ቅርሶቹን ሙሉ በሙሉ ያሉ አንዳች ቅድመ ሁኔታ ሊያስረክቡን እና እንዲሁም እጃቸውን ለመንግሥት ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆኑ ከጥቂት ወራቶች አሥራት በኋላ በ'ነፃ' እንደምንለቃቸው መንግሥታዊ ቃላችንን ስጣቸው።"

"የሚቀበሉን ይመስልሃታል?"

"አንተ አጥንቱን ወርውርላቸው። ጉሮሮአቸው ውስጥ ተሰንቅሮ አልወርድ ካላቸው እንደ አስፈላጊነቱ ሁለተኛውን እማራጭ ትወስዳለህ።"

"ማለት?"

"ቢያንስ የልዕልቲቱና የአምባሳደሩን 'ሰብአዊ ጋሻነት' እንዲያበቃ የጎይል ርምጃ ትወስዳለህ።"

"ያልታሰበ መሰናክል ቢገጥመንስ?"

"መሰናክሎችን መገለል መለለኝ ሥራህ! ለማንኛውም ሜዳውን እያየህ መወሰን ያንተ ፈንታ ነው።"

"እመሰግናለሁ!"

**********//////////**********

አሁን በሁለት መቶ ሜትሮች ርቀት ብቻ ከጠላፊዎቹ ጋር የተፋጠጡት አቶ ግርማይ በርሄ ተጨባጩን እውነታ ከተሰጣቸው ትዕዛዝ ጋር እያመዛዘኑት ሳሉ ኮሎኔል አስፋ እና መጥረቢያው በፍጥነት እርምጃ ወደ አቶ ግርማይ መጡ።

"የማጥቃት ርምጃ ልንወስድ ነው። አመቺው ትዕበት አሁን ነው!" አለ መጥረቢያው።

"እኛም ትዕዛዝዎን ብቻ ነው የምንጠብቀው። በጣም በቀላሉ እናፀዳቸዋለን!" አለ ኩሉኔል አሰፋ።

አቶ ግርማይ ከሰመመን ዓለም ብትት ብሰው የባነኑ ይመስል ድንገት ቀና፣ ቀጥ አሉና . . .

"ትዕዛዜን ጠብቁ። ማንም ተኩስ እንዳይከፍት!" ሲሉ ትዕዛዝ ከሰጡ በኋላ "አጃቢም አልፈልግም" ብለው በቀጥታ ወደ አጋች ታጋች ጠንካራ ይዞታ መራመድ ጀመሩ። ግማሽ መንገድ እንደሄዱ ያፈትም ግማሽ መንገድ ተገዛ ተቀበላቸው።

"ቴንክ ዩ!" አሉት የዘረጋላቸውን ባለ ግማሽ ሊትር የታሸገ ውሃ ተቀብለው እየከፈቱ።

"እንዴት ናቸው?" አሉት ውሃውን ከፍተው ከተጎነጩ በኋላ ባገኟቸው ወደ ልዕልቲቱና አምባሳደሩ አቅጣጫ እየጠቆሙ።"

"አልተመቻቸውም። ግን ነፃ የሚወጡበት ሰዓት የተቃረበ ይመስለኛል።" አላቸው ያፈት።

"ልትለቋቸው?" አሉት ተገርመው።

"እንዴታ። ካሁን በኋላ እዚህ አካባቢ ለእነርሱ ምግብ የሚያቀርብ ሪሊተን ወይንም የእንግሊዝ ኤምባሲ የለም እኮ።"

አቶ ግርማይ ሳይወዱ ፈገጉ። "ከዚያስ ምን ይዛችሁ ልትሄዱ?"

"ቅርሳችንን ብቻ!"

"ጋሻችሁ ምንድነው?"

"አቶ ግርማይ ጋሻችንን ላሳይዎት" አለና ያፈት በወገቡ የታጠቀውን ማካሮቭ ሽጉጥ አውጥቶ፣ መጠበቂያውን ወደ ታች ለቆ፣ በርጋታ ወደ ሰማይ ቀና አደረገውና አንድ ጥይት ተኮሰ። አቶ በርሄ ዐይኖቻቸውን ከላዩ ሳያነቅሉ በገረሜታ አስተዋሉት። ያፈትም ትክ ብሎ ሲመለከታቸው ቆየና ዙሪያዎትን ይመልከቱ!" አላቸው።

"ቦይስ ሬዲ!" አለ መጥረቢያው አፉ ስር በተሰጠፈችው ማይክራፎን።

"ተዘጋጁ!" አለ ኩሉኔል አሰፋም በተመሳሳይ ራዲዮ።

አቶ ግርማይ በዝግታና በርጋታ ዙሪያ ገባውን፣ ኮረብታ ጋራውን፣ ጢሻና ሽለቆውን ሁሉ በዙሪያ ክብ መቃኘት ጀመሩ። እያንዳንዱ የተመለከቱት የምድር ገፅ

በለው፣ በሕዝብ፣ በቀላውስት . . . ያውም የጦር መሣሪያ አስከ አፍንጫው በታጠቀ፣ ከዱር የወጣ አንበሳ በመሰለና ለጠብ ባቆበቆበ ሕዝብ ተሞልቷል፣ ተሸፍኗል!

አቶ ግርማይ በተመለከቱት ነገር መመሰጣቸው ከፊታቸው ላይ ይነበባል።

"ምናልባት ጋሻችሁን እያሳየህኝ ከሆነ ብዙም 'ኢምፕሬስድ' አልሆንኩም!" አሉት ተኮሳትረው።

"እኔም አልጠብቅብዎትም።"

"ይህ የታጠቀ ሕዝብ በመንግሥትና በናንተ መሃል ጣልቃ የሚገባ ከሆነ . . ." አሉና ራሳቸውን በመወዝወዝ መልዕክታቸውን አበቁ።

"አዎን ኃይሉና ብቃቱ አላችሁ ብዬ አምናለሁ። ነገር ግን አሁን አይደለም!" አላቸው።

"መቼ ነው ብለህ ታስባለህ?"

"ልዕልቲቱ፣ አምባሳደሩ፣ እርስዎ እና ጦሩ በሙሉ ከተገደለ በኋላ።"

"አታደርጉትም!" አሉ አቶ ግርማይ።

"እውነት አልዎታለሁ። ልዕልቲቱን እና አምባሳደሩን ከቶም ቢሆን ጫፋቸውን አንነካም። በነፃ አንለቃቸዋለን። ከርስዎ ጀምሮ ያበሻና የፈረንጅ ኮማንዶ ግን የዛሬዋ ጀንበር ስትጠልቅ በሕይወት ኖሮ የሚመለከት አይኖርም!"

"የሳን ሴት ውበትን ለማየትና ለማድነቅ አልመጣሁም!" አሉት በጣም በተረጋጋ ድምፅ።

ያፈት ከልቡ ከትክት ብሎ ሳቀ። 'እኚህ ሰው ነርቭ አላቸው። ፍንክች አይሉም' ሲል አሰበ።

ጆሮአቸው ላይ የተለጠፈው ማይክራፎን መንኮራኮር ሲጀምር ፈጠን አሉና አንድ አምስት እርምጃ ወደ ኋላ ራመድ ብለው በቀስታ እንዲህ አሉ።

"ካሁን በኋላ በስህተት የባረቀች ያንዲት ጥይት ድምፅ እንኳን ቢሰማ፣ እዚህ አጠገቤ የቆመው ባላንጣዬ እንዳረጋገጠልኝ እና እናንተም እንደምታዩት አንዳችንም የዛሬዋን ጀንበር መጥለቅ በሕይወት ቆይተን አናይም።"

"ዝጋ! ካሁን በኋላ ጦርነቱ አብቅቷል!" አሉና ወደ ያፈት ተመለሱ።

"ጠቅላይ ሚኒስትሩ ካቢኒያቸውን አሳምነው በሙሉ ድምፅ ፀድቆ የላኩት የመፍትሄ ሐሳብ ይዤውልህ።"

"ያለሙኝ!"

"ልዕልቲቱን፣ አምባሳደሩን እንዲሁም ቅርሶቹን በሙሉ አስረክባችሁ እጃችሁን ለመንግሥት ስጡ። ፈጣን የፍርድ ሂደት ይደረግና ይፈረድባችኋል። ይህ ለሚዲያ ኮንሳምሽን ብቻ የሚደረግ ሂደት ነው። ቢበዛ ከስድት ወራት በኋላ በ "ምህረት" ነፃ ትወጣላችሁ!"

ያፌት ፈገግ አለ። "የጠበኩት ይህንኑ ነው። ለማንኛውም ልዕልቲቱን እና አምባሳደራችሁን አሁኑኑ በወርቅ ትሪ ላይ አስቀምጬ (በነፃ) አስረክባችኋለሁ። የቅርሶቹ ጉዳይ ግን ያበቃ፣ የተዘጋ ርዕስ ነው። መልሰን ለዘራፊ ፈረንጆች ለማስረከብ አይደለም ይህን ሁሉ ውጣ ውረድና መስዋዕትነት የከፈልነው።"

"አትሳሳት! ቅርሶቹን ከናንተ ተቀብለን ለፈረንጅ የማቀበል ፍላጎት የለንም። ሙዚየማችን ውስጥ በክብር እናስቀምጣቸዋለን።"

ያፌት በግርምት ተመለከታቸው። "አቶ ግርማይ። እነዚህ ቅርሶች በዮኔስኮና በለንደን ሙዚየም የተመዘገቡና ማይክሮ ፊልም የተቀረፁ ናቸው። ሙዚየማችሁ ልታስቀምጧቸው እንደማትችሉ ከርስም የበለጠ የሚያውቅ የለም።"

"ይህን ሁሉ ራስ ምታት ለመንግሥታችን ብትተውለትስ?"

"ራስ ምታቱ ለአንድ መቶ አርባ ዓመታታ ሲወቅረን ኖሯልኮ። ከእንግዲህ እጃችን የገቡትን ቅርሶች በተመለከተ ሪስክ አንወስድም። ለማንኛውም አሁን አምባሳደሩን እና ልዕልቲቱን ልላክልምት" አለና ፊቱን አዙሮ መንገድ ጀመረ።

"ያፌት!"

ዞር ሳይል ጉዞውን ቀጠለ።

አምባሳደሩ፣ ልዕልቲቱና የቀሩት የዘመቻ መቅደላ አባላት በጉጉት ሲጠብቁት ደረሰ።

"እጅህ ከምን?" አሉት ባሕታዊው።

"ያው የምንጠብቀውን 'አጥንት' ነው የወረወሩልን።"

"በዝግጅታችን መሠረት እንቀጥላ" አለ ያሬድ።

"ምንም ጥያቄ የለውም!" አለች ራሄል።

አምባላደሩና ልዕልቲቱ በፀጥታ ቆመው በማይገባቸው ዐማርኛ የሚነጋገሩት እጋኞቻቸውን ይመለከታሉ።

"ዋት ኢዝ ዘ ቬርዲክት?" አሉ ልዕልቲቱ። (ፍርዱ ምንድነው?)

"እሁን ለመንግሥት ባለሥልጣን እናስረክባችኋለን!" አሰ ዶክተር አንዱዓለም። "እስካሁን ለደረሰባችሁ መጉላላት ክልብ . . ."

"አቁመው!" አሉ ልዕልቲቱ እጃቸውን አንስተው። አንዱዓለም ዝም አለ።

"ከናንተ ጋር በቆየሁባቸው ጥቂት ቀናት መጠን የሌለው ትምሕርት ተምሬያለሁ። ሀገሬ ስገባ የማደርገው የመጀመሪያው ርምጃ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ይህንን . . ." አሉና ደረታቸው ላይ ያንጠለጠሉትን ትልቅ ዐልማዝ ያዝ አድርገው "ይህንን አስደናቂና ታሪካዊ አልማዝ ለባለቤቱ የሕንድ ሕዝብና መንግሥት አስረክባለሁ!"

የዘመቻ መቅደላ አባላት በሙሉ በፉጨት የታጀበ ደማቅ ጭብጨባቸውን አቀለጡት።

**********//////////**********

በጥቂት መቶ ሜትሮች ርቀት ላይ ያሉት የእንግሊዝና ኢትዮጵያ ኮማንዶዎች እና አዛዦቻቸው ደግሞ 'ምን እየተደረገ ነው?' በሚል አግራሞት አሻግረው ያያሉ። ያም ሆነ ይህ ሁለቱ እንግሊዛውያን ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ በሰላም የሚለቀቁ መሆናቸውን የተረዳው የኤስ.ኤ.ኤስ ኮማንዶ ጦር አዛዥ ወደ አቶ ግርማይ ተጠጋ።

"እናንተን አምነን እርምጃ የመውሰድ ትዕዛዝ በመጠበቃችን ተሳስተናል። እነዚህ ወንበዴዎች ካዳራሹ ሲወጡ አንድ በአንድ እንደ ትኩስ ኬክ ልንውጣቸው እንችል ነበር።" አላቸው።

የጠቅላይ ሚንስትሩ ረዳት በስላቅ ፈገግ አሉ። "ትኩስ ኬክ ከጉሮሮህ ሳይወርድ ሊያጠፋህም ይችል ነበር!" አሉት።

**********//////////**********

ከብዙ መተቃቀፍ፣ መሳሳም፣ መጨባበጥና የጀርባ ቸብ ቸብ መሰነባበቻ በኋላ ልዕልት ኢዛቤልና የእንግሊዝ አምባላደር በሕይወት ዘመናቸው ሙሉ ተጉዘውት የማያውቁትን እጅግ ረጅሙን ሁለት መቶ ሜትር ወደ ነፃነት መራመድ ጀመሩ።

ምዕራፍ አርባ አምስት

በቡድን በቡድን የተከፋፈለው ሕዝብ ቅርሶቹን እየተሸከመ በዘመቻ መትደላ መሪ በባሕታዊው፡ ፊታውራሪነት ረጅሙንና ውጣ ውረድ የበዛበትን ጉዞውን ይዞ ተመመ።

አስካሁን ድረስ ማንም ያላስተዋለው ቂስ የተሸከመውን ሳጥን ቅሰት እያመሰገነ ከቀሳውስቱ፣ ከተሸካሚው ሕዝብ፣ እንዲሁም ከዘመቻ መቅደላ አባላት ጋር አብሮ እየተጓዘ ነው። የውስጥ አግሮቹ በአስቸጋሪው ጉዞ ተላልጠዋል። ሙቀቱ ያነዳቸዋል።

'አይ የእምነት ነገር' አለ በሐሳቡ። 'ይህን ሁሉ አስቸጋሪ ገፀ ምድር አቋርጦ ገጸም መቅርቶር . . . መመነን ያስገርማል።' ከርቀት ሦስቱ ሄሊኮፕተሮች የደቡብ ሰማይ አድማስ ላይ ጥቁር ነጥብ መስለው ታዩትና በሐሳቡ 'ያልታደላችሁ። የደም ድግስ አመለጣችሁ' አለ።

ከአምስት ሰዓታት እጅግ አስቸጋሪ እና ፊታኝ ጉዞ በኋላ የተከዜን ወንዝ ተንተርሶ ደረቱን የሰጠ ተራራ ሥር ደረሱ። እንደገና በዋናው መሪ መነኩሴ ቀዳሚነት ዝንጀሮ እንኳ የማይደፍረውን ገደል እየቧጠጡ ሽቅብ መውጣት ጀመሩ። ብዙዎች ከነሸክማቸው ወደቁ። ከሁለት ሰዓት አቀበትና ገደል መቧጠጥ በኋላ በመጠኑም ቢሆን ገላጣ የሆነ የተራራው ደረት ላይ ሲደርሱ ሁሉም ከነሸክሙ በቁሙ ወደቀ።

'እዚህ የተራራ ደረት ላይ እነዚህን የመሳሰሉ ዋሻዎች ይኖራሉ ብሎ ማን ያምናል?' አለ አነስተኛ ሳጥን የተሸከመው ቂስ። የውስጥ አግሮቹ ተላልጠው ከመቁሰላቸው በስተቀር ብዙም የደከመው አይመስልም። የዋሻው አንድ ብቸኛ መግቢያ ስፋቱ ከሁለት ሜትር አይበልጥም። መግቢያውን ደብቆ የሸፈነውን አሾማ ቁጥቋጦ መሪው መነኩሴና ጥቂት ሰዎች በብዙ ጥረት ገላልጠውት በርካታ ሚፎች አብርተው ገቡ። ስፋቱ ወይንም ዙሪያ ክቡ አሥር ሜትር የሚሆን ክፍል አለው። ዙሪያውን የሚታየው የዋሻው ግድግዳ እጅግ ጠባብ የሆኑ፣ ቁመታቸው አጫጭር

የተፈጥሮ በሮች አሉት። ውስብስብ እና በጣም በርካታ ወደሆኑ ዋሻዎች ያስገባሉ። ሁሉም የተሸከሙትን ሸክም የዋሻው አዳራሽና በሩ ላይ ከመሩ።

ባሕታዊው ጭነቱን ተሸክመው እዚህ ላደረሱት "ሕዝበ ምእመናን" መንፈሳዊ ምስጋናቸውን እና ምርቃታቸውን ካሰሙ በኋላ ወደ መጡበት እንዲመለሱና የፈጣሪን እና የሃይማኖታቸውን ተልዕኮ በታማኝነትና በዕናት በመፈፀማቸው ቡራኬያቸውን ሰጥተው አሰናበቷቸው።

ጭነታቸውን አራግፈው፣ ቡራኬያቸውን ተቀብለው ቁልቁል የመልስ ጉዞ ከጀመሩት ቀሳውስት መሃል እግሮቹ የተላላጡበት አንድ ቄስ ያስባል። አዕምሮው በሌላ ሐሳብ በመወጠሩ ደግሞ ደጋግሞ መንገድ እየሳተና እያንሸራተተው ዝው ያለ ገደል ከመውረድ ድኗል።

እነዚህ የዘመቻ መቅደላ አባላት ምን አጠፉ? ይህን ሁሉ አደጋና ሕመም የተጋፈጡት፣ ሕይወታቸውን አሳልፈው ለመሰዋት የወሰኑት በግፍ የተዘረፉብንን ብርቅና ድንቅ ቅርሶቻችንን ለማስመለስ ብቻ ነው። እምን! አዲስ አበባ ተመልሼ ስገባ የዋሻውን ጉዳይ በተመለከተ አንዳችም የማቀርበው ሪፖርት አይኖርም።" ሲል "ቄስ" መቶ አለቃ ሳሙኤል ኃብተማሪያም ውሳኔ አሳለፈ።

መደምደሚያ

የቱክሳስ ዩኒቨርስቲ በታሪኩ የሣራውን ዐይነት እንግዳ ተቀብሎ የሚያውቅ አይመስልም። ጎብኚው እንግዳ በድንገት ከተፍ በማለቱና የሚዲያውን ትኩረት ያልሳበ ምስጢራዊ ገብኝት ነው ማለት ይቻላል።

ሚስተር ኦ' ሱሊቫን የምስጢራዊው ማሕበረሰብ መሪና ስውሩ የዓለም ቁሳር ድፍን ጥቁር ከሆነው ካዲላኩ እንደወረደ በአራት ጠባቂዎች ታጅቦ በቀጥታ ወደ ዋናው ያለተዳደር ሕንጻ አመራ።

የራስ ቅሉ ላይ ምናምኒት እንኳ ጸጉር የሌለው የዩኒቨርስቲው ዲን ፕሮፌሰር ደስቲን እንግዳውን የሕንጻው መግቢያ ላይ ተብሎ "VIP" የሚል ምልክት የተለጠፈበት አሳንሱር ውስጥ ይዞት ገባ። አራት እጃቢዎቹም ተከትለው ገቡ። የሕንጻው ምድር ቤት ውስጥ አሳንሱሩ ሲቆምና በር ሲከፈት አዛውንቱ ምሁር "ሰር ኦ' ሱሊቫን በዚህ በኩል ይከተሉኝ" አለና አዛውንቱ እንግዳውን እየመራ በረኸርም እና በኤሌክትሪክ መብራቶች በደመቀ ኮሪዶር ውስጥ ከተራመዱ በኋላ አንድ ትልቅ እና እጅግ በጣም ብሩህ ብርማ መልክ ያለው የብረት በር ላይ ሲደርሱ ቆሙ።

ከበሩ በስተግራ ግድግዳው ላይ የተለጠፈ ሳጥን መሰል ማሥን አለ። ፕሮፌሰሩ ከደረት ኪሱ አንዲት የኤሌክትሮኒክ ካርድ አወጣና በማሽኑ ስንጥቅ ውስጥ ከተታት። ከሦስት ሴኮንዶች በኋላ ካርዱን መልሶ አወጣለትና በሩ ወለል ብሎ ተከፈተ።

"ይከተሉኝ" አለና ዲኑ እንግዳውን እየመራ ይዞት ሲገባ አራቱ ቦዲ ጋርዶቹ በራሱ ከተዘጋው በር ኋላ ቀሩ። በቀጥታ እየመራ ወሰደውና ጠረጴዛ ይሁን መደብ የማይታወቅ ነገር ላይ የተቀመጠ የመስተዋት ሳጥን አጠገብ ሲደርሱ ቆሙ።

ቤቱ በጣም ሰፊና ቀፋፊ ነው። ከብዙ ሽህ፣ እንዳውም ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት የተከናወነ በርካታ ሞት የተከማቸበት ክፍል። አጽም ብቻ።

"ሰር ኦ' ሱሊቫን እባክዎን ከሱሲ ጋር ይተዋወቁ!"

**********//////////**********

"ይህ የኢትዮጵ ራዲዮ ነው ዜና እናሰማለን። ከአንድ ዓመት በፊት በመዲናችን አዲስ አበባ ከተፈጸመው የእገታና የታሪካዊ ቅርሶች ጠለፋ ወንጀል ጋር በተያያዘ ፖሊስ በቁጥጥር ስር ያዋላቸው አራት አስራኤላዊን የተፈረደባቸውን የእስራት ዘመን በጤና ችግር ምክኒያት ሊጨርሱ እንደማይችሉ በሐኪም ስለተረጋገጠ ለእስራኤል መንግሥት ተላልፈው ሊሰጡ ነው ሲል የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ቃል አቀባይ አሳወቀ.....!"

**********/////////**********

ቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ወጪ መንገደኞችን መቆጣጠሪያው ካውንተር ላይ ከዋናው ኢንስፔክተር ያሬስክ ፊት ለፊት ራቅ ብሎ የቆመው ኢንስፔክተር ሳሙኤል (በአዲሱ ማዕረጉ) የተሰፋ መቁረጥ ላብ በጀርባው ኮለል ብሎ ሲወርድ ተሰማው። የቱል አቪቭ በራሪ መንገደኞች "ቼክ" እያደረጉ ነው። 'አብዛኛዎቹ መንገደኞች ሳያልፉ አይቀሩም። ይህን ኮሪዶር ለማምለጫነት አልመረጠቸውም ማለት ነው?....ምናቸው ነው የሳበኝ?' ሲል ሳሙኤል ራሱን ጠየቀ። 'የስልሳ.....የሰም ከሃምሳ ምናምን ዓመት አይበልጣቸውም። ግን ምናቸው ነው የሳበኝ?' ሳሙኤል በፍጥነት እያሰበ አረጋዊቷን መንገደኛ በትኩረት ያያቸዋል። የኢሚግሬሽን ኦፊሰሩ አንዱ መንገደኛ ፓስፖርቱን መርምሮና መልካም ጉዞ ተመኝቶ ካሰናበተው በኋላ ወደ ሳሙኤል ቀና ሲል ትኩረቱን አይቶ ፊቱን አዞረ። ሳሙኤል የሚመለከታቸውን መንገደኛ አያቸው። ሳሙኤልም በዚህች ቅጽበት መታየቱን ያወቀ ይመስል ወደ ኢሚግሬሽን ኦፊሰሩ ዘር ሲል ተያዩ። ምንድነው? እንደማለት በምልክት ሳሙኤልን ጠየቀው።

ምንም! እንደማለት ትከሻውን ናጠና መካከለኛ ሻንጣቸውን ከኋላቸው በጋሪ እያስገፉ የሚያዘግሙትን ሴት ማየት ቀጠለ። ሽበት የወረረው አጭር ጸጉራቸው ላይ ሻሽ አስረዋል። የግራ እጃቸው ከየአምስቱ ርምጃቸው በኋላ ከራሳቸው ላይ ዝንብ የሚያበር ይመስል ወደ ኋላ ሸው ያደርጉታል። ረዥምና ባለ ጥልፍ የራያ ቀሚስ ለብሰው ተመሳሳይ ኩታ ትከሻቸው ላይ ጣል አድርገዋል። አይናቸው ላይ የስኩት

መነጽር ምናልባት ሳሙኤል አስክ ዛሬ ድረስ ካያቸው ሁሉ ትልቁ ሳይሆን አይቀርም። በቀጥታ ወደ ኢሚግሬሽን አፈሰሩ ያስክ አመራ።

"እና ሴትዮ ስማቸው ማነው?"

የኢሚግሬሽን ተቆጣጣሪው ወዲያውኑ ኮምፒውተሩን ነካ አደረገና..... "ወይዘሮ ጸዳለ ገበየሁ፤ ወደ አየሩላሌም ለፋሲካ በዓል የሚንዙ ምእመናን!" አለው።

ሳሙኤል ለትጽበት ታህል ጊዜ ፊቱ ላይ ፈገግታ ሽውታ የታየበት መሰለ። 'ምናቸው ነው የላበኝ?' ክኢሉ የዮዲት ፎቶ ግራፍ አውጥቶ አየት አደረገው። 'አምን እጂ ነው! ባጭሩ የቆረጠችው ጸጉሯ አሁንም ያለ አየመሰላት በግራ እጂ ወደ ኋላ ልትገፋው ትሞክራለች!'

ራቅ ራቅ ብለው የቆሙና የሲቪል ልብስ የለበሱ ሁለት የደህንነት አባላት በጥያቄ መልክ ተመለከቱት። በፍጥነት እያሰበ ነው። አእምሮው በፍጥነት ያስባል። ቅርሶቹን ለማስመለስ ያደረግሽው ተጋድሎና ያስገኘሽው ውጤት ግሩም ድንቅ ነው! ለዚህ ብቻ ነጻ ኽነሽ እንደ ወፍ መብረር ይገባሻል። ግን.....ግን የሰው ሕይወት እጥፍተሻል። እጅችሽ ባንድ ዜጋችን ደም ተጨማልቀዋል!' አለና ቀና ብሎ ለሁለቱ ባልደረቦቹ ባይን ጥቅሻ ብቻ ምልክት ሰጣቸው። ሁለቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ሰላዮች ወደ ዮዲት በፈጣን ርምጃ ተራመዱ።

**********//////////**********

"ማዘር አፍ ዘ ሂውማን ራስ!" አለ የዩኒቨርስቲው ዲን እንዴ ድንትነሽን በእድናቆት፤ እንዴ እንግዳውን በፍርሃት እየተመለከተ። የስኮትላንዱ እንግዳ ግን የሰማ አይመስልም። እንደ እብነ በረድ ደንጊያ ሙት በመሰሉና ከሰባ ዓመታት በላይ ባገለገሉ ዐይኖቹ ድንቅነሽን ት.....ክ ብሎ ያያታል።

"ሰር! ካገሯ ኢትዮጵያ ሌሎችም ተመሳሳይ አጽሞች እየተገኙ....."

"አገሯ? ኢትዮጵያ?" አለና እንግዳው በነዚያ ሙት ዐይኖቹ ሽማግሌውን ዲን ሊመለከተው ቆየና..... እጅግ አስፈሪ፤ ምድራዊ የማይመስል እና የሚያከላላ ሳቁን ለቀቀው። ዲኑ በፍርሃት ተሸብሮና ምን መናገር እንዳለበት ባለማወቅ ግራ ተጋብቶ እነግዳውን ተመለከተው።

"እምን ሰር ኦ ሱሲቫን። ኢትዮጵያዊቷ የሰው ዘር እናት ሱሲ....."

ሽማግሌው ኦ ሱሲቫን ጣቱን ጧ! አድርጎ አጮኸና ዲኑን ዝም አሰኘው። ላቱን ሲያበቃም የደረት ኪሱ ውስጥ ገብቶ በላስቲክ የታሸገ ሲጋር አውጥቶ፣ ላስቲኩን ቀዶ ጣለና ሲጋሩን አፉ ላይ አድርጎ በላይተር አቀጣጠለው። እናም ወደ ድንቅነሽ ዝቅ አለና ያን ግራጫማና የሚከረፋ ጢስ አቦነነባት። ደግነቱ እንኳንስ የትምባሆ ጢስ ጥይትም የማይበሳው መስተዋት ውስጥ ነው የተቀመጠችው።

"ሱሲ ማማ! ዌል ካም ሆም!" አላትና የሲጋር ጢሱን በረዥሙ ለቀቀባትና ወደ ፕሮፌሰር ደስቲን ዞረ። "አንተ ደደብ!" አለው ሽማግሌውን ምሁር። ፕሮፌሰሩ ደንግጦ አመዱ ቡን አለ።

"ሱሲ" ካሁን በኋላ ነጭ ናት! የኛ ናት ገባህ?" አለና እንደ ብራቅ አምባረቀበት።

"የስ ሰር! ገብቶኛል።"

"እንዲት ጥቁር አፍሪካዊት የሰው ዘር ሁሉ እናት የመሆን ብቃት የላትም! ሱሲ ነጭ ናት። ያንን ዲ.ኤን.ኤ. አንትሮፖሎጂ.....ምናምን የምትሉትን ዝባዝንኬአችሁን ተጠቅማችሁ ወይንም አውርታችሁ ሱሲን ነጭ አድርጓት! ነጭ ቀለም ቀቢት! ገባ.....ህ?" አለና ጮኸበት።

"አምን፣ አምን ገብቶኛል። እኛም እየሠራን ያለነው "ልናነጣት" እና እዚሁ ለዘለዓለም ልናስቀራት ነው።" አለው ከመላጣው ወደ ግንባሩ የወረደውን ላብ በመሃረቡ እየጠረገ።

"ጉድ ቦይ! ሱሲን ግሪን ካርድ ስጧት!" አለና ያን አስፈሪና የሚያክላላ ሳቁን በረዥሙ ለቀቀው።

ተፈጸመ



"ኢትዮጵያዊ ድንቅነሽን (ሉሲ) "ነኚ ዋኒ ቀብተሙና ግሪን ካርድ ሰዋተው ፈረንጅ ሰማይረፕ የተቀናበረው ሴራ እስከ ምን ድረስ የተመሰበ ነሙ?

"የመቅደላ አምባ ባእንግሊዝ ጦር ተቃጥሎ ታሪካዊ ቅርሶታችን ተዘርፈው ወደ እንግሊዝ ሀገር ከተጋዙ ከአንድ መቶ ዐርባ ዓመታት ዘኋላ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚንደሶሪ ልዕልት ሲዛዜል የእንግሊዙ አምባሳደር ክሳይፍ የኢትዮጵያ ባሕል ሚንስትር ኢብሬሂም ከመቅደላ የተዘረፉትና ለሰውደ-ርዕይ ክብንደን የመጠት ቅርሶች በቅርስ ለስመሳስ ታጣቂዎች ታግተው ተያዙ!

"የጠፉው ዓለም መገናኛ ብዙሃን ለሰደናቂው ጉዳንታ ድሬማ ቅርሶቹ ከሚተዋወቁ ከሌግዚቢሶኑ ሥፍራ በቀጥታ እያውሬጨ ነው።

"በዚህ ሕዕደናቂና ታሪካዊ ቅርሶታችንን የሚመለከተ ትግል ውስጥ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚንስትር የኃላማት ንጉሥን የሰለሳ ተቀማጭ ሆኖ የሚመጣን ሰለረሪና ጓደሳን ምስጠራዊ ደጅ ጥናት ሀገሪ የመጡ ማመሳረቅሩ ቅርሶቻን ከዘራፊዎች ለመደ የቆረጡ ባመራሮች እንዲሁም ቀዳሰና ሪርክስ ሪዋቂ መንፈሳዊ ጋደሳት እናሰማቸው።

"የኢትዮጵያ ጥንታዊና መስጢራዊ ከወቀትና ዊበባ የፈቀርና ዩኳለማ ጽናት ለሰባ መንፈሳዊና ምንዋ ፍልሚያ ይሸጠቃ ነጅ የኢትዮጵያን "ረቂቅ ነፍሱ የተገለጸበት ድንቅ መጽሐፍ

ዋጋ በር 35.00